# አፄ ምኒልክ

# እና

# የአድዋ ድል

# The Battle of Adwa

## AFRICAN VICTORY IN THE AGE OF EMPIRE

Raymond Jonas

በሬይሞንድ ጀናስ

ትርጉም፡- ሙሉቀን ታሪኩ

© የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያ ዕትም :- ጥቅምት 2006 ዓ.ም.
ሁለተኛ ዕትም:- ጎዳር 2006 ዓ.ም

# ዋና አከፋፋይ

ዩኒቲ መጻሕፍት መደብር

ከለም ሆቴል ወደ ሾላ በሚወስደው መንገድ

ከለም ሆቴል 100 ሜትር ከፍ ብሎ

ስልክ:- 0912 028 794

:- 0911 669 946

የመ.ሳ.ቁ. 4143

## ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | 11 |
| **ክፍል አንድ** | |
| **የአድዋ መንገድ** | |
| ምዕራፍ አንድ:- የንጉሥ ሀልም | 19 |
| በቴዎድሮስ ላይ የተደረገው ዘመቻ:- የወረራ ቅድመ ሁኔታ | 24 |
| የግብፅ በኢትዮጵያ ላይ መነሣት | 29 |
| የኢትዮጵያ የምንግዜም ኃይለኛ ጥንዶች-ምኒልክ እና ጣይቱ | 32 |
| ምዕራፍ ኹለት:- ከአድዋ አቅራቢያ | 36 |
| ምፅዋዕ:- የዘመናት ግዛተ-አፄዎች ማዕከል | 40 |
| ምዕራፍ ሦስት:- ጣሊያን በአፍሪካ | 45 |
| የግብፅ በር ከፋችነት እና የጣሊያን አገባብ | 49 |
| የጣሊያን ወደ ተራራማው የኢትዮጵያ ግዛት መጠጋት | 50 |
| ምዕራፍ አራት:- የነፃነት ዋጋ | 62 |
| ምኒልክ ወደ ወላይታ ያደረጉት ዘመቻ | 65 |
| የምኒልክ ዘመቻ በውጪው አለም እይታ | 70 |
| ምዕራፍ አምስት:- የነጭ ቅጥረኛ ጥቁሮች | 73 |
| የባንዳ ባታሊዮናችን ማደራጀት | 74 |
| ፍቅር በአፍሪካ | 79 |

ምዕራፍ ስድስት፡- አፍሪካ በጣሊያን 84
የሐረር አሥተዳዳሪው መኮንን 90
የራስ መኮንን የጣሊያን ተልዕኮ 97
"የግራማዊነትም ጥበቃ እንዲደረግልኝ እጠይቃለሁ" 101
ምዕራፍ ሰባት፡- "ለአገሬ ውርደት" 106
የኤርትራ አፈጣጠር 109
የሰፈራ ቅኝ ግዛት በኤርትራ 113
ባሕታ ሃጎስ እና ልዑል መንገሻ፡- ከነጭ አባብ ጋር የተደረገ ግብ ግብ 117
ባራቴሪ የኢትዮጵያን ድንበር ጣሰ 121

## ክፍል ኹለት

## የአድዋ የጦር ሜዳ ውሉ

ምዕራፍ ስምንት፡- የምኒልክ ዘመቻ 124
ሕዝባዊ ቅስቀሳ በኢትዮጵያ 125
የዘመቻው አጀማመር 128
ምዕራፍ ዘጠኝ፡- አምባላጌ 132
የጣሊያን ከቅዠቷ መባነን 135
ታሪክ የቀየረው የአምባላጌ ውሎ 139
የመቀሌው ምሽግ 142
የበዓለ-ጥምቀት ለልፍ 145
የተራበ የይሁዳ አንበሳ ሲሳይ 150



ቀድመው ምኒልክ እና ጣይቱ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻቸውን በአውሮፓ አጧጡፈው ነበር።

ከ1878 ጀምሮ አፄ ምኒልክ ከአውሮፓ ጋር ኹለንተናዊ ግንኙነት የሚያደርጉት በአማካሪያቸው ስዊዘርላንዳዊው መሐንዲስ አልፍሬድ ኢልግ በመታገዝ ነበር። በ1890ዎቹ ንጉሡ ኢልግን በተደጋጋሚ ወደ አውሮፓ በመላክ የራሳቸውንና የአገራቸውን ገጽታ ለመገንባት ችለዋል። ኢልግም በተልዕኮው ተራራማውን የኢትዮጵያ መልክዐ ምድር የሚያሳይ ፖስት ካርድ ‹‹የአፍሪካዋ ስዊዘርላንድ›› ከሚል ጽሑፍ ጋር በማያያዝ ኢትዮጵያን ከአውሮፓውያኑ ጋር የበለጠ አስተዋውቋል። በተጨማሪም የምኒልክን ዘውዳዊ ምስል የያዙ ፖስት ካርዶች፣ የመገበያያ ሳንቲሞች፣ የፖስታ ቴምብሮች እና ማኅተሞች በአውሮፓ በማሠራጨት የንጉሡን ሉዐላዊነት ቀድሞ አስተዋውቋል።

በኢልግ በተጨማሪ ተጓዥ ጋዜጠኛ የነበረው ካዝሚር ምንዶን-ቪላል ሄት በ1982 ጀምሮ በተለያዩ የአውሮፓ የኅትመት ውጤቶች ላይ ስለ ምኒልክ እና ኢትዮጵያ በመጻፍ ጉልህ የማስተዋወቅ ሥራን ሠርቷል። የሞንዶን-ቪላልሔት ጽሑፎች ምኒልክን በጉልህ ያስተዋወቀ ሲሸን የንጉሡን ግዛት ከመካከለኛው ዘመን የአውሮፓ ነገሥታት ጋር በማነፃፀር እንዲህ ጽፎ ነበር፡- ‹‹የኢትዮጵያን ንጉሣዊ ግዛተ- አፄ ስመለከት የእኛ የአውሮፓውያን የመካከለኛው ዘመን ነገሥታት ከመቃብር ውጥተው በኢትዮጵያ ተራሮች የተሸሸጉ ያህል ይሰማኛል።›› የእርሱ ዘመን ኢትዮጵያ ከዘመናዊው አውሮፓ ጋር የሚያመሳስላት የዕድገት መስመር ላይ እንደምትገኝ በተደጋጋሚ ጽፏል።

የሞንዶን ጽሑፎች ምኒልክን ከክርስትና ዕምነት ጋር በማያያዝ ለአውሮፓ አስተዋውቀዋል። ምኒልክ በሙስሊም ጎረቤቶቻቸው ላይ ያለውን የበላይነት በማጋነን የጻፈ ሲሆን ምኒልክ በሙስሊሙ የወላይታ ግዛት ላይ ያስመዘገቡት ድል ‹‹መስቀል በጨረቃ ላይ የበላይነቱን ያረጋገጠበት›› በማለት ገልጿል። በአጠቃላይ ጣሊያን

ኢትዮጵያን ለመውረር በዝግጅት ላይ በነበረችበት ወቅት ሞንዶን በጽሑፎቹ ከኢትዮጵያ ጎን ቆሞ ነበር።

ከወረራው በፊት ሞንዶን ስለ ምኒልክ እንዲህ ጽፎ ነበር፦ ‹‹የኢትዮጵያው ንጉሠ-ነገሥት የአውሮፓ ሕዝቦችን አስተሳሰብ ያውቃል። ምክንያቱም የክርስቲያን ሕዝቦችን አመለካከት እና የፍትሕን ሥርዓት ያውቃል።›› በአውሮፓ የተሠራጨው የምኒልክ ምስል ንጉሡ አንገቱ ላይ መስቀል አስረው ያሳይ ነበር። ይህ ደግሞ በአንድ አፍሪካዊ ንጉሥ ላይ ታይቶ አይታወቅም ነገር። በዚህም የተነሣ በርካታ የአውሮፓ ጋዜጦች የምኒልክን ምስል ‹‹የአፍሪካ ክርስቲያናዊ ንጉሥ›› ከሚል የግርጌ ማስታወሻ ጋር ነበር የሚያወጡት።

በተለያዩ መንገዶች ምኒልክ እና ጣይቱ በመላው አውሮፓ እና በአሜሪካ ታዋቂ ሆነዋል። በምዕተ-ዓመቱ መባቻ የፓሪሱ ሙሴ ግሪቪን በሙዚዬም ለጣይቱ እና ምኒልክ የሰም ሐውልት አቁሞላቸዋል። በተመሳሳይም በሻኒቲ ፌይር የምኒልክ ሃውልት ቻርልስ ዳርዊን እና ቤንጃሚን ዲዝራኤል ሐውልት ጎን ተቀምጦ ነበር። ፌሊክስ ፖቲን የተባለ ባለ መደብር ደግሞ ለእያንዳንዱ ጎብኚ የአፄ ምኒልክ እና የጣይቱን ምስል የያዘ ፓስት ካርድ በስጦታ መልክ ይሰጥ ነበር።

የአድዋ ድል በበርካቶች ሕይወት ላይ አሉታዊ ጣጣ አስከትሉ ነበር። ጣሊያን በጦርነቱ ሽንፈትን ባስተናገደች ማግስት በጣሊያን የፍራንሴስኮ ክረ ነፒ አስተዳደር የወደቀ ሲሆን የክረስፒም ሥልጣን አክትሟል። የጣሊያንን ጦር የመራው ጀነራል አሬስቴ ባራቴሪ ከጦርነቱ ቢተርፍም ወደ አገሩ ተመልሶ ከመግባቱ በፊት ነበር ክስ ተመሥርቶበት ጉዳዩ በፍርድ ቤት መታየት የጀመረው። የባራቴሪ የክስ ታሪክ በተለያዩ የጣሊያን ተውኔቶች ላይ ከህደትን፣ ሽንፈትንና የዘር ልዩነትን ለማሳየት ይጠቀስ ነበር።

ከጦርነቱ በኋላ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጣሊያናውያን በምርኮ የተያዙ ሲሆን ክስተቱም ግዙፍ ቁጥር ያለው የነጭ ሠራዊት በጥቁሮች እጅ ላይ የወደቁበት





የመጀመሪያ ታሪክ ሆኖ ተመዝግቧል። ለአንድ ዓመት ያህል በኢትዮጵያውያን እጅ ላይ የነበሩት ምርኮኞች በተደረገላቸው እንክብካቤ እና ኢትዮጵያውያኑ ባሳዩዋቸው ፍቅር ተገርመው ነበር። አብዛኞቹ ምርኮኞቹ ከኢትዮጵያውያኑ ጋር ጥብቅ ወዳጅነት የመሠረቱ ሲሆን የተወሰኑት በትዳር የተሣሠሩ እንደነበሩ ከማስታወሻዎች ላይ ለመረዳት ተችሏል። የእሥረኞቹን አያያዝ በተመለከተ ከራሳቸው ከምርኮኞቹ በተጨማሪ በወቅቱ በተለያየ ሥራ ላይ ተሰማርተው ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የግሪክ፣ የአርመንያ፣ የአይሁድ እና የስዊዘርላንድ ዜጎች በሰፊው ጽፈዋል።

ኢትዮጵያ ላይ የተቃጣው የወረራ ሙከራ ከኢምፔሪያሊዝም መስፋፋት መርሆዎች ያፈነገጠ ነበር። በኢትዮጵያ ለሰፈራ ቅኝ ግዛት የሚመች ሁኔታ አልነበረም፣ የጥሬ ዕቃ አቅራቢ ለመሆን እንዲሁም የኢምፔሪያሊስት አውሮፓን ምርቶች ለመቀበል አመቺ የሆነ ገበያ አልነበራትም። የጣሊያን ቡርጂ መንግሥት ‹‹የጣሊያን ምሥራቅ አፍሪካ›› ለመገንባት በነበረው ቀቢፀ ተስፋ ተገፋፍቶ ነበር ኢትዮጵያን የወረረው። ኮርየሬ ዴላ ሴራ የተባለው የሚላን ጋዜጣ የጣሊያን ፖሊቲከኞች ታላቅ ግዛታቸውን በአፍሪካ እንዲገነቡ በማነሳሳት ይታወቅ ነበር። በተስፋፊነት ሕልም በመገፋፋት ነበር የጣሊያን መንግሥት በአገሩ የነበረውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ችላ በማለት በርካታ ገንዘብ በማውጣት ወደ ወረራ የገባው።

ኢትዮጵያን ሳያስገብር የከሸፈው የጣሊያን የወረራ ሙከራ ለየትኛውም ተስፋፊ ኢምፔሪያሊስት ትምህርት ሰጥቷል። በተለይም ሌሎች ሕዝቦችን በመናቅ ለመበዝበዝ የሚነሱ ወራሪዎች ትምህርት እንዳገኙበታል። ጣሊያን ብቸኛዋ ምሳሌ አይደለችም። በርካታ መንግሥታት ለዘመናት ሊስፋፉና ሌሎችን ሊያስገብሩ ኖረዋል። በእርግጥ መነሻቸው የተለየ ቢሆንም። መንግሥታት ጥሬ ዕቃ ለማግኘት፣ ለምርቶቻቸው ገበያ ፍለጋ፣ ለዜጎቻቸው ሥራ ለመፍጠር፣ እና ለመሳሰሉት ዓላማዎች ሌሎችን ሲወሩ ኖረዋል። ጥቂት የማይባሉ ወራሪዎች የመንግሥታቸውን እና የግዛታቸውን ኃያልነት ለማሳየት ሲሉ ብቻ ወረራ የፈጸሙባቸውን ሁኔታዎች ዐይተናል።

የአድዋ ድል አውሮፓን የዓለም ፖለቲካ እና ዘር ልዕለ ኃያል ከመሆን ያስቆመ ብቸኛው አጋጣሚ ነበር። ከአድዋ በፊት ባሉ ዓመታት በርካታ የአውሮፓ እና የአሜሪካ ጋዜጦች መላው ጥቁር አፍሪካ በአውሮፓ ሙሉ ቁጥጥር ሥር የሚሆንበት ቀን መቃረቡን በእርግጠኝነት ይጽፉ ነበር። የአሜሪካኑ አትላንታ ኮንስቲቲውሽን ጋዜጣም የሚከተለውን ጽፎ ነበር።

*

*«መላዋ አፍሪካ በአውሮፓ መንግሥታት ቅርምት የምትጠናቀቅበት ቀን ቀርቧል። አውሮፓውያኑ በአሜሪካ ያሳኩትን የዘር የበላይነት በአፍሪካ ለመድገም ተዘጋጅተዋል። በአሜሪካ ቀይ ሕንዶችን በማስወገድ ለራሳቸው ዝርያ መኖሪያ መፍጠር የቻሉበትን ብቃት በአፍሪካ ለመድገምም የጥቁር አፍሪካ ዝርያዎችን በቅርቡ ማጥፋት ይጀምራሉ።»* ይሄንን የመሰሰሉ የአውሮፓ የዘር እና የፖለቲካ የበላይነት ስብከቶች በዝተው ነበር።

ይህንን የመሰለ የዘረኝነት እና የተስፋፋ የበላይነት ሕልም ነው እንግዲህ አድዋ ላይ ያከተመው። በደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ አክትሞ የጥቁር ዘር እኩልነት ከመረጋገጡ መቶ ዓመታት በፊት አድዋ ላይ ኢትዮጵያውያን የነጭ አውሮፓውያንን የበላይነት በመስበር የጥቁር እኩልነትን አረጋግጠዋል።

የአድዋን ድል ተከትሎ በመላው ዓለም ተበትነው ያሉ ትውልደ አፍሪካውያን የአድዋ፣ የምኒልክን እና የነጻይቱን አገር ኢትዮጵያን ስም በልዩ ሁኔታ ማንሣት ጀመሩ። እንደ ታላቂቷ ጽዮናዊት ኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ኃይማኖታዊ ጉዞ የሚያደርጉ ጥቁሮች ተበራከቱ። የጃይቲው ቤኒቶ ሲልቪያን እና የምዕራብ ኢንዲያው ጀሴፍ ቪታሊየን ወደ ተስፋይቱ ምድር ኢትዮጵያ ጉዞ ያደረጉ የመጀመሪያዎቹ ጥቁሮች ናቸው። እነርሱን በመከተል እንደ ቡከር ቲ. ዋሽንግተን፣ አይዳ ቢ. ዌልስ፣ ደብሊዩ ኢ.ቢ. ዱቦይስን የመሳሰሉ ታዋቂ ጥቁር አፍሪካውያን ስለ አድዋ እና





ኢትዮጵያ የነጻነት ተምሳሌትነት በስፋት ማውራት ጀመሩ። ከተወሰኑ ትውልዶች በኋላ «ብራስ ተፈሪያን» ስያሜ የሚደረገው ጉዞም የአድዋ ተፅዕኖ ውጤት ነው።

ከአድዋ በኋላ አንዳንድ የአውሮፓ አገራት እና አሜሪካ የኢትዮጵያን ድል መቀበል ሲያዳግታቸው ታይተዋል። አንዳንዶች የጣሊያንን ግዙፍነት በመጥቀስ ማንኛውንም አገር መግዛት እንደምትችል እየገለጹ የኢትዮጵያን ድል ለማኮሰስ ሞክረዋል። ነገር ግን ግዙፍ ግዛተ አፄ (ኢምፓየር) መሆን የትኛውንም አገር ከሽንፈት ሲታደገው አልታየም። በታሪክ እንደተመለከትነው እንደ ፖርቹጋል፣ ቤልጂየም እና ደች (ሆላንድ)ን የመሳሰሉ ግዙፍ ኃይሎች ሰፊ ግዛታቸው ተሸራርፏል። ጣሊያን ከእነዚህ ግዛተ-አፄዎች በምን ትለያለች?

ታሪክ በተለየ መልኩ ልዩ ክስተቶችን ይወዳል። ይህ መጽሐፍ የአድዋን ታሪካዊ ልዩ ክስተትነት ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን ለድሉ አመክንዮአዊ ማረጋገጫ ለመስጠትም የተጻፈ ነው። እንደ አድዋ ዓይነት ልዩ ክስተቶች የታሪክን ተሰምጿዊ ጉዞ በማስቀየስ ሰዎች ለዘመናት ዐምነው ከተቀበሉት ንግርት የተለየ እውነታ እንዳለ ያመላክታሉ። አድዋም ለሰው ልጆች መረዳት የሰጠው ይሄንን ማረጋገጫ ነው።

አድዋ አንዲት አፍሪካዊት አገር ከወራሪ ጋር በመታገል ነፃነቷን ያወጀችበት ታሪካዊ ምስክር ነው። አድዋ ለበርካታ ቅኝ ግዛቶች በራስ የመተማመን ጉልበትን በመስጠት የዘመናት ጥርጣሬያቸውን የገለጠ ድል ነው። ከምንም በላይ ግን አድዋ የታሪክ ዑደት በተለየ አቅጣጫ የሚቀጥልበትን የጨዋታ ሕግ ያስተዋወቀ እውነታ ነው።

ፕ/ር ሬይሞንድ ጆናስ
ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ

# ክፍል አንድ

# የአድዋ መንገድ





## ምዕራፍ አንድ

## የንጉሥ ሕልም

አጋጣሚው ለዘመናዊ ፖሉቲካ ወዳጅነት ምስረታ ተስፋ ሰጪ የሆነ ዕድልን ሚኒልኩ ያጠራጥራል። በዛፍ እንጨት እና በሳር ክዳን ተውቦ ከተሠራው አልፍኝ ውስጥ ወጣቱ የሸዋ ንጉሥ ባማረ ዙፋኑ ላይ እግሮቹን አደራርቦ ተቀምጧል። ራሱ ላይ ያለረው ነጭ የሐር ሻሽ ግንባሩን በክፈል ሸፍኖት ከጀርባው በኩል ትከሻው ላይ ፈርቋል። እንዲህ ግርማ ሞገስ ተላብሶ የተቀመጠው ንጉሥ ምኒልክ የአንበሳ ቆዳ ሰንዶሉ ኹለት የክብር ዘበኞች ግራና ቀኝ ታጅበ ተቀምጠ ፂሙን ያፍተለትላል።

በአልፍኙ ኹለት በሮች በኩል የሚገባው ብርሐን ከንጉሡ አጠገብ ሚቀመጠውን ወጣት መሐንዲስ ያሳያል። በኤደን ከሚገኘው የስዊዘርላንድ ሚሲዮድስና ተቋም ኢቸር ኤንድ ፉሪር የተላከው ወጣት ባለ ሰፊ ደረት ሲሆን ረጅም ፂሙ ካአልፍሬድ ሌኒን ወይም ፍሬድሪክ ኤንግልስ ጋር ያመሳስሉዋል። ወጣቱ መሐንዲስ አልፍሬድ ኢልግ ነበር።

በ1879 ከኢልግ ጋር ሲገናኝ የምኒልክ ዕድሜ ከሠላሳ አምስት ዓመት አይበልጥም ነበር። ነገር ግን የተሸበሸበ የፊቱ ቆዳ እና የፈንጣጣ በሽታ ጥሎበት ያለፈው የጠቃጠቆ ምልክት ወጣቱን ንጉሥ ከዕድሜው በላይ ያረጀ አስመስሎታል ነበር። ምኒልክ መልከ መልካም ባይሆንም በተለያየ ጊዜ ቀርበው ያነጋገሩት ሰዎች ፊቱ ላይ ስለሚነበቡት የደግነት፣ የወዳጅነት እና የአስፈሪነት ገፆች ተናግረዋል።

ፈረንሳዊው የፎቶ ግራፍ ባለሙያ አልፎንሴ ኢውበሪ በ1880ዎቹ ምኒልክን አግኝቶት ነበር። ፈረንሳዊው የምኒልክን አስፈሪ ፊት ሲገልጽ አያይዞ የጠቀሰው የንጉሡን የሚያማምሩ ንቁ ዐይኖች ነበር። በተመሳሳይ ዓመት ከፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወደ ምኒልክ የተላከው ካፒቴን ሎንግ ቦይስ ‹‹የፈንጣጣ ምልክቱ

ሰምኒልክ አስፈሪ ገጽታ የሰጠው ቢሆንም ከጥቂቁር ዓይኖቹ የሚወጣው የወዳጅነት አስተያየት አስፈሪነቱን በመቀነስ የንጉሡን ተወዳጅ ገጽታ ያሳያሉ›› በማለት ተናግሯል።

እንግሊዛዊው ጋዜጠኛ እጉስተስ ዋይልድ በበኩሉ ስለምኒልክ ባለ ስፌ ክፈፍ ጥቁር ባርኔጣ ጽፏል። የንጉሥ ባርኔጣ በዚያ ዘመን አየርላንድ ውስጥ የፀረ-ኤምፔሪያል ተቃውሞ መግለጫ መሸኑን ምኒልክ ማወቁ ቢያጠራጥርም አጋጣሚው ግን ከንጉሡ አቋም ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ጽፎ ነበር። ሌላው እንግሊዛዊ ዲፕሎማት ሰር ሬኔል ሮድ የምኒልክን ገጽታ ‹‹ኃይለኝነት የተሞላ ሲሆን ባሕርያቸው በአክብሮት የተሞላ እና ንጉሣዊ ግርማ ሞገስ የሚታይበት ነው።›› በማለት ተናግሮ ነበር።



*ምስል 1፡ አፄ ምኒልክ*





ከምኒልክ አጠገብ የተቀመጠው አልፍሬድ ኢልግ ባለ እንጨት ፍሬም መነፅሩ መምህር አስመስሎታል። በለሚን ስዊዘርላንዷ ተራራማ ከተማ ፍራውንፌልድ የተወለደው ኢልግ ወደ ዙሪክ በማምራት የኹለተኛ ደረጃ ትምህርትን ተከታትሏል። በ1878 በኢቸር ኤንድ ፉረር ኩባንያ ተቀጥሮ ወደ ቀይ ባሕር አካባቢ ሲመጣ ዕድሜው ሐያ አምስት አይሞላም ነበር። ምኒልክን ለማግኘት ከሶማሌ ጠረፍ እስከ አንኮበር ያደረገው ጉዞ ፈታኝ ሆኖበት ነበር። ወደ ኢትዮጵያ የሚያመሩ ተጓዥ ነጋዴዎችን ጥበቃ ዘይላ ወደብ ላይ ለሳምንታት የተጉላላ ሲሆን፣ ከነጋዴዎቹ ጋር ተገናኝቶ ጉዞ ከጀመረ በኋላም መጉላላቱ ቀጥሎ ነበር። በወቅቱ የነበሩ ነጋዴዎች ከአፋር የጎሳ አባቶች ቀረጥ ለማምለጥ ሲሉ የሚከተሉት አማራጭ መንገድ አንድ ወር ተኩል ይወስድ ነበር።

አልፍሬድ ኢልግ ኢትዮጵያ እንዲመጣ የገፋፋው ከዓመታት በፊት በግብፅ ስኬታማ ቆይታ ያደረገው የአገሩ ልጅ ወርነር ሙዚንገርን ታሪክ ካነበበ በኋላ ነበር። ለግብፅ ንጉሥ ኸዲቭ አስማኤል አማካሪ በመሆን በካይሮ የቆየው ሙዚንገር የንጉሡን የዘመናዊነት እንቅስቃሴ በማገዝ ይታወቃል። በ1870ዎቹ ከቀይ ባሕር እስከ ሱዳን የተዘረጋ ግዛቱን እንዲያስተዳድርለት ንጉሡ ሙዚንገርን ሾሞት ነበር። የሙዚንገርን ስኬት የተመለከተው ኢግል ለዘመናዊነት ካለው ጽኑእ ፍላጎት የተነሣ ነበር ወደ አንኮበር የዘለቀው።

ወጣቱ ንጉሥ ምኒልክም ለዘመናዊነት ፍላጎት ስኬት አጋዥ እንዲሆነው ነበር ኢልግን የቀጠረው። ከምህንድስና ሙያው በተጨማሪ በቀላሉ የመላመድ ችሎታ የነበረው ኢልግ ከኢትዮጵያ አኗኗር ጋር ለመላመድ ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም። ፒሙን ተላጨ፣ ኢትዮጵያዊት ሴት አግብቶ ቤተሰብ መሠረተ፣ አማርኛ ቋንቋም ተማረ። በ1884 ሠላሳ ዓመት የሞላው ኢልግ የግንባታ ዕቅድ አውጥቶ ለምኒልክ አቀረበ። ንጉሡም የቤተ መንግሥት ግንባታ ኃላፊ እና የመንገድ እና ድልድይ ሚኒስቴር አደረጉት።



ምስል 1: ለኔ ምኒልክ



ምስል 2፦ ሰልፍረድ ሊልግ፦ መጋቢት 29 ቀን 1896

በአሮር ጊዜ ቀይታው በንጉሡ ዘንድ ታማኝነትን ያተረፈው ሊልግ በምኒልክ እና በጣይቱ ወደ አውሮፓ ተላከ። የመልዕክቱ ዋና ይዘት የነበረው ለዘመናዊት ኢትዮጵያ ግንባታ አጋዥ የሆኑ ቁሳቁሶችን መግዛት ነበር። ወደ አውሮፓ ካቀና በኋላ ንግሥት ጣይቱ ተጨማሪ ዕቃዎችን እንዲገዛላቸው ደብዳቤ ጽፈውለት ነበር። የንግሥቲ ተጨማሪ ትዕዛዝ የጫማ ቁጥራቸውን እና የተለያዩ የእርሻ ዘመናዊ ቁሳቁሶችን ዝርዝር የያዘ ነበር። ከደብዳቤዎቻው ግርጌ የሚያርፈው የንግሥቲቲ ማህተም እንዲህ ይነበባል። ‹‹ንግሥት ጣይቱ፣ ብርሐን ለኢትዮጵያ››





ሊልግ ከአውሮፓ በርካታ ዘመናዊ ቁሳቁሶችን ጭኖ የመጣ ሲሆን በወቅቱ ካመጣቸው ቁሳቁሶች መካከል አንዳንዶቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ናቸው። የጎትመት መሣሪያ፣ ሰፋፊ ባርኔጣ፣ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ፣ ሳሙና፣ የተለያዩ መጫሚያዎች፣ እና ትራሶችን ጨምሮ በርካታ ቁሳቁስ ነበር ይዞ የተመለሰው።

የምኒልክን በ1889 ዘውድ መጫን ተከትሎ ሊልግ የንጉሡ አማካሪ በመሆን ተሾመ። በዘውድ አማካሪነቱም የእንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ጀርመንኛ እና አማርኛ ቋንቋ ችሎታውን በመጠቀም ጉልህ ሚናን ተጫውቷል። የከተማ ግንባታውን በመቀጠል በ1894 ከእንጦጦ እስከ ቤተ-መንግሥት የሚደርስ የውሃ መስመር ዘረጋ። ከአድዋ ጦርነት በኋላ የጣሊያን ምርኮኞችን በተመለከተ ምኒልክ የሊልግን ምክር ይጠይቁ ነበር። በአጠቃላይ ሊልግ የግንባታ ባለሙያ፣ አስተርጓሚ፣ የመሣሪያ ገዢ፣ ዲፕሎማት እና አማካሪ በመሆን ምኒልክን አገልግሏል።

የሊልግ እና የምኒልክ ወዳጅነት የተመሠረተው ለኢትዮጵያ መፃኢ ዕድል ወሳኝ በሆነ ወቅት ነበር። ወቅቱ በአሜሪካ የቅኝ ግዛት ቀይታቸው እያከተመ የነበረው አውሮፓውያን ጥቁር አፍሪካን እንደ ቀጣይ ማረፊያቸው በመመልከት አዲስ እንቅስቃሴ የጀመሩበት ነበር። በተለይም ከፈረንሳይ አብዮት እና ከናፖሊዮን ጦርነቶች በኋላ አውሮፓውያኑ አዲስ የመስፋፋት እንቅስቃሴ በመጀመር አፍሪካን የዐይናቸው ማረፊያ ያደረጉበት ነበር። በዚህም የተነሣ በደቡባዊ አፍሪካ ከ1815 በኋላ የጀመረው የአውሮፓውያን የሰፈራ ቅኝ ግዛት በሰሜን አፍሪካ ደግሞ በ1830 አልጀሪያን የመጀመሪያ መጻረሻው በማድረግ ቀጥሎ ነበር።

በ1850ዎቹ የአትላንቲክ የባሪያ ንግድ እያከተመ የነበረ ቢሆንም የቤልጅየሙ ንጉሥ እንደ አዲስ የጀመረው የባሪያ ንግድ እንቅስቃሴ የአህጉሪቷን የሚይኑፍ የባሪያ አቅርቦት ለተቀሩት አውሮፓውያን ጠቁሟል። እንደ ፖርቹጋል፣ ሆላንድ እና ቤልጅየምን የመሳሰሉ ትናንሽ ሐገራት በአፍሪካ ታሳቅ ሕልማቸውን ማሳካት እንደሚችሉ ያሳዩበት ወቅትም ነበር።



ከትናንሽ የአውሮፓ አገራት እንቅስቃሴ ጎን ለጎን ትላልቆቹ አገራት አብዛኛውን የአፍሪካ ክፍል በስፋት መያዝ ጀምረው ነበር። ታላቋ ብሪታኒያ ከካይሮ እስከ ደቡባዊው የአፍሪካ ጫፍ ለመያዝ ስትንቀሳቀስ፣ ፈረንሳይ በበኩሏ ሰሜን እና ምዕራብ አፍሪካን ዋና መቀመጫ በማድረግ በምሥራቅ አፍሪካ የሶማሊያ ጠረፍ አካባቢ ተጨማሪ ይዞታን አስከብራለች። የጀርመኑ መራሄ መንግሥት ቢስማርክ በ1884 አውሮፓውያኑን በርሊን ላይ በመሰብሰብ የአፍሪካ ቀጣይ ዕድል በአውሮፓውያን ብቻ እንደሚወሰን አስረግጦ በመናገር ቅርምቱ ሰላማዊ የሚሆንበትን መንገድ አመቻቹ። እንግዲህ አልፍሬድ ኢልግ እና ምኒልክ በ1878 ሊገናኙ የአፍሪካ ዕጣ ፈንታ በአውሮፓውያን እጅ ላይ ሊወድቅ ተቃርቦ ነበር።

## በቴዎድሮስ ላይ የተደረገው ዘመቻ፡- የወረራ ቅድመ ሁኔታ

በ19ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ በበርካታ ግዛቶች ተከፋፍላ ተጠሪነታቸው ለይስሙላ ለተቀመጡ ንጉሠ-ነገሥት ባደረጉ በርካታ ነገሥታት ትተዳደር ነበር። ከምኒልክ በፊት በ19ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ኹለት ጠንካራ ንጉሠ-ነገሥታት ቴዎድሮስ እና ዮሐንስ ነበሩ። ኹለቱም ነገሥታት ከግዛት አስተዳዳሪነት ተነሥተው ዘውድ ለመጫን የበቁት ሽፍትነትን እንደ አማራጭ በመጠቀም ነበር። በኢትዮጵያ ቀደምት ፖለቲካ ባሕል መሠረት ሽፍትነት ሥልጣን ለማግኘት ዓይነተኛ መንገድ እንደሆነ ይታመናል።

የቴዎድሮስ የንግሥና ጉዞ የጀመረው በሽፍትነት ነበር። በ1818 ምዕራብ ጉንደር አካባቢ የተወለደው ካሳ ሃይሉ አባቱ በልጅነቱ ጥሎት ስለሸፈተ በእናት ብቻ ለማደግ ተገድዶ ነበር። በወጣትነት ዘመኑ የነበሩ ፖለቲካዊ ተቀናቃኞቹ ከዝቅተኛው ማሕበረሰብ መገኘቱን ደጋግመው በማንሳት ያሾሟጥጡት ነበር። በተለይም የእናቱን ኮሶ ሻጭነት በማንሳት ስለ መሠረተ-ድህነቱ እና ዘረ-ቢሥነቱ የሚናገሩ በርካቶች ነበሩ።

በወጣትነት ዕድሜው ነበር ካሳ ኃይሉ ሽፍትነትን እንደ ፖለቲካዊ ተቃውሞ መግለጫ በመጠቀም የሥልጣን ጉዞውን የጀመረው። በመቀጠል በግዛቱ ባገኘው ተቀባይነት እና በፈጸመው ፖለቲካዊ ጋብቻ በመንጠላጠል የዘውድ ተቀናቃኞቹን





አንድ በአንድ አስወገደ። በ1855 አፄ ቴዎድሮስ በሚለው የንግሥና ስሙ በደረስጌ ማርያም ቤተክርስቲያን ዘውድ ሲጭን የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነት በማረጋገጥ «ክርስቲያናዊት ኢትዮጵያን» በቀጠናው ልዕለ-ኃያል የማድረግ ዓላማን አንግቦ ነበር። ለዓላማው መሳካት ቁልፍ እገዛ ያደረገለት የ33 ዓመቱ እንግሊዛዊ አማካሪው ዋልተር ፐላውደን ወደ ለንደን በርካታ ደብዳቤዎችን በመጻፍ ስለ አፄ ቴዎድሮስ የዘመናዊነት ሕልም ለንግሥቲቷ አሳውቋል።

ዋልተር ፐላውደን ለእንግሊዟ ንግሥት በተደጋጋሚ በጻፋቸው ደብዳቤዎቹ አፄ ቴዎድሮስ የባሪያ ንግድ ማስቀረታቸውን ጠቅሶ እገሩ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነቷን እንድታጠናክር መክሯል። ክርስትናን እንደ ኹለተኛ ግንኙነት መሠረት በመጥቀስም እንግሊዝና እና ኢትዮጵያ እስላማዊውን የግብጽ መንግሥት በጋራ መቋቋም እንደሚችሉም ፐላውድን ለንግሥቷ አስተያየት ሰጥቶ ነበር።

አፄ ቴዎድሮስ ዘውድ በጫኑ ማግስት ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ ደጋማ ግዛቶች ጀምሮ እስከ ቀይ ባሕር ዳርቻ የሚደርስ ክርስቲያናዊ ግዛተ-አፄ የመገንባት እንቅስቃሴያቸውን ጀመሩ። በ1856 ወደ ሸዋ በመዝመት ግዛቱን ሙሉ በሙሉ አስገበሩ። ቴዎድሮስ ሸዋን ባስገበሩ ማግስት የሸዋው ንጉሥ ሳህለ-ሥላሴ በሕመም ምክንያት ዐረፉ። አፄ ቴዎድሮስም የንጉሡን ልጅ ምኒልክን ወደ ጉንደር ይዘው ተመለሱ። ምኒልክም ከጎንደር አምልጦ ወደ ሸዋ እስከተመለሰበት ወቅት ድረስ በግዞት በአፄ ቴዎድሮስ ሥር ቆይቷል። ከሸዋ በመቀጠል ወደ ሙስሊም አሮሞዎች ግዛት እና የቀይ ባሕር ዳርቻ የሙስሊም ከተሞች ያደረጉት ዘመቻ ለአፄ ቴዎድሮስ ሠራዊት ቀላል ድል አላስገኙላቸውም ነበር።

ከንግሥናም በኋላ የቀጠለው የአፄ ቴዎድሮስ ሽፍታዊ አስተዳደር እና ዘመቻ ለንጉሡ ያተረፈላቸው ነገር ቢኖር በአገር ውስጥ ዐመኔታን ማጣት ነበር። በየዘመቻው ወቅት ወታደሮቻቸው የሚያሳዩት ሽፍታዊ ባሕርይ ገበሬውን አማረረው። በተለይም ምርቱን እና ከብቱን በአፄ ቴዎድሮስ ወታደሮች እየተቀማ የተቸገረው ገበሬ

ለንጉሡ ክስ ሲያስገባ የተሰጠው ምላሽ ‹‹ገበሬው ወታደሩን የመመገብ ግዴታ አለበት›› የሚል ነበር። በዚህ የተነሣም ገበሬው ለአፄ ቴዎድሮስ ‹‹አባ በዝብዝ›› የሚል ቅፅል ስም ሰጣቸው። በመቀጠልም ገበሬዎች ምርት እና ከብቶቻቸውን መሸሸግ ጀመሩ። አፄ ቴዎድሮስም መደናገጥ የጀመሩት በዚያ ወቅት ነበር።

ከአገር ውስጡ ችግር በተጨማሪ የአውሮፓውያኑ የዘገየ ምላሽ እና ዝምታ ንጉሡን አበሳጫቸው። በ1862 ለንግሥት ቪክቶሪያ የፃፉት ደብዳቤ በእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ታፍኖ በመቅረቱ መልስ አልተሳከላቸውም ነበር። በዚህ የተበሳጩት አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን የእንግሊዝ ሚሲዮናውያን ጠራርገው በማሠር ለክርስቲያናዊት ኢትዮጵያ ወንጌል ሰባኪ እንደማያስፈልጋት ተናገሩ። አሥረኞቹን በማስገደድም በመንገድ ግንባታ እና የተለያዩ ሥራዎች አሠማሩ። ንጉሡ ‹‹ሴባስቶፖል›› የሚል ክርስቲያናዊ ስም የሰጡትን መድፍም ያሰሩት በዚያ ወቅት ነበር።

ከሚሲዮናውያኑ በመቀጠል የእንግሊዝ ቋሚ መልዕክተኞችን አሠሩ። እሥረኞቹን እንዲፈቱ በእንግሊዝ መንግሥት በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ንጉሡ በእምቢታቸው ጸኑ። ይባስ ብለውም በ1867 እስረኞችን እንደማይፈቱ በግልጽ አሳወቁ። በቀጣዩ ዓመት እንግሊዝ የታገቱ ዜጎቿን ለማስፈታት በጀነራል ሮበርት ናፒየር የተመራ ጦሯን ወደ ኢትዮጵያ አዘመተች።

በወርኃ ጥር 1868 የእንግሊዝ መርከቦች ከምጽዋ በስተደቡብ የምትገኘው ዙላ ወደብ ደረሱ። በሺዎች የሚቆጠሩ የሕንድ ቅጥረኞች፣ የእንግሊዝ ወታደሮች እና ወደ ሹሰት ሺህ የሚጠጉ የቻይና መንገድ ሠራተኞችን ጨምሮ አጠቃላይ ከሐያ ሺህ በላይ ሠራዊት ዙላ ላይ ተራገፈ። ከወታደሮቹ በተጨማሪ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የጋማ ከብቶች እና አርባ አምስት የሕንድ ዝሆኖች ይገኙበት ነበር። የናፒየር ዘመቻ አወቃቀር በወቅቱ የእንግሊዝን ኩሰንተናዊ ኃይል ለማሳየት በይሁንታ የታቀደ ነበር።







The Napier Expedition. From Roger Acton, *The Abyssinian Expedition and the Life and Reign of Theodore*. London: Illustrated London News, 1868.

ምስል 3፡ የናፒየር ዘመቻ- ክሮርር አክተን ምስል ላይ የተወሰደ (ለንደን ኒውስ፣ 1868)

ከሳምንታት በኋላ የናፒየር ጦር ከቀይ ባሕር ጻርቻ ወደ ተራራማው ሰሜናዊ የኢትዮጵያ ግዛት የሚያደርገውን ጉዞ አጋመሰ። በሕንጻውያን ቅጥር ሠራዊቶች የሚነዱት ዝሆኖች ያልተገጣጠሙ አርምስትሮንግ የጦር መሣሪያዎች ተሸክመው ነበር።

ጣዒንቱ በመጀመሩ በፊት አፄ ቴዎድሮስ በጉዞ ላይ የነበረው የናፒየር ጦር ላይ የሽምቅ ውጊያ ቢከፍቱ ኖሮ ውጤቱ የተሰየ ይሆን ነበር። ነገር ግን አፄ ቴዎድሮስ የመረጡት አካሄድ ወታደሮቻቸውን ጥቂት ዘመናዊ ጠመንጃ፣ ጦር እና ጎራዴ አስታጥቀው በሰቅሰት ዕለት ሚያዝያ 10 ከመድፈኛ እና አልሞ ተኳሽ የናፒየር ወታደሮች ጋር መግጠምን ነበር።



Napier expedition. From Roger Ascott, *The Abyssinian Expedition and the Life and Reign of King Theodore*. London: Illustrated London News, 1868.

የናፒየር ዘመቻ- ክፍተር አሎሶን ምስል ላይ የተወሰደ (በንደን ኒውስ፣ 1868)

ውጤቱን ማንም ሊገምተው የሚችል ነበር። በመቶዎች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሲሞቱ ከሐያ ያልበለጡ የናፒየር ወታደሮች ቆሰሉ። አፄ ቴዎድሮስ ለድርድር ጥያቄ ከማቅረብ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። የተወሰኑ እሥረኞችን ከለቀቁ በኋላ አንድ ሺህ የቀንድ ከብት እና አምስት መቶ በጎችን ለናፒዬር ወዳጅነት ስጦታ በማቅረብ የድርድር ጥያቄ አቀረቡ። ነገር ግን ናፒየር ጥያቄውን ባለመቀበል ግስጋሴውን ቀጠለ።

የናፒየር ወታደሮች መቅደላ ላይ ወደሚገኘው የንጉሡ የመጨረሻ ምሽግ ሲቃረቡ የቴዎድሮስ ጦር በአንፃሩ መበታተን ጀምሮ ነበር። የእንግሊዝ ሠራዊት ወደ ተራራው በመውጣት እሥረኞቻቸውን ለማስፈታት እንቅስቃሴ ጀመሩ። በዚያ ቅፅበት ነበር አፄ ቴዎድሮስ በሸጉጣቸው እራሳቸውን ያጠፉት።

እንግሊዝ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት የመያዝም ሆነ የተለየ ዓላማ አልነበራትም። የእንግሊዝ ፀብ ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር እንጂ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አልነበረም። ዘመቻው እንደተጠናቀቀ ናፒየር ዓዙን ሸክፎ የመልስ ጉዞ የጀመረውም ለዚህ ነበር።

የእንግሊዝ ጦር ከኢትዮጵያ ሲወጣ ለቀጣይ ወረራ የሚሆን መንገድ አመቻችቶ ነበር። ለናፒየር ጦር መተላለፊያ በማመቻቸትና መንገድ በመምራት ልዩ እገዛ ላደረገው ለትግራዩ ካሳ በርካታ የጦር መሣሪያዎችን በመስጠት ነበር ናፒየር ውለታውን የመለሰው። የአፄ ቴዎድሮስ መወገድ እና በእጁ የገባው የእንግሊዝ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የትግራዩ ካሳ በቀጣይ ለሚያደርገው የዘውድ ግስጋሴ ቀና መንገድ እንደሚፈጥሩለት ግልጽ ነበር።

እንግሊዝ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት የመያዝ ፍላጎት ባይኖራትም የናፒየር ዘመቻ ግን ፍላጎቱ ለነበራቸው ግብፅ እና ጣሊያን እንደ መነሻ ማገልገሉ አልቀረም። እንግሊዞቹ ከአገር ውስጥ የኃይል ተፎካካሪ ጋር በማበር እንዴት ንጉሠ ነገሥት





ማስወገድ እንደሚቻል ለግብጽ እና ለጣሊያን አሳይተዋል። ናፒየር የትግራዩን ካሳ በቴዎድሮስ ላይ በማሥነሳት የተሳካ ዘመቻ ማድረጉ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያን ሠራዊት ደካማ የውጊያ ብቃት ለማሳየት ችሏል።

### የግብፅ በኢትዮጵያ ላይ መነሳት

ከአፄ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ባሉት ሦስት ዓመታት የትግራዩ ካሳ ከእንግሊዝ ባገኘው የጦር መሣሪያ በመታገዝ ተቀናቃኞቹን በማስወገድ ሥልጣኑን በእጁ ለማማከል ተንቀሳቀሰ። በወርኃ ጥር በ1872 በአክሱም ጽዮን ማርያም ቤተክርስቲያን ‹‹አፄ ዮሐንስ አራተኛ›› በሚል የንግሥና ስም ዘውድ ጫኑ።

የናፒየርን ዘመቻ ተከትሎ በኢትዮጵያ የተፈጠረውን አለመረጋጋት በመጠቀም ግብፅ የመስፋፋት እርምጃዋን ጀመረች። ኮዲቭ እስማኤል የግብፅን ጥንታዊ ክብር ለመመለስ በማሰብ የግዛት ማስፋፋት እንቅስቃሴውን ወደ ሱዳን፣ ኢትዮጵያ እና ሱማሌ ማድረግ ጀመረ። በ1865 ምፅዋን በመቆጣጠር ስዊዘርላንዳዊውን ወርነር ሙዚንገር የግዛቱ አስተዳዳሪ በማድረግ ምፅዋ ላይ አስቀመጠው።

ከናፒየር ተሞክሮ በመነሳት ኮዲቭ እስማኤል ከኢትዮጵያ ውስጥ በመሆን አፄ ዮሐንስን የሚያዳክምለት ወዳጅ ማፈላለግ ጀመረ። የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ የግዛት ነጻነት እንደሚፈልግና የዮሐንስን ንጉሠ ነገሥትነት ላለመቀበል እንደሚያንገራግር ሲሰማ እስማኤል አጋጣሚውን ሊጠቀምበት ወሰነ። ምኒልክ ከጀርባ አፄ ዮሐንስን እንደሚያዳክምለትም ተስፋ አደረገ።

በ1875 ግብፅ ሐረርን በመቆጣጠር ከሸዋ ወደ ጅቡቲ የተዘረጋውን የምኒልክ የንግድ መሥመር ዘጋች። የምኒልክን ወጪ እና ገቢ ንግድ በማስተጓጎል ዓላማዋን ለማሳካትም ተስፋ አደረገች። እንደ ተጨማሪ መደለያ ለምኒልክ ዘመናዊ የጦር

መሣሪያ በማቅረብ ከአፄ ዮሐንስ ጋር ለሚያደርገው ፉክክር እገዛ ሰጣድረግ ቃል ገባች።

በሰሜን የአገሪቱ ክፍል ጠንካራ ድጋፍ የነበረው አፄ ዮሐንስ ሰግበፅ ተደጋጋሚ ትንኮሳ የሚሸበር አልሆነም። በተሰይም የንጉሡ አስተዳደራሮ ፍፅበናና በክርስትና ዕምነት ላይ የተመሠረተ መሽኑ የግብፅን እስላማዊ ኃይል ለመመከት ሕዝቡን በቀላሉ ማስተባበር ችሎ ነበር። ይሄንን በመመልከት ግብፅ የሙስሊም ሕዝቦች መኖሪያ የኾኑትን የቀይ ባሕር ዳርቻ፣ ምፅዋ እና የሐረር አካባቢን ሰቀቀዳማ ያዘች።

በ1875 ግብፅ ቁጥሩ ወደ ዐሥራ አምስት ሺህ የሚጠጋ ጦሯን በዮሐንስ ላይ አዘመተች። የግብፅን ጦር ይመሩ የነበሩት በ1860ዎቹ ቦአውሮፓ የተሰያዩ የጦር ሜዳዎች ላይ የተሰለፉ የዴንማርክ፣ ጀርመን እና የኦስትሪያ ወታደራዊ መኮንኖች እና ከአሜሪካ የሲቪል ጦርነት የተረፉ የጦር መኮንኖች ነበሩ። የዘመቻው ዋና ዓሳማ አፄ ዮሐንስን በማስወገድ ከቀይ ባሕር በስተምዕራብ እና ከመረብ ወንዝ ባስተሳሰጌን የሚገኘውን ግዛት በቁጥጥር ሥር ማዋል ነበር።

በዘመቻው ዕቅድ መሠረት የምፅዋው ገዥ ሙዚንገር ለምኒልክ የጦር መሣሪያ ለማድረስ ተንቀሳቀሰ። ነገር ግን ቁጥሩ ወደ አራት መቶ የሚጠጋው የሙዚንገር ኃይል ምኒልክ ጋር አልደረሰም። በሕዳር 7 ቀን 1875 በሸዋ የንግድ መስመር ላይ ሕልውናቸው የተመሠረተው የአፋር ሕዝቦች የሙዚንገርን ሠራዊት፣ ኢትዮጵያዊት ሚስቱን እና ልጁን ጨምሮ ገደሏቸው። በተመሳሳይ ዕለት በሰሜን ግንባር የተንቀሳቀሰው የግብፅ ጦር ጉንደት ላይ በዮሐንስ ሠራዊት ከፍተኛ ጉዳት ደርሰበት ተፈታ።

ከጥቂት ወራት በኋላ በአሉላ የተመራ የዮሐንስ ልዩ ኃይል የግብፅን ጦር ጉራ ላይ ድል በመንሰት ከግማሽ በላይ የሚኾኑትን የግብፅ ሠራዊት ሙት እና ቁስለኛ አደረገ። ከጉራው ሽንፈት በኋላ የአስማኤል የተስፋፊነት ሕልም ሙሉ በሙሉ





ጨለመ። ከሦስት ዓመት በኋላ ለአስማኤል መንግሥት መወገድም የጉራ ሽንፈት አስተዋፅዖ ነበረው። ከደማቁ የጉራ ድል በኋላ ኢትዮጵያ ግዛቷን በማስከበር ኤርትራን ጠቅልላ ፖለቲካዊ ድንበሯን የቀይ ባሕር ዳርቻ አደረገች።

በጉራ ላስመዘገበው ደማቅ ድሉ አፄ ዮሐንስ ለጦር መሪያቸው አሉላ የራሥነት ማዕረግ ሰጡት። በመቀጠልም መቀመጫውን አስመራ በማድረግ ባሕሪ ነጋሽን እንዲያስተዳድር ሾሙት። ሰሜናዊውን ቀጠና ለራስ አሉላ በመስጠት አፄ ዮሐንስ ትኩረታቸውን ወደ መሃል አገር አደረጉ።

አፄ ዮሐንስን በግብፅ ወራሪ ኃይል ተፅዕኖ ሥር የወደቁ ሙስሊም ሕዝቦችን በ1880 በመሰብሰብ የክርስትና ዕምነት እንዲቀበሉ፤ አለበለዚያ አገሪቷን ለቀው እንዲወጡ አዘዙ። በመቀጠል ከምኒልክ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር በ1882 ወንድ ልጃቸው ለምኒልክ ሴት ልጅ ዳሩ። ከፖለቲካዊ ጋብቻው በተቃራኒ ምኒልክ የዮሐንስን ዘውድ ለመንጠቅ የተለየ መንገድ ለመጠቀም ወሰኑ። በዚህም ከአፄ ዮሐንስ ጋር የገቡበትን ፖለቲካዊ ጋብቻ በመሠረዝ በጣይቱ ፖለቲካዊ ድጋፍ እየታገዙ ሥልጣኑን የሚቀሙበትን ወቅት መጠባበቅ ጀመሩ።

## የኢትዮጵያ የምንጊዜም ኃይለኛ ጥንዶች፡- ምኒልክ እና ጣይቱ

ጣይቱ ብጡል ከብረት የጠነከረ ልብ ያላቸው ሴት ነበሩ። ምኒልክ ከጣይቱ ጋር ጋብቻ ሲፈጽሙ የሸዋ ንጉሥ ብቻ የነበሩ ቢሆንም ኢትዮጵያን የመምራት ጽኑእ ፍላጎት ነበራቸው። እንደ ቀደምቶቻቸው ቴዎድሮስ እና ዮሐንስ ኹሉ የምኒልክም የዘር ሐረጋቸው ከንጉሥ ሰለሞን እና ንግሥተ ሳባ እንደሆነ ይታመን ነበር። የኹለቱ ጋብቻ ሰጣይቱ ብጡል የንግሥና ትንቢት ፍፃሜን አስገኝቶላቸዋል።




ምስል 4፡- ጣይቱ ብጡል፣ ከሉ ፔቲ ጋዜጣ የተወሰደ (መጋቢት 29 ቀን 1896)





ጣይቱ ብጡል በመልክ መልካምነታቸው እና በሩኅሩኀነታቸው ይታወቃሉ። ‹‹የአረብ›› ዝርያ ካላቸው አሮሞ አያቶታቸው እንደወረሷቸው የሚገመተው ረጃጅም ጣቶቻቸው እና ነጣ ያለ የቆዳ ቀለማቸው ለንግሥቷ ተጨማሪ ውበት ሆኗቸዋል። ሰፊ የእርሻ መሬት እና በርካታ የቤት እንስሳት ባለቤት የኾኑት ጣይቱ ብጡል ከምኒልክ ጋር ከመጋባታቸው በፊት አስቀድሞ ባለጸጋ ነበሩ።

የምኒልክ እና ጣይቱ ጋብቻ በዘመናዊ ፖለቲካ ውስጥ ወደር የማይገኝለት ጋብቻ ነበር። ኹለቱ ጥንዶች በፍጹማዊ መከባበር እና ልባዊ ፍቅር አብረው ኖረዋል። ከመጋባታቸው በፊት ኹለቱም በየፊናቸው ትዳር ነበራቸው። ወጣቱ ምኒልክ ከልዕልት አልጣሽ ቴዎድሮስ ጋር ያደረገው ጋብቻው የመጀመሪያው የነበረ ሲሆን ጋብቻው ከቴዎድሮስ ሞት በኋላ አልዘለቀም ነበር። ቀጥሎ ባፈና ከተባለች መልከመልካም ሴት ወይዘሮ ጋር ጋብቻ ፈጸሙ። እስከ ጣይቱ መምጣት ድረስ ምኒልክ በመልከኛዋ ባፈና ተፅዕኖ ሥር ነበሩ። በ1883 የፋሲካ ዕለት ከጣይቱ ብጡል ጋር ያደረጉት ጋብቻ ከቀድሞዎቹ ኹለት ጋብቻቸው በተለየ መልኩ የተጠና ነበር።

የምኒልክ እና ጣይቱ ጋብቻ በኹሉም ረገድ እንከን አልባ ነበር። ምኒልክ የንጉሥ ሕልም የነበረው ታላቅ ባል ሲሆን፣ ጣይቱ ደግሞ ሐብት፣ ፖለቲካዊ ብስለት እና ከሰሜኑ የአገሪቷ ክፍል ጋር ጥብቅ ቁርኝት ነበራት። የኢትዮጵያ ቀደምት ነገሥታት ከሰሜን አካባቢ የተነሡ በመሆናቸው ለምኒልክ የዘውድ ጉዞ የሰሜኑ ሕዝብ ይሁንታ ወሳኝ ነበር። ጣይቱም ለምኒልክ ይዘውሰት የመጡት ይዜንኑ ወሳኝ የመጫወቻ ካርድ ነበር። በሰሜን አካባቢ የተወለዱት ጣይቱ ብጡል ቤተሰቦቻቸው በጌምድር እና ትግራይን ጨምሮ በሰሜን ሰፊ ዕውቅና ነበራቸው። ከሸዋ የአገሪቷ ክፍል ለመጡት ምኒልክ የሰሜኑን ሕዝብ ተቀባይነት ያስገኙላቸው ጣይቱ ብጡል ነበሩ።

በፖለቲካው ረገድ የጣይቱ አንደበተ ርቱዕ መሆን እና ያላቸው ተሰሚነት ለምኒልክ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል። ጣይቱ ብጡል ከሙስሊም አሮሞ ቤተሰብ



S. M. TAITOU
Impératrice d'Abyssinie

Empress Tayitu. From *Le Petit Journal*, 29 March 1896.

ምስል 4፡- ጣይቱ ብጡል፣ ከሌ ፔቲ ጋዜጣ የተወሰደ (መጋቢት 29 ቀን 1896)

እንደተወለዱ እና ቤተሰቦቻቸው ከወሥራ ስምንተኛው ክፍለዘመን ጀምሮ የክርስትናን ዕምነት እንደተቀበሉ ይነገራል። ከዚያ ጀምሮ የጣይቱ ቤተሰቦች መቀመጫቸውን በሰሜን በማድረግ ከፍተኛ ሀብት እና ተቀባይነት አፍርተዋል። የሚስታቸው ተቀባይነት ነበር ለምኒልክ የሥልጣን ጉዞ መንገዱን ያቀለለላቸው።

ንግሥት ጣይቱ በጠንካራ ፖለቲካዊ አቋማቸው ይታወቃሉ። በተለይ ለአውሮፓውያን የነበራቸው ጥርጣሬ እና የማይወላውል አቋም ከምኒልክ በላይ አስፈሪ አድርጓቸው ነበር። በቤተ-መንግሥት ውስጥ ፀረ-አውሮፓዊ አቋም የነበራቸውን ጎበዝዝት በማስተባበር በተደጋጋሚ የምኒልክን ውሳኔ ማስቀልበስ ችለዋል። የምኒልክ ፖለቲካዊ ማዕከል በአዲስ አበባ እንዲሆን ካስደረጉ በኋላ ንግሥቲቷ የመዲናዋ ዋና ፖለቲካዊ ተዋናይ በመሆን ቀጠሉ።

ምኒልክ ለትዳራቸው ታማኝ እንዳልነበሩ ይነገራል። የንጉሡን በርካታ ቅምጦች በመታገስ ጣይቱ በሆደ ሰፊነት ኮሮአቸውን ገፍተዋል። ከየትኛዋም የንጉሡ ቅምጦች ጋር አሰጥ አገባ ውስጥ ገብተው አያውቁም ነበር። በአንድ ወቅት አንዷን የምኒልክ ቅምጥ በመርዝ መግደላቸው ተወርቶ ነበር። ንግሥቷ ትዳራቸውን ለማስከበር የተለየ እንቅስቃሴ አለማድረጋቸውን የተመለከቱ አንዳንድ ሰዎች ‹‹የዛሬዋ ንግሥት ነገ ተራ ሴት ወይዘሮ ልትሆን ትችላለች›› በማለት ተናግረው ነበር።

የንግሥት ጣይቱ ዕለታዊ እንቅስቃሴ የተጠና እና ዕይታ ለመሳብ ተብሎ የሚደረግ ነበር። ንግሥቲቷ አሻቢ ወይዛዝርቶችን ሲመርጡ የአሻቢዎቻቸው ቆዳ ጠቆር ያለ እንዲሆን ያመቻቹና የራሳቸው ወርቃማ የቆዳ ቀለም ጎልቶ እንዲታይ ያደርጉ ነበር። በመሃል አዲስ አበባ ሲጋር ፈረሳቸው ላይ ሆነው ሲዘዋወሩም የወርቅ ዘርፍ ያለው ጃንጥላ ይይዙ ነበር። እንቅስቃሴያቸው ፖለቲካዊ ዕውቅናቸውን ቢያጎላውም በተደጋጋሚ ለዕይታ መውጣታቸውን አንዳንድ ወግ አጥባቂ ኃይማኖተኞች አልወደዱላቸውም ነበር።





የበርካቶችን ተቃውሞ ንቀው በመተው ጣይቱ የአደባባይ እንቅስቃሴያቸውን ቀጠሉበት። ቀስ በቀስም ፖለቲካዊ ሥልጣናቸውን ማሳየት ሲጀምሩ በተቃዋሚዎቻቸው ዘንድ ሳይቀር ከበሬታን አገኙ። ጣይቱ ስለሚጠሏቸውም ሆኖ ስለሚቃወሟቸው ሰዎች ግድ አልነበራቸውም። በመጨረሻም ፖለቲካዊ ሥልጣንን እንደ ማኪያቬሊ መረዳት የጀመሩት ጣይቱ ብጡል የሚፈልጉትን አገኙ። ይኸውም ደጉ ባለቤታቸው ምኒልክ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ ሲሆን ጣይቱ ደግሞ ተፈሪ ኾኑ።

# ምዕራፍ ኹለት

## ጉዞ ወደ አድዋ

በኔፕልስ የሚገኙ መጠጥ ቤቶች ከአፍ እስከ ገደፋቸው ሞልተዋል። ከተለያዩ የጣሊያን ወታደራዊ ሰፈሮች የመጡት የጦር ሠራዊት አባላት በኔፕልስ የሚያደርጉትን የመጨረሻ የጥቂት ሰዓታት ቆይታ ለመሰናበት ራሳቸው በመጠጥ እያዝናኑ ነበር።

የጣሊያን የወደብ ከተማ የሆነችው ኔፕልስ ወታደሮች ለጉዞ በሚዘጋጁበት ወቅት የተለየ ድባብ ትላበሳለች። ወደ ግራኒሲ የጦር ሰፈር ወታደሮችን ይዘ የሚያልፈው ባቡር ኔፕልስ ላይ ቆሟል። ተሰፋሪ ወታደሮችም ከባቡሩ በመውረድ በወደቧ ያሉትን መጠጥ ቤቶች እና ካፍቴሪያዎች ሞሉ። በጂያርዲኖ ዲ ኢታሊያ የሚገኘው መጠጥ ቤት ለደንበኞቹ የምሽቱን የመጨረሻ ዙር መጠጥ ቀዳላቸው።

በማግስቱ ጠዋት ግራኒሲ የሚገኙት ወታደሮች ለጉዞ ዝግጅታቸውን እያከናወኑ ነበር። ከመሰታወት ፊት ቁሞ የደረት ኒሻኑን የሚያስተካክለው ጌራርዶ ፓንታኖ በኩራት የራሱን ምስል ተመለከተ። የፊቱ ገጽ ላይ ፍጹም ሰላማዊ መረጋጋት ቢመለከትም ስለ ወደፊቱ እርግጠኝነት አልተሰማውም። በተለይም ስለሚሄድበት የአፍሪካ አሕጉር ያለው ዕውቀት ውሱን መሆን አስፈርቶት ነበር።

ነጭ ሽሚዝና ሱሪ እንዲሁም ቡቲ ጫማ ያደረጉ ወታደሮች በመርከቡ መውጣጫ ወደላይ እየጎረፉ ነበር። ደረቅ መሬት ላይ የተሰበሰቡት ሲቪል ዜጎች ለተጓዥ ዘመዶቻቸው ነጭ መሃረቦቻቸውን በማውለብለብ የመጨረሻውን ስንበት በማድረግ ላይ ናቸው። ሌተናንት ፓንታኖ በወታደራዊው ልብስ ያሸበረቁ ወታደሮች ወደ መርከቧ ሲገቡ ተመለከተ።





የመርከቧ ልዩ ክፍል ውስጥ ፓንታኖ እና የልጅነት ጓደኛው ኡምቤርቶ በዝምታ ተቀምጠዋል። ኹለቱም ወደ አፍሪካ ሲዘምቱ የመጀመሪያቸው ነበር። ቀድሞ አፍሪካን የሚያውቁ የጉዞ አጋሮቻቸው የሚያወሩትን በጥሞና ነበር የሚያዳምጡት። ከኹለቱ ጋር በመጓዝ ላይ ከነበሩት መካከል በአቆርዳት ደርቡሽ ላይ ላስመዘገበው ድል ሜዳሊያ የተሸለመው ሌተናንት ቦራ፣ አረብኛ አቀላጥፎ የሚናገረው መድፍ ተኳሹ ሌተናል ካሩሶ እንዲሁም ስለ አፍሪካ በሰፊው የሚዘግበው የትሪቡና ጋዜጣ ዘጋቢ ሉጂ መርካቴሊ ይገኙበታል።

ፓታኖን እና ወታደሮቹን ያሳፈረችው የመንገደኞች መርከብ ‹‹ፖ›› የሚል ስያሜ ነበራት። ጣሊያን ጦር ሠራዊቷን ወደ ውጭ አገር ስትልክ እንደ ፖ ያሉትን የመንገደኞች መርከብ የመጠቀም ልማድ አላት። ፓታኖ መርከቧ ላይ የወጣው በመስከረም አጋማሽ 1894 ዓ.ም ነበር። ከወታደሮቹ ጋር አብረው የሚጓዙ ቤርካታ ሲቪሎች ተሳፍረዋል። ከተሳፋሪዎቹ መካከል በወቅቱ በመላው አውሮፓ ዝናቸው በመናኘት ላይ የነበሩት ‹‹ጉይላሜ እህትማማቾች›› የሰርከስ ቡድን ይገኝበታል። የሰርከስ ቡድኑ ከወታደሮቹ ጋር የሚጓዘው እስከ አሌክሳንድሪያ ብቻ ነበር። በአሌክሳንድሪያ ትርኢታቸውን ካሳዩ በኋላ ደግሞ ዕድል ወደሚጠራቸው ቦታ ያመሩና በመጨረሻም ወደ አውሮፓ ይመለሳሉ።

ባለ ሦስት ምሰሶዋ የእንፋሎት ሞተር መርከብ ፖ የተለያዩ የመንገደኞች ቁሳቁሶችን ከጫነች በኋላ ለጉዞ ዝግጁ ሆነች። ፓታኖ እና ፐርቲኒ የመርከቧ የላይኛው ወለል ላይ ሆነው የወደቡን እይታ በመሰናበት ላይ ነበሩ። ከኹለቱ መኮንኖች ጋር የጉይላሜ እህትማማቾች ወለሉ ላይ ነበሩ። ለትርኢት የሚያቀርቧቸው ዝንጀሮ፣ አዕዋፍ፣ ድብ እና የመሳለሉት እንስሳትም በፍርግርግ ውስጥ ተቀልፎባቸው የተጫኑት በዚሁ የመርከቧ የላይኛው ወለል ላይ ነበር።

ጣሊያን ከሚገኘው ግዙፍ ወንዝ ስያሜዋን ያገኘችው ፖ የኔፕልስን ወደብ ወደ ኋላ በመተው ጉዞዋን ጀመረች። ጥንታዊ ወደቦች በኹለት ሶሬንቶ እና ካፕሪ

መካከል አድርጋ የሞተሯን ጭስ እያሳየች ጉዞዋን ቀጠለች። የዓሣ አጥማጆች መኖሪያ የሽኑትን ፕሮሲዳ እና ኢስቺያንም አለፈቻቸው።


የኔፕልስ ወደብ ከዕይታው ሲሰወር መኮንኑ ፓታኖ የመርከቧን ጉድግዳ መመልከት ጀመረ። ፖ በእርግጥም ያረጀች መርከብ ናት። የተሰነጣጠቀ እና የዛገ ጉድግዳዋን በወርቅማ ቀለም ለመሸሸግ ተሞክሯል። መርከቧ ደቡባዊ አቅጣጫን በመያዝ የሜሲናን ሰርጥ አልፋ ወደ ዋናው የውኃ አካል ገባች። ፓታኖ ወደፊት ሊመለከት በቅርበት የሚታይ ምድር አለመኖሩን ተረዳና አፍሪካ በእርግጥም ሩቅ ነው ሲል አሰበ።

ሉጂ ጎጅ ለግዳጅ ሲጠራ ሚላን ውስጥ ከጓደኞቹ ጋር እየተዝናና ነበር። በብስክሌቱ ወደ ቤቱ በረረ እና ለቤተሰቦቹ እንዲሁም ለወዳጅ ጎረቤቶቹ ወደ አፍሪካ ሊሄድ መሸኑን ተናግሮ ተሰናበታቸው። ከምሽቱ ዐሥራ ኹለት ሰዓት ላይ ሚላን ባቡር ጣቢያ ሲደርስ በርካታ ወታደሮች እና ሽኚ ወዳጅ ዘመዶቻቸው አካባቢውን ሞልተውት ነበር።

«ቻው ማማ» በማለት ነበር ሊሸኙት የመጡ ቤተሰቦቹን ከባቡሩ ውስጥ ሆኖ የተሰናበታቸው። የእባቱ ዐይኖች በእምባ ሊሸፈኑ ተመለከተ። ወዲያውኑ ባቡሩ ጉዞውን ጀመረ። ጎጅ ወደ ኋላ ሲመለከት የሚለን ከተማ መብራት ቀስ በቀስ ሲደበዝዝ አየ። ከአንድ ምሽት የባቡር ጉዞ በኋላ ኔፕልስ የሚገኘው የጦር ሰፈር ደረሰ። ወዲያውኑ ወደ ኤርትራ የሚያደርገውን ጉዞ ጀመረ።








The *Mauchetti* departs from Naples. From *L'Illustrazione Italiana*, 2 February 1896.

**ምስል 5፡ ሚንጌቲ መርከብ ከኔፕልስ ስትነሳ (ጥር 2 ቀን 1896)**

ወደ ምፅዋ የተደረገው ጉዞ ዐሥራ ኹለት ቀናት ነበር የወሰደው። ለተለያየ የመንገድ ላይ ጨዋታ በቂ ጊዜ በመኖሩ ፓታኖ ከወታደሮቹ ጋር ስለሚሄድበት የጣሊያን ቅኝ ግዛት ኤርትራ የተለያየ ውይይት አደረገ። በውይይቱም ቀድሞ ስለ አፍሪካ የነበረውን አስተሳሰብ ቀየረ። ከጣሊያን ከመነሳቱ በፊት አፍሪካ በረኻማ አሊያም ብርካታ አደገኛ አራዊትን በውስጡ የያዘ ጫካ መስሎት ነበር። ስለ ተራራማው ኤርትራ ነፋሻ አየር እና ተስማሚ መኖሪያነት ከጓደኞቹ ሲሰማ ተደሰተ።

የሜዲቴራኒያን ባሕር መግቢያ የሆነው ስዊዝ ካናል ሲደርሱ ሰይድ ወደብ ላይ የነበረውን የጦፈ ገበያ ተመለከተ። በርካታ መርከቦች ዕቃ ይጭናሉ፣ ያወርዳሉ። ፖ ላይ የተሳፈሩ ወታደሮችም በገመድ ገንዘብ ለነጋዴዎች በማቀበል የተለያዩ ፍራፍሬዎች፣ አሳ፣ ጫቦ፣ መጠጥ እና ሲጋራ ገዝተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ሱዊዝ



The *Mourhetti* departs from Naples. From *L'Illustrazione italiana*, 2 February 1896.

ምስል 5፡ ሚንጌቲ መርከብ ከኔፕልስ ስትነሳ (ጥር 2 ቀን 1896)

ካናልን ካለፉ በኋላ ጉዞአቸው አሰልቺ ነበር። ሙቀቱ ኃይለኛ በመሽኑ በርካታ ወታደሮች የጉዞአቸውን ወቅት በእንቅልፍ አሳለፉ።

ሱጂ ጎጂ እና ጎደኞቹ ምፅዋን ለመጀመሪያ ጊዜ የተመለከቷት በጭለማ ነበር። የወደቧ አነስተኛ መብራቶች ከርቀት ይታያሉ። የበለጠ ሲቀርቡ ነበር የወደብ ከተማዋን ውበት የተመለከቱት። የከተማዋን ውበት ለማድነቅ በቂ ጊዜ ነበራቸው። በቅድሚያ ግን ጉዞ እና ሙቀት ያዳከማቸውን በቅሎዎቻቸውን ለማራገፍ ኹሉም መሯሯጥ ጀመሩ።

**ምፅዋ፡- የዘመናት ግዛተ-አፄዎች ማዕከል**

ወደ ባሕር ዳርቻው ቀርቦ መኖር በምፅዋ ውሳኝ ነገር ነው። ለውኃው በቀረቡ መጠን የወደቧን ጤናማ እና ነፋሻ የባሕር ነፋስ ማግኘት ያስችላል። በምፅዋ ዳርቻ የሚታዩ ጥንታዊ ኪነ-ሕንፃዎች የግዛቷን ያለፈ ኃያልነት ያሳያሉ። ዕድሜ ጠገብ የሸኑ የባለጸጋ ቤቶች ከዳርቻው አንድ ማይል ርቀት ላይ በሚገኙ ደሴቶች ላይ የተገነቡ ሲሸኑ ከዋናው መሬት ጋር በእንጨት ድልድይ ይገናኛሉ። ከግራር እና አብደልቃድር ሰርጥ አጠገብ የሚገኙት ደሴቶች ጥንታዊ የመርከብ ግንባታ ቦታዎች እንደነበሩ ይገመታል።

በምፅዋ የሚገኙ የነጋዴ ቤቶች ከሌሎች ይለያሉ። ከተራው ማህበረሰብ ቤቶች ጎላ ብለው የሚታዩት ነጫጭ ቤቶች ባለ ረጃጅም መስኮቶች ሲሆን መስኮቶቹ በቂ ብርሐን እና ነፋሻውን የባሕር ንፋስ ያስገባሉ። ለዘመናት እንደታየው በርካታ ኃያላን ነገሥታት ሲነሱ እና ሲወድቁ ኖረዋል። በምፅዋ የባሕር ዳርቻ ለዘመናት በመኖር ላይ ያሉ የአረብ፣ የሕንድ እና የቱርክ የንግድ ማህበረሰብ፤ዘመን ለማይሽረው የንግድ ሥርዐ-መንግሥት ቋሚ ምስክር ናቸው።

ዊርነር ሚዚንገር በግብፁ ንጉሥ እስማኤል ተሾሞ ምፅዋን ባስተዳደረበት የ1870ዎቹ ዓመታት ታውሱድ ደሴት ላይ ያስገነባው ቤተ-መንግሥት ከርቀት





ይታያል። ከግብፅ ቀጥሎ ጣሊያን ምፅዋን በ1885 ስትቆጣጠር ቤተ-መንግሥቱ እድሳት ተደርጎለት ‹‹ሴራግሊዮ ቤተ-መንግሥት›› የሚል ስያሜ ተሰጠው። ቤተ-መንግሥቱ በኢስታንቡል ቤተ-መንግሥታት መልክ የታነፀ ሲሆን ባለ ኹለት ፎቅ ቁመቱ እና ነጭ ቀለሙ ከርቀት እንዲታይ አስችሎታል። በሕንፃው ግራ እና ቀኝ የተገነቡ መወጣጫ ደረጃዎች ሲኖሩ ከአናቱ የሚታዩ ኹለት መብራቶችም አሉት።

ከሴራግሊዮ አጠገብ የሚገኘው ሌላ ሕንፃ በጣሊያን አስተዳደር የተገነባ የመኮንኖች ክበብ ነው። በርካታ የጣሊያን መኮንኖች በከበቡ በመገኘት በቀዝቃዛ መጠጥ ይዝናኑ ነበር። ከክበቡ ሕንፃ ጀምሮ እስከ ባሕሩ ዳርቻ የተዘረጋ የእንጨት ድልድይ ይገኛል። ክበቡ በምሽት የባሕር ዳርቻውን ውበት ለመመልከት በሚያስችል ሁኔታ ነበር የተገነባው።

ክበቡ ለተራ ወታደሮች አገልግሎት አይሰጥም ነበር። ተራ ወታደሮች ግራር እና አብድል ቃድር ላይ እንዲሰፍሩ ይደረግ ነበር። ለመከከሰኛው ምሥራቅ ወደቦች ካላት ቅርበት የተነሣ በምፅዋ ‹‹የጣሊያን፣ ፊረንሳይ፣ ግሪክ፣ ሕንድ፣ ግብፅ፣ ሱዳን፣ አረብ፣ ኑቢያ፣ ሶሪያ፣ አርሜኒያ፣ እንግሊዝ፣ ጀርመን እና የሌሎች በርካታ አገራት የንግድ ሰዎች ይገኛሉ›› በማለት ሴዛር ፒኒ ጽፎ ነበር።

በምፅዋ የነበሩ ወታደሮች ከአለቆቻቸው በርካታ እገዳ ይደርስባቸው ነበር። ለምሳሌ ያህልም ወታደሮቹ ባሕር ዳርቻው ላይ ገላቸውን እንዳይታጠቡ ይከለከሉ ነበር። የተለያየ የቆዳ በሽታ ሊይዛቸው እንደሚችልም አለቆቻቸው ያስጠነቅቋቸው ነበር። በዚህ የተነሣም በምፅዋ የነበሩ ወታደሮች በባሕር ዳርቻው ከሚገኙ የግሪክ ሻይ ቤቶች ሌላ ስለከተማዋ ብዙ ዕውቀት አልነበራቸውም።

በ1880ዎቹ በምፅዋ የሚገኙ ኹለት ካፍቴሪያዎች ለጣሊያን መኮንኖች እንደ ጽሕፈት ቤት ያገለግሉ ነበር። በ1885 የጣሊያንን መምጣት ተከትሎ ኹለቱ የግሪክ ሻይ ቤቶች ካፌ ሞንቴቤሉ እና ካፌ ጋሪባልዲ በሚል ተሰየሙ። ባለቤቶቹ

ግሪካውያንም አውሮፓዊ ደንበኞቻቸውንም ሆነ የአገሬውን ሰው ላለማስቀየም በኩፍቴሪያቸው ላይ የየትኛውንም አገር የበላይነት የሚያሳዩ ምልክቶችን ላለማሳየት ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር። ብዙም ሳይቆይ በ1880ዎቹ መግባደጃ ላይ ጣሊያንኛ ከአረብኛ ጋር በመርካከር የምፅዋ የንግድ መግባቢያ ቋንቋ ለመሆን ቻለ።

በምፅዋ ታዋቂ ባለጸጋ ነጋዴ የነበረው ጣሊያናዊው አሌሳንድሮ ሴሮር ነበር። በጣሊያን ሊቮርኖ ከአይሁድ ቤተሰቡ የተወለደው ሴሮር በመጀመሪያ ያቀናው ወደ ካይሮ ነበር። በግብፅ ቆይታው ከሕዝብ ጋር ለመቀራረብ እንዲረዳው በማሰብ ስራሱ «አስክንድር» የሚል የቱርክ ስም አወጣ። በመቀጠል ወደ ምፅዋ የመጣው በእንቁ ንግድ ላይ ለመሰማራት አስቦ ነበር። በምፅዋ ቆይታው አስክንድር ሴሮር በሚል ስሙ ይታወቅ የነበረ ሲሆን በአንዳንዶች ዘንድ «እንቁ ነጋዴው» ተብሎ ይጠራ ነበር።

ከጣሊያኖች መምጣት በፊት ሴሮር በተለምዶ የምፅዋ ከንቲባ እንደሆነ ይነገርለት ነበር። የአገሩ ሰዎች የወደብ ከተማዋን ከተቆጣጠሩ በኋላም የሴሮር የእንቁ ንግድ አልተቋረጠም ነበር። በምፅዋ በርካቶች ከወንባቸው በላይ አራቁታቸውን በሚንቀሳቀሱበት የበጋ ሙቀት ሴሮር ሙሉ ልብሱን ለብሶ ነበር የሚዘዋወረው።

በምፅዋ የጣሊያኖች የመጀመሪያ እግር መርገጫ የነበረው መሬት ከአራት ስኩዌር ማይል አይበልጥም። በጠባቧ ቦታ የተጀመረው የጣሊያን የግንባታ እንቅስቃሴ በፍጥነት ነበር ምፅዋን ያጸረሰው። የባሕር ዳርቻውን በአዲስ መልክ ገነቡት፣ በመቀጠልም ሆስፒታል፣ የጦር መሣሪያ እና የማቀዝቀዣ ፋብሪካዎችን አቆሙ። ምፅዋን ከተራራማው የመሐል ኤርትራ ግዛት ጋር የሚያገናኝ የባቡር ሃዲድም የተገነባው በተመሳሳይ ወቅት ነበር።

በምፅዋ የንግድ እንቅስቃሴ ማደጉን ተከትሎ በርካታ አውሮፓውያን ወደ ቀይ ባሕሯ ወደብ መጡ። በምፅዋ ምንም ዓይነት መጠለያ ዛፍ ያልነበረ ሲሆን በርካታ ሻይ ቤቶች እንደ መጠለያም እንደ መዝናኛም ማገልገል ጀመሩ። ቀን ቀን ከተማዋ





ፍጹም ፀጥታ የሚሰፍንባት ስትሆን የተሰየ እንቅስቃሴ ለማድረግ ሙቀቱ አስቸጋሪ በመሆኑ ሰዎች በቤታቸው ነበር የሚያሳልፉት።

ምፅዋ በይበልጥ የምትታወቅባቸው ኹለት ማዕከላዊ ቦታዎች ወይም በተለምዶ ፒያሳ ነበሯት። ቦታዎቹን ባራቴሪ እና ስንአፈ በማለት በ1895 ነበር ጣሊያኖች ሰያሜ ያወጡላቸው። በፒያሳዎቹ ያሉ የንግድ ማዕከላት የማን እንደኾኑ ከአሠራራቸው በቀላሉ መለየት ይቻል ነበር። የሕንድ ሱቆች ጣሪያቸው አጭር ሲሆን የብረት በር አላቸው። ግሪኮች፣ አረቦች እና ሕንዶች በወርቅ ማንጠር ሥራ ላይ የተሰማሩ ነበሩ። በአብዛኛው የሚያመርቱትን የወርቅ ጌጣጌጦች ለአረብ እና አቢሲኒያ ገዢዎች ያቀርቡ ነበር።

በወቅቱ አዲስ በተከፈተው ካፌ አሪየንታሌ ዙሪያ በርካታ የመንገድ ላይ ነጋዴዎች ይርመሰመሱ ነበር። የሕንድ ሱቅ በደረቴዎች የተለያዩ አልባሳትን፣ ኮፍያ እና ጌጣጌጦችን ሲሸጡ ጥቁር አፍሪካውያን ደግሞ ሲጋራ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ሎሚ እና የተለያዩ ፍራፍሬዎችን ያዙሩ ነበር። በአካባቢው የነበሩ የአረብ ነጋዴዎች አነስተኛ ጻስ በማቆም የተለያዩ ጌጣጌጦችን፣ ሽቶዎችን እና እጣን ይሸጡ ነበር። የገበያው አካባቢ በተለያዩ ፍራፍሬዎችና ቁሳቁሶች ሽታ የተሞላ ሲሆን በተለይ በከፍተኛ ጫጫታው ይታወቅ ነበር።

ካፌ ጋሪባልዲ በዘመኑ ታዋቂ የመዝናኛ ሥፍራ ነበር። የተለያዩ የአገሬው አዝማሪዎች ጣሊያናውያኑን በዘፈናቸው ያዝናኑ ነበር። በወቅቱ ዝነኛ የነበሩ የጣሊያንኛ ዜማዎች ይዘፍኑ የነበሩ ሲሆን «ላ ሊታሊያ ሬስታ ሊን አፍሪካ» የተባለው የጣሊያንኛ ዘፈን ተወዳጅ ነበር። ዘፈኑ ጣሊያን በአፍሪካ ስለሚኖራት ቆይታ እያነሳ የሚያሞግስ ነበር። ከካፌ ጋሪባልዲ ሌላ ደግሞ አቅሙ የነበራቸው ግለሰቦች የሚዝናኑበት ዲና ካርሜላ የተባለ መጠጥ ቤት ነበር።

# ምዕራፍ ሦስት

# ጣሊያን በአፍሪካ

የታሪክ ምስክር መጎኛ ቤተ-መዛግብት እና ሙዚየሞች ብቻ አይደሉም። አንዳንድ ጊዜ የምንረግጠውም መሬት የታሪክ ምስክር ሊሆን ይችላል። በሮም የሚገኘው ቺንኩቼንቶ አደባባይም የዚህ ማሳያ ነው። የአደባባዩ ስም ‹‹የአምስት መቶዎች አደባባይ›› የሚል ትርጓሜ አለው። አደባባዩ የ1500ዎቹን የጣሊያን የሕዳሴ ዓመታት ወይም ደግሞ ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የአውሮፓን ገበያ ተቆጣጥሮ የነበረውን የፊያት ቺንኩቼንቶ ሞዴል ለመዘከር አይደለም የተሰየመው።

‹‹አምስት መቶዎች›› ጣሊያን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አፍሪካ ዘምታ ድል በተነሳችበት ወቅት የሞቱ ወታደሮቿን የሚዘክር አደባባይ ነው። ወታደሮቹ የሞቱት ዶጋሊ ላይ በተደረገ ፍልሚያ ወቅት ነበር።

የዶጋሊውን ዘመቻ የጀመረው በመንኮታኮት ላይ የነበረው የአቶማን ቱርክ መንግሥት ነበር። መንግስቱም አስማኤል አንደኛ የተባሉ ንጉሥ ይመሩት የነበረው ዐሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ በጅቡቲ እና ሱዳን መካከል የሚገኘውን የቀይ ባሕር ምዕራባዊ ዳርቻ ሰፊ ግዛት በሥሩ አድርጎ ነበር። በግዛቱ የነበረው የቱርክ አስተዳደር ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል መዝለቅ ችሎ ነበር።

አስማኤል ፓሻ የግብፅ ንጉሥ ምክትል በመሆን በ1867 ከተሾመ በኋላ ግብፅን በአውሮፓ መልክ የመገንባት እንቅስቃሴ ጀመረ። ካይሮን አፍርሶ በፓሪስ መልክ ለመገንባትም መንቀሳቀስ የጀመረው የሹመት ፊርማው ሳይደርቅ ነበር።

የስዊዝ ካናል በ1869 መከፈቱን ተከትሎ የቀይ ባሕር ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ጨመረ። ይሄንን የተመለከተው አስማኤል ፓሻም የግብፅን ግዛት ወደ





በወቅቱ የነበረውን የጣሊያን ወታደራዊ እንቅስቃሴ እና የውጪ ዜጎች መበራከት ተከትሎ በምዕዋ ሌተኛ አዳሪነት ተጀመረ። በመጀመሪያ የነበሩት የቱርክ፣ የጥቁር አፍሪካ እና የግብፅ ሌተኛ አዳሪዎች ብቻ ሲኾኑ የጣሊያን ወታደሮችን መበራከት ተከትሎ በርካታ የምዕዋ ሌቶችም የወሲብ ንግዱን ተቀላቀሉ።

አጠቃላይ የንግድ ምክር ቤት ባይኖራትም ምዕዋ ታላቅ የንግድ ማዕከል መሆን ችላ ነበር። የቀይ ባህሯ እንቁ የሚል ስያሜን ማግኘት የቻለችውም በዚሁ የንግድ እንቅስቃሴዋ ነበር።

ደቡብ ለማስፋት በማሰብ ኢትዮጵያንና እና ሱዳንን ለመውረር ተዘጋጀ። የዓባይ ወንዝ መነሻ የሆነችውን ኢትዮጵያንም በመያዝ ግብፅ የቀይ ባሕርን የንግድ መሥመር እና የዓባይ ሸለቆን በበላይነት የምትቆጣጠርበትን ዕቅድ አወጣ።

የወረራ እንቅስቃሴውን የጀመረው ሱዳን ላይ ሲሆን በጳርፋር ጊዜያዊ አስተዳደሩን በ1874 አቋቋመ። ወደ ኢትዮጵያ በማቅናትም ሐረርን በ1875 ተቆጣጥሮ ለቀጣይ እንቅስቃሴ ዝግጅቱን አፋጠነ። የእስማኤል ቀጣይ እንቅስቃሴ የተገታው የኢትዮጵያ ሠራዊት በ1876 ጉራ ላይ እና በ1883 ደግሞ ሰአቲ ላይ ባደረሰበት ከፍተኛ ጥቃት ነበር።

እስማኤል ግብፅን በዘመናዊ መልክ ለመገንባት የነበረው ሕልም ከገንዘብ ዕቅሙ ጋር አይመጣጠንም ነበር። በመሸኑም የአውሮፓ የብድር አቅርቦት አስፈለገው። አበዳሪ አውሮፓውያንም ለግል ጥቅማቸው ሲሉ የግብፁ ንጉሥ አውሮፓዊ አማካሪዎችን እንዲቀጥሩ ቅድመ ሁኔታ አቀረቡ። ይሄንን ተከትሎም የእስማኤል ፓሻ ስልጣን ቀስ በቀስ ተሸረሸረ።

በ1870ዎቹ እና 80ዎቹ በቀይ ባሕር ዳርቻ እና መሐል አገራት የነበረው የግብፅ አስተዳደር መዳከም ጀመረ። በሱዳን የነበረው የግብፅ አስተዳደርም በሞሃመድ አህመድ ከሚመራው የእስላማዊው ፀረ-ቅኝ ግዛት ቡድን ‹‹መሃዲስት›› ብርቱ ተቃውሞ ገጠመው። ተቃውሞው በተለይም በእንግሊዝ ይተዳደር የነበረው ምዕራባዊ ሱዳን የበለጠ ተጠናክሮ ቀጠለ።

በነበረው ከፍተኛ የሰበካ እና የንግግር ችሎታው በመታገዝ ሞሃመድ አህመድ በርካታ ሱዳናውያን የመሃዲስት እንቅስቃሴውን በመቀላቀል በግብፅ እና እንግሊዝ ኃይሎች ላይ እንዲነሱ ማድረግ ቻለ። በ1881 ወደ ሙሉ ጥቃት በመሸጋገርም የእንግሊዝ እና ግብፅ የጋራ የጦር ሰፈሮች ላይ እርምጃ መውሰድ ጀመረ። በወርኃ ጥቅምት በ1883 በኩሱኔል ዊሊያም ሂክስ የሚመራውን ጦር ደመሰሱ። በመቀጠልም





ካርቱምን ከመሃዲስቶች ለመጠበቅ የተላከው የጀነራል ቻርልስ ጎርደን ጦር ተፈታ። በመጨረሻም መላዋ ምዕራብ ሱዳን በመሃዲስት ቁጥጥር ሥር ዋለች።

እንግሊዝ ከመሃዲስት ጋር ለምታደርገው ትግል የኢትዮጵያ አጋርነት የግድ አስፈልጓት ነበር። የእንግሊዝ ጦር መሃዲስት ከሰሜን እቅጣጫ በሚያጠቃበት ወቅት ኢትዮጵያ ምሥራቁን ክፍል ብትቆጣጠር ድል ማስመዝገብ እንደሚቻል እንግሊዝ አሰላች። በመቀጠልም በ1883 አድሚራል ሥር ዊሊያም ሄዊትን ወደ አድዋ በመላክ አፄ ዮሐንስን በቀላሉ ለማሳመን ቻለች።

አፄ ዮሐንስ ኢትዮጵያ ውስጥ የመሃዲስት ዓይነት እንቅስቃሴ እንዳይፈጠር ባደረባቸው ስጋት የተኮማ ነበር የእንግሊዝን ጥያቄ በፍጥነት የተቀበሉት። ከአገር ውስጡ ስጋታቸው ሌላ በሰሜን የአገሪቱ ክፍል ያለውን የሱዳን እና የግብፅ ተፅዕኖ በመቀነስ የምዕዋ የባሕር በራቸውን የማስከበር ዓላማም ስለነበራቸው የእንግሊዝ ጥያቄ ወቅቱን የጠበቀ ሆኖላቸዋል።

በዚያ ወቅት ምዕዋ ትተዳደር የነበረው በግብፅ ሲሆን ግብፅም አሜሪካዊው አሌክሳንደር ማኮብ ማሰን በአስተዳዳሪነት ቀጥራው ነበር። ወቅቱ ምዕዋ ታላቅ የንግድ ማዕከል የሆነችበት ዘመን ነበር። መነሻቸውን ምጽዋ ያደረጉ ነጋዴዎች ሱዳንን አቋርጠው ወደ ምዕራብ አፍሪካ ያልፉ ነበር። በንግድ መርከቦችም የሚጫኑ ዕቃዎች ወደ አረብ አገራትና ሕንድ የሚሄደው ከምዕዋ በመነሳት ነበር። ኢትዮጵያ በምዕዋ የመጠቀም መብት እንዳላት በመጥቀስ አፄ ዮሐንስ ጦራቸውን እንደሚያዘምቱ የተናገሩበት ወቅትም ነበር። በዚያን ጊዜ የግብፅ ተወካይ የነበረው ማሰን ኢትዮጵያ ምዕዋን መጠቀም እንደምትችል ነገር ግን የባለቤትነት ጥያቄ ማንሳት እንደሌለባት በንቀት የተሞላ መልስ ሰጥቷቸው ነበር።

በሰኔ 1884 አድዋ ላይ የተገናኙት ሰር ዊሊያም ሄዊት፣ አፄ ዮሐንስ እና አሌክሳንደር ማኮብ ማሰን በተለምዶ "ሄዊት ስምምነት" ተብሎ የሚጠራውን የጋራ

ስምምነት ተፈራረሙ። ስምምነቱ አፄ ዮሐንስ በመሃዲስት ተቃዋሚዎች ላይ ወታደራዊ ተፅዕኖ በማድረግ ሱዳን ውስጥ የታፈኑትን የግብፅ ወታደሮች እንዲያስለቅቁ ያዛል። በምላሹ ደግሞ እንግሊዝ በስሜን ኢትዮጵያ የሚገኘው የቦጎስ ግዛት የኢትዮጵያ ግዛት አካል ለመሆኑ ዕውቅና እንደምትሰጥ በስምምነቱ ሰፍሯል። በተጨማሪም ማሰን እና እንግሊዝ ኢትዮጵያ ወጪ እና ገቢ ንግዷን በምፅዋ በኩል እንድታከናውን የሚያስችላትን ዋስትና ለመስጠት ተስማሙ።



Hayes IV. From Lincoln de Castro. *Vella terra dei negus, fugace visio* Milan: Fratelli Treves, 1912.

*ምስል 6፦ አፄ ዮሐንስ አራተኛ*





የሄዊት ስምምነት የፊርማ ቀለም ከመድረቁ በፊት ነበር አለመግባባት የተፈጠረው። በሐምሌ ወር ለአፄ ዮሐንስ የሚደርስ 50 ሳጥን የጦር መሣሪያ የጫነችው ኮርሲካ የንግድ መርከብ ምፅዋ ደርሳ ጭነቷን አራገፈች። የወደቡ አስተዳዳሪዎች መሣሪያው እንዳያልፍ አገዱ። በወቅቱ ለነበረው የወደቡ አስተዳዳሪ አሜሪካዊው ማሰን ድርጊቱን በመኮነን ደብዳቤ የጻፉት የአፄ ዮሐንስ የጦር መሪ የነበሩት ራስ አሉላ ናቸው። ከሦስት ወራት በኋላ ጥቅምት 1883 ላይ አፄ ዮሐንስ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ያዘለ ደብዳቤ ለማሰን ፃፉ። በደብዳቤያቸውም በሄዊት ስምምነት መሠረት ጦራቸውን ወደ ሱዳን ለመላክ የተዘጋጁ ቢሆንም የማሰን አካሄድ ግን ስምምነቱን የሚጥስ መሽኑን ጠቀሱ። ንጉሡ አያይዘውም ጦራቸውን ወደ መሃዲስት ከማዝመት ይልቅ በቀጥታ ወደ ምፅዋ እንደሚልኩ ዛቱ።

### የግብፅ በር ክፋችነት እና የጣሊያን አገባብ

የካቲት አምስት ቀን 1885 ዓ.ም በጋሪባልዲ የሚመሩትን 800 የጣሊያን ወታደሮች ያሳፈረችው አሜጲዮ መርከብ አመሻሽ ላይ ምፅዋ ደረሰች። በወቅቱ ምፅዋን የሚያስተዳድረው የግብፅ ሠራዊት ቦታውን ለጣሊያን ለመልቀቅ በዝግጅት ላይ ነበር። በምፅዋ ቤተ-መንግሥት የጣሊያን እና የግብፅ ባንዲራ ጎን ለጎን ተሰቅሎ አስተዳደራዊ ሽግግር መደረጉ ታወጀ። ለምፅዋ ነዋሪዎች በተነገረው ዐዋጅ መሠረት ከእንግሊዝ፣ ቱርክ እና ግብፅ መንግሥታት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው የጣሊያን መንግሥት የወደብ ከተማዋን እንደሚያስተዳድራት አሳወቀ።

የናፒየር ዘመቻ እና የቤልጅየሙ ንጉሥ ሊዮፖልድ ኮንጎን የመያዝ ስኬት በመመልከት ጣሊያን ኢትዮጵያን በቀላሉ መያዝ እንደምትችል የልብ ልብ ተሰማት። የጣሊያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶም የቤልጅየምን ፈለግ በመከተል ሽዋ አካባቢ ሌት ማረፊያ በተባሰ ቦታ በጣሊያን የጂአግራፊ ማህበር ስም ሳይንሳዊ ማዕከል ገነቡ። በመቀጠልም በ1881 እና በ1883 በጆሲፒ ጉሌቲ እና ጎስታቮ ቢያንቺ የተመሩ አገር አሳሾችን ወደ መሃል ኢትዮጵያ ለማስገባት ሞከሩ።



...ures IV. From Lincoln de Castro, *Nella terra dei negus, pagine varie* ... Milan: Fratelli Treves, 1917.

## ምስል 6፡- አፄ ዮሐንስ አራተኛ

የአሳሾቹ ሙከራ በእንጭጩ የተቀጨው ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ከመጠጋታቸው በፊት አባላቱ በሙሉ በመገደላቸው ነበር። የአሳሾቹ ግድያም ለተወሰነ ጊዜ የኢትዮጵያን ግዛት ከተመሳሳይ ሰርጎ ገቦች ለመከላከል ቢያስችልም በይዘቱም ሆነ በኃይል አሰላለፉ ከፍተኛ ከሆነ ቀጣይ ወረራ በዘላቂ ሊጠብቃት አልቻልም ነበር።

የአሳሾቹን መገደልን ተከትሎ ኢትዮጵያ ለዜጎቿ በቂ የደኅንነት ጥበቃ ባለማድረጓ ጣሊያን ወቀሰች። በመቀጠልም በቀጠናው ያሉ ‹‹ዜጎቿን እና ጥቅሟን ለማስጠበቅ›› በሚል ሽፋን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሠራዊቷን ወደ ኢትዮጵያ ማስጠጋት ጀመረች። የጣሊያኑ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ፓስኳል ስታኒስላኦ ማንሲኒ በጥር 1885 በቱርክ ከነበረው የጣሊያን አምባሳደር ጋር ባደረጉት የቴሌግራፍ ልውውጥ ‹‹የአገራቸውን ጥቅም እና ክብር ለማስጠበቅ›› ጣሊያን ወታደሮቿን ወደ ኢትዮጵያ እንደምትልክ ገልጸው ነበር። ከጥቂት ቀናት በኋላም በምፅዋ የነበረው የግብፅ አስተዳደር በጣሊያን ተተካ።

### የጣሊያን ወደ ተራራማው የኢትዮጵያ ግዛት መጠጋት

እንግሊዝና ግብፅ በሄዊት ስምምነት አፈፃፀም ላይ ባሳዩት ልግመኝነት አፄ ዮሐንስ ተቆጥተው ነበር። ስምምነቱ ኢትዮጵያ የምፅዋን ወደብ መጠቀም እንድትችል በማመቻቸቱ የተደሰቱት አፄ ዮሐንስ ቀስ በቀስ ወደቡን ሙሉ በሙሉ መልሰው እንደሚያገኙ ተስፋ አድርገው ነበር። በፈርማው ወቅትም ምፅዋ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ አስተዳደር እንደምትዘዋወር በማመን ነበር የግብፅ ቆይታ ላይ ያላንገራገሩት።

የእንግሊዝ ተወካዮች በዘኩላቸው ከስዊዝ ካናል መክፈት በኋላ በቀይ ባሕር ላይ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታዋ የጎላውን ምፅዋ ለዮሐንስ መስጠቱ አሳስተማመናቸውም ነበር። ለዚህ ዋናው ምክንያት ደግሞ ፈረንሳይ ምፅዋን ከጅቡቲ ጋር በመቀላቀል ከያዘች እንግሊዝ በቀይ ባሕር አካባቢ የሚኖራትን የበላይነት በቀላሉ ልታጣ ትችላለች የሚለው ፍራቻ ነበር።





የግብፅን መልቀቅ ተከትሎ እንግሊዝ ምፅዋን ለጣሊያን ያሸጋገረችው ወደቡ በኢትዮጵያ እጅ ቢመለስ በቀላሉ ፈረንሳይ ልትወስደው እንደምትችል በመፍራት ነበር። ጣሊያን የእንግሊዝ ታማኝ ወዳጅ ባትሆንም በምፅዋ መቀመጧ ወደቡን ከፈረንሳይ ስጋት ነፃ ያደርገዋል። ምክንያቱም በበርሊኑ ጉባዔ ላይ አንድ አውሮፓዊ አገር የያዘውን ቅኝ ግዛት ሌላ አገር እንደማይነጥቀው የተደረገ ስምምነት ነበር።

በቀይ ባሕር አካባቢ የእንግሊዝ ተወካይ የነበረው አጉስቶስ ዋይልድ ስለ ወቅቱ ሁኔታ ሲናገር፡- ‹‹እንግሊዝ አፄ ዮሐንስ ከተጠቀመችባቸው በኋላ ለጣሊያን አሳልፋ በመስጠት ከፍተኛ ክህደት ፈፅማለች›› ብሎ ነበር። አፄ ዮሐንስ በድርጊቱ ቢናደዱም በቀጥታ ወደ ምፅዋ ለመዝመት አልወሰኑም። ተጨማሪ እንቅስቃሴ ለማድረግ እስካልሞከረች ድረስም የጣሊያንን በምፅዋ መኖር እንደማይቃወሙ ከጣሊያን ተወካይ ጋር በተገናኙበት ወቅት ተናግረው ነበር።

ይሄንን ተከትሎ ከ1886 እስከ 1887 ባሉት ወራት ጣሊያን ከምፅዋ በመነሳት ወደ መሃል ኢትዮጵያ መጠጋት ጀመረች። ጣሊያን ሰአቲ ላይም ምሽግ በመገንባት ለቀጣይ ወረራ መዘጋጀት ስትጀምር በራስ አሉላ ከሚመራው ጦር ጋር ጥር 25 ቀን ፊት ለፊት ተገናኘች። የጉስቱን ፍጥጫ የተሰየ የሚያደርገው በመጠኑ የታጠቀ አፍሪካዊ ጦር ከተደራጀ የአውሮፓ ኃይል ጋር መግጠሙ ነበር። በውጤቱ የኢትዮጵያ ጦር ብርቱ ጉዳት ሲደርስበት ከመድፈኛው የጣሊያን ጦር ግን አንድም ወታደር አልቆሰለም ነበር።

በሚቀጥለው ቀን ዕድል ፊቷን ወደ ኢትዮጵያ አዞረች። የሰአቲውን ምሽግ ለማጠናከር በኮሎኔል ቶማሶ ክሪስቶፋሪስ የሚመራ 540 የጣሊያን እና አምሳ የኤርትራ ተወላጆችን የያዘ ጦር ከምፅዋ ወደ ሰአቲ በመንቀሳቀስ ላይ መኾኑን ራስ አሉላ ደረሱበት። ከአንድ ቀን በፊት የደረሰባቸውን ሽንፈት ለመበቀልም አጋጣሚውን ለመጠቀም ወሰኑ።

ከምፅዋ እስከ ሰአቲ ያለው መንገድ በስንሰለታማ ጉብታ እና ቁጥቋጦ የተሸፈነ ሲሆን መልክአ ምድሩን በመጠቀም የጣሊያንን ጦር ለመቁረጥ አቀዱ። በዘመቻ ዕቅዱም መሠረት ጥቂት ወታደሮቻቸውን ለእይታ ከጣሊያን ሠራዊት ፊት በማሰፍ ቀሪ አምስት ሺህ ወታደሮቻቸውን በተራራው ላይ እንዲመሸጉ አደረጉ።

የጣሊያን ሠራዊት ከእይታ ሲገባ የአሉላ ጦር ከሦስት አቅጣጫ ተኩስ ከፈተ። የጣሊያን ወታደሮች ምንም ዓይነት የመልስ ተኩስ ሳያደርጉ በአሉላ ሠራዊት ተሰቀሙ። ሁኔታውን የተመለከተው ክ/ል ክሪስቶፎሪስ ጥቂት የተረፉ ወታደሮቹን አሰከትሎ ወደ ኋላ በማፈግፈግ በአቅራቢያው ወደሚገኝ ተራራ ወጣ።

ኮሎኔሉ ወታደሮቹን ቦታ ለማስያዝ በመዘጋጀት ላይ ሳለ ነበር በአሉላ ሠራዊት መከበቡን ያወቀው። በቀጣይ ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ከለማንያ በላይ የጣሊያን ወታደሮች በተራራው ላይ ተገደሉ። ዘመቻውን የኢትዮጵያ ወታደሮች ሲገልጹት ‹‹ወደ ሰርግ የመሄድ ያህል ነበር›› ብለዋል።

በአሉላ አስገራሚ የዘመቻ ዕቅድ የጣሊያንን ጦር ዶጋሊ ላይ ሙሉ በሙሉ የደመሰሱት የኢትዮጵያ ወታደሮች ግስጋሴያቸውን በመቀጠል አስከመጨረሻው እንዲቀጥሉ አዝማቾቸውን ጠየቁት። ራስ አሉላም ትንሽ አቅማምቶ በመጨረሻ አካባቢውን ለቆ ተመለሰ።

በዶጋሊው ድንገተኛ የአሉላ ወረራ ወቅት በርካታ የጣሊያን ወታደሮች በአግራሞት ቆመው ኢትዮጵያን ሠራዊት ከመመልከት ውጪ አልተንቀሳቀሱም ነበር። በርካታ የአውሮፓ ጋዜጦች የዶጋሊን አስገራሚ ገድል የዶጋሊን የጦርነት ውሎ ንጉሥ ሊዮኒደስ ሦስት መቶ የስፓርታ ወታደሮችን በመያዝ ከወራሪው የፐርሺያ ጦር ጋር ከተፋለመበት ታሪካዊ ክስተት ጋር በማመሳሰል ዘግበዋል። ዝሰቱን ታሪክች የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር ሦስት መቶ የስፓርታ ሠራዊት እና አምስት መቶ የጣሊያን ወታደሮች ሙሉ በሙሉ መሞታቸው ነበር። ከዚህ ሌላ ግን ስፓርታውያኑ አገራቸውን ከወራሪ ለመከላከል የዘመቱ ሲሆኑ ጣሊያውያኑ ግን የሰው አገር ለመውረር ባደረጉት ሙከራ ላይ ነበር ያለቁት።








The Execution of Dogali, Engraving by Antonio Zoppi, Illustration for Illustrazione Italiana, 29 January 1895.

*ምስል 7፡- የዶጋሊ ውሎ (የጣ ትረቡና ላይ የተወሰደ፣ ጥር 26 ቀን 1895)*

የዶጋሊውን ክስተት የሰሙት የሮም ነዋሪዎች አምስት መቶ የተሰዉ ወታደሮቻቸውን ለማሰብ ለክብራቸው አደባባይ እንዲሰየምላቸው ጠየቁ። ከሮም ዋናው የባቡር ጣቢያ አጠገብ የሚገኘው ቺንኩቼንቶ አደባባይም ለአምስት መቶዎቹ ሰማዕታት መታሰቢያ ሆኖ ከተገነባ በኋላ ሰኔ 5 ቀን ስያሜው ጸደቀ።

ዶጋሊ ላይ በግፍ ለተገደሉባት አምስት መቶ ወታደሮች ካሳ የሚሆን ግዙት ኢትዮጵያ እንድትሰጣት ጣሊያን ጥያቄ አቀረበች። የጣሊያንን ጥያቄ በምንም ዓይነት እንደማይቀበሉት በመጥቀስ አፄ ዮሐንስ ለእንግሊዟ ንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ ላይ አስታወቁ። በደብዳቤያቸው ጨምረው እንደገለጹት የዶጋሊው ጦርነት የተከሰተው እንግሊዝ የሄዊት ስምምነትን ባለማክበሯ መሸኑን በመጥቀስ ወቅሰዋል።

በርካታ አውሮፓውያን ራስ አሉላ አነስተኛ ቁጥር የነበረውን የጣሊያን ጦር መማረክ ሲችል በግፍ መግደሉ ትክክል አለመሸኑን በመጥቀስ ወቅሰው ነበር። አፄ



The Legend of Bagdad. From *Le Tribunal Illustré*, 29 January 1895.

ዮሐንስም አሉላን በመከላከል ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ ጀነራላቸው አገሩን ከወራሪ ከመከላከል ውጪ ማንም አገር ላይ ጥቃት አለመፈጸሙን ተናግረው ነበር። ከኹለቱ ወገን የሚነሳው ወቀሳ እና ምላሽ እንዳለ ሆኖ የዶጋሊው ምላሽ አንድ መንግሥት አገሩን ከወራሪ ለመጠበቅ የሚወስደው የመከላከል እርምጃ እንደነበር ግልጽ ነው።

ሮም የነበሩት ሰር ጆን ሳቪል ለእንግሊዝ ንግሥት በጻፉት ደብዳቤ ጣሊያን ዶጋሊ ላይ ለተፈጸመባት ግፍ ካሳ እንደምትፈልግ በተደጋጋሚ እየገለጸች መሆኗን አሳውቋል። ኢትዮጵያ አስፈላጊውን ካሳ የማትከፍላት ከሆነ ሐያ አምስት ሺህ ወታደሮችን በመላክ ራስ አሉላን ለመቅጣት እየዛተች መሆኗንም ሳቪል ጠቁመው ነበር። በደብዳቤያቸውም ጣሊያን ራስ አሉላን ፍለጋ ወደ መሃል ኢትዮጵያ የምትዘምት ከሆነ የዶጋሊ ዓይነት ሁኔታ ሊጠብቃት እንደሚችል እንዲሁም ራስ አሉላን መያዝ ያለው ጠቀሜታ እንዳልታያቸው አሳስበውም ነበር።

*ኸማስፈራራያዋ በተጨማሪ ጣሊያን በኢትዮጵያ ድንበር ላይ ያሳትን ይዞታ በማስፋት ከኢትዮጵያ ጋር የንግድ ግንኙነቷን በማጠናከር የኢትዮጵያን ምርቶች ለመግዛት ለቅጸለች። ለካሄዷ አጠራጣሪ ዓላማን ከደርባው የያዘ ካልሆነ በስተቀር ለጣሊያን ታሳት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው ጥሬ ዕቃ ኢትዮጵያ ኢታመርትም። በተጨማሪም የጣሊያን ሕዝብ የመንግሥታቸውን የመስፋፋት እርምጃ ለይደግፍም* በማለት ነበር ሰር ጆን ሳቪል የጣሊያንን የወረራ ዕቅድ አገራቸው እንግሊዝ እንድታስብበት ያስጠነቀቁት።

እንግሊዝም ካይሮ በነበረው ቋሚ መልዕክተኛዋ ጀራልድ ፓርታል የሚመራ የዲፕሎማቶች ቡድን ወደ ኢትዮጵያ ላከች። ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት መስጠቷን ለኢትዮጵያ ላለማሳወቅ ፓርታል ባለሙሉ ሥልጣን መልዕክተኛ እንዳልሆነ በሹመት ደብዳቤው ላይ ጠቅሳ ነበር። ዕድሜው በሐያዎቹ አጋማሽ የሚገኘው ፓርታል በኢቶን ዩኒቨርስቲ የዲፕሎማሲ ትምህርት የቀሰመ ሲሆን የኢትዮጵያ ተልዕኮውን በከፍተኛ





ጉጉት ነበር የተቀበለው። በጉዞው ወቅት ኹሉንም እንቅስቃሴ እና ክስተት በጉዞ ማስታወሻው ያሰፈረ ሲሆን በኋላም በእንግሊዝ ተወዳጅ ከኾኑ የጉዞ እና አሰሳ ታሪኮች ጋር አብሮ አሳትሞታል።

የፓርታል ተልዕኮ ከመጀመሪያው ነበር እንቅፋት የበዛበት። ከሄዊት ስምምነት በኋላ እንግሊዝ ላይ ዕምነት ያጡት አፄ ዮሐንስ ፓርታል የሚመራው የዲፕሎማቶች ቡድን የጣሊያንን የጦር ጉዳት ካሳ ጥያቄ ለማስፈጸም የመጣ ስለመሸኑ ተጠራጠሩ። በንግሥት ቪክቶሪያ ማኅተም ለአፄ ዮሐንስ የተሳከው ደብዳቤም የንጉሡን ጥርጣሬ አጠናክረው። ደብዳቤው ‹‹ጣሊያን ወደ ኢትዮጵያ ዘልቃ የገባችው ነጋዴ ዜጎቿን ለመጠበቅ ሲሆን የራስ አሉላ ጥቃትም ይፄንን ያላገናዘበ ነበር›› በማለት እንግሊዝ ለጣሊያን ያላትን ወገንተኛነት ያሳየ ነበር።

ፓርታል በጥቅምት 1887 ወደ ምፅዋ በማምራት ነበር ተልዕኮውን የጀመረው። በምፅዋ ቆይታው የጣሊያንን የጦር ጉዳት ካሳ ጥያቄ በዝርዝር ተቀበለ። በጥያቄዋ መሠረትም ጣሊያን ዶጋሊ[1] ሰኔቲ እና ሌላም በአቢሲኒያ ግዛት ሥር ያልኾኑ ቦታዎች እንዲሰጧት ዘረዘረች። የጣሊያንን ጥያቄ የያዘው ፓርታል ወደ አፄ ዮሐንስ ለመቅረብ በራስ አሉላ በኩል ማለፍ ነበረበት። በመኾኑም ከምፅዋ በቀጥታ ያመራው የዶጋሊው ባለ ታሪክ ራስ አሉላ ወደሚገኝበት አስመራ ነበር።

ራስ አሉላ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ የጀግንነት ቦታ ካላቸው ጥቂት አርበኞች አንዱ ነው። አሉላ ቀጭን፣ ለግላጋ ወጣት ሲሆን ጎድንዳ ዐይኖቹ እና ከብ ፊቱ የተሰየ ውበት ይፈጥሩለታል። ከፓርታል ጋር ሲ፣ ሲናኝበት ወቅት ከሐር የተሠራ ሽሚዝ እና ሱሪ የለበሰ ሲሆን ከበላዩ ደግሞ የአንበሳ ቆዳ ደርቦ ነበር። በቀኝ ትከሻው ጠመንጃ የታጠቀ ሲሆን በብር ያጌጠ ጋሻ ደግሞ በግራ እጁ ይዞ ነበር።



The young Abuna. From Lincoln de Castro, *Nella terra dei negus, pagine raccolte in Abissinia* Milan: Fratelli Treves, 1915.

### ራስ አሉላ

ራስ አሉላን በቅርብ ከሚያውቁት መካከል የእንግሊዝ መልዕክተኛ የነበረው አንስተስ ዋይልድ አንዱ ነበር። ዋይልድ ለአሉላ ከፍተኛ ክብር የነበረው ሲሆን የአሉላን ተክለ ሰውነት እና ባሕርይ እንዲህ ነበር የገለጸው፡- *«ራስ አሉላ በአጠቃላይ ጠይም አንግሊዛዊ ይመስላል። መልከመልካም ወጣት ሲሆን የሚያማምሩ ዐይኖች እና ሰልካካ አፍንጫ የታደለ ነው። ለንደበተ-ርቱዕ ከመሸኑም በላይ በአስልነት ያምናል። ለዚህ ማሳያም በዙሪያው የነበሩ አማካሪዎቹ ሙስሊም እና ክርስቲያን መሆናቸውን መመልከቱ በቂ ነበር።»* የኹለቱ መልካም ወዳጅነት የዘለቀው ራስ አሉላ ከአድዋ ጦርነት በኋላ ባልተጠበቀ ሁኔታ እስከሞተበት ዕለት ድረስ ነበር።

ፖርታልን በአስመራ የተቀበለው ራስ አሉላ ዋይልድ ከገለጻው ፈጽሞ የተለየ ነበር። ከሄዊት ስምምነት በኋላ አንደ አፄ ዮሐንስ አሉላም በእንግሊዞች ከሃዲነት ተበሳጭቶ ነበር። በመሸኑም ፖርታል የጣሊያንን ጥቅም ለማስጠበቅ የተላከ መሸኑን የተረዳው ራስ አሉላ አስተያየቱ በጥርጣሬ የተሞላ ነበር። አስመራ የነበረው የራስ አሉላ ጽ/ቤት የተለየ ግርማ ሞገስ ነበረው። በሳር የተከደነው የቤቱ ጣሪያ መሃል ላይ





መስቀል ይታያል። ከመስቀሉ አናት ላይ የተቀመጠው ኩብ ቅርፅ ባለቤቱን ከሁዳ እንደሚለይለት ይታመን ነበር።

ፖርታል ወደ ራስ አሉላ እልፍኝ ሲገባ ውስጡ ጨለምለም ያለ በመሸኑ ለሰከንዶች ያህል ዐይኑን ለማላመድ ቆመ። ከእልፍኙ ጥግ ላይ በቀይ ወንበር ላይ የተቀመጠውን ራስ አሉላ እና በርካታ አሻቢዎቹን የተመለከተው ፖርታል በአድናቆት አፉን ከፍቶ ነበር። የወቅቱን ሁኔታ ሙሉ በሙሉ የጻፈው ፖርታል ራስ አሉላን በተለየ ሁኔታ ነበር የገለጸው። *"ዋቆጣ ቀለሙ ከበርካታ የትግራይ ለካባቢ ወንዶች ለንዥር ሲታይ ጠቆር ያለ ሲሆን ብሩህ ዐይኖቹ እና ነጫጭ ጥርሶቹ ከርቱት ይታያሉ። የራስ አሉላ ዓይነት ዐይኖችን ከዚህ በፊት የተመለከትኩት ኑብር እና አቦ ሸማኔ ላይ ብቻ ነበር። በለው ፊት ላይ እነዚያን ዓይኖች ዐያለሁ ብዙ አልጠበቅሁም ነበር።"* በማለት ፖርታል የራስ አሉላን የተለዩ ዐይኖች ገልጿቸዋል።

ፖርታል ከአሉላ ጋር ለመገናኘት ሲያመራ ያማረ የዲፕሎማት ሙሉ ልብስ ነበር የለበሰው። ራስ አሉላ በበኩሉ ሐምራዊ የሃር ሽሚዝ የለበሰ ሲሆን ከአጠገቡ የነበረው ጠረጴዛ ላይ የማርቲኒ-ሄንሪ ጠመንጃው ተደግፏል። የአልፍኙ ግድግዳ በተለያዩ የአራዊት ቀንድ እና ቆዳ አጊጧል። በተሰቀሉት የአራዊት ቀንዶች ላይ የተለያየ ሞዴል ያላቸው ጠመንጃዎች ተንጠልጥለው ይታያሉ።

ፖርታል ውይይቱን የጀመረው ለአሉላ ስጦታ በማቅረብ ነበር። ስጦታውም በዘመናዊነቱ አሉላ ከታጠቀው ማርቲኒ-ሄንሪ ጠመንጃ የተሻለ የሆነው ዊንቼስተር ጠመንጃ ከ500 ጥይት ጋር ነበር። ስጦታው በአሉላ ላይ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ አለማምጣቱን ቅጭም ካለ ገጽታው ላይ መረዳት ይቻል ነበር።

የፖርታል ዋና ተልዕኮ ከአፄ ዮሐንስ ጋር በመገናኘት የሰላም ድርድር ማድረግ የነበረ ቢሆንም ጣሊያን ለዶጋሊው ውሉ ዕውቅና እስክትሰጠች ድረስ እንደማይደራደር አሉላ አሳወቀው። ጣሊያን የጠየቀችውን የጦር ጉዳት ካሳ



The young Mula. From Lincoln de Castro, *Nella terra dei negus, pagine raccolte in Abissinia*. Milan: Fratelli Treves, 1913.

በተመለከተም አሉላ ለፖርታል የነለጸለት እንዲህ በማለት ነበር፡- ‹‹ጣሊያን ለአቲ መውረድ የምትችለው አፄን የርም ፖሎ ለማድረግ ከተስማማች ብቻ ነው።›› ፖርታል ከአፄ ዮሐንስ ጋር እንዳይገናኝ የፈለገው አሉላ መልዕክተኛውን ለዐሥር ቀናት ያህል የቁም እሥረኛ አድርጎ አስቀመጠው።

ፖርታልን እንዲያስገባው የሚያዝ መልዕክት ለአሉላ ደረሰው። ንጉሡ ጦራቸውን ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ በሚያዘምቱበት ወርኃ ነሐሴ አሸንጌ ሐይቅ አቅራቢያ ፖርታል እንዲያገኛቸውም አሉላ አመቻቸ። ፖርታል እና ባልደረቦቹ የንጉሡ ጦር ሲያልፍ ከመንገድ ዳር እንዲመለከቱ ታስቦበት እንደነበር ያለውን ግምት በማስቀደም በወቅቱ የተመለከተውን ወታደራዊ ሰልፍ ፖርታል የገለጸው እንደሚከተለው ነበር።

> ‹‹አፄና ጓደኞቹ ቢኾ በፅለቱ የተመለከትነው የወታደር ብዛት በጥንቃቄ ነበር ያሰላነው። በአንድ ደቂቃ ውስጥ ያለፉትን ወታደሮች በመቁጠር ጀምረን አጠቃላይ ሠራዊቱ ለማለፍ የወሰደበትን ሰዓት ያገነን። በዚህ መሠረት በማስላት የወታደሩ ቁጥር ከ70 ሺህ እስከ 80 ሺህ እንደሚደርስ ገመትን። ከሠራዊቱ መካከል ባማረ በቅሎው ላይ ሆኖ ነበር ንጉሡን የተመለከትነው። ባለቀይ ጥለት ነጭ የለበሻ ሸማ የለበሰ ሲሆን ፊቱም በክፈል ተሸፍኗል። የንጉሡ ቀይ የሐር ጃንጥላ ከተራው ወታደር የተለየ ምልክት ለጥቷቸዋል።

ፖርታል አፄ ዮሐንስንም ሆነ የኢትዮጵያን ሙሉ የጦር አሰላለፍ ሲመለከት የመጀመሪያው ነበር። ንጉሡ ለውጊያ ዝግጁ መሆናቸውንም ያረጋገጠው ሰልፉን በመመልከት ነበር።





ፖርታል ከንጉሡ ጋር በተገናኘበት ወቅት ያመጣላቸውን የቁንጅስተር ጠመንጃ እና የጦር ሜዳ መነጽር በስጦታ መልክ አቀረበ። አፄ ዮሐንስም በምላሹ ሙሉ የኢትዮጵያ ልብስ፣ የእንበሳ ለምድ፣ ጦር እና ጋሻ አበረከቱለት። ልብሱን በጣም ስለወደደውም ወደ ካይሮ ሲመለስ በቀጥታ ያመራው ወደ ፎቶ ግራፍ ባለሙያ ነበር።

ድርድሩ ፖርታል እንደጠበቀው አልነበረም። አፄ ዮሐንስ ከአሉላ በላይ የከረረ አቋም ይዘው ነበር የጠበቁት። በድርድሩ ወቅትም ‹‹ሉዐላዊ ክብሬ የተጣለው እኔ ሆኜ ሳለሁ ለምን ጣሊያን ልትቀጣኝ ትዝታሰቸኝ?›› በማለት ነበር አፄ ዮሐንስ እምቢታቸውን ለፖርታል የገለጹለት። ድርድሩ ያልተሳካለት ፖርታል በነሐሴ ወር ወደ ምፅዋ ተመለሰ። በተመሳሳይ ወቅት አፄ ዮሐንስ ጦራቸውን በደበልጥ ወደ ሰሜን በማስጠጋት በምፅዋ እና አስመራ መካከል የምትገኘው ጊንዳ ላይ መሸጉ። የጣሊያን ምሽግ ከነበረበት ለአቲ የነበራቸው ርቀትም በጣም ጠበበ።

አፄ ዮሐንስ ጣሊያንን ለመውጋት በተዘጋጁበት ወቅት የማሄጂ ጦር ምዕራባዊ ግዛታቸውን እንደወረረ ሰሙ። ወራሪው ኃይል ጥር 21 ቀን 1888 የጎጃሙን ንጉሥ ተ/ኃይማኖት ድል በመንሳት ወደ ጎንደር አልፎ በከተማዋ ላይ ከፍተኛ ውድመት እደረሰ። ወራሪው ኃይል በርካታ አብያተ-ክርስቲያናት ጨምሮ ቤቶችን በቃጠሎ አወደመ።

አፄ ዮሐንስ ጦራቸውን ወደ ጎንደር ለማዝመት ሲወስኑ ራስ አሉላ በቅድሚያ ጣሊያንን መምታት እንደሚሻል ሀሳብ አቀረበ። ንጉሡ የአሉላን ሀሳብ ሳይቀበሉ መላው ጦራቸውን እንዲሁም ራስ አሉላን አስከትለው ወደመጡበት ተመለሱ። በሚያዝያ 1888 ለአቲ ብቻ ሳይሆን አስመራም ያስ በቂ የመከላከያ ሠራዊት ጥበቃ ሆነው ቀጣይ እጣቸውን በመጠባበቅ ላይ ነበሩ።

ጣሊያን በዮሐንስ ላይ ተጨማሪ ጫና ለማሳደር መንቀሳቀስ የጀመረችው ቀድሞ ነበር። ራስ አሉላ በአስመራ ጌራልድ ፖርታልን ተቀብሎ ባናገረበት ወቅት የጣሊያን ተወካዮች ደግሞ በአዲስ አበባ የምኒልክን አጋርነት ለማግኘት በመደራደር

ላይ ነበሩ። በዮሐንስ ላይ እንዲነሳ ሰማሳመን ጣሊያን ለምኒልክ የጦር መሣሪያ ስጦታ እና የልዩ ወዳጅነት ጥሪ አቀረበችለት። ምክንያታቸው የተለያየ ቢሆንም ጣሊያን እና ምኒልክ የአፄ ዮሐንስ መዳከምና መውደቅ ላይ ተመሳሳይ አቋም ነበራቸው።

ንግሥናቸው በሸዋ ግዛት ብቻ የተወሰነው ምኒልክ አፄ ዮሐንስን በማስወገድ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የመሆን ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው። ፍላጎታቸውን በፍጥነት ለማሳካትም የአፄ ዮሐንስን ሞት ጨምሮ የትኛውንም መንገድ ለመጠቀም ዝግጁ ነበሩ።

አፄ ዮሐንስ በበኩላቸው የምኒልክን ዳተኝነት ጠንቅቀው ያውቃሉ። ምኒልክን ለማስገዛትም በ1870ዎቹ ጦራቸውን መላክ ግድ ብሏቸው ነበር። ንጉሠ-ነገሥትነታቸውን በጉልበት የተቀበለው ምኒልክ በየትኛውም አጋጣሚ ዙፋናቸውን ለመነቅነቅ እንደሚሞክር የሚያውቁት ዮሐንስ፣ ጣሊያንን ለመግጠም ወደ ሰሜን ባቀኑበት ወቅት ምኒልክን ያለ በቂ ተከታታይ ትተው መምጣታቸው አሳስቧቸው ነበር። የምኒልክን የዘውድ ጥማት የተመለከቱት ጣሊያን ደግሞ ፍላጎቷን ከምኒልክ ጋር በማቀራረብ አፄ ዮሐንስ ላይ በጋራ ለመነሳት ተዘጋጀች። በመሸኑም ለምኒልክ የንጉሰ ንጉሥትነት ጉዞ እጋዥ በመሆን ለመለሰፍ ወሰነች።

ስለ ኢትዮጵያ በተለየ የአድናቆት ስሜት ተሞልቶ ይናገር የነበረው አጉስተስ ዋይልድ በአንድ ወቅት ስለ ምኒልክ የሚከተለውን ፅፎ ነበር። ‹‹ምኒልክ በከፍተኛ ጉጉት የተሞላ ሊሆን ዮሐንስን ከማስወገድ የሚገታው ነገር ያለ አይመስልም።›› የዋይልድ ገለጻ በአብዛኛው እውነት ቢሆንም በወቅቱ ግልጽ ያልነበረው ምኒልክ በጣሊያኖች ገንዘብ ተደልሎ ዮሐንስን ለመጣል መነሳቱ ነበር። በወቅቱ የምኒልክን ትክክለኛ ፍላጎት ጣሊያኖች በቀላሉ ሊገነዘቡት አልቻሉም ነበር።

በደቡብ በምኒልክ የማይጨበጥ አቋም እንዲሁም በሰሜን በጣሊያን የወረራ ስጋት የተወጠሩት አፄ ዮሐንስ ጦራቸውን በቀጥታ ያዘመቱት በምዕራብ የአገሪቱ





ክፍል ወረራ በፈጸመባቸው የመሃዲስት ጦር ላይ ነበር። አጉስተስ ዋይልድ በምኒልክ አካሄድ ላይ የነበረውን ጥርጣሬ ከጊዜ በኋላ ነበር የጻፈው። እንደ ዋይልድ ከሆነ "ምኒልክ አፄ ዮሐንስን ለመጣል በምስጢር ከመሃዲስት ወራሪዎች ጋር ሳይስማሙ አልቀሩም" በማለት የሸዋው ንጉሥ እገር የመክዳት ድርጊት እንደፈጸሙ ጽፏል።

በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ የዮሐንስ ሠራዊት ብልጫውን ይዞ ነበር። ከአፍታ በኋላ አፄ ዮሐንስ ከመሃዲስት በተተኮሰ ጥይት ሲቆስሉ ጦራቸው በመሃዲስት መበለጥ ጀመረ። በርካታ የኢትዮጵያ ሠራዊት የቆሰሉ ንጉሣቸውን በመከበብ የመከላከል ውጊያ እያደረጉ ማፈግፈግ ጀመሩ። በኹለተኛው የውጊያው ዕለት ውሉ የመሃዲስት ጦር የኢትዮጵያን ሠራዊት በመውረር የአፄ ዮሐንስን ራሳ ማርኮ ጭንቅላታቸውን ቆርጦ ወሰደ። ለእንፀባራቂ ድላቸው ማረጋገጫም የንጉሡን ጭንቅላት ለቀናት ያህል በካርቱም አደባባይ ለዕይታ አስቀምጠውት ነበር።

የዮሐንስን ዘውድ ማን ይረከበዋል? በሞት አፋፍ ላይ ሳሉ አፄ ዮሐንስ ልጃቸው መንገሻ የዘውዳቸው ወራሽ እንዲሆን ተናዘው እንደነበር ይነገራል። የሚቹ ኑዛዜም መንገሻ ለዘውዱ እንዲንቀሳቀስ መንገድ ከፍቶለታል። የአባቱን ዘውድ ለመውረስ ግን ከፍተኛ የሆነ ተግዳሮት ከፊቱ ይጠብቀዋል።

# ምዕራፍ አራት

## የነጻነት ዋጋ

አዲስ አበባ ከዘመቻ በመመለስ ላይ የነበሩትን ባለድል ንጉሥ ምኒልክ ለመቀበል ሽርጉድ እያለች ነበር። በወላይታ ሕዝብ እና ንጉሥ ላይ ጥር 18 ቀን 1895 ድልን የተቀዳጁት ምኒልክ ከአንድ ቀን በኋላ አዲስ አበባ ሲደርሱ ደማቅ አቀባበል ይጠብቃቸዋል። ንጉሡ አዲስ አበባ መግቢያ ላይ የደረሱት በጥቅምት ዋዜማ በክተራ በዓል ስለነበር ምሽቱን በክተማ ዳርቻ በማሳለፍ በዕለተ ጥቅምት ወደ መሃል ለመግባት ወሰኑ። በጥምቀት ዋዜማ ለዚያውም በያም ዕለት አዲስ አበባ በመግባት ድላቸውን ለሕዝብ ያሳበሰሩት በሕዝቡ ዘንድ በያም ቀን ድልን ማብሰር የመጥፎ ዕድል አመላካች መሸኑ ስለሚታመን ነበር። በመሸኑም ንጉሡ በዕለተ ጥምቀት ለመግባት የክተራ በዓልን ከክተማዋ ውጪ አሳለፉ።

በማግስቱ ደማቁ የንጉሡ የአገባብ ሥርዓት የተጀመረው በካህናት ሰልፍ ነበር። በባለድባብ ጃንጥላ እና የቀሳውስት አልባሳት የደመቀው ሰልፍ ታቦታትን በማጀብ በዝግታ አለፈ። ከድል የተመለሰው ሠራዊት ካህናት እና ቀሳውስቱን ተከትሎ ተመመ። ቁጥራቸው ወደ ሠላሳ የሚጠጉ ባለ ነጋሪት፣ አታሞ እና እምቢልታ ሰልፈኞች ከፊት ሆነው ለፈረሰኛ ወታደሮች መንገድ እየመሩ አለፉ።

በበርካታ የጦር መሪዎቻቸው የታጀቡት ምኒልክ ከሰልፈኛ ሠራዊቱ መካከል ታጅበው በዝግታ ይራመዳሉ። አፈ ንጉሣቸው ከፊት ሆኖ ሲመራቸው ከጀርባቸው ደግሞ በርካቶች ጥሩንባ እየነፉ ተከተሏቸው። የመንሳ ፋከራ እና ሽለላዎችን ተከትሉ ‹‹የእንኳን ደኅና መጡ›› ተኩስ ተደረገ። በመቀጠል ከጎዳር ወር ጀምሮ ባሉቻቸው፣ ልጆቻቸው እና ወንድሞቻቸው ዘመቻ ቆይተው የተመለሱላቸው ሴቶች በከፍተኛ ድምፅ እልልታቸውን አሰሙ።





የድል መልስ ፌሽታው እንደ ጥንታዊ ሮማውያን ሥነ-ሥርዓት እርስ በእርስ በመሞጋገስ ላይ የተመሠረተ ነበር። ባለድል ነገሥታት በወታደሮቻቸው ይሞገሳሉ፣ ይሠደሳሉ። ሕዝቡም ባለድል ሠራዊታቸውን በከፍተኛ ድምፅ እየሙሽ ይቀበላቸዋል።

የወታደሮች እና የምርኮዎች ሰልፉ በአጠቃላይ ሦስት ቀናት የፈጀ ነበር። የወላይታ የኢኮኖሚ መሠረት እርሻ እና ከብት እርባታ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የምኒልክ ሠራዊት እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ከብት ይዞ ነበር የተመለሰው። በተጨማሪም ወደ ዐሥራ አምስት ሺህ የሚደርስ የወላይታ ሠራዊትም በምርኮ ተይዞ ሙጥኝል። ምርኮኞች በባርነት ከማገልገል የተሰየ ዕድል አይጠብቃቸውም። በዘመቻው ለተሳተፉ የምኒልክ ወታደሮች ብሽልማት መልክ እስኪከፋፈሉ ድረስ በግዞት ይቆያሉ።

የሰልፉ ከፍተኛ ድምቀት የነበረው የምርኮኛው የወላይታው ንጉሥ ጦር ያሰፈበት ነበር። የምኒልክን ወረራ ለመከላከል ሕዝቡን በጥሩ ሁኔታ አደራጅቶ የተዋጋ ቢሆንም አልተሳካለትም ነበር። የምርኮኛው ንጉሥ ጦና በሰልፉ መናር የምኒልክን ድል ምሉዕነት አስመስክሮ ነበር። የጦና በምርኮ መያዝ በወላይታ ሕዝብ ዘንድ የነበረውን ከበሬታ በማሳጣት ሕዝቡ ምኒልክን እንዲያከብር ያደርጋል። ምርኮኛውን ለሕዝቡ ማሳየት ያሰውን ፖለቲካዊ ትርፍ ምኒልክ ቀድመው ስለተረዱ ነበር ቀስለኛውን ንጉሥ ጦና አክመው የሰልፉ አክል ያደረጉት።

የጦና የፍርድ ሂደት የተጀመረው ከቀናት በኋላ ነበር። ንጉሥ ጦና ከርስትናን ለመቀበል ከተሰማማ በኋላ ምኒልክ ይቅርታ እደረጉለት። ከይቅርታው በኋላም ነጭ የሐር ልብስ እና ጥቁር የንጉሥ ካባ በአግባቡ አልብሰው ፎቶ ግራፍ አሥነስተውታል። በወቅቱ ከምኒልክ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነጭ ሻሽ በራሱ ላይ ተጠምጥሞ ዘውድም ተጫነለት። ንጉሥ ጦና ፎቶግራፍ በተነሳበት ወቅት ፊቱ ላይ የሚታየውን ስሜት ለመግለጽ ያስቸግራል።

ንግሥናውን በማጽደቅ ምኒልክ ጦናን ወደ ወላይታ ገባርነቱ ለመመለስ የወሰኑት ንጉሡ ሕዝቡን እርሳቸው ከሚልኳቸው እንደራሴዎች የተሻለ ስለሚያውቅ ነበር። ሽንፈቱን በጸጋ በመቀበሉም ምንም ዓይነት የማፈንገጥ ሙከራ እንደማያደርግ ገምተው ነበር። ከፍተኛ ቁጥር ያለው የወላይታ ሕዝብ በምርታማነቱ ይታወቃል። በመሆኑም ጦናን ወደ ግዛቱ በመመለስ ዓመታዊ ግብርን በአግባቡ በመሰብሰብ እንዲልክላቸው ነበር ምኒልክ ያሰቡት።

የወላይታው ዘመቻ ለምኒልክ ወታደራዊ ድል እና ኢኮኖሚያዊ ጉልበትን ቢፈጥርላቸውም በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ቁጣን ቀስቅሰባቸዋል። አውሮፓውያን አፍሪካ ውስጥ ለሚደረግ የእርስ በእርስ ጦርነት ግድ እንደሌላቸው ያሰቡት ምኒልክ ስሕተታቸውን የተረዱት ዘግይተው ነበር። የፈረንሳይ መልዕክተኛ የነበረው ጂን ጋስተን ቫንደርሄይም ወደ አውሮፓ ሲመለስ ስለምኒልክ ውስጣዊ ዘመቻ በማጋሰጥ የንጉሡ ድርጊት እንዲወገዝ አደረገ።

ምኒልክ ቫንደርሄይምን ማመን አልነበረባቸውም። ለፈረንሳይ ኑጋዴዎች ገበያ ለማፈላለግ በ1884 ከረምት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ቫንደርሄይም የምኒልክን አመኔታ ለማግኘት ብዙ ጊዜ አላስፈለገውም። የዘመቻ ስኬታቸውን እንዲመለከት እና ለአውሮፓ ምስክርነቱን እንዲሰጥላቸው በማሰብ ነበር ምኒልክ ዐሥራ ኹለት አኻቢ መድበውለት ወደ ወላይታ የወሰዱት። ቫንደርሄይም አጋጣሚውን በመጠቀም የጋዜጠኝነት ሥራውን ተያያዘው። ቫንደርሄይም ፈረንሳዊው ፓውል ሶዳር በሠራው የፎቶ ካሜራ በመታገዝ የወላይታውን ዘመቻ ሙሉ ታሪክ ለመያዝ ቻለ።

ምኒልክ ወደ ወላይታ ያደረጉትን ዘመቻ እንደ ክርስቲያናዊ ቅዱስ ተግባር ነበር የተመለከቱት። የወላይታ ሕዝብ ቀድሞ ክርስቲያን እንደነበሩ እና በ17ኛው ክፍለዘመን በአህመድ ኢብን ኢብራሂም አል-ጋዚ ዘመቻ አማካይነት ወደ እስልምና እንደተቀየሩ የሚያምኑት ምኒልክ በዘመቻቸው የወላይታን ሕዝብ ከእስልምና ጭቆና





ነፃ እንደሚያወጡ በማሰብ ነበር ዘመቻቸውን ያካሄዱት። የወላይታ ሕዝብ መሳኪ ዕድል በተሰይም ከምኒልክ ወረራ በኋላ የኃይማኖት ለውጥ ግዴታ ነበር የሆነው።

ጦና የምኒልክን ጦር ኃያልነት መቋቋም አልቻለም። ምኒልክ ዘመቻቸውን ባወጁበት ወቅት ቁጥሩ ከ80 ሺህ በላይ የነበረው ሠራዊታቸው በምሥራቅ አፍሪካ እጅግ ግዙፍ መሸኩን ያስመሰከረ ነበር። በአፄ ዮሐንስ ሞት ዋዜማ የምኒልክ ጦር በቁጥሩም ሆነ በይዘቱ የዮሐንስን ጦር በልጦ ነበር። ለጣሊያን፣ ፈረንሳይ እና ለግለሰብ የጦር መሣሪያ ነጋዴዎች ምስጋና ይግባቸው እና የምኒልክ ሠራዊት ዘመናዊ የጦር መሣሪያም ታጥቆ ነበር። ከዚህ አንፃር ሲገመገም የወላይታ ጦር ከምኒልክ ሠራዊት ፊት መቆም የማይችል ነበር።

የምኒልክ ጦር መንቀሳቀስ ሲጀምር እቴጌ ጣይቱ ብጡል በወላይታ ላይ ሊደርስ የሚችለውን አስፈሪ አልቂት በመገመት ምኒልክን እና የጦር አዝማቾቻቸውን ሳይቀር ተማፅነው ነበር። በዚህ ውጥረት መካከል ንግሥቲቷ ታመው አልጋ ሲይዙ ምኒልክ አጋጣሚውን ተጠቅመው ዘመቻውን አዘዙ። በጥቂት ቀናት እንደሚመለሱም ለንግሥቲቷ ተናግረው ነበር።

## ምኒልክ ወደ ወላይታ ያደረጉት ዘመቻ

ምኒልክ ለዘመቻ የመረጡት የክረምቱ ማለቂያ የሆነው ወርኃ ጎንቻር ነበር። የአጠቃላይ ዘመቻው መሪ አድርገው የሾሙት የራስ ሚካኤልን ጦር ነበር። ምኒልክ ከእስልምና ወደ ክርስትና የተቀየሩትን ራስ ሚካኤል በመሪነት ሲመርጡ አንድም የራስ ሚካኤልን ታማኝነት ለመፈተሽ በሌላ በኩል ደግሞ የሙስሊሙ የወላይታ ሕዝብ ቀጣይ ዕጣ ፈንታ ከራስ ሚካኤል ተመሳሳይ መሸኩን ለማመላከት ነበር። በራስ ሚካኤል ሰባት ሺህ ሠራዊት ፊት አውራሪነት ከዐሥራ ሦስት ሺህ እስከ ዐሥራ ስምንት ሺህ የሚደርስ ቁጥር ያለው የምኒልክ ጦር የጦናን ሠራዊት ለማፍረክረክ ተንቀሳቀሰ።

የዘመቻ እንቅስቃሴው በአጠቃላይ ሲታይ የሚንቀሳቀስ የጦር የጎራዴ እና የድንኳን ጫካ ነበር የሚመስለው። እያንዳንዱ ራስ እና አዝማች የየራሱን አሻቢ እና ወታደር አስከትሎ ነበር የሚንቀሳቀሰው። በአሰላለፋቸውም የምኒልክ ጦር የራሶችን እና የአዝማቾችን ጦር እንደየተዋረዳቸው እና ማዕረጋቸው አስከትሎ ነበር የሚጓዘው። ስንቅ እና ትጥቅ ከተጫኑት የጋማ ከብቶች በተጨማሪ ማር፣ ቅቤ እና በርበሬ ያዘሉ ሴቶችም አብረው ዘምተዋል።

ምኒልክ ለንግሥት ጣይቱ ብጡል ቃል የገቡት ዘመቻው በአጭር ጊዜ እንደሚጠናቀቅ ቢሆንም እስከ ታኅሳስ ወር መጨረሻ ድረስ የዘመቻው ዜና አዲስ አበባ አልደረሰም ነበር። ዘመቻው ከተገመተለት ጊዜ በላይ እንዲወስድ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ምኒልክ የወላይታን ጦር አሳንሰው መገመታቸው ነበር። የወላይታ ሕዝብ በቀይ ሰም መሬት ላይ የተመሠረተ የግብርና ህይወቱ ሀብታም ያደረገው ቢሆን ከግብርናው በተሰየ ግን ጠንካራ ተዋጊ መኾኑ ለወራሪው የምኒልክ ጦር አዳጋች ሆኖበት ነበር።

የወላይታ አመራር በውጊያው ወቅት ያሳየው ብቃት የሚደነቅ ነበር። ንጉሥ ጦና እየመጣበት የነበረውን ግዙፍ ጦር ለመግጠም የመረጠው ስልት የሽምቅ ውጊያን ነበር። ጦራቸው የወላይታ ግዛት እንደደረሰ ምኒልክ ንጉሥ ጦና እጁን ይሰጥ ዘንድ እንዲህ ሲሉ ጠየቁት። ‹‹ሕዝብህን አታስፈጅ፤ ግዛትህንም አትጣ። እጅ ስጥ። ግብርንም ክፈል።›› በወቅቱ የነበሩ የምኒልክ ጸሐፍት የንጉሥ ጦና ምላሽ እንዲህ እንደነበር ጠቅሰዋል።

‹‹ክርስቲያኖች ወደ ግዛቴ እንዲገቡ አልፈቅድም፤ ለእነርሱም አልገብርም። ለመፋለም ዝግጁ ነኝ።››

የንጉሥ ጦና ሠራዊት የመከላከል እርምጃ የጀመረው ገና የምኒልክ ጦር በመንገድ ላይ ሳለ ነበር። ጉድንድ በመቆፈር እና ወጥመድ በማጥመድ ቀድሞ





የተዘጋጀው የጦና ሠራዊት በርካታ የምኒልክ ወታደሮች እና የጋማ ከብቶች ላይ ጉዳት አደረሰ። በተጨማሪም የምኒልክ ሠራዊት ቁጥቋጦ በመመንጠር እንዲሁም መንገድ በማስተካከል ስለተጠመደ ነበር ዘመቻው ተጨማሪ ቀናትን የወሰደው።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ወላይታ መዲና ሲቃረብ የጦና ሠራዊት በማፈግፈጉ ሽንፈቱን ማዘግየት ቻለ። ያም ሆኖ ግን ንጉሥ ጦና የወላይታን ሕዝብ ያለምንም ተከላካይ ለምኒልክ ሠራዊት ጥሎ ነበር የሸሸው። የጦናን የሽምቅ ውጊያ ደግፈዋል በሚል ሰበብ የምኒልክ ሠራዊት በተራው ሕዝብ ላይ እርምጃ መውሰድ ጀመረ። ራስ ሚካኤልም ሠራዊታቸውን በማዝመት በርካታ የወላይታ መኖሪያ ቤቶችን እና የንብ ቀፎዎችን በእሳት አወደሙ።

የበርካታ መንደር ነዋሪዎች ለምኒልክ ሠራዊት እጃቸውን ሰጡ። አንዳንዶች ደግሞ የምኒልክን ሠራዊት መንደራቸው ከመድረሱ አስቀድሞ ለሠራዊቱ የዛፍ ቅርንጫፍ በማሳየት ተንበረከኩ። ምርኮኞችም በፈቃዳቸው ለምኒልክ ለመሰለል እና ጦና የመሸገበትን ቦታ ለመጠቆም ተስማሙ።

ንጉሥ ጦና የመሸገበት ቦታ እንደታወቀ የምኒልክ ሠራዊት ስንቅ እና ትጥቅ አቅራቢዎችን ወደ ኋላ በመተው በምሽት ዘመተ። እስከ አባያ ሐይቅ ድረስ በመዝመትም የጦናን ይዞታ በምዕራብ እና በምሥራቅ አቅጣጫ በመክበብ መውጪያ አሳጡት። ከበባው እየጠበበ መኾኑን የተመለከተው ንጉሥ ጦና የማምለጥ ሙከራ ቢያደርግ ራሱን እንደሚያጠፋ ገባው። ቀጣዩ ሥራ የምኒልክ ግዙፍ ሠራዊት እና የጦር መሣሪያው ነበር።

ታኅሳስ 11 ቀን የጦና ሠራዊት ባልቻ በሚመራው የመድፈኛ ብርጌድ ተከበበ። በሰላሙ ቀን የምኒልክ ግምጃ ቤት ኃላፊ በመሆን የሚያገለግሉት ባልቻ በጦርነቱ ወቅት የመድፈኛው ጦር መሪ በመሆን አገልግለዋል። የባልቻ ሠራዊት የሚተኩሳቸው ጥይቶች በጦና ሠራዊት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከተሉ። በከባ ቅጠል

ተሸፍነው የነበሩት የጠና ወታደሮች ቀስት ለመወርወር ብቅ ሲሉ የተቀበላቸው የባልቻ ሠራዊት ጥይት ነበር።

ንጉሥ ጠና ታኅሳስ 13 ቀን በቁጥጥር ሥር ቢውልም ጦርነቱ ግን ለቀናት ቀጥሎ ነበር። ታኅሳስ 18 ቀን የመጨረሻው ዘመቻ ተጠናቀቀ። ንጉሥ ጠናም በምኒልክ ፊት ቀርቦ የሚከተለውን የፀፀት ንግግር አደረገ።

*«የእራሴን ክብር ማስቀደሜ ሌሎች ክርስቲያን ወንድሞቼ እና ሕዝቤም ተጨፍጭፎ ከመሞከት ለእንተ እጅን ብሎ ይሻል ነበር። የሕዝቡ ሞት ለእኔ ይሁን።»*

ንጉሥ ጠና ለሕዝቡ ማለቅ ራሱን ተጠያቂ በማድረግ ይናዘዝ እንጂ በወላይታ የተደረገው ግድያ እና ዘረፋ ቀድሞ በሐረር እና በክፋ ዘመቻ የተሳተፉትን የምኒልክ ሠራዊት አባላት ሳይቀር ያስደነገጠ ነበር። በርካታ አጋሮቻቸውን በጠና የሸመቅ ውጊያ ያጡት የራስ ሚካኤል ሠራዊት አባላት በበቀል ስሜት ተገፋፍተው ብዙ ቁጥር ያለው የወላይታ ሕዝብ ገደሉ። ግድያውን ያቆሙት ከምኒልክ ቁጥታ ትዕዛዝ ከደረሳቸው በኋላ ነበር።

ወራሪው ጦር በምርኮ ላያዛቸው የወላይታ ተወላጆችም ርኅራኄ አሳይቶም ነበር። ዘመቻው የዐይን ምስክር የነበሩ የታሪክ ጸሐፍት ጭፍጨፋውን የገለጹት እንዲህ በማለት ነበር። «የወላይታ ሕዝብ በአንዲት ደንበር ነበር የተፈጀው።» ይህ በእርግጥ የተጋነነ ቢሆንም ምኒልክ የሚች እና ምርኮኛ ወላይታዎች ቁጥር እስከ 18 ሺህ እንደሚደርስ ተናግረዋል። የወቅቱ ታሪክ ጸሐፊ የሚቹ ቁጥር 18 ሺ 987 እንደነበር ቢጽፍም ሻንደርሃይም በዘኩሱ ቁጥሩ ከዚያ በታች መሸኑን ነበር የገለጸው።

በአውሮፓ እንደሚታወቀው ዥሉ በአፍሪካ የሚደረጉ ጦርነቶች ለባለድሉ በርካታ የሐብት ማጋበሻ አጋጣሚዎች ናቸው። በእርግጥ ሐብቱ የሚገኘው በአጋጣሚ





ሳይሆን ጦርነቱ ራሱ የሚደረገው የሐብት ማግኛ አጋጣሚን ለመፍጠር ነው። የምኒልክ ወታደሮችም በወላይታ ዘመቻ ወቅት በጭነትም ሆነ በሽክም አቅማቸው የፈቀደላቸውን ያህል ዘርፈው ተመልሰዋል። የወትቱን ዘረፋ ሻንደርሄይም ሲጽፈው ወታደሮቹ ከጎመን ጀምሮ ዶሮ፣ የቀንድ እና የጋማ ከብት ዘርፈዋል። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የወላይታ ተወላጆችም በባርነት ተጓዙ።

በ1888 የተከሰተው የከብት በሽታ የበርካታ ኢትዮጵያውያንን እና የከብቶቻቸውን ሕይወት እንደቀጠፈ ይታወሳል። በሽዋ አካባቢ እጅግ በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ በወረርሽኙ ያለቀ ሲሆን እንዳንዶች የሚቹ ቁጥር ከአጠቃላይ ሕዝቡ ሲሶ ያህል እንደነበር ይናገራሉ። ምኒልክ ወደ ወላይታ ዘምተው ሲመለሱ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የወላይታ ሕዝብ በግዞት ይዘው መመለሳቸው ምናልባትም በወረርሽኙ ያለቀው ሕዝባቸውን ቁጥር ለመመለስ ያለመ መሐሪ ይመስላል።

በዘመቻው ከተገኘው የምርኮ ሐብት ውስጥ ከፍተኛው መጠን ለምኒልክ ነበር የተሰጠው። ከሠላሳ አምስት ሺህ የቁም ከብቶች ግማሹን እንዲሁም በባርነት ከተጓዙት ዐሥራ ስምንት ሺህ ምርኮኞች ደግሞ አንድ ዐሥረኛ የሚሸኑት የምኒልክ ድርሻ ነበሩ። ምኒልክ ድርሻቸው የነበሩት አንድ ሺህ ስምንት መቶ ምርኮኞች እጅ ላይ የመለያ መስቀል ምልክት በእሳት እንዲነቀሱ አደረጉ። በመልስ ጉዞው ወቅት የምኒልክ ምርኮኞች ከወታደሩ ጋር ተቀላቅለው እንዲጓዙ ተፈቅዶላቸው ነበር።

በመልስ ጉዞው ወቅት ታኅሳስ 29 ቀን የምኒልክ ሠራዊት መንገድ ላይ እረፍት በማድረግ ደማቅ የወታደራዊ ሰልፍ ትርዒት አሳየ። ምኒልክ በተዘጋጀላቸው ማረፊያ ድንኳን ሥር ተቀምጠው ነበር። ምርኮኛው ንጉሥ ጠና እና የጦር አዝማቾቹ ከምኒልክ እግር ሥር ተቀምጠው ወታደራዊ ትርዒቱን ተመለከቱ። በሰልፉ መጀመሪያ ላይ ፈረሰኛ ወታደሮች እግረኞችን አስከትለው በማለፍ ተመሙ። በመጨረሻም የመልስ ጉዞው ከመጀመሩ በፊት ትርዒቱ በተደረገበት ጉብታ ላይ መኖሪያ ቤት

እንዲሠራላቸው በማዘዝ ምኒልክ የአዲሱን ግዛት ወደ ማዕከላዊ አስተዳደራቸው መቀላቀል አወጁ።

### የምኒልክ ዘመቻ በውጪው ዓለም ዕይታ

ዘመቻው ለምኒልክ ያስገኘላቸው ስኬት ወታደራዊ ብቻ አልነበረም። ከውጪ ወራሪ ለመከላከል ያስፈልጋቸው የነበረውን ገንዘብም ከዘመቻው ማግኘት ችለው ነበር። ጦራቸው ከጣሊያን ጦር ጋር ከመግጠሙ በፊት ወታደራዊ አቋሙን ለመፈተሽ የቻለበት ተግባራዊ ዘመቻም ነበር - የወላይታው ዘመቻ። በዘመቻው የተገኘው ድል እና ልምድ ለአዳዲስ ምልምል ወታደሮች ከፍተኛ ልምድ አስገኝቶላቸዋል።

በዘመቻው ምኒልክ ከፈረንሳዊው ነጋዴ ሊዮን ቼፍኔክስ ላይ የገዟቸውን ወሥራ አምስት ሺህ ግራስ ጠመንጃ ለመሞከር ቻሉ። በርካታ ቁጥር የነበረው ጠመንጃ ስድስት ወይም ሰባት ዙር ከተኮሰ በኋላ ባዶውን ቀስፋ ለማውጣት ባለመቻሉ ከጥቅም ውጪ የሆነበት አጋጣሚ ነበር። በጠመንጃቸው ብልሽት የተነሣም በርካታ የምኒልክ ሠራዊት ጦር እና ጎራዴ በታጠቁት የጠና ወታደሮች እጅ ላይ ጥሏቸው ነበር።

የቫንደርሃይምን የወላይታ ዘመቻ ዘገባ በርካታ የአውሮፓ ጋዜጠኞች በተቀባበሉት ማግስት ይምሮ ምኒልክ ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ገቡ። በአውሮፓውያን ዘንድ ቦጥበሻነት እና ስብዓዊነት ይገለጽ የነበረው የእፍረካው ክርስቲያን ንጉሥ ምኒልክ ገጽታ ጥቀርሻ ለበሰ። ኮሳሊያን ጋር ለመዋጋት በከፍተኛ ሞራላዊ ብቃት ላይ ለነበሩት ምኒልክ የአውሮፓ ጋዜጠኞች ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድረው ነበር። ቫንደርሃይም በዘገባው ምኒልክ እና ወታደሮቻቸው ምርኮኞችን በባርነት መከፋፈላቸውን ማጋለጡን ተከትሎ ምኒልክ በባሪያ ፈንጋይነት ተወቀሱ። ይህንን ተከትሎ የአውሮፓ የባሪያ ንግድ ክልክላው የጦር ምርኮኞች፣ የቤት ውስጥ ሠራተኞችን እና ሙስሊሞችን አለማጠቃለሉን በመጥቀስ በአውሮፓ ሰፊ ክርክር ተነሳ።





የቫንደርሃይም ዘገባ ስላስከተለው ተቃውሞ ምኒልክ የሰሙት ዘግይተው ነበር። የአጸፋ ዘገባ እንዲጽፍላቸው ከሰሚር ሞንዶን - ቪዳይሌትን አግባቡ። ሞንዶን በሚያዝያ ወር ለ«ሌ ቴምፕልስ» ጋዜጣ በሳከው ዘገባ የወላይታውን ዘመቻ ውጤት ከታሪክ እና ከኃይማኖት አንባብ ነበር ያስቀመጠው። የሞንዶን ዘገባ ከሞላ ጎደል ይህንን ይመስል ነበር።

*«የወላይታ ለገረ መንግሥት ከብዙ ከፍለዘመናት በፊት የኢትዮጵያ ግዛት አካል የነበረ ነው። የወላይታ ሕዝቦች ለዘመናት የተጫነባቸውን የእስልምና ተፅዕኖ ተቋቁመው ክርስቲያናዊ ባሕላቸውን ጠብቀው ቆይተዋል። የምኒልክ ዘመቻ የግፍ ወረራ ሳይሆን የቀድሞ ግዛትን የማስመለስ እና ክርስትናን የመጠበቅ ቅዱስ ተግባር ነው። መሳቀል በጨረቃ ላይ የበላይነቱን ባሳየበት በዚህ ዘመቻ ለዘመናት ከእናት ሀገሩ የተለየው ግዛት ወደ ክርስቲያን አገዛዝ ተመልሷል። ምስጋና ለሬሚንግተን እና ግራስ ጠመንጃዎች ይሁን እና ጋይል ጋይልን ገዝቶታል።*

የምኒልክን ዘመቻ በተመለከተ በመላው አውሮፓ የተነሣው ተቃውሞ አፀፋ ሲጽፍ በኢትዮጵያ እና አውሮፓ መካከል ላለው ክርስቲያናዊ ቁርኝት ትኩረት ሰጥቷል። በአንዱ ጽሑፍም «አፄ ምኒልክ ከአውሮፓውያን የሚጠብቁት አስተያየት በክርስቲያናዊ ፍትሕ እና መረዳዳት ላይ የተመሠረተ ነው።» ብሎ ነበር።

ሞንዶንን ካገኙ በኋላ ምኒልክ ቫንደርሃየምን ፊት ነሱት። ከቤተ መንግሥታቸው በግልጽ የገፉት ቫንደርሃይምም ዓዙን ጠቅልሎ ስጥቂት ሳምንታት እረፍት ለማድረግ በሚል ሰበብ ወደ ሐረር ለመሄድ ተዘጋጀ። ምኒልክ መልካም አሸኛኘት ቢያደርጉለትም ለሃገሩ ገዢ ራስ መኮንን አደይዘው በላኩት ደብዳቤ ቫንደርሃይምን ወጥመድ ውስጥ ለማስገባት ቀድመው ወጥነው ነበር። በሐረር ስለሚጠብቀው የሽፍጥ አቀባበል እና ሴራ ለቫንደርሃይም የነገሩት በቤተ-መንግሥት የነበሩ ወዳጆቹ ናቸው።

ከታጠቁ አጃቢዎቹ ጋር በመሆን የሐረር ጉዞውን የጀመረው ሻንደርሃይም በመንገድ ላይ ሳለ አስቸኳይ ደብዳቤ መላክ እንዳሰበት ለአጃቢዎቹ ተናገረ። በመሸኑም ወደ ራስ መኮንን ከመሄዱ በፊት ወደ ጠረፍ እንዲያደርሱት እጥፍ ክፍያ እንደሚከፍላቸው ቃል በመግባት አጃቢዎቹን አግባባ። ሐረርን ወደ ጎን በመተውም በቀጥታ ወደ ጅቡቲ አመሩ።





# ምዕራፍ አምስት

## የነጭ ቅጥረኛ ጥቁሮች

‹ዶጋሊ› እና ‹‹አምስት መቶዎቹ›› የሚሉት ቃላት በጣሊያን ሕዝብ ዘንድ ኢ-ፍትሃዊ ተስፋፊነት የሚያስከትለውን ቅጣት የሚያስታውሱ ቃላት ናቸው። በርም የቆመው የአምስት መቶዎች ሰማዕታት ሐውልት የጣሊያን መንግሥት ወደፊት ሰሚያደርገው ወረራ ለድጋፍ ማግኛ እንደ መሣሪያ ሊጠቀምበት አስቧል። ለጣሊያን ጥቅም ለመዋጋት ዝግጁ የሆኑ ቅጥረኛ አፍሪካውያን እያሉ ለምን የጣሊያን ውድ ልጆች ለጦርነት ይማገዳሉ?

ከዶጋሊ በኋላ ጣሊያን ከአፍሪካ ቅጥረኛ ወታደሮችን ለመመልመል ወሰነች። ግብፅ በ1870ዎቹ ኢትዮጵያን ለመውረር ስትዘጋጅ በርካታ አውሮፓውያን እና አሜሪካውያን ወታደሮችን ቀጥራ ነበር። በአሜሪካ የእርስበእርስ ጦርነት የተሳተፉትን ጨምሮ በ1864ቱ እና በ1866ቱ የአውሮፓውያን ጦርነቶች የተሰማሩ የዴንማርክ፣ ጀርመን እና አስትሪያ ወታደሮችን ቀጥራ ነበር። በወቅቱም ቅጥረኛ መኮንኖች የግብፅ ጦርን በመምራት ኢትዮጵያን ወርረው ነበር።

ጣሊያንም በተመሳሳይ በምሥራቅ አፍሪካ የነበራትን የጦር ኃይል ለማጠናከር ከአካባቢው ነዋሪዎች ልዩ የወታደራዊ ቅጥር ጥሪ አቀረበች። የጣሊያን ማስታወቂያ በቀጠናው በስፋት ከተሰራፈ በኋላ በርካታ የቀይ ባሕር ዳርቻ ነዋሪዎችን ጨምሮ የሱዳን ዜጎችን እንዲሁም እስክ ጎንደር እና ሸዋ በመዝለቅ ኢትዮጵያውያን ቅጥረኛ ወታደሮችን መመልመል ቻለች። የዘር፣ የቋንቋ እና የኃይማኖት ልዩነት ባለማድረግም ኹሉን አቀፍ የሆነ ምልመላ በማድረግ ሙስሊም እና ክርስቲያን አባላት ያሉት ምልምል ሠራዊት ገነባች።

ምልምሎችን ሰብስቦ በማሰልፍ የመረጣ ሥራው ይጀመራል። አውሮፓዊ መኮንኖች በሰልፈኞቹ መካከል በመዘዋወር አካላዊ ብቃታቸው እና ዕድሜያቸው ለወታደራዊ ግልጋሎት ብቁ ያልሆኑትን የመለየት ሥራ ይሠራሉ። የተመረጡትን ምልምሎች ርቀቱ እስከ ዐሥር ማይል በሚደርስ ጋራ እና ሸንተረር ላይ በማስሮጥ በፈረስ የሚከታተሏቸው አውሮፓውያን መኮንኖች ምርጫቸውን ይቀጥላሉ። በሩጫው ተጻክመው የሚንጠባጠቡትን በመተው ባለ ጥሩ ትንፋሽ የሆኑትን ጥቂት ምልምሎች ለቀጣይ ሥልጠና ያጫሉ።

ከአካል ብቃት ፈተናው ቀጥሎ የጤና ምርመራ ይደረጋል። ጤነኞች ተሰይተው ገላቸውን እንዲታጠቡ ከተደረገ በኋላ ወታደራዊ የደንብ ልብስ ይታደላቸዋል። በምሥራቅ አፍሪካውያን ዘንድ የተለመደ የነበረውን ነጣ ያለ ቁምጣ እና ሸሚዝ ነበር የታደሉት። ቁምጣው ጉልበታቸው አካባቢ ጠባብ ሆኖ ዳሌያቸው አካባቢ ደግሞ ሰፋ ተደርጎ የተሰፋ ነበር።

ወታደራዊው የደንብ ልብስ አብዛኞቹ ምልምሎች ከዚያ በፊት ለብሰውት የማያውቁት ዓይነት ምርጥ ልብስ ነበር። ከቁምጣና ሸሚዙ በተጨማሪ አጭር ኮት እና ቀይ ከፍያ ተጨምሮላቸው ደመቁ። በመጨረሻም የነፍስ ወከፍ ጠመንጃ እንዲሁም በቀይ ቀዳ የተሠራ የጥይት ማስቀመጫ ዝናር ታደላቸው።

### የባንዳ ባታሊዮኖችን ማደራጀት


ልዩ የመለያ ቀበቶ የተሰጣቸው አዳዲሶቹ ምልምሎች በተለያዩ ቀጠናዎች ተመደቡ። የመጀመሪያዎቹ አራት ባታሊዮን አባላት አራት የተለያዩ ቀለማት (ቀይ፣ ሰማያዊ፣ ሃምራዊ እና ጥቁር) ቀበቶዎችን ያጠለቁ ሲሆን እንደየቀለማቱ ቅደም ተከተል አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ እና አራተኛ አገር በቀል ባታሊዮን የሚል መጠሪያ ተሰጥቷቸው ነበር።






የጣሊያን ጦር ከምፅዋ በመነሳት ወደ ደጋማው የኢትዮጵያ ክፍል መንቀሳቀስ ሲጀምር ተጨማሪ ወታደር አስፈልጎት ነበር። አራት ተጨማሪ ባታሊዮን በመመልመል በአጠቃላይ እያንዳንዱ አንድ ሺህ አባል ያለው ስምንት የባንዳ ባታሊዮን ማዋቀር ቻለች። አዳዲሶቹ ባታሊዮኖች ባለ መስቀለኛ የስኮትላንድ መታጠቂያ እንዲሁም አረንጓዴ፣ ነጭ እና ቢጫ ቀለማት ያሏቸውን ቀበቶዎች እንዲታጠቁ ተደረጉ።

በጥንታዊ የኦቶማን አጠራር ‹‹ባሺ-ቡዙቅ›› ወይም ‹‹አስካሪ›› የሚል ስያሜ የተሰጣቸው አዳዲሶቹ ምልምሎች በነጭ ወታደራዊ ዩኒፎርሞቻቸው ይታወቁ ነበር። ወንጀል ሠርተው በመሸሽ ላይ የነበሩ እንዲሁም የባሪያ ንግድን በመሸሽ ላይ የነበሩ ሰዎች የአስካሪ ውትድርናውን በየጊዜው መቀላቀል ቀጠሉ። በነቅቱ ውትድርና የምግብ፣ የልብስ እና የገንዘብ ዋስትናን ማረጋገጫ ተደርጎ ስለሚታይ በርካቶች የጣሊያንን ምልምል ጦር ተቀላቀሉ።



Askari recruits. From *L'Illustration*, 21 December 1895.

ምስል፦ የአስካሪ (ባንዳ) ምልምል ወታደሮች (ላ ኢሉስትሬሽን - ታኅሳስ 21 ቀን 1895)



ምስል፡- የአስካሪ (ባንዳ) ምልምል ወታደሮች (ሳ ኢሉስትሬሽን - ታኅሳስ 21 ቀን 1895)

አንድ አስካሪ ምልምል የአንድ ዓመት ኮንትራት ከፈረመ በምላሹ የሚያገኘው የቀን ክፍያ አንድ የጣሊያን ሊራ ከአምሳ ሳንቲም ነበር። ከአውሮፓውያን ወታደሮች ክፍያ አንፃር ሊታይ አነስተኛ ቢመስልም በዘመኑ ለአንድ አፍሪካዊ ወታደር ትልቅ ዋጋ ነበረው። አንድ አስካሪ ወታደር በክፍያው በቂ ኑሮ መምራት የሚችል ሊሆን ሚስት አግብቶ ቤተሰብ መመስረትም ሆነ ከአንድ ዓመት በኋላ የግል በትሱ መግዛት ያስችለዋል።

የውትድርና ሥራው ከሚያስገኘው ገቢ በላይ ለተቀጣሪዎች የከበሬታ ምንጭም ሆኖላቸው ነበር። በመላው ምሥራቅ አፍሪካም ሆነ በኢትዮጵያ ማህበረሰብ ውስጥ ወታደር የተለየ ክብር ይሰጠዋል። ቅጥረኛ ወታደሮቹ ለአንድ ዓመት ካገለገሉ በኋላ የሚያገኙት ክፍያ ከግብርና የተሻለ ኑሮ እንዲመሩ ያስችላቸዋል። በዘመኑ ውትድርና የተሻለ ሕይወት አማራጭ ነበር።

በአስካሪ ምልመላው ጣሊያን ዜጎቿም ባይሽኑ ለጥቅሟ የሚዋጉ ቆራጥ እና ቀልጣፋ ወታደሮችን መመልመል ችላለች። ቅጥረኞቹ ለአውሮፓውያን ወታደሮች አስቸጋሪ በሽኑት የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ደጋማ ቦታዎች ላይ በተሻለ ብቃት መሰለፍ ችለዋል። ከሰድስት ሺህ ጫማ በላይ ከፍታ ያላቸው ተራሮች ላይ ለመንቀሳቀስ የሞከሩ የአውሮፓ ወታደሮች ብርዱን መቋቋም ሲሳናቸው የአገሬው ቅጥረኛ ግን በአስገራሚ ጥንካሬ ይጓዝ ነበር።

አስመራ የነበረው ፖል ላሪባር በእዙ ሥር የነበሩትን ቅጥረኛ ወታደሮች በመያዝ ከአስመራ በ118 ማይል ርቀት ወደምትገኘው አቆርዳት እንዲንቀሳቀስ በታዘዘ ወቅት በእሩ የነበሩት ቅጥረኛ አስካሪዎች ርቀቱን ለመጨረስ የወሰደባቸው ጊዜ ሦስት ቀናት ብቻ ነበር። ይህም ማለት በቀን (በዐሥራ ኹለት ሰዓት) ከሠላሳ ማይል በላይ መጓዛቸውን ያሳያል። በአውሮፓውያን ዘንድ በፈጣን ተጓዥነታቸው የሚታወቁት የናፖሊዮን ወታደሮች በቀን መጓዝ የቻሉት ርቀት ከሐያ አምስት ማይል ያልበለጠ ነበር።





የአስካሪ ቅጥረኞቹ ፈጣን የመጓዝ ችሎታ የጣሊያን ሠራዊት ከኢትዮጵያ ባላንጣው ጋር እንዲስተካከል ዕድል ፈጥሮለታል። በ1895ቱ ወታደራዊ ዘመቻ ወቅት እንደታየው በመሸሽ ላይ ለነበረ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሳይቀር ፈታኝ የነበረው ክጣሊያን ጎን የተሰለፉት ቅጥረኞች ፍጥነት ነበር። አስካሪ ቅጥረኞቹን ባያሳልፉ ኖሮ ጣሊያኖች የኢትዮጵያን ሠራዊት ፈጣን ግስጋሴ መገዳደር ያስቸግራቸው ነበር።

አስካሪ ወታደሮች በአውሮፓውያን መኮንኖች እዝ ሥር የነበሩ ቢሆንም አንዳንድ ልዩ ብቃት ያሳዩ አስካሪዎች መካከለኛ ወታደራዊ ማዕረግ ይሰጣቸው ነበር። የደረጃ ዕድገት ያገኙ ቅጥረኞች በቀይ ወታደራዊ ቆባቸው ላይ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ጨርቆች ያስሩ ነበር።

የቅጥረኞቹ መኖር ለጣሊያን ወታደራዊ መኮንኖች ከፍተኛ እረፍት እና መዝናናትን ፈጠረላቸው። የጣሊያን መኮንኖችም የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች የነበራቸውን ከበሬታ ማግኘት ቻሉ። የየዕለቱ ዘመቻ በተጠናቀቀ ቁጥር የቅጥረኞች ቀጣይ ሥራ የነበረው ለጣሊያናውያን መሪዎቻቸው ማረፊያ ዳስ እና ድንኳን መጣል ነበር። በተጨማሪም አለቆቻቸውን በግል ጠባቂነትም ያጅቡ ነበር። የአንዳንድ መንደሮች ነዋሪዎች ለጣሊያን ወታደሮች እንዲያቀርቡ የሚገደዱት ምግብ ለጣሊያናውያን አለቆቻቸው የሚመጥን ጣዕም እንዳለው እንዲሁም ያልተመረዘ መሽኑን ለማረጋገጥ ቀድመው ይቀምሱት የነበሩት ቅጥረኛ አስካሪዎቹ ነበሩ።

ለቀጣሪዎቻቸው ታማኝነታቸውን ለማረጋገጥ ሲሉ በወገኖቻቸው ላይ እርምጃ የሚወስዱ አንዳንድ አስካሪዎችም ታይተዋል። በአንድ ባታሊዮን ሥር የሚገኙ ቅጥረኞች እርስ በእርሳቸው የሚጠቃቁበት አጋጣሚ የታየ ሲሆን በአብዛኛው ግን በመካከላቸው ልዩ መግባባት ይታይ ነበር።

የጣሊያን ወታደራዊ ባህል ከሌላ አውሮፓውያን ልዩ የሚያደርገው ቤተሰባዊ ተሳትፎን መፍቀዱ ነበር። የጣሊያን ወታደሮች ሚስት እና ልጆቻቸውን አስከትለው እንዲዘምቱ በመፍቀድ ዘመቻውን ቤተሰባዊ ለማድረግም ችሳለች። የቅጥረኛው ወታደር ሚስት እና ልጆች የዘመቻው አጋዥ የሽኑበት አጋጣሚ በተደጋጋሚ የታየ ሲሆን በተለይም መቀሌ ላይ በተደረገው ጦርነት ጥይት እና ቦምብ የማቀበል ኃላፊነት ላይ ተሰማርተው የነበሩት የአስካሪ ሚስቶች እና ወጣት ልጆች ናቸው።

የጣሊያን ወታደራዊ መሪዎችን ያስገረሙ አንዳንድ ኹነቶችም ተስተውለው ነበር። አስካሪ ወታደሮች በምሽግ ቁፋሮ ወቅት የጣሊያን ወታደራዊ መዝሙሮችን ይዘምሩ ነበር። ከበርካታ የጣሊያን መኮንኖች የጉዞ ማስታወሻዎች ላይ እንደታየው መኮንኖች ለአስካሪዎቹ ታማኝነት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

በርካታ አስካሪዎች የጣሊያንን ቋንቋ እና ባህላዊ ሁኔታ ለመልመድ ይሞክሩ ነበር። ቁጥሩ ከ3600 በላይ ከሚገመተው ቅጥረኛ ሠራዊት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሸኑት የጣሊያንን ቋንቋም ሆነ ወታደራዊ ትዕዛዝ አይረዱም ነበር። በአንድ ወቅት ጣሊያናዊው ጀነራል አንቶኒዮ ባልዲሴራ ቅጥረኞችን ከጣሊናውያን ጎን ለማላለፍ የነደፈውን ሀሳብ ሮም ውድቅ አድርጋበታለች። ይህ የሚያሳየው የወቅቱ የጣሊያን ጦር አሰላለፍ የነጮች የበላይ አለቃነት ላይ ያተኮረ እንደነበር ነው።

በምልመላ ወቅት ጣሊያን ኃይማኖታዊ መስፈርትን ባለመጠቀሟ የተነሣ ሙስሊም እና ክርስቲያን አስካሪዎችን መልምላ ነበር። የተለያየ ኃይማኖት ቢኖራቸውም በቅጥረኞቹ መካከል ፍጹማዊ መግባባት ነበር። ለምሳሌ ያህል ጣሊያናች ያቀርቡላቸው የነበረውን ሥጋ ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ ቅጥረኛ በአንድ ላይ ይመገቡ ነበር።





## ፍቅር በአፍሪካ

አስካሪ ወታደሮች በወታደራዊ ዘመቻው ወቅት የግላዊ ሕይወት ግንኙነት የማድረግ ነጻነት ነበራቸው። በመኾኑም ሚስቶቻቸውን ይዘው ይዘዋወሩ ነበር። የጣሊያን ወታደሮች ግን በአንፃሩ የወታደራዊ ደንቡ ይህንን እንዲያደርጉ ያግዳቸው ነበር። በ1895 ማብቂያ አካባቢ ቁጥራቸው ወደ ዐሥር ሺህ የሚገመት የጣሊያን ወታደሮች በኢትዮጵያ የተሰማሩ ቢሆንም ክከፍተኛ መኮንኖች ውጪ ሚስቶቻቸውን አስከትለው እንዲዘምቱ አይፈቀድላቸውም ነበር። የአጠቃላይ ጦሩ ምኩትል አዛዥ የነበረው መኮንን ብቻ ሮዛሊያ ፒያናቪያ የተባለች ሚስቱን አስከትሎ አስመራ እንደመጣ ይታወሳል።

በዘመቻው ወቅት አውሮፓውያኑ ምን ያህል በውሲብ እንደተፈተኑ ማሰብ ቢቻልም የነበረውን እውነታ ግን መዘገብ አስቸጋሪ ነበር። የበርካታ ወታደሮች የጉዞ ማስታወሻ ከወሲብ ጋር ተያያዥ የነበሩ እውነታዎች አድበስብሰው ያለፉት ቢሆንም እንድ ጭምጭምታ መኖሩን ግን በተለያዩ አጋጣሚዎች ለመስማት ተችሏል። ይኸውም ፊኒዮሎ የተባለ አንድ የጣሊያን ወታደር በወታደራዊ ካምፑ አካባቢ ‹‹ወይዘሪት›› ተብሎ ይታወቅ እንደነበር ነው።

ጣሊያናውያኑ በ1936 ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲዘምቱ የጣሊያን ዝርያ ክብር እንዲጠብቁ የሚያስገድዱ በርካታ ደንቦች ተጥለውባቸው ነበር። በ1880ዎቹ ግን አስገዳጅ ደንቦች አልነበሩም። እንደማንኛውም የወደብ ከተማ በምዕዋ ሴተኛ አዳሪዎች የነበሩ ሲሆን፤ በአስመራና በተለያዩ ከተሞች የነበሩ የጣሊያን ጦር ሠራዊት አባላት ሴተኛ አዳሪዎችን ከመጎብኘት ይልቅ ክኤርትራዊ ሴቶች ጋር ትዳር መሰል ግንኙነትን መመስረት መርጠው ታይተዋል። የጣሊያናውያኑ ቅምጥ የነበሩ እንስቶች ‹‹ማዳማ›› በሚል የማዕረግ ስማቸው ይጠሩም ነበር። ጀነራል ጁሌፕ አሪሞንዲ ውበቷ ወደር የሌለው ኤርትራዊት አግብቶ እንደነበር እና አድዋ ላይ ከመሞቱ በፊትም አብሯት ይኖር እንደነበር ይታወሳል።

በጣሊያን ወታደሮች እና በኤርትራ ወይዛዝርት መካከል የነበረው የፍቅር ግንኙነት የትዳር ያህል ጥብቀት የነበረው ቢሆንም አንዳንድ መጎራበቶች ግን ይስተዋሉበት ነበር። ሲዛር ኔራዚኒ በኤርትራ የጣሊያን ልዩ መልዕክተኛ በነበረባቸው ዓመታት ከአንዲት ኤትራዊት ጋር ፍቅር መሥርቶ አሰብ ይኖር ነበር። የሚገርመው ታዲያ ኔራዚኒም ሆነ ፍቅረኛው የየራሳቸው ፍቅረኞች ነበሯቸው። ኔራዚኒ ሞግ ከተባለች ሴት ፍቅር ያዘውና ከመጀመሪያዋ ፍቅረኛው መኖሪያ አጠገብ ቤት ተከራይቶ ሲያስቀምጣት ፍቅረኛው በበኩሏ ሮዜንትሬተር ከተባለ የስዊዝ መካኒክ ጋር ግንኙነት ጀመረች።

በአንዳንድ አጋጣሚዎች እንደታየው የፍቅር ግንኙነቶች ወደ ሕጋዊ ጋብቻ ማደግ የቻሉበትም አጋጣሚ ነበር። ክሪስ ፕሮቲ በማስታወሻዋ እንደገለጸችው የአገሬው ሰዎች ሴት ልጆቻቸውን ለአውሮፓዊ ወታደሮች ለመዳር የተለየ ጥረት ያደርጉ ነበር። የጣሊያን ወታደሮች በጥሎሽ መልክ የተሟላ ቤት፣ እህል እና ጥሬ ገንዘብ ይከፍሉ ነበር። የልጃገረድ አባት የተዋበ ሰጋር በቅሎ በስጦታ መልክ ያገኝ ነበር። ልጅቷም ጣሊያናዊ በማግባቷ ‹‹ማዳማ›› የሚለውን የማዕረግ ስም በማግኘት ከሌሎች የተለየ ክበራታን ታገኛለች። በርካታ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ለአውሮፓውያን በመዳር አፍሪካዊ ዘራቸውን ከነጭ ጋር ማዳቀል መቻላቸውን እንደተለየ ክብር ያዩት ነበር።

የአንድ ጣሊያናዊ እጮኛ የሆነች ‹‹ማዳማ›› ባለቤቷ ወደ አውሮፓ ከተመለሰም በኋላ ማዕረጓን ይዛ ትቀያለች። በትዳር ወቅት ያካበተችውን ሐብት እና ዝና በመጠቀምም ሌላ አውሮፓዊ ወይም የአገሯን ሰው ማግባት ትችላለች።

በዚህ መሰል የፍቅር ግንኙነት የሚወለዱ ክልስ ልጆች በማህበረሰቡ ተቀባይነት እና ክበራታን ለማግኘት ይቸገራሉ። ከወራሪው የናዚ ወታደር እንደተወለደ ፈረንሳዊ ሕፃን ልጅ ዥሱ ማህበረሰቡ ህፃኑን ኤርትራዊ እንደ ወራሪ ጣሊያናዊ





ይመለከት ነበር። ከተወለኑ ጊዜያት በኋላ ግን ክልስ ልጆች በኤርትራዊያን ተቀባይነት ማግኘት የቻሉ ሲሆን አንዳንዴም የተሻለ ክብር ይሰጣቸው ነበር።



ምስል፡- ጣሊያናዊ ወታደር ከኤርትራዊት ባለቤቱ ጋር

በኢትዮጵያ ተመሳሳይ የነጭ እና ጥቁር ጋብቻዎች እንደነበሩ የሚጠቁሙ ነገሮች ይታዩ ነበር። አጉስተስ ዋይልድ የጣሊያን እና ኢትዮጵያን ስምምነት ሐተታ ለ‹‹ማንቺስተር ጋርዲያን›› ጋዜጣ ለመዘገብ ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ወቅት አንዲት ነጭ ሴት አግኝቶ ነበር። ሴቷ በ1868ቱ የናፒየር ዘመቻ ወቅት ከእንግሊዝ ወታደር እና ኢትዮጵያዊት እንስት የተወለደች ስትሆን በአካባቢው ነዋሪ ‹‹እንግሊዟ›› በሚል ስሟ ነበር የምትታወቀው። ዋይልድ ባገኛት ወቅት እንስቷ ከኢትዮጵያ ወንድ ጋር ከመሰረተችው ትዳር አንዲት ሴት ልጅ ወልዳ ነበር።



From SAI Archive at the University of Naples

በተለያዩ የምሥራቅ አፍሪካ በታዎች በተለይም በኤርትራ ከጣሊያን አባት የተወለዱ ክልስ ልጆችን ማየት የተለመደ ሲሆን ማህበረሰቡም ቀስ በቀስ ክልሶቹን መቀበል ጀምሮ ነበር። ጣሊያናዊው ሜጀር ጀነራል ፒየትሮ ቶሴሊ በ1895ቱ ዘመቻ ወቅት ሲሞት ከኤርትራዊት ሚስቱ የወለደው ወንድ ልጅ ነበረው። ኤርትራዊቷ ሴላ ባል ስታገባ አዲሱ ባሏ ክልስ እንጀራ ልጁን ተቀብሎ ማሳደግ የቻለ ሲሆን ለሚች የሥጋ አባቱ መታሰቢያ እንዲሆንም ክልሱን ጴጥሮስ በማለት ሰይመውት ነበር።

የበርካታ ክልስ ልጆች አባቶች በጦርነት ወቅት ሲሞቱ እንዲሁም ግዴታቸውን አጠናቀው ወደ አገራቸው ሲመለሱ ልጆቹ ያለ አባት ይቀሩ ነበር። ሮዛሊያ ፒያናሺያ የተባለችው የአንድ ጣሊያናዊት መኮንን ሚስት በርካታ አባት አልባ ክልስ ሕፃናትን ሰብስባ ትረዳ እንደነበር ይታወሳል። ‹‹አባዲ›› የተባለች ክልስ ሕፃን ኤርትራዊት እናቷ ከሞተችባት እና አባቷም ወደ አገሩ ጣሊያን ከተመለሰ በኋላ በአደራ የተቀበለቻት ፒያናሺያ ነበረች። ‹‹አባዲ›› የሚለውን ስም ‹‹ማሪያኒያ›› በሚል ከቀየረችላት በኋላ የማሳደግ ኃላፊነቱን መወጣት ጀመረች።

የወቅቱን የቅኝ ግዛት አስተዳደር በማስፈቀድ የመጀመሪያውን የወላጅ አልባ ሕፃናት መንደርም ለመገንባት ቻለች። አስተዳደሩ የመንደሩ መገንባት የወታደሩን ወሲባዊ ተግባር በማበረታታት ችግር ሊፈጥር ይችላል በማለት መጀመሪያ ላይ ቢቃወምም በኋላ ግን ፈቀደላት። ማሪያኒያ የመጀመሪያዋ የማዕከሉ ልጅ ስትሆን በመቀጠል መንደሩን አንጀሊና፣ ቪቶሪያ፣ ሊቺኖ፣ አሬስቲ እና ጂዮሽኒኖ የተባሉ ወላጅ አልባ ክልስ ሕፃናት ተቀላቀሉ።

የሮዛሊያ አንቅስቃሴ በመጠናከር በአስመራም ተመሳሳይ መንደር ለመገንባት ቻለች። በአስመራ እና በጣሊያኗ ከተማ ጂኖላ ተመሳሳይ የነበሩ የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶችን በማድረግም የወላጅ አልባ ክልሶቹን ማዕከላት የበለጠ አጠናክረቻቸው። ከ28 ሺህ ሊሬ በላይ ገንዘብ በማሰባሰብም በርካታ ሞግዚቶችንና መምህራንን በማዕከሉ ቀጠረች። በመቀጠል በርካታ የካቶሊክ መነኮሳት ማዕከሉን በመምህርነት ለመደገፍ ከጣሊያን ድረስ መጡ።





የፒያናሺያ ሕፃናት ማዕከል የወላጅ አልባ ሕፃናቱን ሕይወት የመታደግ ተግባር ቢፈጽምም የአውሮፓውያኑ እና አፍሪካውያኑ የፍቅር ግንኙነት አንዲሁም የአስካሪ ቅጥረኛ ወታደሮች ተሳትፎ በኹለቱ ሕዝቦች መካከል መተሳሰርን ለመፍጠር የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል። ማቋማዎች እና አስካሪዎች በሚያገኙት የገንዘብ እና የደረጃ ክብር በመገፋፋት ከጣሊያውያኑ ጋር ቁርኝታቸውን በማጥበቅ ለቅኝ ገዢዎች ቀይታ የተሻለ ሁኔታን ፈጥረዋል።

# ምዕራፍ ስድስት

## አፍሪካ በጣሊያን

የአፄ ዮሐንስ ልጅ የሆነው መንገሻ ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃ ባይኖረውም መልከመልካም እና የተሰየ መስህብ የታደለ ነበር። እጅግ ውብ ከሆነው ገጹ በተጨማሪ ያማረ አለባበሱ የማንንም እይታ ሊማርክ ይችላል። በበርካታ ፎቶዎች ላይ እንደሚታየው ፀጉሩን ሹሩባ ይሠራ የነበረ ሲሆን ጀሮውም ላይ ሎቲ ያንጠሰጥል ነበር። ከአልባሳቱ በተጨማሪም እጅግ ማራኪ መዓዛ የነበራቸውን ሽቶዎችን ይቀባም ነበር። በዘመኑ ሽቶ ያመጡ የነበሩት ሙስሊም ነጋዴዎች በመሆናቸው የአገሬው ሰው ሽቶ መቀባትን ከኃይማኖት አልባነት ጋር ያገናኙ ነበር።

ልዑል አልጋ ወራሽ መንገሻ ከሕዝቡ የሚነሳበትን የሴታሴትነት እና ለስላሳነት ሽሙጥ መቋቋም ቢችልም የአባቱን ዘውድ ለመውረስ የማይችል መኾኑን ሲጠቋቆሙበት ግን መፍረክረክ ጀመረ። የመንገሻ እናት በታሪክ ስሟ ያልተጠቀሰች አንዲት የዮሐንስ ዕቁባት እንደሆነች እና መንገሻም የዮሐንስ ሕጋዊ ልጅ እንዳልሆነ ሕዝቡ ውስጥ ለውስጥ ማውራት ቀጥሎ ነበር።

በ1889 ከመሃዲስቶች ጋር በመዋጋት ላይ ሳሉ ቆስለው የነበሩት አፄ ዮሐንስ ቃሬዛ ላይ ሳሉ የዘውዳቸው ወራሽ ወንድ ልጃቸው መንገሻ እንደሆነ መናዘዛቸውን መንገሻ እንደ ሕጋዊ መረጃ ያቀርብ ነበር። የዮሐንስን ሞት ተከትሎ በተደረገው የዘውድ ሽሚያ መንገሻ ሙሉ በሙሉ ከውድድር ውጪ ተደረገ። የአባቱን ዘውድ ከምኒልክ ላይ ለመንጠቅም የግድ ብዙ መልፋት ያስፈልገው ነበር።

የመንገሻ ዋና መተማመኛ የነበረው አሉላ ሲሆን ይህ የአፄ ዮሐንስ ታላቅ የጦር መሪ ለንጉሡ የነበረውን ታማኝነት እርሳቸው መተማ ላይ ከሞቱ በኋላ በልጃቸው ደግሞታል። አሉላ የኢትዮጵያን ጻር ድንበር ከውጪ ወራሪ ኃይሎች





ጥቃት የጠበቀ እና ለወራሪዎች በተለያዩ የጦር እውዳሚዎች ታላቅ ትምህርትን የሰጠ ታላቅ የጦር መሪ ነው። በ1870ዎቹ ተደጋጋሚ የወረራ ሙከራ ያደረገውን የግብፅ ጦር ጉራ እና ለአቲ ላይ ድል ነስቶ መልሷል። በ1880ዎቹ በግብፅ እግር የተተካውን የጣሊያን ወራሪ ኃይል ዶጋሊ ላይ ሙሉ በሙሉ በመደምሰስ የውርደት ካባ አከናንቧቸዋል። ከዶጋሊው ሽንፈት በኋላ በርካታ ጣሊያናውያን አሉላን ‹‹ኢትዮጵያዊው ጋሪባልዲ›› በማለት ከዘመናዊት ጣሊያን መሥራቹ ጋሪባልዲ ጋር ሲያመሳስሉት ተደምጠዋል።

የአሉላ ድጋፍ እያለው እንኳን መንገሻ የሥልጣን የወራሽነት ሚናውን በአግባቡ ማላየት አልቻለም ነበር። በአሉላ እና መንገሻ መካከል የነበረው ልዩነት የመወለድ እና የጀግንነት ንፅፅር ነበር። መንገሻ የዘር ሐረጉን መሠረት በማድረግ ዘውዱን ለመውረስ ሲንቀሳቀስ ሕዝቡ ግን አድናቆትን ይሰጥ የነበረው በጀግንነቱ ለሚያውቀው አሉላ ነበር። ታሪክ አሉላን የሚያወሳው ‹‹በዘመናዊ ታሪክ ተወዳዳሪ የሌለው አፍሪካዊ ጀነራል›› በማለት ነው። በዚህ የተነሣም የዘውድ ወራሹ መንገሻ ምስል ከአሉላ አንፃር ሲታይ ፈዛዛ ነበር።

የአፄ ዮሐንስን ሞት ከምኒልክ የተሻለ ሊጠቀምበት የተዘጋጀ አልነበረም። የሸዋው ንጉሥ የራሱን ጦር ከማደራጀት ጎን ለጎን ከጣሊያን ጋር ምስጢራዊ ጓደኝነቱን አጠናክሮ የዮሐንስን ሞት ወይም ከሥልጣን የመወገድ አጋጣሚ ሲጠባበቅ ነበር። ወጣቱ ጣሊያናዊ መልዕክተኛ ፒየትሮ አንቶኔሊ ኢትዮጵያ ከደረሰበት ከ1879 ጀምሮ ከምኒልክ ጋር ወዳጅነቱን ሲያጠናክር ከርሟል። የምኒልክ እና የጣሊያን ወዳጅነት ጣሊያን በ1885 ምፅዋን ስትይዝ ከአፄ ዮሐንስ ጋር ግልጽ ቅራኔ ውስጥ በመግባት ከምኒልክ ጋር ቁርኝቷ ጠነከረ። ዮሐንስን የጋራ ጠላት በማድረግ የጣሊያን እና የምኒልክ ወዳጅነት ጠነከረ። የአንቶኔሊ ዋና ተልዕኮ የነበረው እንግሊዝ ዮሐንስን በአፄ ቴዎድሮስ ላይ እንዳሥነሳችው ሁሉ ጣሊያንም ምኒልክን አፄ ዮሐንስን ለማጥፋም እንድትጠቀምበት ማስቻል ነበር።

ምኒልክ ከጣሊያን የሚያገኘውን ድጋፍ ላስግጣት ሲል የጣሊያን መጠቀሚያ ለመሆን ተስማማ። ከጣሊያን በሚቀርብለት የጦር መሣሪያ ኃይሉን አጠናክሮ ዮሐንስን መገዳደር እና ግዛቱን ማስፋት ችሎ ነበር። የዶጋሊን ውርደት ተከትሎ ጣሊያን አሉላን እና ዮሐንስን ለመበቀል ስትዘጋጅ የምኒልክን ድጋፍ እንደምታገኝ ተስፋ አድርጋ ነበር። ለዚህም ስትል ዐሥር ሺህ የሬሚንግተን ጠመንጃ ከአራት መቶ ሺህ ጥይት ጋር ለምኒልክ ለማቅረብ ቃል ገባች።

ምኒልክ የአንቶኒሊ ዋና ተልዕኮ ኢትዮጵያን መከፋፈል እንደሆነ የተረዳው በፍጥነት ነበር። በተጨማሪ የጎጃሙ ንጉሥ ተክለኃይማኖት እና የወሎው ራስ ሚካኤል ከአፄ ዮሐንስ ተፅዕኖ ነፃ በመሆን የየራሳቸውን ግዛት ለመገንጠል መዘጋጀታቸውንም ምኒልክ ተረድቷል። በርካታ የግዛት አስተዳዳሪዎች የአፄ ዮሐንስን ብቸኛ የከልጣን ባለቤትነት ከልባቸው አልተቀበሉትም ነበርና እንደ ዘመነ መሳፍንቱ ጊዜ የየራሳቸውን ግዛት የሚያስተዳድሩበትን አጋጣሚ በመጠባበቅ ላይ ነበሩ።

የአንቶኒሊ ስሌት የነበረው አጉሩ ጣሊያን የቀይ ባሕር ወደብ የነበሩትን ምፅዋ እና ዚይላን በመያዝ የምኒልክን የባሕር በር አማራጭ በእጇ ለማስገባት ነበር። አንቶኒሊ በግሉ አፄ ዮሐንስ አገሪቷን አንድ አድረገው መግዛታቸውን ያደንቃል። ነገር ግን እርሳቸው በሆነ መንገድ ቢወገዱ በርካታ የሥልጣን ተቀናቃኞች ስለሚኖሩ አገሪቷ በእርስ በእርስ ግጭት እንደምትበታተንም ገምቶ ነበር። ግምቱ ከተሳካም አጉሩ ጣሊያን ምኒልክን በመጠቀም የተበታተነችውን አገር በቀላሉ መቀዝቀዝ እንደምትችል ተስፋ አድርጓል።

በ1880ዎቹ አንቶኒሊ ከርም አዲስ አበባ በመመላለስ አጉሩ ምኒልክ ጋር መልዳራዊ ስምምነት የምታደርግበትን መንገድ ለማመቻቸት ሲጥር ከርሟል። የስምምነቱ ዓላማ የነበረው አፄ ዮሐንስ በምኒልክ ላይ ቢዘምቱ ጣሊያን በቀጥታ ጣልቃ በመግባት ቀዩ ባሕር ዳርቻ እስከ አስመራ ያለውን ግዛት ትወርራለች። የጣሊያን ወረራ የዮሐንስን ኃይል በማዳከም ምኒልክን ይደግፋል። በዚህ ስምምነት





መሠረት ምኒልክ የጣሊያንን ወዳጅነት ለማግኘት በማለም በአፄ ዮሐንስ ሥር የነበረውን የአገራቱን ግዛት ለጣሊያን አሳልፎ መስጠቱ አልቀረም። አፄ ዮሐንስም የምኒልክ እና የጣሊያንን ሽፍጥ እንዳወቁ ምኒልክን ከሳናቸው ለማድረግ ተንቀሳቀሱ። ለምኒልክ በጻፉትም ደብዳቤ ‹‹ኹለታችን በጋራ ከቆምን በእግዚአብሔር እገዛ እናሸንፋለን›› በማለት ጥያቄ አቅርበውለት ነበር።

ምኒልክ ከጣሊያን ጋር ያደረጉት ስምምነት አደገኛ የፖለቲካ ጥልፍልፍ ውስጥ ጨምሯቸው ነበር። አካሄዳቸውን በተደጋጋሚ ሲቃወሙ የነበሩት ባለቤታቸው ጣይቱ ሲሸኑ በዘውድ ም/ቤቱ የሚገኙ የትግራይ አካባቢ ተወላጆችም በምኒልክ አካሄድ ደስተኛ አልነበሩም። ጣይቱ አንቶኒሊን በተደጋጋሚ ፊት በመንሳት ለባለቤታቸው ተቃውሞአቸውን ቢያሳዩም ምኒልክ ግን አፄ ዮሐንስ በሕይወት እስካሉ ድረስ ከአንቶሲም ሆነ ከጣሊያን ጋር መራራት እይፈልጉም ነበር። ምኒልክ ከጣሊያን ጋር ወዳጅነታቸውን በአንድ በኩል በማጥበቅ በሌላ ወገን ደግሞ ከፈረንሳይ ጋር መቀራረብ ጀምረው ነበር። በአልፍሬድ ኢልግ አበረታችነት ለፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ጁሴስ ግሬቪ በጻፉት ደብዳቤም ራሳቸውን የጣሊያን እና የዮሐንስ ግጭት ለመፍታት የሚጥር ገለልተኛ አድርገው ነበር ያስቀመጡት።

ምኒልክ በአፄ ዮሐንስ ላይ በምስጢር ቢያሴርም አገር ወዳድነቱን አላጣም ነበር። ራሱን ለጣሊያን የጦር መሣሪያ አቅርቦት በሽያጭ እንዳላተረበ ኹሉ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም አሳልፎ አልሰጠም። ዐፄ ዮሐንስ የምኒልክና የጣሊያንን ሽፍጥ ዮሐንስ ቢያውቁም ለእርምጃ አልቸኮሉም ነበር። ሥልጣናቸውን ላለመቀበል ያንገራገሩትን በመቅጣት የሚታወቁት አፄ ዮሐንስ የጎጃሙን ንጉሥ ተ/ኃይማኖት ጻተኝነት ተገንዝበው የጦሪ መሪያቸው አሉላን ልከውበት ነበር። አሉላም ንጉሡን ለማሳደድ በተራሮች መካከል እንዲሸሽ አድርጎ አዋርዶታል። በምኒልክ ላይ በ1888 ተመሳሳይ የቅጣት እርምጃ ከመውሰድ ያገዳቸው አንድም የሸዋ ርቀት ሲሆን ሌላው ደግሞ የመሃዲስት ወራሪ ኃይል መቃረብ ነበር።

ዮሐንስ ከመሃዲስት ወራሪ ጋር ለመዋጋት በዝግጅት ላይ ሳሉ አንቶኔሊ ደብዳቤዎችን፣ ስጦታዎችን፣ 4,700 የራሚንግተን ጠመንጃዎችን እና 220,000 ጥይቶችን ይዞ አዲስ አበባ ደረሰ። በዚያ ወቅት ምኒልክ ከመቶ ሺ አባላት በላይ ያሉት ሠራዊት በመገንባት ኃይሉን ከአፄ ዮሐንስ ጋር አስተካክሎ ነበር። ጣሊያንም ለምኒልክ ልዩ ድጋፍ በማድረግ በቀጠናው ታላቅ ጦር እንዲገነባ አስችላው ነበር።

ምኒልክ የባለቤታቸው ጣይቱ ብጡልን ርስት ለመጎብኘት ውጫሌ ሳሉ ነበር የአፄ ዮሐንስን መሞት የሰሙት። በጉጉት ሲጠብቁት የነበረውን ዜና ተከትሎ ራሳቸውን ‹‹ንጉሠ ነገሥት›› አድርገው ሾሙ። የምኒልክ እርምጃ የዮሐንስን ዘውድ ለመውረስ በዝግጅት ላይ ለነበረው መንገሻ ክፍተኛ ጫና ፈጠረበት። በረጅም ዘመን ታሪኳ ኢትዮጵያ በሰሜን ነገሥታት በተለይም በትግራይ ስትመራ ኖራለች። ምኒልክ ይህንን የረጅም ዘመን ታሪክ በመቀልበስ የአገሪቷን በትረ ሥልጣን ወደ ደቡብ ሲያዞሩ ሰሜናውያኑ በደቡባውያኑ በተለይም በሸዋ ላይ አቁሙ፣ ውስጣቸውም በከፍተኛ ጥላቻ ተሞላ።

ምኒልክ ዘውዱን ወደ ደቡብ ማዞራቸውን ተከትሎ ከተቆረቆረች ዐሥር ዓመት ያልሞላት አዲስ አበባ የአገሪቷ አዲስ ርዕሰ መስተዳድር (መዲና) ሆነች። አፄ ዮሐንስን ለመፎካከር የተገነባው የምኒልክ ጦርም እጅግ ኃያል የነበረ በመሆኑ በአገሪቱ የተለያዩ ግዛቶች የነበሩትን ተቀናቃኞች አደብ ማስገዛት እንደሚችል አረጋገጠ።

የምኒልክ ለዘውድ መቃረብ ያስደሰተው ሌላ ሰው ፔትሮ ኢንቶኔል ነበር። ከመጀመሪያ ጀምሮ በድጋፍ እና ክትትል ያጎለበተው ንጉሥ የአገሪቷ ርዕሰ ብሔር ለመሆን መዘጋጀቱን በመረዳትም ግንኙነቱን በፊርማ ለማረጋገጥ መሯሯጥ ጀመረ።

የአንቶኔሊ የልፋት ውጤት ደግሞ ግንቦት 2 ቀን 1889 ዓ.ም ውጫሌ ላይ የተፈረመው የኹለትዮሽ ስምምነት ነው። ስምምነቱ (አንቀጽ 14) የባሪያ ንግድን





ሙሉ ለሙሉ ለማስቀረት እንዲሁም (አንቀጽ 18) ጣሊያን ከኢትዮጵያ ጋር የንግድ ልውውጥ እንድታደርግ ቅድመ ሁኔታን ለመፍጠር ያለመ ነበር።

የስምምነቱ አወዛጋቢ አካል የነበረው በአንቀጽ 17 ላይ የሰፈረው ቅድመ ሁኔታ ነበር። በአንቀጹ ድንጋጌ መሠረት ኢትዮጵያ የውጪ ግንኙነቷን በጣሊያን ተወካይነት ለማካይነት ለማድረግ የምትገደድ ሲሆን ይህም ማለት ኢትዮጵያ በጣሊያን ሞግዚትነት የምትተዳደር ትሆናለች። በስምምነቱ አንቀጽ 19 ላይ እንደሰፈረው የሰነዱ አማርኛ እና ጣሊያንኛ ቅጂ እኩል ተቀባይነት እንዳላቸው ቢገልጽም በስምምነቱ አማርኛ ቅጂ ላይ አለመግባባት ተፈጠረ። ይህ አለመግባባት ወደ ከፍተኛ ጡዘት ደረጃ ደርሶ በመጨረሻ አድዋ ላይ በጦርነት ተጠናቀቀ።

የጣሊያኑን ንጉሥ ኡምቤርቶ በመወከል ፒየትሮ አንቶኔሊ ከአፄ ምኒልክ ጋር የተፈራረመው የውጫሌ ውል በኹለት ሉዐላዊ አገራት መካከል የተደረገ እኩልነት መገለጫ ነው። ኢትዮጵያ ቀድሞ በአውሮፓ ባገኘችው ዕውቅና የተነሣ ነበር የኹለትዮሽ ስምምነቱን ለመፈረም የበቃችው። የኹለትዮሽ ስምምነቱ በ19ኛው ክፍለዘመን አንድ አውሮፓዊ አገር ከአፍሪካ አገር ጋር ያደረገው የመጀመሪያ ሕጋዊ ስምምነት እና ቀድሞ ያልነበረ ኹነት ነው።

ስምምነቱ በርካታ ነገሮችን አስከትሏል። ስምምነቱ ለምኒልክ ንጉሠ ነገሥትነት ዋስትና መሆን ቻለ። በተጨማሪም ምኒልክ ሥልጣንን በግዛት የለወጡበትም ጭምር ነበር ስምምነቱ። በመኾኑም ከፊርማው በኋላ ጣሊያን ኔሐሴ 1889 ላይ ከምፅዋ በመንቀሳቀስ ደጋማውን የኤርትራ ክፍል በመያዝ መቀመጫዋን አስመራ አደረገች። የጣሊያን ወረራ ለመንገሻ የይስሙላ ሥልጣን ፍጻሜን ሲሰጥ ራስ አሉላን ደግሞ በጣም አስቆጥቷል። ጣሊያን በአፄ ዮሐንስ ላይ እንዳደረገችው ኹሉ የመንገሻንም ሰሜናዊ ሥልጣን ጥያቄ ውስጥ አስገባችው።

ምኒልክ በበኩላቸው በትረ ሥልጣናቸውን የማረጋገጥ ሥራ ጀመሩ። የተሊያዩ የግዛት አስተዳደሮች ላይ የሥጋ ዘመዶቻቸውን በመሾም ተጠሪነታቸውን በቀጥታ ስራሳቸው አደረጉ። የጣይቱ ወንድም ለሆነው ወሌ የራሥነት ማዕረግ በመስጠት ቀድሞ ከነበረው ይዞታ ላይ ተጨማሪ ግዛት እንዲያስተዳድር ሾሙት። የምኒልክ የእክስት ልጅ የኾኑት መኮንን ደግሞ የሐረር ገዢነታቸው ጸና። በመጨረሻም ከሰሜኖቹ መንገሻ እና ራስ አሉላ በቀር መላው የአገሪቷ ግዛቶች በምኒልክ ታማኞች አስተዳደር ሥር ኾኑ።

በመቀጠል ለውጫሌ ስምምነት ማረጋገጫ ለመስጠት ኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ልዑካን ቡድኗን ወደ ሮም ለመላክ ተዘጋጀች። በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን ተልዕኮ እንዲመሩ በምኒልክ የተመረጡት መኮንን ነበሩ።

### የሐረር አስተዳዳሪው መኮንን

ምኒልክ በአርባ አምስት ዓመት ዕድሜያቸው የንጉሠ ነገሥትነት ዘውዳቸውን ሲጭኑ አብዛኛውን ኃላፊነት በወጣቱ የአጎታቸው ልጅ ራስ መኮንን ጫንቃ ላይ ነበር የጣሉት። የግብፅን መዳከም እና የአፄ ዮሐንስን እና አውሮፓውያን የዶጋሊ ውዝግብ እንደ አጋጣሚ በመጠቀም ነበር 1887 ምኒልክ ጦራቸውን በማዝመት ሐረርን በቁጥጥራቸው ሥር ያዋሉት። ሰር ሪቻርድ በርተን ስለ ሐረር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ሲናገር *«ሐረማ ላይ ይዞታ ያለው ኃይል የሐረርን ፂም በለጀ መያዝ ይችላል»* ብሎ ነበር። ምኒልክም የከተማዋን የንግድ ጠቀሜታ እና የባሕር በር መሰመርነት ቀድመው በመረዳት ነበር የያዝዋት። ወታደሮቻቸው ከተማዋን በተቆጣጠሩ ማግስት የግዛት አስተዳዳሪነት ሥልጣኑን ለ35 ዓመቱ ራስ መኮንንም ሰጡ።

የሐረር ከተማ ቁመቱ እስከ ዐሥራ አምስት ጫማ በሚደርስ የግንብ አጥር የተከበበች ናት። በዙሪያዋ አምስት በሮች ሲኖሩ ዐሥራ አምስት የጥበቃ ማማዎች አሉ። በወቅቱ የነበረው የከተማዋ የጥበቃ ሥርዓት ከሶማሊያ ጠረፍ በአፋር በርሃ





አቋርጠው ይመጡ የነበሩ ነጋዴዎችን ያስገርም ነበር። አንድ ተጓዥ ነጋዴ ሐረርን «በቸኩሌት የተገነባች» ትመስላለች ብሎ ነበር።

ሐረር በበርካታ ነጋዴዎች ምልልስ የምትደምቅ ከተማ ናት። አብዛኛው ነዋሪ ኦሮሞ ሲሆን ብዙ ቁጥር ያላቸው የአደሬ ተወላጆችም በሐረር ይኖራሉ። ከኹሉቱ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ በተጨማሪ አረብኛ፣ ግሪክ፣ ሂንዲ፣ ጣሊያንኛ፣ ፈረንሳይኛ እና እንግሊዝኛ በሐረር ይነገሩ ነበር። በዐሥር ሺህ የሚቆጠሩ የከተማይቱ ነዋሪዎች በከተማዋ እምብርት አካባቢ ስብስብ ብለው ይኖሩ ነበር። በሐረር የገበያ ማዕከል የማይሸጥ ነገር የለም። የተለያዩ የአዝዕርት ዓይነቶች፣ ፍራፍሬዎች፣ አትክልት፣ አልባሳት፣ ቡና፣ የቁም ከብት እንደሁም ሥጋ ሳይቀር ለሽያጭ ይቀርቡ ነበር።



Ras Makonnen. From Gaëtan Sellassie, *Chronique du règne de Ménélik II, roi des rois d'Ethiopie*. Paris: Maisonneuve Frères, 1930.

*ምኒልክ ራስ መኮንን*



Ras Makonnen. From Gabriel Sellassie, *Chronique du règne de Ménélik II, roi des rois d'Ethiopie*. Paris: Maisonneuve Frères, 1930.

ምስ፡- ራስ መኮንን

በርካታ አውሮፓውያን ጎብኚዎች ሐረር ከሰሜን አፍሪካ ከተሞች ጋር እንደምትመሳሰል በተለያዩ ጊዜያት ገልጸዋል። ግብፅ እና ሸዋ ሐረርን ለመያዝ በተለያዩ ጊዜያት ሲፎካከሩ ቆይተዋል። በመጨረሻም ምኒልክ ከተማዋን በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው «ይህ የእስላም አገር አይደለም። ዅሉም ይሄንን ይወቅ» በማለት ዐወጁ። በመቀጠልም ራስ መኮንን የከተማዋን ትልቅ መስጊድ አስፈርሰው በጣሊያን የሕንፃ ባለሙያዎች እገዛ ትልቅ ቤተ-ክርስቲያን አስገነቡ።

ሐረር የጠረፍ ነጋዴዎች መዳረሻ ብቻ ሳትሆን ከፍተኛ ዋጋ ያለው የቡና ገበያም ጭምር ነበረች። ምኒልክ ወደ ደቡብ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ባደረጉት የመስፋፋት ዘመቻ በግዛታቸው ሥር ካደረጉዋቸው ይዞታዎች መካከል ሐረር እና ወላይታ ከፍተኛ ጠቀሜታ አስገኝተውለታል። የዅለቱ ግዛቶች የሐብት መጠን የአድዋውን ዘመቻ ስኬታማ ማድረግ አስችለዋል። ከለዳዲሶቹ ግዛቶች ምኒልክ ከፍተኛ ገቢ መሰብሰብ ችለዋል። በሐረር ልዩ የቀረጥ ሥርዓት በመጣል ከጀመሩት የግብር መሰባሰብ እርምጃ ቀጥሎ በከተማዋ የነበሩ የአውሮፓዊ ነጋዴዎች ብድር እንዲያቀርቡ አስከማስገደድ ደርሰው ነበር። ምኒልክ የተፈለገውን ያህል ገቢ ከሐረር መሰብሰብ ቢችሉም የከተማዋ የንግድ እንቅስቃሴ ለማገገም በርካታ ዓመታት አስፈልጓታል።

የሐረር ገዢ በመሆን በምኒልክ የተሾሙት ራስ መኮንን ከተማዋን ከማስተዳደር እና ግብር ከመሰብሰብ የዘለለ ኃላፊነት ተጥሎባቸው ነበር። ሐረር በመቀመጥ ወደ አዲስ አበባ የሚመጡትን እንግዶች በመቀበል ወደ ምኒልክ ያስተላልፉ ነበር። በርካታ አዝ ጎብኚዎችን እና ዲፕሎማቶችን ይቀበሉ የነበረው ሐረር ከመድረሳቸው በፊት የእንድ ቀን መንገድ ሲቀራቸው ነበር። መኮንን በአግባቡ የታጠቁ ፈረሰኞቻቸውን በመላክ እንግዶችን አሳጅበው እስከ ሐረር ያስመጧቸውም ነበር።





በሐረር ጎላ ብሎ ከሚታየው ባሰ ዅለት ፎቅ ሕንፃው ቤተ-መንግሥታቸው ነበር ራስ መኮንን እንግዶችን የሚቀበሉት። እንደ እንግዶቹ ደረጃ የተለያየ የአቀባበል ሥርዓት ቢያደርጉም ራስ መኮንን በመልካም እንግዳ ተቀባይነታቸው ይታወቃሉ። ብዙውን ጊዜ እንግዳ በሚቀበሉበት ወቅት ይለብሱ የነበረው ጥቁር የሐር ሽሚዝ ሲሆን የሸሚዙ ቁልፎች ከወርቅ የተሰሩ ነበሩ።

መልክ መልካሙ ራስ መኮንን ኦሮሞ ሚስታቸውን በሞት ከተነጠቁ በኋላ ድጋሚ አላገቡም። ለሚስ ሚስታቸው ያላቸውን ታማኝነት ለሐረር ከተማ እና ለሕዝቦቿ ያላቸው ታማኝነት ማሳያ እንደነበር ይነገርላቸዋል። በዚያም ነበር በሐረር ሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትን ያገኙት። ብዙ ጊዜ ከቤተ መንግሥታቸው በመውጣት ሕዝቡ መካከል ይዘዋወሩ ነበር። ያለምንም አጃቢ አንድ አስጎብኚያቸውን ብቻ አስከትለው መንቀሳቀሳቸው በሕዝቡ ዘንድ የነበራቸውን ከበሬታ እና ተወዳጅነት ያሳያል።

በርካቶች በራስ መኮንን ምሁራዊ አስተዳዳሪነት እና ጥበበኝነት ይስማማሉ። በርካታ ባላንጣዎቻቸው ሳይቀሩ ይህንኑ ይመሰክራሉ። ሰር ጄምስ ሬኔል ሮድ «የተዋጣለት ዐዋቂ» በማለት ነበር መኮንን ያሞገሳቸው።

ራስ መኮንን በብዙዎቹ ዘንድ የምኒልክ ዘውድ ወራሽ እንደሚኾኑ ቢገመትም በ1906 ነበር ከዚህ ዓለም በሞት የተሰዩት። በርካታ ባሕርያትና ስብዕናቸውን ለልጃቸው ራስ ተፈሪ አውርሰው ነበር የሞቱት። ወራሽ ልጃቸውም ከአገራቸው አልፈው በበርካታ የአፍሪካ ስደተኞች ዘንድ የራስተፈሪያን ዕምነት እና ፍልስፍና ማዕከል በመሆን ይታወቃሉ። ራስ መኮንን ምኒልክን ተክተው መሥራት ባይችሉም ልጃቸው በ1930 ዓ.ም ኃይለሥላሴ በሚል የንግሥና ስም ዘውድ ጭነዋል።

የራስ መኮንን መቀመጫ የሆነችው ሐረር የጲፕሎማቶች መግቢያ በር ብቻ ሳትሆን የባሕል እና ኃይማኖት ማዕከልም ጭምር ነበረች። ከቀይ ባሕር ዳርቻ በተነሳ የእስልምና እና የኢትዮጵያ ደገኞች ዕምነት በሆነው፡ ክርስትና ዕምነት ሥርዓት

የተቀረጸ የአኗኗር ዘይቤዋ፣ የቤት አሠራር እና የአሰባበስ ሥርዓቶቿ ሐረርን ከመሳከሰኛው ምሥራቅ ከተሞች ጋር አንጂ ከየትኛውም የጥቁር አፍሪካ መንደር ጋር አያመሳስላትም።

የንግድ እንቅስቃሴዋ ጫፍ በነካባቸው በ1880ዎቹ ሐረር የበርካታ ፈረንሳዊ፣ ጣሊያናዊ፣ ሕንድ፣ አርመን እና ግሪኮችን ቀልብ ስባ ነበር። በርካቶቹ ከአውሮፓ የተለያዩ አልባሳትን እና የጦር መሣሪያዎችን ለአፍሪካ ገበያ የሚያቀርቡት ሐረርን ማዕከል አድርገውም ነበር። እንደ ፈረንሳዊው ገጣሚ አርተር ራምቦ ያሉ የትልልቅ ኩባንያ ተወካዮችም ሐረርን መቀመጫቸው አድርገው የወጪ እና ገቢ ንግዳቸውን ያከናውኑ ነበር።

ራምቦ በ1880 ለመጀመሪያ ጊዜ ሐረር የመጣው መቀመጫው በኤደን የነበረውን ባርዱ ኩባንያ ወክሎ ነበር። በ1885 ግን ውክልናውን በመተው ለምኒልክ የጦር መሣሪያ ለማቅረብ ወሰነ። ከአውሮፓ ያስመጣቸውን ያገለገሉ የጦር መሣሪያዎች ለምኒልክ አቀረበ። ምኒልክም የመሣሪያውን ዐሥር ከመቶ በአንር ውስጥ ገቢ መልክ ከቀረጡበት በኋላ የቀረውን ለመግዛት ዋጋ ቀረጡለት። ክፍያውን ሐረር ሲደርስ ራስ መኮንን እንደሚፈጽሙለት በመናገር ምኒልክ ሲያለናገቡት አልተቃወመም ነበር።

ሐረር ደርሶ ክፍያውን ከተቀበለ በኋላ የተረፈው ነገር ቢኖር ለአፍሪካ ነገሥታት እና የጎሳ መሪዎች መሣሪያ ማቅረብ የዋጋ ድርድር ለማድረግ እንደማያስችል ነበር። በመሸኩም በበርካታ ግሪኮች ቁጥጥር ሥር በነበረው የአገር ውስጥ ገበያ በመግባት ለግለሰቦች መሣሪያ ለመቸርቸር ወሰነ።

በወቅቱ አዋጭ የነበረው የባሪያ ንግድ ቢሆን ሐረርም በሽዋ እና በጠረፍ አካባቢ ማዕከል ላይ በመገኘቷ ለባሪያ ንግዱም ማዕከል ነበረች። ከጠረፍ እስከ ሐረር በተዘረጋው የንግድ መስመር ላይ አምስት የንግድ ማዕከላት የነበሩ ቢሆንም ሦስቱ





ብቻ ነበሩ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚደረግባቸው። እነርሱም በእንግሊዝ ሥር የነበረው ዘይላ እና በፈረንሳይ ቁጥጥር ሥር የነበሩት አቦክ እና ታጁራ ናቸው።

የታጁራ ሰርጥ እና እስከ ሐረር የተዘረጋው የ182 ማይል የንግድ መሥመር በኢብራሒም አቡበክር እና ዐሥራ ሹሰት ልጆቹ ቁጥጥር ሥር ነበር። በርካታ አውሮፓዊ የንግድ አጋሮቹን ቡና በመጋበዝ የሚታወቀው አቡበክር የንግድ ቀጠናውን በመቆጣጠሩ ሰዕቃ ዋጋ የሚያቀርበው እርሱ ብቻ ነበር። በርካቶች ነጋዴዎች ‹‹ሕጋዊ ዘራፊ›› በሚል ጥቅል ስሙ ይለዩት ነበር። በንግድ መስመሩ ይካሄድ የነበረውን የባሪያ ንግድም ይቆጣጠር የነበረው አቡበክር ነበር። በርካታ አውሮፓውያን እንግዶች ከአቡበክር ጋር በተገናኙበት ወቅት የማይረሷቸው ሹሰት መለያዎችን ሲሆን ከእጁ የማይለየውን የመቁጠሪያ ዶቃ(መስበሐ) እና በተደጋጋሚ በፊት ጥርሱ ፍንጨት በኩል ምራቁን ‹ጢቅ› ማድረጉን ነበር።

የአቡበክር ጎሳ አባላት ከጠረፍ አካባቢ ስለማይንቀሳቀሱ የሐረሩ ገዢ ራስ መኮንን ከአቡበክር ጋር መልዕክት ይለዋወጡ የነበረው በነጋዴዎች አማካይነት ነበር። በሹሰቱም ወገን የነበረው ፍላጎት የንግድ መስመሩ እክል ሳይገጥመው ንግዱ እንዲከናወን ነበር። የአቡበክር ከፍተኛ ገቢ የነበረው ቀይ ባሕርን አሻግሮ በሚልካቸው ባሮች ሲሆን የባሪያ አቅርቦቱም የኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢ ነበር። ምኒልክ በሌላ ወገን የንግድ መስመሩ ብቸኛ የመሣሪያ ማስገቢያ እና ወጪ ንግድ ማከናወኛቸው በመሸኩ የባሪያ ንግድ እንቅስቃሴውን በማስቆም አቡበክርን ማስከፋት አልፈለጉም ነበር። በመሸኩም ምኒልክ ከአቡበክር ጋር ከመስማማት ውጪ አማራጭ አልነበራቸውም።

እንግሊዝ በዘይላ እና ሌሎች የቀይ ባሕር ወደቦች ሊካሄድ የነበረውን የመሣሪያ እና የባሪያ ንግድ ስታስቆም የምኒልክ እና የአቡበክር ሀልውና በጋራ ትብብር ላይ የተመሠረተ በመሸኩ ኹሰቱ ተሰማሙ። አቡበክር ከበርካታ ዘረፋ እና ግድያ ጋር ስሙ ቢያያዝም ምኒልክ ወዳጅነታቸውን አላቆሙም ነበር። በ1886 ባራል ላሸሬ በተባሉ የፈረንሳይ ነጋዴዎች ላይ ግድያ የተፈጸመ ሲሆን ብዙኃን የድርጊቱ

ባለቤት አቡበክር እንደሆነ እና የፈረንሳይ ባሕር ኃይል የባሪያ ንግድ እንቅስቃሴውን በመረበሹ የወሰደው የበቀል እርምጃ እንደሆነ ገምተዋል።

አቡበክር ነጋዴ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ጎሳዎች መካከል የግንኙነት መስመርም ነበር። በጠረፍ ካሉ ሶማሌዎች ጋር ብዙ ጊዜውን ቢያሳልፍም የዘር ሐረጉ ከአፋር ጋር በመገናኘቱ ከአፋር የጎሳ መሪዎች ጋርም ጥሩ ግንኙነት ነበረው። በመሆኑም ከታጁራ የሚነሳ ጭነቱን ወደ ሐረር ለማሳሰፍ የአፋርን የንግድ መስመር በነጻነት መጠቀም ችሉ ነበር። አቡበክር በ1885 ሲሞት ልጆቹ የንግድ እንቅስቃሴውን ወረሱ። ወደ ሸዋ በርካታ ዕቃ በማስገባት በመልስ ጉዟቸው ደግሞ ወደ አረብ ባሕረሰላጤ የሚያሻግራቸውን ባሪያ ወጣቶች ይዘው ይመለሱ ነበር።

ሐረር ላይ የተቀመጡት ራስ መኮንን ከምኒልክ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት የአገሪቷን ወጪ እና ገቢ ንግድ ይቆጣጠሩ ነበር። ምኒልክም ኾኑ ራስ መኮንን የባሪያ ንግድ እንቅስቃሴውን ለማቆም ፍላጎት ነበራቸው። ይህንን እንዲያደርጉ ያስገደዳቸው የአገሪቱ ዋና የወጪ ንግድ በባሪያ አቅርቦት ላይ የተመሠረተ በመኾኑ ነበር። ከኹሉም በላይ ግን የባሪያ ንግዱን ማቋረጥ የንግድ መስመሩን ባለቤቶች ስለሚያስቀይም ብቸኛውን የባሕር በር እንዳያሳጣቸውም ሰግተው ነበር።

ሪቻርድ ፓንክረስት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊ ታሪክ በዳሰሰበት ሥራው የባሪያ ነጋዴዎች በ1880ዎቹ በየሦስት ወሩ ከሸዋ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ባሪያ ያግዙ እንደነበር ጽፏል። በ1890ዎቹ አጋማሽ ላይ ግን ምኒልክ የባሪያ ንግዱን ለማስቆም ቁርጥ ውሳኔ ላይ በመድረስ በርካታ የባሪያ ገበያዎችን ያፈረሱ ሲሆን የታወቁ የባሪያ ፈንጋዮችን እጅ በማስቀረጥ ቀጥተዋል። በዚያ ሁኔታ የባሪያ ወጪ ንግዱ ቢቆምም በአገር ውስጥ ግን ባሮች በሠርግ፣ በለቅሶ፣ እና በመሳሰሉት አጋጣሚዎች በስጦታ መልክ ይቀርቡ ነበር። ይህ የስጦታ ሥርዓት እስከ 1903 ድረስ ዘልቋል።





እንደ ነጋዴዎች ኹሉ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ወደ ሐረር እና ሸዋ መግባት የጀመሩት ራስ መኮንን ሐረር ሳሉ ነበር። ሉዊስ ታውሪን የተባሉ የካቶሊክ ቄስ በ1881 ወደ ኢትዮጵያ በመግባት የሮም ካቶሊካዊ ሚሲዮን የማቋቋም እንቅስቃሴ ጀመሩ። ቄስ ታውሪን የባሪያ ንግዱን በመቃወም ዕድሚያቸው ከ15-30 የነበሩ ወጣት ባሮችን ለመታደግ ከነጋዴዎች ላይ ይገዙ ነበር። የገዟቸውን ወጣቶች ወደ ካቶሊክ በመቀየር ያስተምሩም ነበር። ወጣቶቹም በመቀጠል በተሰያዩ የግል ሥራዎች እና የወንጌል ሥርጭት ተግባር ተሰማሩ። ቄስ ታውሪንን የተኳቸው መጋቢ አንድሬ ሻሮሱ በ1884 ወደ ሐረር ያቀኑ ሲሆን ከአምሳ ዓመታት በኋላ በ1930ዎቹም መጋቢው እዛው ነበሩ።

በሐረር ቆይታቸው ራስ መኮንን በርካታ የዲፕሎማሲ ልምድ አካብተዋል። በከተማዋ ይገቡ እና ይወጡ ከነበሩ በርካታ የአውሮፓና አረብ ነጋዴዎች ጋር ያደርጉ የነበረው ውይይት ለዲፕሎማሲያዊ ዕውቀታቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

የመኮንንን የላቀ የዲፕሎማሲ ችሎታ የተረዱት አፄ ምኒልክ ወደ ሮም፣ ሴንት ፒተርስበርግ፣ ፓሪስ እና ለንደን ልዑካንን ሲልኩ በመሪነት የመረጡት ራስ መኮንንን ነበር። የፈረንሳዩ ሌ ፔምፐስ ጋዜጣ ራስ መኮንንን በተደጋጋሚ አሞግሶ የጻፈ ሲሆን በኢትዮጵያ መንግሥት ከምኒልክ ቀጥሎ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ እንደኾኑም መስክሮላቸዋል። በአዲስ አበባ እና በመላው አገሪቱ ክፍል የነበሩ ጎበዛዝት የምኒልክ መኮንንን መመረጥ ተከትሎ ቢያጉረመርሙም ቅሉ ምኒልክ የውጫሌን ስምምነት ለማጠቃለል ወደ ሮም መኮንን ለመላክ የወሰኑት ያለምንም ማቅማማት ነበር።

### የራስ መኮንን ተልዕኮ በጣሊያን

በራስ መኮንን የተመራው የኢትዮጵያ የዲፕሎማቶች የልዑካን ቡድን ነሐሴ 27 ቀን 1889 ሮም ሲደርስ ክስተቱ ለአፍሪካ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ድል ነበር። የኢትዮጵያ ልዑካንን የሮም ጉብኝት ልዩ እና አንፀባራቂ የሚያደርገው በጥቁር አፍሪካ

እና በዘመናዊ አውሮፓ መካከል የተደረገ የመጀመሪያው ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መሸኑ ነው።

የልዑካኑ ጉብኝት የጀርመኑ አቶ ቮን ቢስማርክ ከአምስት ዓመታት በፊት በርሊን ላይ በጠራው ስብሰባ የአፍሪካ ቀጣይ ዕጣ ፈንታ በአውሮፓውያን ቅኝ ገዢዎች ፍላጎት እንደሚወሰን ለተናገረው ምላሽ የሰጠም ነበር። በ1884 የበርሊን ኮንፈረንስ አንድም የአፍሪካ መንግሥት አልተጋበዘም ነበር። የመኮንን ዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ ለአሳፋሪው የቢስማርክ ንቀት የመጀመሪያውን አፍሪካዊ ምላሽ የሰጠ ሲሆን ቀጣዩ እና ከፍተኛ ዋጋ የተከፈለበት ምላሽ የተሰጠው ግን በ1896 የአድዋ ጦርነት ነበር።

በመኮንን የተመራው የልዑካን ቡድን በሐምሌ ወር 1889 ከሐረር ሲነሳ ፒየትሮ ኢንቶኔሊ እና ሉጂ ካፑቺም ጉዞውን ተቀላቀሉ። ዘይላ ደርሰው ኮሎምቦ መርከብ ላይ የተሳፈረው የልዑካን ቡድን አስተርጓሚ የነበረውን ዮሴፍ ንጉሴ፣ የእርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ቄስ የሸኑትን ወደልሚካኤልን ጨምሮ አምስት ከፍተኛ ልዑካንን ከዐሥራ ሦስት አጃቢዎቻቸው እና ሐያ አንድ አገልጋዮቻቸው ጋር የያዘ ነበር።

መርከቧ የጣሊያን ንብረት ብትሆንም የተሰቀለባት ሰንደቅ ዓላማ የኢትዮጵያ ነበር። አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለም ያለው ሰንደቅ መካከሉ ላይ መስቀል የያዘ ባለ ዘውድ የይሁዳ አንበሳ ምስል ነበረው። በመርከቧ ላይ በክብር የተሰቀለው ሰንደቅ የኢትዮጵያን ሉዐላዊነት ለዘመናዊው ዓለም ያሳወቀ የመጀመሪያው ታሪካዊ ኹነት ነበር።

የውጫሌ ስምምነት ጣሊያን የኢትዮጵያ ጠባቂ ወይም ሞግዚታዊ አስተዳደር እንደሆነች አስቀምጧል። በመሸኑም ጣሊያን ያላትን የማስተዳደር ኃይል ለኢትዮጵያ ልዑካን ሰማሳየት ተዘጋጅታ ነበር። ልዑካኑን የያዘችው ኮሎምቦ የጣሊያኗ ኔፕልስ ከተማ ከመድረሷ በፊት አቀባበል ያደረገላት የጣሊያን ባሕር ኃይል ነበር። ልዑካኑ





ከስትሮም በሊ እስክ ኔፕልስ በባሕር ኃይል ታጅበው በመጓዝ ነሐሴ 21 ቀን የኔፕልስን መሬት ረገጡ። ግማሽ ሚሊዮን ነዋሪዎች ያሏት ኔፕልስ የሚላንን ያህል ትልቅ ባትሆንም የጣሊያንን የቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ የሚያቀነቅነው የItalian Geographical Society መቀመጫ በመሆኗ ነበር የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች እንዲጎበኟት የተደረገው።

ልዑካኑን በርካታ ዲፕሎማቶች፣ ባለሥልጣናት እና የጦር ሠራዊት አባላት የተቀበሏቸው ሲሆን ለክብራቸውም መድፍ ተተኩሶላቸዋል። እንግዶቹ በተዘጋጀላቸው ልዩ ባቡር ሆነው ቡቶሌዶ በኩል አድርገው ወደ ካፓዲሞንቴ ቤተ-መንግሥት አመሩ። ቤተ-መንግሥቱ የኢትዮጵያውያኑን ቀልብ ለመሳብ ሲባል ልዩ እድሳት ተደርጎለታል። በቤተ-መንግሥቱ ለእንግዶቹ ቤቲ የሸኑ መኝታ ክፍሎች የተዘጋጁ ቢሆንም አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ከቤት ውጪ ማደርን ነበር የመረጡት። ውስጥ ያደሩትም ቢሸኑ ጠመንጃ እና ጎራዴያቸውን ከጎናቸው አድርገው ነበር።



The Ethiopian diplomatic mission to Italy, 1889. From SAI Archive at the University of Naples "L'Orientale". Silvana Palma, *Archivio storico della Società africana d'Italia*. [illegible] Naples: Istituto Universitario Orientale, 1997.

***ምስል፡- የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ልዑካን በጣሊያን (1889)***



The Ethiopian diplomatic mission to Italy, 1889. From SAI Archive at the University of Naples "L'Orientale"; Silvana Palma. *Archivio storico della Società africana d'Italia; [illegible]*. Naples: Istituto Universitario Orientale, 1997.

**ምስል፡- የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ልዑክን በጣሊያን (1889)**

በኔፕልስ ቆይታቸው ወቅት መኮንን እና ልዑካኑ በሳንካርሎ ቲያትር አፒራ ተጋብዘዋል። ወደ ካሴርታ በመሄድም የባርበን መዝናኛ የነበረውን ያማረ ቤተ-መንግሥት ጎበኙ። የአንድ ሳምንት የኔፕልስ እና ካምፓንያ ቆይታቸውን ጨርሰው ነሐሴ 27 ቀን 1889 በባቡር ወደ ሮም አመሩ።

የኢትዮጵያ ልዑካን ጣሊያን በደረሱበት ተመሳሳይ ወቅት ምፅዋ የነበረው የጣሊያን ጦር ወደ አስመራ ተንቀሳቀሰ። ለአፄ ምኒልክ ስለ እንቅስቃሴው በተጻፈ ደብዳቤ ሠራዊቱ የምፅዋን ሞቃት አየር መላመድ ባለመቻሉ ወደ ቀዝቃዛዋ አስመራ እንደተንቀሳቀሰ ነበር የተገለጸላቸው። የወታደሩ እንቅስቃሴ ከራስ መኮንን ጉብኝት ጋር እንዲገጣጠም የተደረገው የኢትዮጵያ እና ጣሊያን ወዳጅነት መጠናከሩን ለማሳየት ነበር።

የጣሊያን ሠራዊት ወደ አስመራ መንቀሳቀስ በአገረ ጣሊያን ሕዝብ ዘንድ ተቃውሞ አሥነስቶ ነበር። የሻቲካንን ጋዜጣ ጨምሮ በርካታ የጎትመት ውጤቶች የጣሊያንን መንግሥት ወረራ በመቃወም ላይ ነበሩ። የመንግሥት ልሳን እንደሆነ የሚታወቀው ትሪቡና ጋዜጣ ‹‹የቅኝ ግዛት ወረራ ድርጊት›› በማለት ጽፎ የአስመራን መወረር ተቃውሟል።

የልዑካን ቡድኑ ሮም የደረሰው ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ነበር። በርካታ ጣሊያናውያን በአገራቸው መንግሥት የቅኝ ግዛት አካሄድ ለመቃወም የኢትዮጵያ ልዑካንን መምጣት በመጠባበቅ ላይ ነበሩ። በርካታ ቁጥር ያላቸው ጣሊያናውያን ደግሞ የዶጋሊውን ሞፍጨፋ በማስታወስ ለተቃውሞ ወጥተዋል።

ራስ መኮንን ከባቡር ሲወርዱ የተቀበሏቸው ጀነራል ኤሚሊዮ ፓላቪቺኒ እና ሌሎች የመንግሥት ተወካዮች ነበሩ። ከባቡር ጣቢያው ዙሪያ በርካታ ተቃዋሚዎች የተሰበሰቡ ሲሆን እነርሱን ለመበተን የመጣ በርካታ የፖሊስ ሠራዊትም ተሰልፎ





ነበረ። የተቃውሞ ግርግሩ እስኪበተን ድረስ የኢትዮጵያ ልዑካን በአንድ ፋርጎ ውስጥ እንዲቀመጡ ተደረገ። የወቅቱን ተቃውሞ በርካታ የጣሊያን ጋዜጦች ‹‹ኃላፊነት የጎደለው›› እንዲሁም ‹‹ያልተገባ›› በማለት ገልጸውታል።

ተቃዋሚዎች ከተበተኑ በኋላ ኢትዮጵያውያኑ በልዩ ጥበቃ ሥር ሆነው ወደ ቪላ ሚራፊዮሪ ተወሰዱ። በቪላው የነበረው መስተንግዶ እጅግ የተሟላ ነበር። በኢትዮጵያ ባህል መሰረት ለእርድ የተዘጋጁ በግ እና በሬ ነበሩ። የምግብ እልፍኙ በኢትዮጵያ ወግ መሠረት አነስተኛ በጠረጴዛ እና ከፍ ባሉ ወንበሮች ተዘጋጅቷል።

በኹለተኛው ቀን አመሻሽ ላይ ልዑካኑ ከተማዋን ጎበኙ። ራስ መኮንን የቪክቶር ኢማኑኤል ዳግማዊን መቃብር በመጎብኘት ፊርማቸውን አስቀመጡ። በባቡር ጣቢያው የተፈጠረው ግርግር እንዳይደገም በማሰብ በጉብኝቱ ወቅት ጠንካራ የደኅንነት ጥበቃ ተደርጎ ነበር።

### ‹‹የግርማዊነትዎ ጥበቃ እንዲደረግልኝ እጠይቃለሁ››

የራስ መኮንን ዋና ተልዕኮ የጀመረው ነሐሴ 29 ነበር። በዕለቱ በከፍተኛ ወታደራዊ ሰልፍ የታጀበው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን የጣሊያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶ ወደነበሩበት ኩሪናል ቤተ-መንግሥት አመራ።

የንጉሡ ማረፊያ ክፍል ሲደርሱ የተቀበሏቸው ንጉሡ ብቻ አልነበሩም። ጠቅላይ ሚኒስትር ፍራንሴስኮ ክሪስፒን ጨምሮ ኹሉም ሚኒስትሮች፣ የጦር ሠራዊት ጀነራሎች እና የግዛት አስተዳዳሪዎች ተገኝተዋል። ኻለበርካታ ዓመታት የጣሊያንን እና የምኒልክን ግንኙነት ሲያጠናክሩ የነበሩ የጣሊያን ልዑካን - ፒየትሮ አንቶኔሊ፣ አጉስታ ሳሊምቤኒ፣ ሴዛር ኔራዚኒ፣ ሱጂ ካፑቺ እና ሊዮፓልዶ ትራቬርሲ - ከንጉሥ ኡምቤርቶ አጠገብ ቆመዋል።

በኢትዮጵያ ንጉሣውያን ሥርዓት እና ወግ መሠረት ራስ መኮንን ከንጉሥ ኡምቤርቶ ፊት በማጎንበስ ሰላምታ አቀረቡ። ሰላምታው ተጠናቅቆ ቦታቸውን እንደያዙ ንጉሡ በጨዋ ደንብ ስለ ጉዟቸው እና ስላጋጠማቸው ነገሮች ጠየቋቸው።



Umberto receives the Ethiopian diplomatic mission. From *Illustrazione italiana*, 1889. Widener Library, Harvard College Library, ICA Emig

***ምስል፦ የጣሊያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶ የኢትዮጵያ ጳጳሱማቶችን በቤተ-መንግሥታቸው ሲቀበሉ***

ዋናው ውይይት የተጀመረው በከፍተኛ ጥንቃቄ የተመረጡ ቃላትን በመጠቀም ነበር። የመጀመሪያው ተናጋሪ የነበሩት ራስ መኮንን ሲሆኑ በአስተርጓሚያቸው ዮሴፍ ንጉሤ አማካይነት የአፄ ምኒልክን መልዕክት አስተላለፉ። ***‹‹የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ ለኹለቱ አገራት የጋራ ጥቅም ሲባል ከአዣርም የንግድ ሰምምነት ማድረግን ይገልጻሉ››*** በማለት ነበር ራስ መኮንን መልዕክቱን ማስተላለፍ የጀመሩት። በመቀጠልም፦ ***‹‹ለኢትዮጵያ እና በዙሪያዋ ለሚገኙ የጣሊያን ይዞታዎች ሰላም እና ደኅንነት ሲባል የግርማዊነትም ጥበቃ እንዲደረግልኝ እጠይቃለሁ››*** የሚለውን የአፄ ምኒልክ መልዕክት ቃል በቃል አቀረቡ። በወቅቱ በቦታው ተገኝተው የመኮንንን ንግግር ያዳመጡ ሰዎች ሲረዱ የሚችሉት ነገር ግልጽ ሲሆን ይኸውም ራስ መኮንን በምኒልክ ስም የጣሊያንን ጥበቃ መጠየቃቸው ነው።






ንጉሥ ኡምቤርቶም በምላሻቸው እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል። ***‹‹መልዕክትሀን ተቀብያለሁ። ለኹለቱ አገራት የጋራ ጥቅም ሲባል የተገባውን ሰምምነት ለመጠበቅ ቃል እገባለሁ። በጠየቃችሁኝ መሠረትም እኔና መንግስቴ ለአገራችሁ ጥበቃ ለማድረግ ቃል እንገባለን።››***

ራስ መኮንን በሕጋዊነት ሊያጸድቁት ወደ ጣሊያን የተጓዙበት የውጫሌ ሰምምነት ኢትዮጵያን በጣሊያን ጥበቃ ሥር ለማድረግ ያስማማ እንደሆነ ጣሊያኖች ያተርባሉ። በስምምነቱ ሰነዱ ውስጥ ‹‹ጥበቃ›› ወይም ‹‹የሞግዚት አስተዳደር›› የሚሉ ቃላት ባይጠቀሱም የራስ መኮንን ተማፅኖ እና የንጉሥ ኡምቤርቶ ምላሽ ብቻውን የጣሊያንን ‹‹የጥበቃ›› መብት ያረጋገጠ ነበር። የመኮንን እና የንጉሡ ውይይት ቃል በቃል በጋዜጦች የወጣ ሲሆን በዚያ ወቅት ጣሊያን የነበሩት የኢትዮጵያ ልዑካን ማስተባበል ይችሉ ነበር። በውይይቱ የተፈጠሩ አለመግባባቶች ከነበሩም ራስ መኮንን ምላሽ ለመስጠት እና ለማስተባበል በቂ ዕድል ነበራቸው።

ይህ የማጭበርበሩ አንድ አካል ነበር? ታሪኩ ገና መጀመሩ ነበር።

የኡምቤርቶ እና የመኮንንን የጋራ መግለጫ በመስማት ውይይቱ ተጠናቀቀ። በመቀጠል ከአፄ ምኒልክ የተላኩ ስጦታዎችን ልዑካኑ ለንጉሡ አቀረቡ። ስጦታዎቹም በወርቅ ያጌጠ ጦር እና ጋሻ፣ አምስት የአሮሞ የፈረስ ኮርቻ፣ ነጋሪት፣ ኹለት ገንቦ ጠጅ፣ ሠላሳ ትልልቅ የዝሆን ጥርስ እና አንዲት የዝሆን ግልገል ከነሕይወቷ ነበሩ።

ጳጳሱማሲያዊ ተልዕኮው ሊጠናቀቅ ልዑካኑ ጉብኝት ማድረግ ቀጠሉ። ላ ስፔዚያ፣ ሞንዛ፣ ቱሪን፣ ቦሎኛ፣ ሚላን፣ ሞዴና እና ቬኒስን በማስጎብኘት የጣሊያን መንግሥት በኢትዮጵያ ጥበቃ ማድረግ እንደሚችል ለልዑካኑ አሳየ። ንጉሥ ኡምቤርቶ እና ባለቤታቸው ንግሥት ማርጋሪታ ልዑካኑን ሞንዛ በሚገኘው ቤተ-



Umberto receives the Ethiopian diplomatic mission. From *L'Illustrazione Italiana*, 1889. Widener Library, Harvard College Library, IC AFrica.

ምስል፡- የጣሊያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶችን በቤተ መንግሥታቸው ሲቀበሉ

መንግስታቸው ጋበዙ። በጉብኝቱ እጅግ የተደሰቱት ራስ መኮንን የቱሪን ከተማን ‹‹መንግሥተ-ሰማያት›› በማለት ሲያሞግሱ የኮሞን ሐይቅ ደግሞ ‹‹ማንም ከዚህ መሄድ አይፈልግም›› በማለት አድንቀው ተናግረዋል።

የራስ መኮንን ልዑካን መስከረም 19 ቀን ወደ ሮም በመመለስ የውጫሌ ስምምነት ላይ ስለሚገቡ ተጨማሪ ነጥቦች ከጣሊያን መንግሥት ጋር ተወያዩ። ጥቅምት 1 ቀን ኔፕልስ ላይ በተደረገ የፊርማ ሥነ-ሥርዓት ተጨማሪ ነጥቦቹ ሕጋዊ ኾኑ። በአዲሱ ማስተካከያ መሠረት ጣሊያን የያዘቻቸው የኢትዮጵያ ግዛቶች በጊዜያዊነት የራሷ እንዲኾኑ ተደነገገ። ስምምነቱ በክረምቱ ወራት ጣሊያን የያዘችው መሬት ማለትም አስመራን ጨምሮ ከመረብ ወንዝ ባሻገር ያለውን የኢትዮጵያ ግዛት ሰጣሊያን አሳልፎ የሰጠ፣ ያፈጠጠ የመሬት ወረራ ነበር።

በተጨማሪ ነጥቦቹ ማስተካከያ ስምምነት መሠረት ኢትዮጵያ ከጣሊያን ላይ የ4 ሚሊዮን ሊሬ ብድር የምታገኝ ሲሆን ግማሹ በፊርማው ወቅት ለኢትዮጵያ የሚሰጥ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ ኢትዮጵያ ከጣሊያን ለምትገዛቸው ቁሳቁሶች የሚከፈል ይሆናል። የብድር ስምምነቱ የጣሊያንን ምርቶች ለኢትዮጵያ ለመሸጥ ያመቻቸ ሲሆን ለኢትዮጵያ ግን ሌላ አጣብቂኝ ፈጥሮባታል። ይኸውም ብድሩን ለመክፈል ራስ መኮንን ያቀረቡት አማራጭ የሐረር ከተማን የቀረጥ ገቢ ነበር። በመኾኑም በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ኢትዮጵያ ብድሩን ባትከፍል ጣሊያን ሐረርን በመያዝ ብድሯን እስክታሰመልስ ድረስ የሐረርን የንግድ ገቢ ትቆጣጠራለች።

በስምምነቱ የተጨመሩት ማስተካከያዎች ለጣሊያን ተስማሚ ቢኾኑም ለኢትዮጵያ ግን አደገኛ ነበሩ። በወቅቱ ኢትዮጵያ ስምምነቱን ለመፈረም አስገዳጅ አጣብቂኝ ውስጥ ነበረች። አገሪቷ በዙሪያዋ ከሚያንጎራብቡ አውሮፓውያን ሉዓላዊነቷን ለመጠበቅ በመታገል ላይ ነበረች። ከዚያም በላይ ደግሞ ባጋጠማት ድርቅ የተነሣ የእርሻ ምርቷ የተጎዳ ሲሆን የገንዘብ እጥረትም አጋጥሟት ነበር። በዚያ የተነሣም





ኢትዮጵያ ከጣሊያን ብድሩን በመውሰድ በምላሹ ጣሊያን ኤርትራን እንድታስተዳድር ዕውቅና ሰጠች።

ስምምነቱ ከጊዜ በኋላ ጣሊያን እና ኢትዮጵያን ያወዛገበ ቢሆንም ምኒልክም ኾኑ ራስ መኮንን ለጣሊያን ዕውቅና በመስጠት አስመራን እንድታስተዳድር ሲፈቅዱ ቦጎስ፣ ሃማሬን፣ እና አካለ ጉዛይንም ጭምር አሳልፈው ሰጥተዋል። በብድር ስምምነቱ መሠረት ጣሊያን ሐረርን ለመያዝ የሚያስችላትን መብትም አግኝታለች።

# ምዕራፍ ሰባት

## ‹‹ለአገሬ ውርደት›››

የጣሊያን አካሄድ የተለሳለሰ ቢመስልም ችግር ማስከተሉ አልቀረም ነበር። ‹‹ለአገሬ ውርደት የሆነ ተግባር እንደሆነ ደርሼበታለሁ›› አፄ ምኒልክ ለጣሊያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶ መስከረም 27 ቀን 1890 በጻፉት ደብዳቤ የጠቀሱት ነበር። ይህ ደብዳቤ የተጻፈው ከራስ መኮንን የዲፕሎማቶች ቡድን የጣሊያን ጉዞ አንድ ዓመት በኋላ ነበር።

ከደብዳቤው አንድ ዓመት በፊት በወርኃ ጥቅምት ምኒልክ ‹‹ንጉሠ ነገሥት›› ሆነው በአንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን በአቡነ ማቴዎስ ተቀቡ። በመቀጠልም ንግሥናቸውን ለማሳወቅ ለበርካታ የአውሮፓ መንግሥታት ደብዳቤ ፃፉ። እንግሊዝና ጀርመን በጥቅምት 1890 ለምኒልክ በጻፉት ምላሽ ኢትዮጵያ በሞግዚት አስተዳዳሪዋ ጣሊያን በኩል ከኹለቱ አገራት ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቷን ማድረግ እንደሚኖርባት አቋማቸውን አሳወቁ።

የኹለቱ አገራት ምላሽ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጣን አሥነሣ። ለመሆኑ ኢትዮጵያ በሞግዚት አስተዳደሩ ተስማምታለች? ይህ ጥያቄ የውጫሌ ስምምነትን ትርጓሜ ለመከለስ መንገድ ከፍቷል። ስምምነቱ በአማርኛ እና ጣሊያንኛ የተረቀቀ ሲሆን የስምምነቱ 17ኛው አንቀጽ በኹለቱ ቋንቋዎች የተለያየ ትርጉም ነበረው። አፄ ምኒልክ ለንጉሥ ኡምቤርቶ በጻፉት የተቃውሞ ደብዳቤ እንደገለጹት የጣሊያንኛው ቅጂ ኢትዮጵያ ከሌሎች አገራት ጋር ግንኙነት ማድረግ የምትችለው በጣሊያን መንግሥት አማካይነት እንደሆነ የሚደነግግ ሲሆን፣ የአማርኛው ቅጂ ግን ኢትዮጵያ ‹ከፈለገች› በጣሊያን በኩል ግንኙነት የማድረግ አማራጭ እንዳላት መጥቀሱን አስታውሰው ነበር። የእንግሊዝና ጀርመን ምላሽ በጣሊያን በኩል ለኢትዮጵያ ሲላክ ኹሉም ነገር ግልጽ ሆነ።





ብዥታው የታሰበበት ነበር? ለአድዋ ጦርነት መነሻ የሆነው የአንቀጽ 17 የትርጉም ስሕተት ወይም ‹‹የትርጉም መሰወጥ›› ሴራ እንደሆነ ግልጽ ነው። በአርግጥ ስምምነቱ በግልጽ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን ‹‹የሞግዚት አስተዳደር›› የሚል ቃል በየትኛውም አንቀጽ ውስጥ አልተጠቀሰም። ቃሉን የፈጠረው በአንቀጽ 17 የሰፈረው የቋንቋ አጠቃቀም ነበር።

የአንቀጽ 17ቱን የትርጉም ብዥታ አፄ ምኒልክ ቀድመው አልተረዱትም ለማለት ያስቸግራል። ምኒልክ የጀርመን እና እንግሊዝ ምላሽ በጣሊያን በኩል የደረሳቸው ስምምነቱን ከፈረሙ ከአንድ ዓመት በኋላ ነበር። የተቃውሞ ድምጽ ማሰማት የጀመሩትም ዘግይተው በመኾኑ ስለ አንቀጹ የትርጉም ስሕተት ሳያውቁ ያን ያህል መቆየታቸውን መቀበል ያስቸግራል።

ራስ መኮንን ስምምነቱን ሕጋዊ ለማድረግ በ1889 ክረምት ወደ ጣሊያን ባመሩበት ወቅት ‹‹የሞግዚት አስተዳደር (Protettorato)›› የሚለው ቃል በበርካታ የጣሊያን ጋዜጦች የፊት ገጽ ላይ ሰፍሮ ነበር። የራስ መኮንን የልዑካን ቡድን በጣሊያን ለበርካታ ሳምንታት በቆዩበት ወቅት የተፈጠረውን ግርታ ማጥራት ይችሉ ነበር። ራስ መኮንን እና ንጉሥ ኡምቤርቶ ተገናኝተው ሲነጋገሩም ‹‹የሞግዚት›› ግንኙነት ላይ አተኩረው ነበር። ራስ መኮንን ‹‹በንጉሠ ነገሥቴ ስም የእርስዎን ጥበቃ እጠይቃለሁ›› በማለት ሳቀረቡት የጥበቃ - ‹‹ሞግዚትነት›› - ጥያቄ ንጉሡ ኡምቤርቶ ሲመልሱ ፡- ‹‹ለአገርዎ ጥበቃ ለማድረግ በራሴ እና በመንግሥቴ ስም ቃል እገባለሁ።›› ብለው ነበር።

ራስ መኮንን በቀላሉ የሚታለሉ ዓይነት ሰው አይደሉም። በምኒልክ ቤተ-መንግሥት አካባቢ ራስ መኮንን ታማኝ እንዳልኾኑ የሚጠቅሱ መሰፍንት እና ጎበዛዝት ነበሩ። በምኒልክ እና ‹‹ወንድሜ›› በሚሏቸው ራስ መኮንን መካከል የነበረውን ወዳጅነት ስንመለከት ራስ መኮንን በምኒልክ ላይ ክሕደት ይፈጽማሉ ማለት

አስቸጋሪ ነው። ራስ መኮንን በአዲስ አበባ እና ሮም ዙሪት የተለያዩ ቃላት ተናግረው ይሆን? በዘመናዊው የጋዜጦች ታሪክ አንድ ዘገባ በዙሪቱም አገራት ሲገኝ እና ሊነበብ መቻሉን ስናስብ ራስ መኮንን ምኒልክን ለመክዳት ሮም ሳሉ ‹‹ሞግዚት›› የሚለውን ቃል ለመጠቀም የሚያሳስታቸው አይመስልም።

በሌላ በኩል የአንቀጽ 17ቱን የትርጉም ስሕተት ምኒልክ ሊጠቀሙበት አስበው በስሌት ተንቀሳቅሰውም ሊሆን ይችላል። በመኾኑም ራስ መኮንንን ወደ ሮም በመላክ ስምምነቱን ሕጋዊ በማድረግ እና የአራት ሚሊዮን ሊሬ ብድር ተቀብለው እንዲመጡ በማድረግ ከጣሊያን ጋር ወዳጅነታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ አሸጋገሩ። ከአንድ ዓመት በኋላ ሥልጣናቸውን አማክለው ኢትዮጵያን መግዛት ሲችሉ አፄ ምኒልክ ለዘውድ ካበቃቻቸው ወዳጃቸው ጣሊያን ተፅዕኖ ነፃ ለመሆን መንቀሳቀስ ጀመሩ።

ምኒልክ ተቃውሞአቸውን እንደተበደለ ወዳጅ በለስላሳ ቃላት ነበር ለጣሊያን ማለማት የጀመሩት። በወቅቱ የዘውድ ተቀናቃኞቸው የነበረውን ራስ መንገሻ ሙሉ በሙሉ እስኪያስወግዱ ድረስ ጣሊያንን ማስቀየም አልፈለጉም ነበር። ለዚህ ደግሞ ዋናው ምክንያታቸው የነበረው ጣሊያን በምፅዋ በኩል ለመንገሻ የጦር መሣሪያ እንዳታቀብል ማድረግ ነበር። ኃይላቸውን አጠናክረው መጪውን ለመቀበል ዝግጁ እስኪኾኑ ለአንድ ዓመት ያህል የውጫሌን ስምምነት ከመቃወም ታቀቡ።

በአፍሪካ የጣሊያን የጦር መሪ የነበረው አንቶኒዮ ባልዲሴራ የምኒልክን ስሌት ቀድሞ ነበር የተረዳው። አገሩ ጣሊያን አፄ ዮሐንስን ለማዳከም የምኒልክን ጉልበት ማፈርጠሚ ትክክል መኾኑን ነገር ግን የሳሊያንን ፍላጎት በኢትዮጵያ በዘላቂ ለማስፈጸም ሚዛን የሚያስጠብቅላት እና የምኒልክ ተፎካካሪ የሆነ ኃይል ማዘጋጀት እንዳለባት ነበር ሲናገር የቆየው።

የምኒልክ የረጅም ጊዜ ወዳጅ የነበረው ፒየትሮ አንቶኒሊ በበኩሉ የምኒልክ ሥልጣን መያዝ ለጣሊያን ጠቀሜታ እንደነበረው ያምን ነበር። ጣሊያን ስትደግፈው የነበረው ምኒልክ ሥልጣኑን ካደላደለ በኋላ በቀላሉ የምትፈልገውን ነገር ለማስፈጸም እንደምትችል ፒየትሮ ያምናል።





ባልዲሴራ የተለየ አመለካከት ነበረው። ምኒልክ ጣሊያንን በፒየትሮ አንቶኒሲ በኩል እንዳታለላት በመግለጽ አንዱ ሥልጣኑን ካደላደለ በኋላ ጣሊያንን ወደጎን እንደሚገፉት ተናገረ። በመኾኑም ጣሊያን በአንቀጽ 17 ላይ ስለተፈጠረው የትርጉም ስሕተት በማስረዳት ጊዜዋን ከምታጠፋ ይልቅ ምኒልክን የሚያዳክምላት የውስጥ ወዳጅ ማዘጋጀት ይበጃታል። ለዚህም የዮሐንስ ልጅ መንገሻ ጥሩ የጣሊያን ምርጫ ይሆናል። የባልዲሴራ ዕምነት የሮማውያን ዘመን መስፋፋት መርህ ‹‹ከፋፍለህ ውረር›› Divide et impera ዓይነት ነበር።

የባልዲሴራ አማራጭ ተቀባይነት አላገኘም ነበር። ጣሊያን ለበርካታ ዓመታት የሸዋውን ምኒልክ ስትረዳ ቆይታለች። ከራስ መንገሻ ጋር በመመሳጠር ምኒልክን ለማዳከም መሞክር በጣሊያን ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም። ምክንያቱም ከመንገሻ ጋር ለመመሳጠር ጣሊያን ከጦር መሪው ራስ አሉላ ጋር በጋራ መሥራት ይኖርበታል። የዶጋሊውን ሞፍጨፋ በመመልከትም ከአሉላ ጋር መሥራት ጣሊያንን ከፍተኛ የፖለቲካ አጣብቂኝ ውስጥ ይከታታል። ባጋጠመው ከፍተኛ ውጥረት የተነሣ በመጨረሻም ባልዲሴራ በገዛ ፍቃዱ ሥራውን ለቀቀ።

## የኤርትራ አፈጣጠር

በባልዴሴራ የተመራው የጣሊያን ሠራዊት በነሐሴ 1889 ያለምንም የተኩስ ድምፅ አስመራን በቁጥጥር ሥር አዋለ። በምሥራቅ አፍሪካ ታሪክ የተለየ ክስተት ከመፈጠሩ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ በወርኃ ታኅሳስ ጣሊያን ኤርትራን በቅኝ ግዛቷ ሥር ማድረጓን አስታወቀች። ‹‹ኤሪትሮስ›› የሚለው የግሪክ ቃል በመጠቀምም ለግዛቱ ‹‹ኤርትራ›› የሚል ስያሜ ሰጠች። የቃሉ ትርጉም ‹‹ቀይ›› ማለት ሲሆን ቀይ ባሕርን የሚወክል ነበር። ቃሉ የመካከለኛው ዘመን የሮማውያን ኃያልነት የሚያስታውስ ሲሆን አዲሲቷ ቅኝ ግዛት ኤርትራም የሮማውያን መነሣት እና ሕዳሴ ማሳያ ሆነች።

ባልዲሴራን በመተካት አስመራ የተቀመጠው ጀነራል ባልዴሴራ አሬሮ ለአፄ ምኒልክ እና ለኢትዮጵያ ወዳጅነቱን ለማሳየት መጣጣር የጀመረው ገና ከጅምሩ ነበር። ጥያቄው ግን ‹‹ምኒልክ የአሬሮን ወዳጅነት ይፈልጉ ነበር?›› የሚለው ነው። የምኒልክን ልብ ለማግኘት ይጣጣር የነበረው አሬሮ ወዳልተረጋጋው የትግራይ ግዛት በመዝመት ቀጠናውን አረጋግቶ ምኒልክን ለማስደሰት ዐቀደ። ሰርም በጻፈው

ደብዳቤም ወደ ትግራይ በመዝመት የዮሐንስ መቀመጫ የነበረችውን አድዋ ተቆጣጥሮ ምኒልክን ሊጠብቃቸው ማሰቡን ገለጸ። ዕቅዱ የጣሊያንን ዐቅም እና ወዳጅነት ለምኒልክ ለማሳየት እንደሚያስችል ገምቶ ነበር። እንደታቀደው ከተሳካም ምኒልክ በታሪካዊቷ ቅድስት ከተማ አክሱም ዘውዳቸውን የሚጭኑ ይሆናል።

ሮም ለጀነራሉ በጻፈችው ምላሽ ኤርትራ ላይ ምሽጉን እንዲያጠናክር ብትገልጽም ጀነራሉ ኤርትራን ለመከላከል የተሻለው አማራጭ ትግራይን መያዝ እንደሆነ ሰሮም በጻፈው ምላሽ አሳወቀ። በዚያ ጊዜ ነበር አንቶኔሊ ለበርካታ ዓመታት ምኒልክን በማለሳለስ የገነባው ወዳጅነት አደጋ ላይ ሊወድቅ መኾኑን የተረዳው። በዚያው ፍጥነት ጀነራሉ እንዳቀደው ወደ ትግራይ የሚዘምት ከሆነ ሥራውን በፍቃዱ ሊለቅ እንደሚችልም አንቶኔሊ ተናገረ። ነገር ግን ጀነራል ኦሬሮን ያስቆመው አልነበረም። የሚቀጥለው የኦሬሮ ደብዳቤ ሰሮም የተጻፈው ጥር 26 ቀን 1890 ከአድዋ ከተማ ነበር።

ጣሊያን የኤርትራ ቅኝ ግዛት መፈጠሯን ባወጀች በአንደኛው ወር የኦሬሮ ወደ አድዋ መዝመት አደገኛ ውጥረት ፈጠረ። መላው ኢትዮጵያዊ ዜጋ የጣሊያንን የመስፋፋት እንቅስቃሴ አውቋል። አፄ ምኒልክ ለጣሊያን ያሳዩትን መለሳለስም መቃወም ጀምሯል። አፄ ምኒልክ በጣሊያን ኹለንተናዊ ድጋፍ የዮሐንስን ዘውድ ለመውረስ ቢችሉም በመጨረሻ የጣሊያን ጉዳይ አስፈጻሚ መሆናቸውን አልተቀበሉም። ኦሬሮ እንዳቀደው ወደ አክሱም በማምራት የንግሥና ሥርዓታቸውን በጀነራሉ ድጋፍ ቢፈጽሙ ኖሮ ከሕዝባቸው ሊነሳባቸው የሚችለውን ተቃውሞ ገምተዋል። በመኾኑም ወደ ትግራይ በመሄድ ከጣሊያን ሠራዊት ጋር የመገናኘት ዕቅዱን አነሱ።





አፄ ምኒልክ የጣሊያንን ስሌት በሴላ መንገድ ለመጠቀም ወሰኑ። የኦሬሮ ሠራዊት ትግራይን በማረጋጋት እና ራስ መንገሻን በማስፈራራት ቢረዳቸው መልካም መኾኑን በማስላት ከጣሊያን ጋር ያላቸውን ግንኙነት በሰሱ ለመያዝ መጠንቀቅን መረጡ። በመኾኑም የጀነራል ኦሬሮን ሠራዊት ለመገናኘት በሚመስል መንገድ ወደ ትግራይ ጉዞ ጀመሩ። በዘግታ ያደረጉት የትግራይ ጉዞ በእንዳርታ በኩል ነበር ያለፈው። በእንዳገድ የትግራይ አካባቢዎች ወታደሮቻቸውን ላለመቀሰብ ከተቃወሙ የትግራይ ገበሬዎች መጠነኛ ተቃውሞም ያጋጠማቸው ምኒልክ በተደጋጋሚ የወሰዱት እርምጃ የማያዳግም ነበር። በተቃዋሚ ገበሬዎች ላይ የወሰዱት እርምጃም ለመንገሻ የሚፈልጉትን መልዕክት አስተላልፎላቸዋል።



ራስ መንገሻ ከደቡብ አቅጣጫ በመገስገስ ላይ ባለው የምኒልክ ሠራዊት እና ከሰሜን እየተጠጋው በነበረው የጣሊያን ጦር መካከል መኾኑን ዐወቀ። ለመዋጋት ቢሞክር የሚያጋጥመውን አደጋ በመገመትም እጁን ለመስጠት ወሰነ። በ300 ወታደሮቹ ታጅቦ ወደ ትግራይ በመገስገስ ላይ ወደነበሩት አፄ ምኒልክ በመሄድም ድንጋይ ተሸክሞ እጁን ሰጠ። የመንገሻ መዝበርከክ የዮሐንስን ዘውድ ለመውረስ የነበረው ሽኩቻ ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ በምኒልክ አሸናፊነት መጠናቀቁን አመላከተ።

ጀነራል ኦሬሮ በአንባሩ አደጋ ላይ ወደቀ። ከአንቶኔሊ ጋር ከፈጠረው ልለመግባባት በተጨማሪ አልታዘዝ ባይነቱ ከኃላፊነቱ እንዲነሳ አደረገው። በወርኃ ሰኔ ኦሬሮን በመተካት ኦሬስቴ ባራቴሪ ወደ ኤርትራ መጣ። ተተኪው ባራቴሪ የጣሊያን ቅኝ ግዛት የወታደራዊ እና የሲቪል አስተዳዳሪ በመሆን ነበር የተሾመው።

*ምስል፦ ኦሬስቴ ባራቴሪ*



ምስል፡- ኦሬሎቱ ባራቲሪ

ኡምቤርቶ ባራቴሪ በአስትሪያ እጅ በነበረችው የሰሜን ጣሊያኗ ግዛት ትሬንቲኖ በ1841 ተወለደ። የወሥራ ሰባት ዓመት ልጅ ሳለ የጁሴፔ ጋሪባልዲን ‹‹ቀይ ሰባሽ›› ሠራዊት ተቀላቅሎ የሲሲሊን ግዛት ከጣሊያን ጋር ለመቀላቀል በተደረገው ውጊያ ተሳተፈ። በወታደራዊ ሥራው ስኬታማ መሆን የቻለው ኡምቤርቶ ቬኒሺያን ከአስትሪያ ነፃ ለማውጣት በተደረገው ውጊያም ተሳትፏል። በ1876 የጀነራልነት ማዕረግ ካገኘ በኋላ የጣሊያን ብሔራዊ ምክር ቤት አባል መሆን ቻለ። ወደ ኤርትራ ተሹሞ ሲመጣ ዕድሜው 35 ዓመት ገደማ ይሆን ነበር።

ባራቴራ በሰሜን አፍሪካ በነበረው የጣሊያን ሠራዊት ውስጥ በማገልገል ላይ ሳለ ነበር የጣሊያን የተስፋፊ ውጣቶች መፈልፈያ የነበረውን ‹‹የጂአግራፊ ማህበር›› የተቀላቀለው። በግሉ የቤልጂየሙ ንጉሥ ሊዎፖልድ አድናቂ የነበረ ሲሆን ንጉሡ በ1880ዎቹ ኮንጎን በመውረር አንዲት ትንሽ አውሮፓዊ አገር ሰፊ ግዛተ-አፄ መገንባት እንደምትችል ያሳዩበትን አጋጣሚ ያደንቃል።

ባራቴሪ ጥልቅ አንባቢ ነበር። ምፅዋ በደረሰበት ወቅት በአስተዳዳራዊ ሥራው ከኢትዮጵያ የሚገጥመውን ብርቱ ተቃውሞ እና ግፊት ሰመቋቋም የሚችልበትን መንገድ አጥንቶ ጨርሶ ነበር። ሥልጣኑን እንደተረከበም በኤርትራ የነበሩ የጎሳ መሪዎችን ሰብስቦ አገሩ ጣሊያን ከራስ መንገሻም ሆነ ከአፄ ምኒልክ ብዝበዛ በተለየ መልኩ የተሻለ አስተዳደር እንደሆነች ለማሳመን ጥሯል።

ባራቴሪ ለሥልታዊ መግቢያነት የተጠቀመው መንገድ በሽፍታነቱ ይታወቅ ከነበረው ባጎታ ሐጎስ ጋር ወዳጅነትን መፍጠር ነበር። ባጎታ ከምጽዋ ወደ መሐል አገር ይደረግ በነበረው ንግድ እንቅስቃሴ ላይ የዘረፋ ተግባር ይፈጽም ነበር። በአፄ ቴዎድሮስ እና አፄ ዮሐንስ ዘመን የዘረፋ ሥራው ተቃውሞ ገጥሞት ነበር። የጣሊያን መምጣት ከኢትዮጵያ ነገሥታት ደጋጥመው የነበረውን ተቃውሞ በተወሰነ ደረጃ ቀንሶለት ነበር። ባራቴሪም ሽፍታውን ባህታ በማግባባት ወዳጁ በማድረግ የሰንሃይቲ አካባቢ አስተዳዳሪ እንዲሆንም ሾመው።





ሹመቱ ሰባህታ የኢኮኖሚ እና ወታደራዊ ኃይል ጨመረለት። ለአገልግሎቱ ክፍያ ይሆን ዘንድም ከሚያስተዳድረው ግዛት ከሚሰበሰበው ግብር ዐሥር በመቶውን እንዲወስድ ባራቴሪ ፈቀደለት። ባህታ የካቶሊክ ዕምነት ተቀብሎ እንደነበርም ይነገራል። ጣሊያን ይዞታዋን ካጠናከረችባቸው መንገዶች መካከል አንዱ የነበረው የተለያዩ የጎሳ መሪዎችን እና የግዛት አስተዳዳሪዎችን ወደ ካቶሊክ ኃይማኖት ተከታይነት መቀየር ነበር።

## የሰፈራ ቅኝ ግዛት በኤርትራ

ጎዳር 10 ቀን 1893 በድምሩ እምሳ አባላት ያሏቸው ዘጠኝ የጣሊያን ቤተሰቦች ኤርትራ ደረሱ። የሰፋሪ ጣልያናውያን ኤርትራ መድረስ ጣሊያን በማደግ ላይ የነበረው ሕዝቧን የምታሰፍርበት የውጪ ግዛት ማግኘቷን አመላካች ነበር። ጣሊያን ኤርትራ የቅኝ ግዛቷ መሆኗን ካወጀች ከአንድ ዓመት በኋላ በ1891 የጣሊያን የፓርላማ አባላት ምፅዋን በመጎብኘት ኤርትራ ጣሊያናውያንን ለማሰፈር አመቺ መሆኗን አረጋግጠው ተመለሱ። ዘመኑ በየዓመቱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አውሮፓውያን ወደ ብራዚል፣ አርጀንቲና እና አሜሪካ በመሄድ አዲስ ሕይወት እንዲጀምሩ የአውሮፓ መንግሥታት የሚያበረታቱበት ነበር። ጣሊያንም ዜጎቿን በአዲሷ ቅኝ ግዛት ኤርትራ ለማስፈር ተዘጋጀች። የሰፈራ ፕሮግራሙ ዋና አቀንቃኝ የነበረው የፓርላማ አባል ሲዎፖልዶ ፍራንቼቲም ይህንኑ አቋም ማራመድ ጀመረ።

የጣሊያን መንግሥት መሬት የሌላቸውን ገበሬዎች በመደገም በኤርትራ እንዲያሰፍር ፍራንቼቲ ሃሳብ አቀረበ። ሰፋሪዎቹ በኤርትራ ሰፋፊ የእርሻ ሥራ በማከናወንም ለጣሊያን የምግብ እና የፋብሪካ ግብዓት አቅራቢ መሆን እንደሚችሉም ጨምሮ አቀረበ። ከተወሰኑ ባለሥልጣናት ጥቂት ተቃውሞ ቢገጥመውም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን የፍራንቼቲ ሃሳብ በጣሊያን መንግሥት ተቀባይነት አገኘ።

የጣሊያን መንግሥት በፍጥነት የሰፈራ ፕሮግራሙን ጀመረ። አንድ የጣሊያን ገበሬ ቤተሰብ ለአምስት ዓመት በተከታታይ የሚያርሰው ሐያ ሄክታር መሬት በኤርትራ እንደሚሰጥ በመጥቀስ ቅስቀሳው ተጀመረ። ሰፋሪዎቹ ወደ ኤርትራ የሚያደርጉትን የጉዞ ወጪ መንግሥት የሚሸፍን ሲሆን የዘር፣ የእርሻ መሣሪያ፣ ተሰብ-እና መኖሪያ ቤትም እንዲሁ ተዘጋጅቶላቸው ነበር። የመጀመሪያ ዓመት ምርታቸውን እስኪያገኙ ድረስም በአነስተኛ የወለድ መጠን የጣሊያን መንግሥት ብድር ሰማቅረብ ቃል ገባ።

የሰፈራ ፕሮግራሙ አስተባባሪ የነበረው ፍራንቼቲ ከ1893 እስከ 1895 ባሉት ዓመታት ለእርሻ አመቺ የሆነ አራት መቶ ሺህ ሄክታር መሬት በኤርትራ ዝግጁ አደረገ። በመሬት ዝግጅቱ ወቅት የበርካታ ኤትራውያን የመሬት ይዞታ ተቀነሰ። የመጀመሪያዎቹ ሰፋሪዎች ከኹለት የጣሊያን መንደሮች ነበር የተመረጡት። ሰባቱ የሰፋሪ ቤተሰቦች ሉምባርድ ግዛት ከምትገኘው ማኔንታ መንደር የመጡ ሲሆን የቀሩት ኹለት ቤተሰቦች ደግሞ የሲሲሊ ግዛት አካል ከሆኑት ፔዳራ እና ካታንያ መንደሮች ነበር የመጡት።

ከአስመራ በስተደቡብ ሠላሳ ማይል ርቃ የምትገኘው አዲ ኡግሪ የመጀመሪያዋ የሰፈራ መንደር ሆና ተመረጠች። ለመንደሯ ‹‹ኡምቤርቶ አንድ›› የሚል ስም ተሰጣት። ሰፋሪዎቹ እንደደረሱ ለእያንዳንዳቸው ኹለት የሳጅ ቤቶች፣ ስምንት የቀንድ ከብቶች፣ ዐሥር ዶሮ እና አንድ የአሳማ ግልገል ተሰጣቸው። ዘጠኙ ሰፋሪ ቤተሰቦች በቤታቸው አቅራቢያ የተዘጋጀላቸውን መሬትም ተረከቡ። ኡምቤርቶ የሰፋሪዎች መንደር በወርኃ ግንቦት 1893 ሲመረት የመሬት ጠረጋ እና የመስኖ ቦይ ሥራ ተጠናቆ የነበረ ሲሆን የወይን እና ቡና ችግኝ ተክሳ ተጀምሮ ነበር።

በምርቃት ሥነ-ሥርዓቱ ዕለት ትልቅ ድንኳን ተጥሎ ነበር። ከጣሊያን ወታደሮች ጋር ወደ ኤርትራ የመጡት የካቶሊክ ቄስ አባ ቦኖሚ ሰፋሪዎች የሚጥጥማቸውን ችግር በፈጣሪ ጸጋ እንዲቋቋሙ በማበረታታት የእርሻ መሬት እና





መኖሪያ ቤታቸውን ባረከላቸው። ከጥቂት ሳምንታት ቡኋላ በሰኔ ወር የመጀመሪያዋ የኤርትራ የሰፋሪዎች ልጅ ሮዛሊያ ኦልዛኒ ተወለደች።

የሰፈራው ፕሮግራም ተቃውሞ የገጠመው ወዲያውኑ ነበር። በደቡብ ጣሊያን የነበሩ ገበሬዎች መንግሥታቸው በትኛ ግዛት ለሰፈሩ ገበሬዎች የሚያደርገው ድጎማ ፍትሐዊ አለመኾኑን በመናገር ተቃውሙ። ኹለተኛው ተቃውሞ የተነሣው ደግሞ ከመሬታቸው በተፈናቀሉ የኤርትራ ደጋማ አካባቢ ነዋሪዎች ነበር።

በወቅቱ በከብት በሽታ ምክንያት የተነሣው ረኃብ የበርካታ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎችን ሕይወት አመሰቃቅሉ ነበር። ሸዋን በኩል ከሕንድ ከገቡ ከብቶች የተነሣው ወረርሽኝ ከ1888 እስከ 1892 የበርካታ ገበሬዎችን እና ከብቶቻቸውን ሕይወት ቀጥፏል። በበርካቶች ግምት ከአንድ አስረኛ እስከ አንድ ሦስተኛ የሚደርስ መጠን ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ በበሽታው እና በሽታው ባስከተለው ርሃብ አልቋል። ከወቅቱ መጠነ ሰፊ ተውሰ ለማየትም በመታገል ላይ የነበረው ደገኛ ገበሬ ለም መሬቱ ተነጥቆ ለነጭ ሰፋሪዎች መሰጠቱን ተቃወመ።

ፍራንሲስኮ ክሪስፒ ለወታደራዊ አታቹ ክርም ባስተላለፈው መልዕክት ሠራዊቱ መሬቱን በመተው ሰፋሪዎችን ከዋታት እንዲከላከል አዘዘ። ቀድሞ የነበረው የክሪስፒ ፅቅድ ሰፋሪዎችን በማስታጠቅ የጣሊያን ገበሬ ሠራዊትን በኤርትራ ማደራጀት ነበር። በፅቅዱም ገበሬ ሠራዊቱ መሬቱን እና ኤርትራን እንደሚጠብቅ ተስፋ አድርጎ ነበር። ፅቅዱን የተረዱ የኢትዮጵያ ገበሬዎች ሰማመፅ ጊዜ አልወሰዱም ነበር።

የኤርትራው ተቃውሞ በሸዋ ከተደረገ አንድ ሥነ-ሥርዓት ጋር ታሪካዊ መገጣጠም ነበረው። ምርኮኛው ልዑል መንገሻ እና አዝማቹ ራስ አሉላ አዲስ አበባ የሚገኘው የምኒልክ ቤተ-መንግሥት የደረሱት ሰኔ 2 ቀን 1894 ዓ.ም ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ላይ ነበር። እጃቸውን በሰጡበት ወቅት እንዳደረጉት ኹሉ ወደ ምኒልክ ቤተ-

መንግሥት ግቢ ሊቃረቡ ድንጋይ በትከሻቸው ተሸክመው ነበር። መንገሻ ወደ ምኒልክ መንበር ሊቃረብ በግንባሩ ተደፍቶ ሰላምታ ሲሰጥ በግቢው የነበሩ የምኒልክ ወታደሮች ወደ ሰማይ በመተኮስ የንጉሣቸውን ድል አደመቁ።

የዕለቱ ንጉሣዊ ሥነ-ሥርዓት የዘመናዊት ኢትዮጵያን መፈጠር የመጨረሻ ምዕራፍ የዘጋ ነበር። ምክንያቱም በመንገሻ ሥር የነበረው የትግራይ ግዛት ከሸዋ ጋር የተጠቃለለበት አጋጣሚ ነበር። በጣሊያን እና በምኒልክ ተከብቦ የነበረው መንገሻ ምንም አማራጭ ስላልነበረው ግዛቱን ሰንጉሥ ነገሥቱ አስረከበ። በዚያው ዓመት መጨረሻ ነበር በኤርትራ ጣሊያን ላይ ተቃውሞ መነሣት የጀመረው።



Francesco Crispi. From John Grand-Carteret, *Crispi, Bismarck et la Triplice: allegeance en caricatures*. Paris: C. Delagrave, 1891.

*ምስል፦ ፍራንሲስኮ ክሪስፒ (ፓሪስ 1891)*





**ባሕታ ሓጎስ እና ልዑል መንገሻ፦ ከነጭ እባብ ጋር የተደረገ ግብግብ**

በክሐሴ 1894 በእንዱ ምሽት ባህታ ሓጎስ ሰገነይቲ በነበረው የጣሊያን አስተዳዳሪ መኖሪያ ቤት ራት ተጋብዞ ተቀምጧል። ገበታው ከፍ እንዳለ ባህታ እና ግብረአበሮቹ ቤቱን ለቀው መውጣት እንደጀመሩ ወደኋላ በመመለስ ጋባዡን ጣሊያናዊ በማነት ከወንበር ጋር አሠሩት። ‹‹ገደል ግባ ጣሊያን አሁንም ታሳቅ ናት!›› በማለት ጣሊያኑ ባህታ ላይ ጮኸበት። ባህታም ‹‹ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ታሳቅ ናት!›› በማለት ታጋቹ ላይ ጮኸበትና ወዲያውኑ ተኩሶ ገደለው። እገሩን በመክዳት፣ ሃይማኖቱን በመቀየር እና የጣሊያን አሽከር በመሆን ይታወቅ የነበረው ሽፍታው ባህታ በመጨረሻም አገሩን መረጠ።

የባህታ ወታደሮች ኹለት የጣሊያን ቴሌግራፍ ባለሙያዎችን አግተው ወሰዱ። ለታጋቾቹ ‹‹ከእናንተ ጋር የግል ፀብ የለኝም›› በማለት ባህታ ተናግሮ ነበር። ጣሊያን ለሰፋሪ ዜጎቿ ሰም የእርሻ መሬት ለማቅረብ ስትል የአገሬውን ሰው ማፈናቀሏ ነበር ታማኟ ባህታን እንዲያምፅ ያደረገው። ከመሬቱ ቡተጨማሪም በርካታ የኤርትራ ሴቶችንም በማስገደድ እና በማማለል የወታደሮች ቅምጥ ‹‹ማዳማ›› ማድረጓ ነበር ያስቀጣው። በኢትዮጵያ ማህበራዊ ሥርዓት ለዘመናት የቆየ ዕምነት አለ። ይኸውም የአገሬው ሰው በአገሩ፣ በሴቶቹ እና በመሬቱ ከመጡበት አለመመለሱ ነበር።

የነጭ የዘር መድልዎ በግልጽ የታየበት የጣሊያን አካሄድ በርካታ የባህታ ወገኖችን አስቆጣ። ባህታ ለዘረኝነቱ ምላሽ ሲሰጥም ‹‹ነጭ እባብ ከነደፈህ መድኃኒቱንም ማግኘት ቀላል አይደለም›› በማለት ተናግሮ ነበር ሕዝቡን ለአመፅ ያነሳሳው።

በአመፁ ሦስተኛ ቀን በጀነራል ፒየትሮ ቶሴሊ የሚመራ አንድ ሺህ አምስት መቶ የጣሊያን ወታደር ወደ ሰገነይቲ ተንቀሳቀሰ። ባህታ ለመከላከል ያሰለፈው ሠራዊት ከሰባት መቶ በታች ነበር። ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመቱ ቀላል



ccesso Crispi. From John Grand-Carteret, *Crispi, Bismarck et la Triplice en caricatures*, Paris, C. Delagrave, 1891.

ምስል፡- ፍራንሴስኮ ክሪስፒ (ፓሪስ 1891)

ነበር። ታጋቾችን በነፃ በመልቀቁ ዘውትር ይመሰገን የነበረው ባህታ ከጣሊያን ጋር ባደረገው የአመፅ ውጊያ ሃላይ በተባለ ቦታ በበርካታ ጥይት ተደብድቦ ሞተ። ከባህታ ሞት በኋላ የአገሬው ሕዝብ ትግሉን ሊያስቀጥለው የሚችል መሪ በማጣቱ ቂሙን በልቡ በመያዝ አመፁን ሰጊዜው አቆመ።

የባህታ ሞት በተሰማ በማግስቱ መንገሻ ጦሩን ከአድዋ በስተምሥራቅ ወደምትገኘው ኢንጪቾ አዘመተ። በወቅቱ ቁጥሩ ወደ ዘጠኝ ሺህ የሚጠጋውን ጦር ሲያዝምት መንገሻ ለሸፋን የተጠቀመው ‹‹ሙስሊም ደርቪሽ›› እየመጣ በመሸኑ ኢንጪቾ ላይ ሊመሸግ እንደሆነ ነበር። ነገር ግን መንገሻ በቀጥታ ያመራው በአቅራቢው ወደ ነበረው የጣሊያን ምሽግ ነበር።

አፈስቱ ባራቴሪ የመንገሻን መምጣት እንደሰማ ነበር ፀ ሺህ አባላት ያሉት ሠራዊቱን ወደ ደቡብ አቅጣጫ ያዘመተው። መንገሻ ያለ ምንም በቂ መከላከያ የተዋትን የአድዋ ከተማ ታኅሳስ 28 ቀን በቀጥጥሩ ሥር አዋለ። የከተማው ነዋሪ መንገሻ ያለ ምንም ጠባቂ ስለተወው በማኩረፉ የኤርትሬን ሠራዊት ያለምንም መከላከል ነበር ያስገባው። በተለይ ቀሳውስት እና ካህናት ለኦፈስቲ ያሳዩት የወዳጅነት አተባበል ያልተጠበቀ ነበር።

የአድዋን መያዝ የሰማው የመንገሻ ጦር ከነበረበት ቦታ ለመንቀሳቀስ አልሞከረም ነበር። ባራቴሪ እንዳደረገው ሹሉ መንገሻም አድዋን በመተው በቀጥታ ወደ ኤርትራ በመግባት ምፅዋን ጨምሮ አጠቃላይ ኤርትራን መያዝ ይችሉ ነበር። መንገሻ ያንን ማድረግ ቢችል ኖሮ አዞ ወዳጅነቱን በማስመስከር የአጡትን ዘውድ ለመውረስ ቢጣጣር የሕዝብ ድጋፍ ማግኘት ይችልም ነበር።

አፄ ምኒልክ ዘንድ የደረሰው ጭምጭምታ መንገሻ የባራቴሪን ጦር ደምስሶ ወደ ምፅዋ እየገሰገሰ መሸኑ ነበር። በእርግጥ ይህ ተራ ወሬ ነበር። ባራቴሪ በአድዋ ለሦስት ቀናት ከቀየ በኋላ መንገሻ ወደ ኤርትራ ለመንቀሳቀስ መዘጋጀቱን ሲሰማ





ጦሩን ወደ መጣበት መለሰ። በመልስ ጉዞው ከመንገሻ ጋር ላለመናናት የቻለውን ጥንቃቄ አድርጓል። ምክንያቱም የመንገሻን ጦር ፊት ለፊት ለመግጠም በቂ ኃይል አልነበረውም። በኹለቱ ጦር አስላለፍ መሠረት ኹለት የመንገሻ ወታደር ለአንድ የባራቴሪ ወታደር ሊደርስ ይችላል።

ጥር 12 ቀን 1895 የባራቴሪ ሰላዮች የመንገሻ ጦር ክአቲት ላይ መመሸጉን ደረሱበት። የመንገሻ ሠራዊት የጠላት ጦር መጠጋቱን ባላወቀበት ሁኔታ ነበር በማግስቱ ጦርነቱ የተጀመረው። ቢጦርነቱ እሽናፊ ባይኖርም በመንገሻ በኩል በርካታ ወታደሮች ሞተዋል። ጥር 14 ምሽት ላይ መንገሻ ቀሪውን ሠራዊት አስከትሎ በጭለማ ወደ አድዋ አፈገፈገ። ጥር 15 ባራቴሪ የመንገሻን ምሽግ ሲቆጣጠር አንድም የመንገሻ ሠራዊት አላጋጠመውም።

ባራቴሪ በዚያው ቅፅበት መንገሻ ያመለጠበትን መንገድ ይዞ ወደ ኋላ ተመለሰ። የመንገሻን ጦር በማሳደድም በማግስቱ እኩለ ቀን ላይ ሰንአፈ ላይ ደረሰበት። የጣሊያን መድፍ የመንገሻን ካምፕ ሙሉ በሙሉ ደበደበ። የመንገሻ ማረፊያ የነበረውን ድንኳን ሳይቀር አቃጠሉት። መንገሻም የተረፉ ወታደሮቹን አስከትሎ ሸሸ።

በመድፍ ከተቃጠለው የመንገሻ ማረፊያ ድንኳን የተገኘው የግል ማሕደር ለባራቴሪ ቀጣይ እርምጃ መንገድ ጠቋሚ ነበር የሆነለት። ቀጣይ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ግን የካቲት 1 ቀን 1895 ከመንገሻ ደብዳቤ ደረሰው። ደብዳቤው የይቅርታ ይዘት ያለው ሲሆን ‹‹ሰይጣን አሳስቶኝ እንጂ ኢትዮጵያን የመውረር ሃሳብ አልነበረኝም›› በማለት ነበር መንገሻ ባራቴሪን ይቅርታ የጠየቀው።

መንገሻ ለማስተባበል ቢሞክርም ባራቴሪ ግን የመንገሻን ተከሳሽነት ሴራ ብሎርኮ ካገኘው የግል ማህደሩ ውስጥ አግኝቷል። በማህደሩ ከነበሩት በርካታ መረጃዎች መካከል ምኒልክ እና መንገሻ የተለዋወጧቸው ደብዳቤዎች ይገኙ ነበር።

በአንዱ ደብዳቤው አፄ ምኒልክ ‹‹ጠላቴ›› ሲሉ የገለጻቸውን ጣሊያኖች እንዲያጠቃ መንገሻን መላካቸው ታወቀ። ከዚህ በተጨማሪም ባህታ ሓጎስ አመፅ ጀርባ ምኒልክ እና መንገሻ እንዳሉበት ባራቴሪ አረጋገጠ። በአጠቃላይ ጣሊያኖች ደጋፈው ለሥልጣን ያበቃቸው አፄ ምኒልክ ከአሻቸው እንደወጣ አረጋገጠላቸው።

ጣሊያን የምኒልክ ኃይል ለመጠባበቅ እንዲያስችላት መንገሻ እና አሉላን በምኒልክ ላይ ለማሥነሳት ዐቅዳ ነበር። ነገር ግን መንገሻ ምኒልክን መምረጡን ካረጋገጠች በኋላ ዕቅዷን ሰርዛለች። በባራቴሪ ከተደበደበ በኋላ መንገሻ ጦሩ በመጫከሙ የአንድ ተራ ሽፍታ ያህል እንኳን ጥንካሬ አልነበረውም። የመንገሻ መጫከም ለጣሊያን አንድ ጠላት ቢቀንስላትም በሌላ በኩል ግን ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ በምኒልክ ዘውድ ሥር መጠቃለል ቻለች።

ባራቴሪ መንገሻን ለመውጋት ያወጣው የጦር ወጪ በአጠቃላይ ከ10 ሺህ ፓውንድ (ግማሽ ሚሊዮን ሊሬ) በታች ነበር። የጦር ወጪውን አነስተኛ ካደረጉለት ምክንያቶች መካከል አንዱ የነበረው ባራቴሪ በርካታ አፍሪካዊ አስካሪ ወታደሮችን በአነስተኛ ደሞዝ ቀጥሮ በማዋጋቱ ነበር። ከገንዘቡ በተጨማሪ የሚችን አውሮፓውያንም ቁጥር አነስተኛ ለማድረግ ችሉ ነበር። ሰሮም በጻፈው ደብዳቤ እንደገለጸው በአጠቃላይ ዐሥራ አንድ ወታደር ሲሞትበት ሠላሳ ደግሞ ቆስለውበታል። ከሚቾቹ መካከል ነጭ ወታደር አለመኖሩንም ጠቅሶ ነበር።

ባራቴሪ በ1894 እና ዮ1895 በአነስተኛ የገንዘብ ወጪ እና መስዋዕትነት ያገኛቸው ድሎች የኢትዮጵያን ጦር ዝቅ አድርጎ እንዲመለከት አድርጎታል። ባህታን እና መንገሻን ማሸነፉ የምኒልክን ጦር አሳንሶ እንዲመለከት አስቻለው። የተሳሳተ የጣሊያን ግምት በከፍተኛ ዝግጅት ላይ ለነበሩት አፄ ምኒልክ መልካም ዕድል እንደሆነላቸው የታየው በአድዋው የውጊያ ውሎ ነበር።





## ባራቴሪ የኢትዮጵያን ድንበር ጣሰ

በአነስተኛ ድሉ የተኩራራው ባራቴሪ ትግራይን በመውረር ኤርትራን በዘላቂነት ከኢትዮጵያ ጥቃት ለመከላከል የሚያስችለውን ቦታ ለመያዝ ተዘጋጀ። ከአድዋ እስከ አዲግራት የተዘረጋውን ተራራማ ይዞታ ለመውረርም ዕቅድ አወጣ። ትግራይን መውረሩ ከአፄ ምኒልክ ምን ሊያስከትልበት እንደሚችል ሳያስብ ነበር የካቲት 3 ቀን 1895 አዲግራትን በቁጥጥሩ ሥር ያዋላት።

አዲግራት በአፍሪካ ከፍተኛ ሥፍራ ላይ ከሚገኙ ጥቂት ከተሞች አንዷ ናት። ከከተማዋ በምሥራቅ አቅጣጫ ያሉ ወንዞች ወደ ቀይ ባሕር የሚገቡ ሲሆን በምዕራብ ያሉት ደግሞ የዓባይ ገባር ናቸው። ከተማዋ የአጋሜ ምድር ማዕከል ስትሆን ተስማሚ አየር እና ጥሩ ወታደራዊ ጠቀሜታ አላት። ጣሊያን በ1895 አዲግራትን መያዝ ከፍተኛ ጠቀሜን አስገኝቶላታል።

ከአዲግራት ምዕዋ ያለው ርቀት አነስተኛ መሆን በራሱ ለጣሊያን መልካም ነበር። በአጠቃላይ ከምዕዋ ጀምሮ ጊንዳ፣ አስመራ፣ ጎራ፣ ከሉቲት፣ ሰንአፈ፣ ባራኪት እና አዲግራት ላይ ጣሊያን ጠንካራ ምሽግ ገነባች። ከወታደራዊ ጠቀሜታዋ በተጨማሪ አዲግራት ለጣሊያን የሰፈራ ቅኝ ግዛት ተመራጭ ቦታ መሆኗን ባራቴሪ ሰሮም በጻፈው ደብዳቤ ገልጿል።

አዲግራትን ከተቆጣጠረ በኋላ ባራቴሪ ሊያሳካ ያልቻለው ነገር ቢኖር መንገሻን መያዝ ነበር። ጦሩን እስከ መቀሌ በመላክ ቢያሳድም መንገሻ ግን አልተገኘም። ባራቴሪ የራሱን ጦር በመምራት ወደ ምዕራብ ዘምቶ ከአድዋ እስከ አክሱም አሰሰ። ወደ ደቡብ እስከ አምባላጌ ድረስም እንዲሁ። እግረ መንገዱንም ለአሰሳ የወጣቸውን ቦታዎች በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ የጣሊያንን ቅኝ ግዛት አሰፋ። ነገር ግን ተጨማሪ ቦታዎችን በያዘ ቁጥር የአስተዳደር ቁጥጥሩ እየላላ ኤርትራም ያለ ጠንካራ መከላከያ ለኢትዮጵያ ወረራ ቀላል እየሆነች መሆኗን ባራቴሪ የተረዳው ቆይቶ ነበር።

አዲስ የተያዙ የትግራይ አካባቢዎች ለሰፈራ አመቺ እንደሽኑ የተመለከተው ባራቴሪ መሬቱን በሹሰት መንገድ ለሰፈራ ማመቻቸት ጀምሮ ነበር። የተሻለ ለምነት ያላቸውን ቦታዎች ለጣሊያን ዜጎች እንዲሁም መለስተኛ የሽኑትን ለቅጥረኛ ‹‹አስካሪ›› ወታደሮች በማከፋፈል በዚያውም ጠንካራ የመከላከያ ሰፋሪ ጦር መገንባት ነበር ዕቅዱ።

የዕቅዱን ዝርዝር ወደ ሮም በመላክ ለአጠቃላይ ዘመቻው የሚያስፈልገው 13 ሚሊዮን ሊሬ እንዲለከለት ጠየቀ። ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ በምላሹ 9 ሚሊዮን ሊሬ አብቃቅቶ እንዲጠቀም በተጨማሪም የጦርነት ወጪውን በወረራው ከሚገኘው የዘረፋ እና የምርኮ ንብረት ላይ እንዲጠቀም አዘዘው።

ባራቴሪ ግራ ተጋብቶ በውጥረት ቆየና በመጨረሻም በቦታው ሰው እንዲተካ ለሮም አሳወቀ። ክሪስፒም የባራቴሪን መልቀቂያ ውድቅ አድርጎ ለምክክር እና ተጨማሪ የዘመቻ ዕቅድ ዝግጅት በግንቦት ወር 1895 ወደ ጣሊያን አስጠራው።

ሮም ሲደርስ የጀግና አቀባበል ተደረገለት። ‹‹የክሉቲት እና የሰንአፈ ጀግና›› በሚል ማዕረግም ኒሻን ተሸለመ። በሽልማቱ እና አቀባበሉ ተደስቶ ስለነበር ሥራውን እንደ ቀድሞው ባልዲሴራ ላለመልቀቅ ወሰነ።

ክሪስፒ እና ባራቴሪ የዘመቻ ዕቅድ በማውጣት ላይ ሳሉ በማቲም አምባሪያኒ የተመራ የተቃዋሚዎች ቡድን ጣሊያን የቅኝ ግዛት ጠረራዋን እንድታቆም ጠየቁ። ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ጥያቄያቸውን ሲመልስ ኤርትራ ለጣሊያን ዓይነተኛ የስፈራ አማራጭ መሆኗን አስረግጦ ነበር የተናገረው።

ባራቴሪ የጠየቀውን የዘመቻ ወጪ ተቀንሶ ዐሥር ሚሊዮን ሊሬ ተፈቀደለት። እረፍቱን ከቤተሰቡ ጋር አሳልፎ በወርኃ መስከረም ወደ ኤርትራ የመልስ ጉዞውን ጀመረ። በስገር ፍቅር እና የተስፋፊነት ፍላጎት የታወረው ባራቴሪ ለስገሩ ጣሊያን ከእርሱ የምትፈልገውን ኹሉ ሊሰጣት ቃል ገብቶ ነበር ወደ ኤርትራ የተመለሰው።





# ክፍል ኹለት

# የአድዋ የጦር ሜዳ ውሎ

# ምዕራፍ ስምንት

## የምኒልክ ዘመቻ

የምኒልክ ‹‹ክተት›› ዐዋጅ የተነገረው በመስከረም ወር በአንዱ ቅዳሜ ነበር። ዕለቱ በአዲስ አበባ ደማቅ ገበያ የሚቆምበት ነው። ኹለት ዐዋጅ ነጋሪዎች ገበያተኛውን በመሰብሰብ የንጉሡን ዐዋጅ አሰሙ። ኢትዮጵያ ለጦርነት መዘጋጀት ጀመረች።

በጥር 1895 የመንገሻን በጣሊያን መደምሰስ የሰሙት ምኒልክ እርምጃ ለመውሰድ አልቸኮሉም። በመቀጠልም በወርኃ የኑቲት የጣሊያን ወራሪ ኃይል ወደ ትግራይ በመዝለቅ እስክ ደቡባዊው አሸንጌ ሐይቅ ድረስ ወረራ ሲፈጽምም ለመከላከል አልተንቀሳቀሱም።

የምኒልክን ዝምታ ከፍራቻ ጋር በማያያዝ የተረዱ በርካታ አውሮፓውያን ነበሩ። ንጉሥ ተክለኃይማኖት እና የጣሊያኑ ጀነራል ፒየትሮ ቶሴሊ ግን የምኒልክ ዝምታ አደጋ እንዳረገዘ ደጋግመው ተናግረዋል። በምኒልክ ዝምታ የተበረታታችው ጣሊያን በአጠቃላይ ወደ ሰባት ሺህ ስኩዌር ማይል ስፋት ያለው ቦታ በወረራ ያዘች። በአጠቃላይ ስፋቱም ከቤልጀየም የሚበልጥ ቦታ ነበር። የጣሊያን መስፋፋት ቀጥሎ በመጪረሻም የታቦተ ጽዮን መቀመጫ የሆነችውን ቅድስቲቱን አክሱም ወረረች። በኢትዮጵያ ታሪክ ያለፉ ነገሥታት በሙሉ የማይደራደሩበት ነገር ቢኖር አክሱምን ለጠላት አሳልፎ መስጠትን ነው።

የምኒልክ ዝምታ መሰበር የተጀመረው ከአክሱም መያዝ በኋላ ነበር። የንግሥና ዘውዳቸውን ከጫኑ ስድስት ዓመታት ቢያልፍም ምኒልክ ትግራይን አልነበኙም ነበር። ክልሉን በተለያዩ የጦር መሪዎቻቸው በኩል ሲያስተዳድሩ ነበር የቆዩት። በመጪረሻም ጣሊያን መላውን የትግራይ አካባቢ ስትይዝ ምኒልክ ለመጀመሪያ ጊዜ ትግራይን በመነካካት የአገራቸውን ግዛት ለማስከበር ተነሱ።





### ሕዝባዊ ቅስቀሳ በኢትዮጵያ

አፄ ምኒልክ ከቤተ መንግሥታቸው አካባቢ በሚነሳ ተቃውሞ እጣብቂኝ ውስጥ ገብተዋል። ባለቤታቸው ጣይቱ እና ወንድማቸው ራስ ወሌ ከሰሜናዊ ወዳጆቻቸው መንገሻ እና አሉላ ጋር በመሆን ጣሊያን ላይ ጦር እንዲያዘምቱ ምኒልክን ወተወቷቸው። ወታደራዊ ዘመቻ የሚደረገው ወትትን በመጠበቅ በመኸኑ ምኒልክ የከረሙቱ ወራት እስኪያልፍ ለመጠበቅ ወሰኑ።

ከመጋረዝ ጀርባ በመሆን ምኒልክ የዘመቻ ዕቅድ መንደፍ ጀመሩ። በሚያዝያ 1895 አዲስ የጠመንጃ እና ጥይት ግብር ጣሉ። ከሙስሊም ደርቪሾች ጋር የነበረውን ፍጥጫ ለማርገብ በርካታ ፈረሶችን እና ቡና በስጦታ መልክ ላኩላቸው። ኃይማኖታዊ ልዩነታቸውን ወደ ጎን በመተውም ጥቁርነታቸው ላይ ተመርኩዘው የጋራ ጠላታቸውን እንዲለዩ ለደርቪሾች ጥሪ አቀረቡ። ለደርቪሽ በጻፉት ደብዳቤም አፄ ምኒልክ እንዲህ ብለዋል፦ *‹‹ለኔም ለንደ ለናንተ ጥቁር ነኝ። በአንድ ላይ በመሆን የጋራ ጠላታችንን መውጋት ይኖርብናል።››*

ከረምት እንደወጣ በወርኃ መስከረም 1895 አፄ ምኒልክ አገር አቀፍ ‹‹ክተት›› አወጁ። ወራሪው የጣሊያን ጦርም ግዛታቸውን ለቅቆ እንዲወጣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ አስተላለፉ።

ከዐዋጁ በፊት ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጦር ሠራዊት አልነበራትም። አገሪቷን ለዘመናት ከወራሪ የጠበቃት የሕዝቡ ጠንካራ ወታደራዊ ልምድ ነበር። በአገሩ እና በኃይማኖቱ ስም ለሚደረግለት ጥሪ ሕዝቡ በፍጥነት ምላሽ በመስጠት ይታወቃል። ወታደራዊ ትዕዛዝ በቀጥታ ከንጉሡ ወደ ራስ ደመርጫል። በመቀጠልም ወደ ግዛት አስተዳዳሪዎች እና የቀበሌ/ሰፈር ሹማ ሹሞች ይደርሳል።

የክተት ዐዋጁ ከቤተ-መንግሥት በተነገረበት ቅጽበት በርካታ መልዕክተኞች በአገሪቱ የተለያዩ አቅጣጫዎች ተበትነው ዐዋጁን አዳረሱ። ወንዱ ጦር፣ ጎራዴ፣


ጋሻ፣ ጠመንጃ እና ያለውን መሣሪያ ከወሥር ቀን ስንቅ ጋር ዝግጁ አደረገ። ሴቶች ለስንቅ የሚሆን ዳቦ፣ ስርበፊ እና ቅቤ አዘጋጁ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ወንዶች በኢትዮጵያ ባሕል መሠረት መሣሪያ እና ጎራዴያቸውን በቀኛ ጎናቸው ታጥቀው በየቀዬአቸው መሸለል ጀመሩ። በየግዛቱ ያሉ ዜጎች ከአጎራባች ግዛቶች ጋር በመገናኘት ጉዞ የሚጀምሩበትን ዕለት እና ቦታ ወሥነው ጉዞ ጀመሩ።

ወታደር የመመልመሉ ተግባር በፍጥነት ቢከናወንም በምልመላው ወቅት የምልምሎቹ ታማኝነት ዋናው የትኩረት ነጥብ ነበር። ስሸዋ ንጉሥነት በመነሳት የመላ አገሪቱ መሪ መሆን የቻሉት አፄ ምኒልክ በአብዛኛው አገሪቱ በነበሯቸው ታማኞቻቸው አማካኝነት በርካታ ሠራዊት ማሰባሰብ ቻሉ። የራስ መኮንን፣ ራስ ወሌ፣ ንጉሥ ተክለኃይማኖት፣ መንገሻ እና አሉላ ድጋፍ አስፈላጊ ነበር። በምልመላ ሥራው ወቅት ጣሊያኖች የገመቱት በጦርነቱ ወቅት የምኒልክ ቅይጥ ሠራዊት በመበታተን ከፋተኛው እንደሚበዛ ነበር። በዚያም የተነሣ የምኒልክ ሠራዊትም ሆነ መላዋ ኢትዮጵያ በእጃቸው እንደሚወድቁ በመጠባበቅ ላይ ነበሩ።

የምኒልክ ሠራዊት ከአዲስ አበባ በመነሳት ጉዞውን የጀመረው ጥቅምት 11 ቀን ነበር። ከደቡብ የተነሣው ጦር ወረኢሉ ላይ የሰሜኑ ደግሞ አሸንጌ ሐይቅ አቅራቢያ እንዲቀላቀላቸው አፄ ምኒልክ ቀድመው አሳውቀዋል። የምኒልክ ወታደር ባለፈባቸው ቦታዎች ሹሱ እርሶ እደሩ ስንቅ በማቀበል እና በማበረታታት ነበር የሸኘው።








Route of the Adwa Campaign, Addis to Adwa

*ካርታ - የአድዋ ዘመቻ የጉዞ መስመር (ከአ.አ እስከ አድዋ)*




Route of the Adwa Campaign, Addis to Adwa

*ካርታ - የአድዋ ዘመቻ የጉዞ መስመር (ከአ.አ እስከ አድዋ)*

## የዘመቻው አጀማመር

ጣይቱ እና ምኒልክ ከሠራዊቱ ጋር በመሆን ነበር ጉዞውን የጀመሩት። የኹሉቱ መናር ሠራዊቱን ከወዲሁ ከማነቃቃቱ በተጨማሪ መንገድ ላይ የሚተላለፈውን የሠራዊት ቁጥር ከፍ አድርጓል። ምኒልክና ጣይቱ በጉዞው ወቅት ታል የሸኩ የግዛት አስተዳዳሪዎች በታላቸው መሠረት ሠራዊት፣ ትጥቅ እና ስንቅ ማቅረባቸውንም መታዘብ ችለዋል።

በዘመቻው ወቅት በምኒልክ የሚመራው ሠራዊት መሃል ጎዳና ይዞ ሲጓዝ የራስ መሌ እና ንጉሥ ሚካኤል ጦር ደግሞ ግራና ቀኝ ተራራውን በመያዝ አጅቧቸዋል። የጉዞው ሥልት በቂ የጥበቃ ደኅንነት ከመፍጠሩ በተጨማሪ የወታደሩን መላክም ቀንሷል። የሠራዊቱን ጉዞ የተመለከቱ ሰዎች የሠራዊቱን ነጭ ሽማ እና የሚያብረቀርቅ ጦር እና ጋሻ እንደማይረሱት ተናግረዋል።

በዘመቻው ወቅት ጣይቱ ብጡል ከምኒልክ በላይ ጎልተው ታይተዋል። የተመረጡ አሻሚዎቻቸው ድባብ ጥላ በመያዝ በበርካታ ሠራዊት አጅበዋቸው ነበር የሚጓዙት። ጣይቱ ያስከተሉትን ጦር ይመሩ የነበሩት ባልቻ፣ ከጦር መሪነታቸው በተጨማሪም የምኒልክ ግምጃ ቤት ኃላፊ እና የዘውድ ጠባቂም ነበሩ።

ጣይቱ በሺህ የሚቆጠሩ ታጣቂዎችን ብቻ አልነበረም ያስከተሉት። ከመቶ በላይ አባላት የነበሩት የሙዚቀኞች ቡድንም ጭምር እንጂ። በሰላሙ ቀን ጣይቱ ሰበንና ልዩ ፍቅር የነበራቸው ሲሆን በአድዋው ዘመቻም በርካታ እዝማሪያን እና በገና ደርዳሪዎችን አስከትለዋል። የጣይቱ ፈረስ በመከተል የተሰያዩ የዘመቻ ዘፈኖችን፣ ፉከራዎችንና ሽለላዎችን በማሰማት ነበር የሙዚቀኞች ቡድን ያጀባቸው።







*ምስል፦ ጣይቱ በዘመቻ ጉዞ ላይ (የካቲት 14 ቀን 1896)*

የየዕለቱን ጉዞ የሚጀምሩትም ሆነ የሚያጠናቅቁት የንጉሡን እና የንግሥቷን ማረፊያ ድንኳን የሚሸከሙት የሠራዊት አባላት ነበሩ። በልዩ መጠሪያው ‹‹ደስታ›› በመባል የሚታወቀው ባለቀይ መጋረጃ የንጉሡ ልዩ ድንኳን ‹‹አልፍኝ›› የሚባለውን የጣይቱ ማረፊያ እንዲሁም ‹‹አዳራሽ›› በመባል የሚታወቀው የነገሥታቱ አገልጋዮች ማረፊያ ድንኳኖች በመስመር እንዲጣሱ ሲደረግ ሠራዊቱ የዕለቱን ጉዞ ማጠናቀቁን ያሳውቃሉ። ወደ ሚቀጥለው ቀን የጉዞ መስመር በሩን በማዞር ነበር ‹‹ደስታ›› የሚከተለው። ሌሎቹ ድንኳኖች በሙሉ ከንጉሡ ማደሪያ ኋላ ነበር የሚጣሉት።

የንጉሡ ቀይ ድንኳን ከፍ ያለ ሰፍራ ላይ ከተተከለ በኋላ ወዲያውኑ የንጉሡ አገልጋዮች ሥራቸውን ይጀምራሉ። በዐሥራ አምስት በቅሎ ተጭኖ የሚጓዘው የንጉሡ እግር መርገጫ በአግባቡ ይነጠፋል። መንበራቸውም ቦታውን ሲይዝ



ምስል፡- ጣይቱ በዘመቻ ጉዞ ላይ (የካቲት 14 ቀን 1896)

በዙሪያው አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለማት ያሏቸው በርካታ የሸማ ጨርቆች በመንበሩ ዙሪያ ይሰቀላሉ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ የንጉሡ የጉዞ ቤተ-መንግሥት ባማረ ሁኔታ ተገንብቶ ለእራት እና የምሽት መዝናኛ ዝግጁ ይሆናል።

የድንኳኖቹ አቀማመጥ እና ቦታ አያያዝ የባለድንኳኑን መሳፍንት ደረጃ እና ማዕረግ ያሳያል። ከንጉሡ ድንኳን በቅርበት የተጣለ ድንኳን ያለው ሰው የቅርበት ደረጃው ከፍተኛ ነው። ከምኒልክ ድንኳን አጠገብ የነበረው የግምጃ ቤቱ ድንኳን ሲሆን ከእርሱ ቀጥሎ ደግሞ የንጉሡ እና የንግሥቷ አልባሳት የሚቀመጥበት ድንኳን ቦታውን ይይዛል። በተለምዶ «የልብስ ድንኳን» ከሚባለው ቀጥሎ የክቡር ዘበኛ እና የካህናት ድንኳን ይተከላል። ከካህናቱ ጀርባ የንጉሡን ጨምሮ የበርካታ ፈረሶች መቆሚያ ሥፍራ ሲሆን ከፈረስ ጋጣው ቀጥሎ የምግብ ማብሰያ ድንኳኖች ይተከላሉ። የንጉሡ ቤተ-መንግሥት አገልግሎት በጉዞ የማይጓደል ሲሆን ለእንጀራ፣ ለወጥ፣ ለጠጅ እና ለጠላ ብቻ የየራሳቸው ድንኳኖች ይጣሉ ነበር።

የምግብ ማብሰያ ድንኳኖች የንጉሡ ማረፊያ የመጨረሻውን መስመር ይይዛሉ። ከማብሰያዎቹ ቀጥሎ የራስ መንገሻ፣ የራስ መኮንን እንዲሁም የምኒልክ አፈ-ንጉሥ ድንኳኖች ይተከላሉ። ከሦስቱ ድንኳኖች ቀጥሎ የበርካታ ከፍተኛ ወታደራዊ አዛዥ ድንኳኖች ይታያሉ። ከአዛዦቻቸው ጀርባ እጅግ በርካታ ድንኳኖች የሚጥሉት ተራ ወታደሮቻቸው ነበሩ። በአጠቃላይ የምኒልክ ሠራዊት ጊዜያዊ ማረፊያ ታላቅ የድንኳን ከተማ ይመስላል።

ሠራዊቱ በቀን ከአምስት ሰዓታት በላይ እንዳይጓዝ ንጉሡ አዘው ነበር። ከአዲስ አበባ እስከ አሸንጌ ሐይቅ ድረስ የተደረገው ጉዞ ዝግተኛ የነበረ ሲሆን ጣይቱ እና ምኒልክ አጋጣሚውን በመጠቀም በሕዝቡ ዘንድ ያገኙትን ተቀባይነት ለመገምገም ችለዋል። በየመንገዳቸው የሚደረግላቸውን አቀባበል እና አሸኛኘት በመመልከትም የሕዝቡን ይሁንታ ማግኘታቸውን አረጋገጡ።





የምኒልክ ድንኳን አሸንጌ ሐይቅ ዳርቻ በተጣለበት ታጎሳስ ወር አጋማሽ ላይ የሠራዊቱ ቁጥር ከሙቶ ሺህ ይልቅ ነበር። ሠራዊቱ ጠንካራ የውጊያ ሞራል የነበረው ሲሆን በዘመኑ ማለፊያ የነበረ ጠመንጃም ታጥቋል። የጦሩ አለሳለፍ በቁጥር ሲሰላ ለአንድ የጣሊያን ወታደር አራት የኢትዮጵያ ወታደሮችን የማሰለፍ ያህል ነበር።

የወራሪው ጣሊያን ጦር ስለ ኢትዮጵያ ሠራዊት ብዛት እና ጥራት የተዛባ መረጃ ነበር ያለው። ሠራዊቱን ዝቅ አድርጎ ከመገመቱም በላይ ከምኒልክ ቤተ-መንግሥት ሆን ተብሎ የተነገሩ የማደናገሪያ ወሬዎችንም የጣሊያን ሠራዊት እንደ እውነተኛ መረጃ ተቀብሏቸው ነበር። አፈትልከው ከወጡት የማደናገሪያ ወሬዎች መካከል የራስ መኮንን መክዳት፣ የንጉሥ ተክለኃይማኖት ልብ መሸፈት እና የምኒልክ በመብረቅ ተመትቶ መሞት ይገኙበት ነበር። እያንዳንዱ የሰሙት ወሬ ጣሊያኖች የሚጥሙት የኢትዮጵያ ጦር የተሰነጣጠቀ እና አነስተኛ የውጊያ ሞራል ያለው መሸኑን አሳምኗቸው ነበር።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## አምባ'ላጌ

ፒየትሮ ቶሴሊ የ17 ዓመት ወጣት ሳለ ነበር ቱሪን ከሚገኘው ‹‹ሪያሌ›› የጦር አካዳሚ የተመረቀው። አካዳሚው ከ16 ዓመት በታች ያሉ ልጆችን የማይቀበል ቢሆንም የቶሴሊ ክህሎት ግን የተለየ ስለነበር ተቀበሉት። ከሦስት ዓመት ተከታታይ ሥልጠና በኋላ 1878 መድፈኛ በመሆን ተመረቀ።

በጣሊያን ቆይታው ለስምንት ዓመታት ያህል ምንም የወታደራዊ ማዕረግ ዕድገት ያላገኘው ቶሴሊ ከጣሊያን ውጪ በሚገኙ ቅኝ ግዛቶች የመሥራት ፍላጎት አደረበት። አገሩ ጣሊያን በ1885 ምፅዋን ስትቆጣጠር ጀምሮ ወደ ቀይ ባሕር አካባቢ ለመሄድ አለቆቹን ይወተውት ነበር። በመጨረሻም በ1888 እግሩ ምፅዋን ረገጠ።

በኤርትራ ቆይታው ከፍተኛ ስኬት መጎናጸፍ ቻለ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የደረጃ እና የደሞዝ ዕድገትም አገኘ። በኤርትራ ይሳካለት እንጂ በአገሩ ጣሊያን ከፍተኛ የፀረ-ቅኝ ግዛት ተቃውሞ ተፈርሞ ነበር። በ1890ዎቹ ወደ ጣሊያን በማምራት ስለ ምሥራቅ አፍሪካ የቅኝ ግዛት ዕድል ለማብራራት ሞክሯል። የሮምን ቀደምት ገናናነት ለመመለስ መራራ ትግል፣ የተግባር ውሳኔ እና ፈጣን እርምጃ እንደሚያስፈልግም ‹‹ፐሮ አፍሪካ ኢታሊካ›› በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፉ ለጣሊያናውያን መልዕክት ለማስተላለፍ ሞክሯል።







Pietro Toselli and friends. From *Illustrazione italiana*, 5 January 1896

***ምስል፦ ፒየትሮ ቶሴሊ እና ጓደኞቹ (ጥር 5 ቀን 1895)***

ኮአቲት እና ሰንአፈ ላይ መንገሻን በ1895 ድል መንሳት የቻለው ቶሴሊ ጦሩን ወደ መሃል ትግራይ ለመግፋት ወሰነ። በወቅቱ በአውሮፓውያን ዘንድ የነበረው ዕምነት ትግራይ በምኒልክ ላይ በቀላሉ ለማመፅ የተዘጋጀ እንደሆነ ነበር። በዚህ የተገፋፋው ቶሴሊ በትግራይ ይኖራሉ በማለት የገመታቸውን አማፅያን በማስተባበር ቀጠናውን ለማተራመስ አቀደ። በመጀመሪያ እርምጃውም ሼህ ታሳ የተባሉ የጎሳ መሪን መልምሎ ሥራውን ጀመረ።



Photo from Bandini and Ilg cards. From L'Illustrazione Italiana, 5 January 1896

ምስል፡- ፒየትሮ ቶሌሊ እና ጓደኞቹ (ጥር 5 ቀን 1895)

ቶሴሊም ሆነ ሌሎች አውሮፓውያን የተሳሳተ ግምት እንደነበራቸው የተረዱት የጣሊያን እና የሺህ ታላ ጥምር ኃይል አምባ አላጌ ላይ ብርቱ የመከላከል ውጊያ ሲገጥመው ነበር። የሕዝቡን ተቃውሞ ችላ በማለት ዅሰት ሺህ አባላት የነበሩትን ሠራዊት አምባላጌ ላይ በማስፈር ነበር ቶሴሊ የምኒልክን ሠራዊት ለመጠበቅ የወሰነው።

ከዐሥር ሺህ ሜትር የሚበልጥ የባሕር ጠለል ከፍታ ያለው አምባላጌ ተፈጥሮአዊ ምሽግ ነበር። ከወታደራዊ ጠቀሜታው በተጨማሪ በሸዋ እና ትግራይ መናኛ መንገድ ላይ መገኘቱ ልዩ ጠቀሜታም ነበረው። አምባላጌ ላይ የመሸገው ቶሴሊ ተልዕኮው ምን እንደሆነ ግልጽ አልነበረም። ለመሸኑ የምኒልክ ጦር አምባ አላጌ ሲደርስ ይገጥመዋል ወይስ በዝምታ ያልፈዋል? ያልተመለሰ ጥያቄ ነበር።

ከአምባላጌ በስተሰሜን ሠላሳ አምስት ማይል ርቀ ከነበረው አለቃው አሪሞንዲ ጋር መልዕክት በመለዋወጥ ቶሴሊ በአምባ አላጌ መሸነ ቆየ። ከወራት በኋላ ግን የዅሰቱ የጣሊያን መኮንኖች ግንኙነት ሻከረ። ቶሴሊ በሚያዝያ ወር በርም በጻፈው ደብዳቤ ከአሪሞንዲ ጋር መግባባት አለመቻሉን አሳውቆ ሰኔ ላይ ሙሉ በሙሉ ግንኙነቱን አቋረጠ።

የቶሴሊ ዅሰት ሺህ ሠራዊት ከግዙፉ የምኒልክ ጦር ጋር ሲነፃፀር ዐይን ውስጥ ቢገባ የማይቆረቁር ጉድፍ ያህል ነበር። ቶሴሊ የመሸገበትን የአምባላጌ አካባቢ ለማስለቀቅ ምኒልክ አይዋጉም። ግዙፍ ጦራቸው ቶሴሊን አምባላጌ ላይ አልፎ በመሄድ የግንኙነት መስመሩን ቢዘጋበት ከቀናት በኋላ ሠራዊቱ በቀላሉ እንደሚያልቅ ግልጽ ነበር።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ምኒልክ አደባ አላጌን ሰልለ ዓላማ ሊጠቀሙበት ወሥነው ነበር። በበርካታ አውሮፓውያን ምኒልክን እንደሚክዳ የተነገረበት ራስ መኮንን የሚፈተንበት ቦታ ነበር - አምባ ላጌ። ይህንን ጥርጣሬ ለማረጋገጥም ምኒልክ





ጦሩን ከፊት እንዲያስቀድም መኮንንን አዘዙት። መኮንን የጣሊያን ወዳጅ ሆኖ ምኒልክን የሚክዳ ከሆነ ብቸኛው መፈተኛ ሊሆን የሚችለው ሠራዊቱን ከጣሊያን ሠራዊት ጋር ማፋጠጥ እንደሆነ ነበር አፄ ምኒልክ የወሰኑት።

## የጣሊያን ከትዝታ መባነን

የመኮንን ሠራዊት አምባ ላጌ ደርሶ ሲመለከት ነበር ቶሴሊ አገሩ ከማትችለው ባሳጋራ ጋር መጋጨቷ የተገለጠለት። ስለ ምኒልክ ዘመቻ አዲስ አበባ ከሚገኘው የጣሊያን ስለላ ቡድን የደረሰው መረጃ ጦሩ በዅሰት ቡድን የዘመተ ሲሆን እያንዳንዱ ቡድን ዐሥራ ዅሰት ሺህ ሠራዊት ብቻ እንደነበረው ይገልፃል። ንጉሥ ተክለኃይማኖት በማመፁ ምኒልክ ወደ ጎጃም እንደዘመተ እና የራስ መኮንን ጦር ብቻውን ወደ ሰሜን መንቀሳቀሱን በተመለከተ የተሳሳተ መረጃ ነበር ቶሴሊ የደረሰው።

መንገሻ፣ አሉላ፣ ተክለኃይማኖት እና መኮንን የከፈቸው አፄ ምኒልክ ከመንደራደር ይልቅ ሠራዊታቸውን ለማንቀሳቀስ እንደማይሞክሩ ነበር የጣሊያን ግምት። ግምቷን ያጠናከረላት ደግሞ በተደጋጋሚ ጦሯ ወደ ትግራይ ሲገባ የምኒልክ ምላሽ አለመስጠት ነበር።

ጣሊያን የተሳሳተ ግምት በመያዝ ምኒልክን እንደ ፈሪ ብቷመለከትም የምኒልክ ዝምታ ግን ምክንያታዊ ነበር። በ1890 ትግራይን በመቆጣጠር በሥርዓተ ንግሥናቸው ወደ አክሱም እንዲመጡ ጣሊያን ስትጋብዛቸው አፄ ምኒልክ አልተቀበሉም። በ1894 ጣሊያን አድዋን በመቆጣጠር መንገሻን ለምኒልክ ለማስረከብ ያደረገችውንም እንቅስቃሴ ምኒልክ በጥሞና ነበር የተመለከቱት።

የጣሊያን የተሳሳተ ግምት እንዳለ ሆኖ በ1895 ነገሮች በሙሉ የተለየ መልክ ያዙ። መንገሻ እና አሉላ እንዲሁም የቀሩት የትግራይ መሳፍንት እና ነበዛዝት ከምኒልክ ጎን በመሰለፍ አገራቸውን ከጣሊያን ለመከላከል ወሰኑ።

ቶሴሊ የጠበቀው መካከለኛ መጠን ያለው ሠራዊት ነበር። በመንገሻ ወይም በራስ ወሌ የሚመራ 4500 ጦር ሲጠብቁ የነበሩት የቶሴሊ ወታደሮች አምባላጌ ላይ ሆነው ቁልቁል የተመለከቱት ሠራዊት ከቅኝታቸው አባነናቸው። ቁጥሩ ከአርባ ሺህ የሚልቀውን የራስ መኮንን ጠንካራ ሠራዊት ተመልክቶ ነበር ቶሴሊ ለፀበኛ አለቃው አስቸኳይ ደብዳቤ የጻፈው። ‹‹እጅግ በጣም ብዙ ናቸው›› በማለት ቢፅፍም የተመለከተው የአፄ ምኒልክን የፊት ተሰላፊ ሠራዊት ብቻ መሽኑን ግን አላወቀም ነበር።

ታኅሳስ 5 ቀን ራስ መኮንን አምባላጌ ደርሰው ለቶሴሊ በጻፉት ደብዳቤ ይዘታውን በፍጥነት ሰቅቆ ካልወጣ እርምጃ ለመውሰድ እንደሚገደዱ ገለፁ። የራስ መኮንን ደብዳቤ እጅግ የተለሳለሰ እና በምኒልክ አስገዳጅነት የዘመቱ መሆናቸውን የሚገልፅ ዓይነት ነበር። ‹‹የንጉሡ ጦር ከኋላዬ እየተከተለኝ ሲሆን እሽንጌ ሐይቅን አልፈዋል። እዚህ የምቆም ከሆነ ከኋላዬ ይደርሱብኛል›› በማለት ነበር ራስ መኮንን ለቶሴሊ የፃፉት።

ቶሴሊ የመኮንን ጦር በመግጠም ራሱን ለሞት አሳልፎ መስጠት እንደሌለበት ገብቶታል። ከመኮንን ደብዳቤ መንፈስ የተረዳው ራስ መኮንን በምኒልክ ግፊት መዝመታቸውን ነበር። በተጨማሪም በ1889 ጣሊያንን በመሳብኘት ብርቱ ወዳጅነት መመስረታቸውንም ሲጠቀምበት ወሰነ። ለራስ መኮንን በጻፈው ምላሽ ቀደምት የኢትዮጵያ ነገሥታት አፄ ቴዎድሮስ እና መንገሻ ከአውሮፓውያን ጋር በመፋለም የተሸነፉባቸውን የመቅደላ እና ሰዓቲ ውኒያዎች በመጥቀስ በዚህኛው ጦርነት ምኒልክ ቢሸነፉ በጣሊያን ወዳጅነት መንበረ-ሥልጣኑን እንደሚይዙ በመግለፅ ሊያግልላቸው ሞከረ።

ራስ መኮንንን ለማግባባት ቢሞክርም በውስጡ ግን ከፍተኛ ፍርሃት እንደነገሰበት ነበር። አምባላጌ ከቶሴሊ ጋር የነበረው ሌላ የጣሊያን ወታደር ሉጂ ካኖቬቲ ለአህቱ ‹‹ጦርያ በጻፈው ደብዳቤ የመኮንንን ሠራዊት ግዙፍነት ጠቅሷል። ‹‹እኛ





*አንድ ሺህ ስንሆን እነርሱ 20 ሺህ ናቸው። ሰማችን በታሪክ መዛግብት እንደሚፃፍ ተሰፋ አለኝ። ከዚህ የበለጠ ሽልማት የምናገኝ ግን አይመስለኝም።››*

ቶሴሊ ከፊቱ በነበረው የመኮንን ሠራዊት መበለጡን ቢረዳም አምባ ላጌን ለቆ ለመውጣት ግን የጀነራል አሪሞንዲን ትዕዛዝ መጠበቅ ነበረበት። ቶሴሊ እጅ ባይደርስም ጀነራሉ እንዲወጣ የሚያዝ ደብዳቤ የጻፈለት ቀድሞ ነበር። ቶሴሊ በመጨረሻው ምሽት አምባ ላጌ ከሚገኘው የማደሪያ ድንኳን ለጀነራል አሪሞንዲ የጻፈው ደብዳቤ በከፊል እንዲህ ይነበባል፦

> *በዚህ ምሽት ከስሬ የመሸገው የጠላት ጦር ያቀጣጠለው እሳት ይታየኛል። የጦሩ ካምፕ መንገሻ ከአቲት ሳይ ከገነባው እጅግ ይበልጣል። በጊዜ ወደ ኋላ በመመለስ ሃይላችንን ማሰባሰብ ይኖርብናል። ካልሆነ ግን መላው ኤርትራን ለመከላከል አንችልም።*

ይህ ደብዳቤ ለቶሴሌ የመጨረሻው ነበር።

ታኅሳስ 6 ቀን የኢትዮጵያ ጦር ለውጊያ ተዘጋጀ። በዕለቱ ከሰዓት በኋላ ዐሥር ሰዓት አካባቢ የጀነራሉን ምላሽ ቶሴሊ ጋር ደረሰ። ሰድስት የእግረኛ ሠራዊት ባታሊዮን እና ዥለት መድፈኛ ቡድን እንዲላክለት እና ታኅሳስ ሰባት በማለዳ እንደሚደርሱ አሳወቀው። ቶሴሊም አጠራጣሪውን ደብዳቤ ተመልክቶ ከማፈግፈጉ በፊት ሀሳቡን ቀየረ።

ታኅሳስ 7 ቀን ከጠዋቱ 12:30 የመኮንን ሠራዊት ማጥቃት ጀመረ። ራስ መኮንን ቀድሞ ባደረጉት ጥናት አንድ ሺህ ሦስት መቶ ቅጥረኛ አስካሪ(የባንዳ) ወታደሮችን የያዘው አራተኛ የጣሊያን ባታሊዮን ጠንካራ እንደሆነ አውቀዋል።

ከቅጥረኞቹ በተጨማሪ ቁጥሩ ከ350 የሚልቅ የራስ ስብሃት እና ሺህ ታላ ወታደርም ከጣሊያን ጎን ተሰልፏል። ራስ መኮንንም የኹሉቱ ባንዳዎች ጦር ላይ አተኮሩ።

ቶሴሊ በዙሪያው የተወሰኑ ታማኝ አስካሪዎችን በማቆም ለራሱ ልዩ መከላከያ አደረገ። የራስ ስብሃትን ጦር ቀድሞ በማዝመትም ሞቱን ለማራዘም ተጣጣረ። የስብሃት ጦር በግራ የሺህ ታላ ደግሞ በቀኙ ሆነው ከአምባላጌ ወደ ቶሳራ የሚወስደውን መንገድ ዘጉት። ከኹሉቱ ጀርባ ደግሞ በሌተናንት ጀነራል ቮልፒቼሊ የሚመራ የኤርትራ ምልምል ሠራዊት ተሰለፈ። በቶሴሊ የሚመራው አራት መድፍ ደግሞ በመሃል ሆኖ አምባውን ያዘ።

ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ መኮንን ጥቂት ወታደሮችን በቀኝ መስመር ወደነበረው የሺህ ታላ ሠራዊት በመላክ በቀላሉ ደመሰሱት። በግራ የተሻለ ይዞታ የነበረውን የራስ ስብሃት ጦር እንዲደመሰስ ራስ ወሌ ሰባት ሺህ ወታደሮቹን እንዲያንቀሳቅስ አዘዙት። ኹለት ሰዓታት የፈጀው የወሌ እና ስብሃት ጦርነት ሲጠናቀቅ የባንዳው ሠራዊት ሙሉ በሙሉ ተደምስሶ ነበር።

ሦስት ሰዓት አካባቢ ራስ መኮንን የሚመሩት 15 ሺህ ሠራዊት በቀጥታ ወደ ቶሴሊ የመድፍ አጥር ገሰገሰ። የቶሴሊ መድፈኞች የሚተኩሱት ጥይት በአየር ላይ በመፈንዳት ከሥር የነበሩትን የመኮንን ሠራዊት በፍንጥርጣሪው ጎዳቸው። መሬት ደርሰው የፈነዱትም ከፍተኛ ጉዳት አስከተሉ።

አራት ሰዓት ከመሸኑ በፊት በመንገሻ እና አሉላ የተመራው ዐሥራ ሦስት ሺህ ጦር አምባላጌ ደርሶ የጣሊያንን ሠራዊት በቀኝ በኩል ማጥቃት ጀመረ። በውጊያ ውሎው ግራ እና ቀኝ የነበሩትን መንቀሳቀሻ ሙሉ በሙሉ በመዝጋት የቶሴሊን ጦር መሃል ላይ በመክበብ ራስ መኮንን የውጊያ ስልታቸውን ውጤታማነት አስመሰከሩ።





ቶሴሊ ወደ መቀሌ ሲሸሽ የሚችልበትንም ሰሜናዊ አቅጣጫ በመያዝ መፈናፈኛ አሳጡት።

በኢትዮጵያ ጦር ብዛት እጅግ የተበለጠው ቶሴሊ ጀነራል አሪሞንዲ የላከለት ደጀን እስኪደርስ ድረስ ለመዋጋት ወሰነ። በፍጥነት ወደ አምባው በመውጣትም ገዢ መሬት ያዘ። ከዓምባው ላይ ቁልቁል በመተኮስም በርካታ ኢትዮጵያውያን ሙት እና ቁስለኛ አደረገ።

ስድስት ተኩል ሲሆን የተባለው ድጋፍ እንደማይደርስ የተረዳው ቶሴሊ ለማፈግፈግ ወሰነ። የአምባውን ጫፍ በመልቀቅ መሸሽ የጀመረው የቶሴሊ ቀሪ ሠራዊት በኢትዮጵያ ተበለጠ። በርካታ የጣሊያን ወታደሮች እና የጋማ ኮብቶቻቸው ራሳ አምባውን ሞላው። የተወሰኑ ወታደሮችም ከአምባው ላይ እየወደቁ ወደ ገደል ሲገቡ ታዩ። የሌተናንት ማርዚዮ ማንፍሬዲኒ በቅሎ በጥይት ተመትቶ ተንገዳገደ እና ጌታውን እንደጫነ ወደ ገደል ወረደ።

ሰባት ሰዓት ላይ ጦርነቱ ሙሉ በሙሉ ተጠናቀቀ። ከአምባው ውጊያ የተረፉት ወታደሮችም ሽሽታቸውን ቀጠሉ። የተረፈው የጠላት ጦር አምባውን ለቅቆ ወደ መንደር ሲጠጋ የአገሬው ገበሬ ቦጥይት ተቀበለው።

### ታሪክ የቀየረው የአምባላጌ ውሎ

ለጣሊያን እና ወዳጆቿ የአምባ ላጌ ውሎ ጀግንነት የፈፀሙበት እንደሆነ ነበር የተገለጸው። ቶሴሊ በጀግንነት ከበርካታ የኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር መዋደቁን መላው አውሮፓ አወራለት። የጀርመን፣ አስትሪያ እና ፈረንሳይ ጋዜጦችም የጣሊያን ሠራዊት በአምባላጌ የፈፀመውን ጀግንነት አናፈሱ።

ቡጣሊያን በተለይ የተደበላለቀ ስሜት ነበር የተፈጠረው። የቅኝ ግዛት ዘመቻውን በመቃወም ይታወቅ የነበረው የጣሊያን ምክር ቤት በዘቀል ስሜት

ተገፋፍቶ ለቀጣይ ዘመቻ የሚሆን ገንዘብ እንዲመድብ ጠየቀ። መንግሥትን በመቃወም የሚታወቀው ‹‹ኮሪየሬ ዴላ ሼራ›› ጋዜጣ በበኩሉ ወረራውን ‹‹አብደት›› በማለት አውግዞታል። የሮም ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በመንግሥታቸው ላይ ተቃውሞ በመውጣት ‹‹ቪቫ ምኒልክ!›› በማለት የኢትዮጵያውያን ንጉሥ ሲያወድሱ ተደምጠዋል። የተማሪዎቹ ተቃውሞ ምናልባትም በአውሮፓ ታሪክ በዓይነቱ የመጀመሪያ ሳይሆን አይቀርም።



*ምስል፦ የአምባ ላጌ ጀግና ራስ መኮንን (ከሊ ፔቲት ጋዜጣ ታኅሳስ 29 ቀን 1896)*





የአምባላጌው ድል ለኢትዮጵያ ከፍተኛ መነሣሣትን በመፍጠር ሰለድዋ ድል አስተዋፅኦ አድርጓል። በራስ መንገሻ ፈጣን ሽንፈት ኢትዮጵያን ዝቅ አድርገው የገመቱ አውሮፓውያንም ከአምባላጌ በኋላ ግምታቸውን ለማስተካከል ተገድደዋል።

የአምባላጌውን ድል ምኒልክ የሰሙት ዓላማጣ ሳሉ ነበር። የድሉን ዜና ለማብሰር ሌሊቱን ሙሉ ሲጋልብ ዓላማጣ የደረሰው መልዕክተኛ መንገድ ላይ ላገኛቸው የምኒልክ ሠራዊት አባላት ዜናውን አበሰረ። ወታደሮቹም ዜናውን ሰምተው በማዘን ‹‹ይሄንን ኹሉ መንገድ ተጉዘን የመጣነው ላንዋጋ ለመመለስ ነበር?›› በማለት እርስ በእርስ ተያዩ።

በምኒልክ ላይ አምፀው የነበሩ በርካታ የአገር ውስጥ ኅበዛዝት እና መሳፍንትም የአምባላጌውን ድል ከሰሙ በኋላ ከምኒልክ ጎን ቆሙ። ዋፍላ ላይ በጊዜያዊነት ያረፉት አፄ ምኒልክ በርካታ አማፅያንን ተቀብለው ከጦሯቸው ጋር ቀላቀሉ። የጎጃሙ ንጉሥ ተክለኃይማኖትም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወታደር ለምኒልክ የላከው የአምባ ላጌውን ዜና ከሰማ በኋላ ነበር።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አምባ ላጌ የተለየ ስፍራ ይዟል። የደቡብ እና ሰሜን ኢትዮጵያ ሠራዊት በመተባበር የጋራ ጠላታቸውን ለመደምሰስ የተዋጉበት ግንባር ነው፤ አምባ ላጌ። ከኹሉም በላይ ግን የፖለቲካ ልዩነት የከፋፈላቸው የአገሪቷ ኅበዛዝት ውስጣዊ ችግራቸውን ለጊዜው በመተው ባጋራ አገራቸውን የተከላከሉበት የተለየ ታሪክ ነበር።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ከአምባላጌ ወደ አድዋ ያደረገው ጉዞ በወኔ የተሞላ ነበር። ጦር ሠራዊቱ ከውጊያ በፊት ድሉን ያረጋገጠ ይመስል ነበር። ለመሸነፉ ማነው? የሞግዚት አስተዳዳሪ? ለማስተዳደር የመጣው ጦር በሚተዳደር ተሸንፎ የለምን?



ምስል፡- የአምባ ላጌ ጀግና ራስ መኮንን (ከሌ ፔቲት ጋዜጣ ታኅሳስ 29 ቀን 1896)

## የመቀሌው ምሽግ

ቶሴሊ አምባላጌ ላይ የከፈለው መስዋዕትነት በጣሊያን እንደተሰማ ነበር በርካታ ወጣት ወዶ ዘማቾች ወደ ኢትዮጵያ ለመዝመት የተዘጋጁት። የጣሊያን መንግሥትም አጋጣሚውን ተጠቅሞ አርባ ሺህ ወታደሮችን መለመለ። ከታኅሳስ 16 እስከ ጥር 5 ባሉት ቀናትም በዐሥራ አንድ መርከቦች ተጭነው ወደ ምፅዋ ጉዞ ጀመሩ። በኹለተኛው ዙር ጉዞ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ወታደሮችን እና በርካታ ቶን ትጥቅ እና ስንቅ የጫኑ የጣሊያን መርከቦች ከጥር 12 እስከ የካቲት 1 ባሉት ቀናት ጉዞአቸውን ወደ ምፅዋ ጀመሩ።

ጀነራል አሪሞንዲ የአምባላጌውን ዜና እንደሰማ ነበር መቀሌን ለመልቀቅ የወሰነው። ነገር ግን በመቀሌ ቆይቶ የሚሆነውን ለመቀበል መረጠ። ባራቴሪ መቀሌ ላይ ምሽጉን እንዲያጠናክር ጄሌፕ ጋሊያናን ላከ። የጋሊያኖ ወታደሮች ስሰ አምባ ላጌው ውሎ የሰሙት ታኅሳስ ሰባት እኩለ ሌሊት ላይ ከአምባላጌ ተርፈው መቀሌ ከደረሱት የቶሴሊ ወታደሮች ነበር።

ታኅሳስ ወር ያለፈው የጣሊያን ወታደሮች ከባንዳ ቅጥረኞቻቸው ጋር በመሆን መቀሌ ላይ ምሽግ ሲገነቡ ነበር። በመቀሌ የነበሩ አብያተ-ክርስቲያናት ሳይቀሩ የጥይት እና ቦምብ ማስቀመጫ ኾኑ። በአጠቃላይ ርዝመቱ 230 ጫማ፣ ከፍታው 16 ጫማ እንዲሁም እስከ ስድስት ጫማ የሚደርስ ውፍረት የነበረው ምሽግ ተገነባ። ለዋናው ምሽግ መከላከያ እንዲኾኑ በርካታ አነስተኛ ምሽጎች በዙሪያው ተቆፍረው እና ተከበውም ነበር።

በምሽግ የነበረው የጣሊያን ሠራዊት ምግብ ለማፈላለግ ታኅሳስ 9 ቀን ከምሽጉ ወጣ። የአምባላጌውን ዜና የሰማው የአካባቢው ሕብረተሰብ ለጣሊያን ስንቅ የሚሆን ነገር ላለመሸጥ ተስማምቶ ግልጽ ጥላቻውን አሳየ። የሕዝቡ ጠላትነት እየከፋ በመምጣቱ ከመቀሌው ምሽግ ወደ አስመራ ይደረግ የነበረውን ግንኙነትም አቋረጡ። በመኾኑም የጣሊያን መልዕክተኞች ምሽት እየጠበቁ ብቻ ነበር የሚንቀሳቀሱት።





ጋሊያኖ በምሽግ ያለ ሠራዊቱን ሞራል ከፍ ለማድረግ ሲል ወይን፣ ቡና፣ ሲጋራ እና የተለያዩ መጠጦችን በራሽን ያደርሳቸው ነበር። በሞቅታ የተበረታቱ የጣሊያን ወታደሮች በልቡሙሉነት የኢትዮጵያን ጦር እንደሚደመስሱ ይናገሩ ነበር። ይሄንን የተመለከተው ጋሊያኖ ለአለቃው ጀነራል ባራቴሪ በጻፈው ደብዳቤ ‹‹የሠራዊቱ የውጊያ ሞራል ከፍተኛ ነው›› ብሎ ነበር።

ታኅሳስ 19 ቀን ከጠዋቱ 4 ሰዓት አካባቢ የጣሊያንን ሠራዊት ስሜት የቀየረ ክስተት ተፈጠረ። ይኸውም ከመቀሌው ምሽግ በስተደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ ከፍተኛ አቧራ ተነስቶ የመቀሌን ሰማይ እንደ ደመና ሸፈነው። አቧራውን ያሥነሳው ከአምባላጌ ወደ መቀሌ በመገስገስ ላይ የነበረው የራስ መኮንን እግረኛ እና ፈረሰኛ ሠራዊት ነበር። ሠራዊቱ የጣሊያንን ምሽግ ለመክበብ አመቺ በሆነው የምሽጉ ሰሜናዊ አቅጣጫ ከፍታ ቦታ ላይ ሰፈረ። ሠራዊቱ የያዘው ቦታ የጣሊያን ሠራዊትን የግንኙነት መስመር እንዲሁም የማምለጫ መንገድ ለመዝጋት አመቺ ነበር።

ራስ መኮንን ጦራቸውን ቦታ ባስያዙ በኹለተኛው ቀን ለጋሊያኖ ደብዳቤ ላኩለት። ራስ መኮንን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሠራዊት እና ከጋሊያኖ ሠራዊት የተሻለ ጥገር ቦታ ይዘው ሳለ ለጋሊያኖ የላኩት ደብዳቤ የተሰላለሰ መኾኑ አስገራሚ ነበር። የራስ መኮንን ደብዳቤ እንደሚከተለው ይነበባል፦

*እንደምን ለሱ? ለፈጣሪ ምስጋና ይድረሰውና እኔ ከነመላው ሠራዊቴ በጣም ደህና ነኝ። የእርስዎስ ወታደሮች እንዴት ናቸው?*

*ከለላምታዬ በመቀጠል የምገልፅልዎ ነገር ቢኖር ጦርዎ የመሸገበትን ቦታ ለቅቆ እንዲወጣ በንጉሠ ነገሥቴ ስም እጠይቅዎታለሁ። የክርስቲያን ደም እንዲፈስ ፈፅሞ አልሻም እና ሠራዊትዎን ይዘው ይወጡ ዘንድ እጠይቃለሁ።*

*ወዳጅዎ መኮንን*

ጋሊያና የራስ መኮንንን ደብዳቤ የተመለከተው በጥርጣሬ ነበር። የመኮንን ጥያቄ እና መሰላሰል የምኒልክ ሠራዊት እስኪደርስላቸው ጊዜ ለመግዛት የታለመ ነበር የመሰለው። ጋሊያኖ የጻፈው ምላሽም የሚከተለው ነበር።

*ተጻፈ ለራስ መኮንን፣ የሸዋ ጦር የፊት አዝማች፣ ከመቀሌ ምሽግ ለዛሽ። እንደምን አሉ? እኔ ከነሙላ ሠራዊቴ ደህና ነኝ። ወታደሮችም ደህና እንደሸኑ ተሰቶ አደርጋለሁ። ለጥያቄም ምላሽ ይሆን ዘንድ በንጉሴ ስለታዘዝሹ ቦታውን ለቅቄ እንደማልወጣ ላሳውቅዎት ይገባል። ማድረግ ያለብዎን ያድርጉ። ሠራዊቴ ዘመናዊ ጠመንጃ እና ቦንብም መታጠቁን ላስታውሰዎት።*

*ወዲም ጋሊያኖ*

ራስ መኮንን ታኅሳስ 25 ቀን ኹስተኛ ዙር ደብዳቤ ቢፅፉም ከጋሊያኖ የተለየ መልስ አላገኙም። ታኅሳስ ሠላሳ ቀን ሦስተኛ ደብዳቤአቸው ከነጭ መሃረብ ጋር ባወታደር አስይዘው ወደ ጋሊያኖ ምሽግ ላኩ።

በሦስተኛው ደብዳቤ ጋሊያኖን የጠየቁት ቁስለኛ ወታደሮቻችን የሚያክምላቸው ሃኪም እንዲልክላቸው ነበር። ጋሊያኖም የክሙ ሐኪም የነበረው ሞዜቲን ወደ ራስ መኮንን በመላክ ለአንድ ቀን የሕክምና አገልግሎት ሰጥቶ ወደ ካምፑ ጊዮርጊስ ከተባለ የራስ መኮንን ወታደር ጋር ኑመለሱ።

ሞዜቲ ምሽቱ እንደደረሰ ሲኞሊያኖ ስለ ራስ መኮንን ሠራዊት ብዛት አብራራለት። ሞዜቲን አጅቦ የመጣው ጊዮርጊስ በምሽጉ ግብኛ ተደርጎለት የነበረ ሲሆን ብዙ ብራንዲ ከጠጣ በኋላ መለፍለፍ ጀመረ። 100 ሺህ ሠራዊት ያለው





የምኒልክ ጦር በመምጣት ላይ መኾኑን፣ ጦሩ መድፍ መታጠቁን እና ምኒልክ ምፅዋ ቤተ-መንግሥት ተቀምጠ ጠጅ እንደሚጠጣ መዛቱን ጊዮርጊስ ለጋሊያኖ ዘከዘከ። ጋሊያኖም የምኒልክ ፍላጎት ትግራይን ማስለቀቅ ብቻ ሳይሆን ጣሊያንን ከመላው አፍሪካ ነቅሎ ማስወጣት እንደሆነ ተገለጠለት።

የራስ መኮንን ጦር የማጥቃት እርምጃ ሳይወስድ ለቀናት በዝምታ መቀመጡ ጋሊያኖን አጠራጠረው። ጥር 1 ቀን የመኮንን ሠራዊት የጋሊያኒን ምሽግ ከብቦ ጨረሰ። ጥር 3 ቀን ለጋሊያኒ በጻፉት የመጨረሻ ደብዳቤ ራስ መኮንን ‹‹በአምባላጌ የቶሴሊን መጨረሻ አስታውስ። ምሽጉን አስረክበኝ፣ ተጨማሪ ደምም አታፍስስ። ይህንን ብታደርግ ከነሙሉ ጓዝህ እስከ ምጽዋ ድረስ ልሸኝልህ ቃል እገባልሃለሁ።›› በማለት ከረር ያለ መልዕክት አስተላለፉ።

### የበዓሉ-ግምቀት ሰልፍ

ጥር 6 ቀን ከጻፈው የግል ማስታወሻ ጋር በማያያዝ ጋሊያኖ ስለ በዓሉ-ግምቀት ፅፎ ነበር። በዕለቱ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ወታደር ከምሽጉ በተቃራኒ አቅጣጫ ሲተምም መመልከቱን እና ወታደሮቹም የምኒልክ መሆናቸውን ከራሱ ሠራዊት ማረጋገጡን ጋሊያኖ ፅፎ ነበር። ‹‹የምኒልክ ቀይ ድንኳን ከፊት በመሆን ወታደሩን አስከትሎ ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ አለፈ።››

በጥምቀት ማግስት የምኒልክ ሠራዊት ማረፊያ ቦታውን ያዘ። ጣይቱ ብጡል ከአንዱ ስሜናዊ ርስታቸው ያስመጡትን ከፍተኛ መጠን ያለው ቅቤ፣ በርካታ የቀንድ ከብት እና ከአምስት መቶ በላይ በጎች ለሠራዊቱ ስንቅ አከፋፈሉ። የስንቅ እደላው ወታደሩ ለቀጣይ ትዕዛዝ ዝግጁ እንዲሆን ያመላከተ ነበር። የመቀሌው ጥቃት ሊጀመር ተቃርቧል።

የኢትዮጵያ ጦር ጥር 7 ቀን ከዋናው የጣሊያን ምሽግ ራቅ ያሉ ኹለት የቅኝት ማማዎችን በማጥቃት ነበር የጀመረው። ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ሠራዊት ፈጣን እና የተቀላጠፈ የጥቃት እርምጃ ተገረሙ። በመጀመሪያው የውጊያ ውሎ ቀድሞ ቦታ የያዘው የጣሊያን ሠራዊት በርካታ የኢትዮጵያ ወታደሮችን ገደለ። ለዕለቱ ከፍተኛ ኪሳራ ጣይቱ፣ አሉላ፣ መንገሻ እና ምኒልክ ተጠያቂ ያደረጉት ራስ መኮንንን

ነበር። ለቀናት በመደራደር ባባከኑት ጊዜ ጣሊያን ምሽጉን እንዲያጠናክር በቸልታ መመልከታቸው ተገቢ እንዳልነበረም ወቀሱ። በሁኔታው የተበሳጩት አፄ ምኒልክም ለቸልታቸው መቀጫ ይሆን ዘንድ ራስ መኮንን የራሳቸውን ወታደሮች በማስቀደም ምሽጉን እንዲሰብሩ አዘዙ።

ጥር 8 ቀን የኢትዮጵያ መድፍ የጣሊያንን ምሽግ ሲደበድብ ቢውልም ምሽጉን ሰመስበር ግን አልቻለም። የኢትዮጵያ ሠራዊት በአጠቃላይ ዐሥራ ኹለት መድፍ ያስለፈ ሲሆን ኹለቱ ከአምባላጌው ውጊያ በምርኮ የተገኙ ነበሩ። የመድፈኞቹን የተስተካከለ ዒላማ የተመለከተው ጋሊያኖ «የኢትዮጵያ ወታደሮች ሳይሆን አውሮፓውያን መሆን አለባቸው» በማለት ተደንቆ ነበር። የኢትዮጵያ ሠራዊት የታጠቀው ሆች ኪስ መድፍ ከጣሊያን መድፍ የተሻለ ጥራት የነበረው ሲሆን የተሻለ ርቀት ይሸፍናል።



Makonnen's forces attack Mekele. From *L'Illustration*, 22 February 1896.

*ምስል፦ የመኮንን ሠራዊት የመቀሌን ምሽግ ሲያጠቃ (ከ ላ ኡሉስትራዚዮኔ ሊታሊያና፣ ጥር 2 ቀን 1896 የተወሰደ)*






ጥር 9 ቀን የራስ መኮንን ጦር በምሽጉ ላይ መጠነ-ሰፊ የማጥቃት ዘመቻ ከፈተ። ነገር ግን ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ወታደር አለቀ። በዕለቱ በተከሰተውም እልቂት ጣይቱ እና ምኒልክን ጨምሮ ንጉሥ ተክለኃይማኖት እና አቡነ ማቴዎስ ራስ መኮንንን በአገር ክህደት ተግባር ወቀሱት። በእልቂቱ ልባቸው የተሰበረው ራስ መኮንን «ታማኝነቴን እንዴት ላረጋግጥ እችላለሁ?» በማለት አምርረው ጠየቁ። በወቅቱ የተሰጣቸው ምላሽ «ምሽጉን እንዲገነቡ ጊዜ የሰጠሃቸው አንተ ነህ። ስለዚህ ምሽጉን ማፍረስም ያንተ ኃላፊነት ነው» የሚል ነበር።

ጥር 10 ከእኩለ ሌሊት በኋላ በእልህ የተሞሉት ራስ መኮንን ሦስት ተከታታይ ጥቃት ሰነዘሩ። በስድስት፣ ስምንት እና ዐሥር ሰዓት ያደረጓቸው የማጥቃት ሙከራዎች ስኬታማ አልነበሩም። የጣሊያን ጦር በአብሪ ጥይት ታግዞ የራስ መኮንን ጥቃት መከተ። ራስ መኮንን ጥር 11 ቀን ሠራዊታቸው ለምሽጉ መውጫ የሚሆን መሳላል እንዲያዘጋጅ አዘዙ። ከሌሊቱ 9 ሰዓት ጭለማውን አስታክከው ሠራዊታቸውን ወደ ግምቡ አስጠጉ።

መጀመሪያ ላይ በቀላሉ ግንቡን መውጣጣት የጀመሩት የራስ መኮንን ወታደሮች የጣሊያንን ምላሽ ማስተናገድ የጀመሩት በአስገራሚ ሁኔታ ነበር። ንጋት ሊቃረብ ከስድስት መቶ በላይ የመኮንን ወታደሮች የምሽጉ ግድግዳ ሥር ተዘርረው ነበር። የወታደራቸውን ከፍተኛ ሞት የሰሙት ራስ መኮንን በቁጥታ የገሰገሱት ወደ ምሽጉ ነበር። ራሳቸውን ለጣሊያን ጥይት አጋልጠው ለሞት የተዘጋጁትን ራስ መኮንን የታደጋቸው ራስ አሉላ ነበር። በተደጋጋሚ ሲወቅሳቸው የነበረው ራስ አሉላ በመጨረሻም ነፍሳቸውን መታደጉ ጨዋነቱን ነበር ያሳየው።

ጥር 11 ቀን በምኒልክ ዘመቻ ጥቁር ቀን ነበር። በአምባላጌው ድል ወኔው ተነሳስቶ የነበረው ሠራዊታቸው በመቀሌው ውጊያ ከፍተኛ አልቂት አጋጠመው። ይህንን ተከትሎም በጦራቸው ላይ ከፍተኛ የውጊያ ሥራል ውድቀት ተመለከቱ።



ምስል፡- የመከንን ሠራዊት የመቀሌን ምሽግ ሊይጠቃ (ከ ሳ ሉሱስትራዚዮኔ ኢታሊያና፣ ጥር 2 ቀን 1896 የተወሰደ)

ምኒልክ እና ራስ መኮንን በንጉሡ ድንኳን ውስጥ ፊት ለፊት ተቀምጠው ተላቀሱ። ከድንኳኑ ውጪም የሴቶች የለቅሶ ድምፅ ይሰማ ነበር።

‹‹ይህ ቀን ለኢትዮጵያ ጥቁር ነው።›› በማለት ለቅሶአቸውን አቁመው ነበር አፄ ምኒልክ ራስ መኮንንን እሥነስተው ያቀፉት። ‹‹ይህ ታማኝ ታዛዥ ነው›› በማለትም ለከፍተኛ ሹማምንቶቻቸው የራስ መኮንንን ታማኝነት መለከሩላቸው። የአፄ ምኒልክ ምስክርነት የራስ መኮንንን ተደጋጋሚ ወቀሳ እና ውንጀላ በመጨረሻም አስቆመ።

በመጨረሻም አፄ ምኒልክ የማጥቃት እርምጃው እንዲቆም አዘዙ። መቀሌ ያለ ምንም መስዋዕትነት ከጣሊያን እጅ የምትወጣበት አንድ አማራጭ ነበር።

የጣሊያን ምሽግ በጉሉም ረገድ እንከን የለሽ አልነበረም። ቋሚ የውሃ አቅርቦት አልነበረውም። የሠራዊቱ ብቸኛ የውሃ አቅርቦት የነበሩት ኹለት ምንጮች ከምሽጉ ውጪ ግራና ቀኝ የሚገኙ ሲኾኑ ከርቀታቸው አንፃር ከምሽጉ ሆኖ ለመከላከል አይቻልም ነበር።

ይህንን ችግር የተረዳው ካፒቴን ቶርኩአቶ ቤኑቺ ምሽግ ውስጥ ኹለት የውሃ ጉድጓድ ያስቆፈረው የምኒልክ ጦር ከመድረሱ አንድ ሳምንት በፊት ነበር። እያንዳንዳቸው 13 ሺህ ጋሎን ውሃ መያዝ የሚችሉ ኹለት ጉድጓዶችን ምሽግ ውስጥ በማስቆፈር በውሃ እንዲሞሉ ተደረገ። በመቀጠልም ለወታደሩ ውሃ በራሽን እንደሚከፋፈል ጥብቅ ማስታወቂያ ተነገረ። በራሽኑ መሠረትም ለጋማ ከብቶች በቀን አምስት ሊትር፣ ለከፍተኛ መኮንኖች ኹለት ሊትር እንዲሁም ለተራ ወታደር አንድ ሊትር ውሃ ብቻ መከፋፈል ተጀመረ።

ጥር 8 ቀን በንግሥት ጣይቱ ሃሳብ አመንጪነት የኢትዮጵያ ሠራዊት ኹለቱን ምንጮች ተቆጣጠረ። ምንጮቹ ከዋናው የምሽግ ክልል ራቅ ብለው





በመገኘታቸው የተነሣ ጣሊያኖቹ ምንጮቹን መጠበቅ አልቻሉም ነበር። በምሽግ ውስጥ የተጠራቀመው ውሃ ሊያልቅ ሲቃረብ የዕለት ራሽኑን በመቀነስ የቀረው ውሃ ለዳቦ መጋገሪያ ብቻ እንዲውል ተወሰነ። ከፍተኛ መኮንኖች በውሃ ምትክ ወይን መጠጣት ጀመሩ።

የውሃውን ምንጭ ከተቆጣጠረ በኋላ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከዋናው መከላከያ አጥር ተጠግቶ ምሽግ መቆፈር ጀመረ። የመድፈኛው ብርጌድ የጣሊያን ወታደሮች በምንም ዓይነት ምሽጉን ለቀው እንዳይወጡ በጥይቱ አስቆማቸው። በጭለማ ብቻ እየተንቀሳቀሱ እስከ ዋናው አጥር የሸቦ መከላከያ መጠጋት የቻሉት የኢትዮጵያ ወታደሮች በጣሊያን ምሽግ ውስጥ የነበሩትን ባንዳ ወታደሮች ማስጠንቀቅ ጀመሩ። ባንዳዎቹ ከቻሉ ራሳቸውን እንዲያተርፉ ነገር ግን ከጣሊያን ጎን ሆነው መዋጋት ከቀጠሉ ከፍተኛ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው ነበር ያስጠነቀቋቸው።

በመከላከያው አጥር ውስጥ የነበሩት የጣሊያን ባንዳ ወታደሮች በውኃ ጥም መሰቃየት የጀመሩት ዕለታዊ የውኃ ራሽናቸው ወደ ኹለት ኩባያ ዝቅ እንዲል ከተወሰነበት ጥር 13 ጀምሮ ነበር። በጉድጓድ የነበረው ውኃ በርካታ ነፍሳት እና ትሳትል ስለረባበት ከጥር 17 ጀምሮ ለወታደሩ ይታደል የነበረው የተበከለ ውኃ ነበር።

በኢትዮጵያ ሠራዊት ተከብቦ በምሽጉ አጥር ውስጥ የነበረው ጀነራል ጋሊያኖ ብቸኛ ተስፋው ባራቴሪ ደጋፊ ኃይል በመላክ ሊያተርፈው እ ሚችል ነበር። የባራቴሪ ኹለት ባታሊዮን ጦር ጥር 9 ቀን አዲግራት ቢደርስም ወደ መቀሌ በመዝመት የጋሊያኖን ጦር የማትረፍ ዕቅድ አልነበረውም። ባራቴሪ የአምባላጌውን ሽንፈት ደግሞ መቀሌ ላይ ማየት ካልፈለገ የነበረው ብቸኛ አማራጭ ከምኒልክ ጋር መደራደር ነበር።

አፄ ምኒልክ በበኩላቸው ከጊዜ ጋር ትግል ላይ ነበሩ። የያዙትን ግዙፍ ሠራዊት ለብዙ ቀናት መመገብ አይችሉም። በመሸኑም በፍጥነት መንቀሳቀስ ካልቻሉ በርካታ ወታደሮቻቸውን በርሃብ እና ጥማት ሊያጡ ይችላሉ።

## የተራበ የይሁዳ አንበሳ ሲሳይ

ጣሊያን ለሽምግልና የመረጠችው ፒየትሮ ፌልተርን ነበር። ፌልተር ለመጀመሪያ ጊዜ በ1881 ወር ኢትዮጵያ የመጣ ሲሆን ለዓመታት በንግድ ሥራ በመቅየቱ ከጣይቱ፣ ምኒልክ እና ራስ መኮንን ጋር መቀራረብ ችሏል። ለድርድሩ አመቺ እንዲሆን ፒየትሮ ወደ ምኒልክ የጦር ሰፈር ያመራው ጀነራል ጋሊያኖን ይዞ ነበር።

ፒየትሮ በድንኳናቸው ያገኛቸው አፄ ምኒልክ በጣም ተቀይረው ነበር። በጠይም ፊታቸው ውትሮም አስፈሪ ምገስን ይሰጣቸው የፈንጣጣ ምልክት የባሰ አፍጥጦ ይታይ ነበር። በጦርነቱ አስጨናቂነት «የበሰጠ ጠቁረው እና አስፈሪ ሆነው» እንዳገኛቸው ተናግሯል። በይሁዳ አንበሳው ፊት ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበው ጋሊያኒ የተቆጡት የአንበሳ ሲሳይ ሊያደርጉት እንደሚችሉ በማሳብ በፍርሃት ተብረከረከ።

ጋሊያኖ ለመብረክረኩ ምክንያት ነበረው። በመቀሌ ላለቀው በርካታ የኢትዮጵያ ሠራዊት ኃላፊነቱን የሚወስደው እርሱ ነበር። «ለመሸኑ ይዜን ሰው ፊቲ ያመጣኸው ለምንድን ነው?» በማለት ነበር በቁጣ የነደዱት አፄ ምኒልክ ፊልተርን የጠየቁት። ፌልተርም በከፍተኛ ትሕትና የእርሳቸው አንድ ጀነራል በጣሊያኑ ንጉሥ ፊት ቢቀርብ በከፍተኛ አክብሮት እንደሚቀበሉት በማስታወስ ንጉሥ የንጉሥን መልዕክተኛ የሚያከብረው እንደ ንጉሥ መሸኑን በተግፅኖ ገለጸላቸው።

አፄ ምኒልክ ለአንዱ አሻቢያቸው በጆሮው የሸነ ነገር ተናገሩ። አሻቢው ድንኳኑን ለቅቆ ወጣና በፍጥነት አንድ ኮርቻ የተጫነ በቅሎ ይዞ ተመለሰ። ስለ በቅሎው ሲናገር ፊልተር «በሕይወቴ እንደዚያ ያማረ በቅሎ ተመልክቼ አላውቅም። የንጉሡ የራሳቸው መሆን አለበት» ብሎ ነበር።





«ውድ ፌልተር፤ እንደምታውቀው እኛ ድሀ ሕዝቦች ነን። ይህ ስጦታ ወዳጅህ ጋሊያኖን እንደሚያስደስተው አልጠራጠርም» በማለት ምኒልክ በቅሎውን ለጋሊያኖ ሰጡት። ንጉሡ አፋቸውን በጋቢያቸው ሲሸፍኑ ንግግራቸው የመጨረሻ መሸኑን አመላከተ። ጋሊያኖ ምንም ቃል ሳይተነፍስ የቀረበለት በቅሎ ላይ ወጥቶ ወደ መቀሌ ሸምጥ ጋለበ።

አፄ ምኒልክ እና ፊልተር ስምምነት ላይ የደረሱት ጥር 19 ቀን ነበር። አፄ ምኒልክም ጋሊያኖ እና ሠራዊቱ ምሽጉን ለመልቀቅ ከተስማሙ ከነመላ ጓዛቸው፣ ትጥቃቸው፣ ሴቶቻቸው እና ልጆቻቸው እንደሚለቋቸው ተስማሙ። ጥር 20 ቀን ጋሊያኖ በመቀሌው መከላከያ ግንብ አናት ላይ ነጭ ሰንደቅ እንዲውለበለብ አዘዘ።

የጋሊያኖ ወታደሮች በኢትዮጵያ ሠራዊት ጥበቃ ሥር ሆነው እንደሚጓዙ ምኒልክ አስገነዘቡ። የጋሊያኖ ወታደሮች ጓዛቸውን ለመጫን በቂ የጋማ ከብት ስላልነበራቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ በቅሎዎችን ከምኒልክ ጦር ለመዋስ ተገደዱ። ለኪራይ ክፍያም ሐያ አምስት ሺህ ሊሬ ለመክፈል ሀሳብ አቀረቡ።

ጥር 21 ቀን የጋሊያኖ ሠራዊት ምሽጉን ለቅቆ መውጣት ሲጀምር ለወራት የዘለቀው ፍጥጫ ፍፃሜ አገኘ። ምሽጉ ሙሉ በሙሉ እንደተለቀቀ የኢትዮጵያ ሠራዊት በሰዓታት ውስጥ አፈራረሰው። ዋናው የምሽጉ ማማ ላይም የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተሰቀለ።

የጋሊያኖ ሠራዊት በሰላም መውጣት ዜና በጣሊያን ሲሰማ ከፍተኛ ደስታ ተፈጠረ። በርካታ የጣሊያን ጋዜጦች ዜናውን እንደ ከፍተኛ ድል ነበር የተገነዘቡት። ጋሊያኖም ከፍተኛ የደረጃ ዕድገት አገኘ። በጣሊያን ከነበረው በተቃራኒ ግን የተለያዩ የአውሮፓ ጋዜጦች ጣሊያንን አንኳሰው ነበር የፃፉት። የፈረንሳዩ «ሌ» ፔቲት ጀርናል ጋዜጣ የጠቅላይ ሚኒስትር ፍራንሴስኮ ክሪስፒን ምስል በኮርቱን የፊት ገፁ ላይ ያወጣው ከአፄ ምኒልክ ጋር በማያያዝ ነበር። በምሳሉ ላይ ወታደራዊ ልብስ

የለበሰው ክሪስፒ የምኒልክን ጥቁር ዓይን በፍርሃት ሊመለከት ይታያል። በርካታ የዓለም ጋዜጦች ይህንኑ ምስል ተቀባብለውታል።

የንጉሥ ኡምቤርቶ ወዳጅ የነበሩት የደርመኑ ንጉሥ ካይዘር ዊልሽልም የእንኳን ደስ ያለህ መልዕክታቸውን በፍጥነት ነበር ለጣሊያኑ አቻቸው የላኩት። ከደስታ መግለጫቸው ጋር አያይዘውም ጋሊያኖን ለመሸለም ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን ጋሊያኖ እና ባራቴሪ የጥንት የሮማውያንን ገድል መድገማቸውን አወድሰዋል።

ጋሊያኖ የተበረከተለት ሽልማት እና ዝና ከሠራው አንፃር ሲታይ ተገቢው አልነበረም። ነገር ግን በጥቂት ሠራዊቶቹ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የአፄ ምኒልክ ሠራዊት መቀሌ ላይ በማቆም ለባራቴሪ ጊዜ መግዛት ችሏል። ባራቴሪም ጊዜውን ተጠቅሞ አዲግራትን ለመያዝ ችሏል።

አፄ ምኒልክ የሰሜኑን ጉዞ የጀመሩት ጥር 22 ሲሆን የጋሊያኖን ሠራዊት በመያዝ ነበር የተንቀሳቀሱት። በሠራዊታቸው አሰላለፍ ከፊት የመንገሻ ሠራዊት ሲቀድም በመቀጠል ደግሞ የጋሊያኖ ሠራዊት ይከተላል። ዋናው የምኒልክ ሠራዊት ደግሞ ከጋሊያኖ ቀጥሎ የሚንቀሳቀስ ሲሆን መቀሌ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት የራስ መኮንን ጦር የኋላ ደጀን በመሆን ምኒልክን ይከተላል።

ከመቀሌ በኋላ ባለው ጉዞ በምኒልክ ጦር እና አዲግራት ላይ በመሸገው የባራቴሪ ጦር መካከል ምንም መከላከያ አልነበረም። ለሠራዊታቸው ደኅንነት ሲሉ ነበር የጋሊያኖን ጦር ከጦራቸው ጋር ቀላቅለው ሰመጓዝ የወሰኑት። ከመቀሌ የተማሩት ነገር ቢኖር ከመሸገ ጠላት ጋር መዋጋት ከፍተኛ መስዋዕትነት እንደሚያስከፍል ነበር። የጋሊያኖን ሠራዊት እስከያዙ ድረስ ግን ባራቴሪ ጥቃት እንደማይከፍት ያውቃሉ።

አዲግራት ከመድረሳቸው በፊት ነበር አፄ ምኒልክ ሠራዊታቸውን አጉላ ላይ ለሹሰት ቀናት ያሳረፉት። ከእረፍት በኋላ ጉዟቸውን ሲቀጥሉ ግን በአዲግራት የሚያልፉ አስመስለው ወደ ምዕራብ ነበር ያመሩት። ጥር 29 ቀን ሃውዜን ላይ





በማረፍ ወደ አዲግራት የሚወስደውን የሰሜን አቅጣጫ በመተው ወደ አድዋ የሚወስደውን የምዕራብ መንገድ ተያያዙ።

ሠራዊታቸው አዲግራትን ወደ ኃን ትቶ ባለፈበት ወቅት በቦታው የነበረው ባራቴሪ ሊለነዘር ከሚችለው ጥቃት ለመከላከል እንደ ጥይት አብራጅ ያዘጋጁት የጋሊያኖን ጦር ነበር። ጥር 30 ቀን የጋሊያኖን ሠራዊት በመልቀቅ ከባራቴሪ ጋር እንዲቀላቀሉ አደረጉ። ጋሊያኖን ጨምሮ ዐሥር ከፍተኛ መኮንኖች ግን አብረዋቸው ለጥቂት ቀናት እንዲቆዩ ምኒልክ ወሰኑ።



Menelik, the Lion of Judah. Photograph taken by Alfred Ilg in 1896. From Völkerkundemuseum der Universität Zürich; credit: © Völkerkundemuseum der Universität Zürich, VMZ Sammlung.

***ምስል። የይሁዳ አንበሳ - ፋንሞዊ አፄ ምኒልክ (ለልፍሬድ ኢልግ በ1896 ካነሳው ፎቶግራፍ የተወሰደ)***



Menelik, the Lion of Judah. Photograph taken by Alfred Ilg in 1896. From Völkerkundemuseum der Universität Zurich; credit: © Völkerkundemuseum der Universität Zürich, VMZ 805 (1896).

**ምስል፡- የይሁዳ አንበሳ - ቋንቋዊ አፄ ምኒልክ (ሰልፍሬድ ኢልግ በ1896 ካነሳው ፎቶግራፍ የተወሰደ)**

አፄ ምኒልክ አዲግራት ላይ የነበረውን የጣሊያን ጦር አልፈው በመሄድ ቦታ ያዙ። በዚያ ወቅት ነበር ሰላም ወዳድ መሆናቸውን ለአውሮፓውያን በማሳየት የተወረረው ግዛታቸውን በድርድር የማስመለስ ፍላጎት ያሳዩት።

የካቲት 5 ቀን ባራምባራስ አማኑኤልን ወደ ባራቴሪ የላኩት አፄ ምኒልክ ጦራቸውን ከሃውዜን በማንቀሳቀስ በአድዋ አቅራቢያ ወዳለችው ጉንዳብታ እንደሚያመሩ ገለፁ። በጉንዳብታ ለአምስት ቀናት በመቆየትም ከጣሊያን ልዑካን ጋር ስመደራደር ፈቃደኛ መሆናቸውን ለባራቴሪ አሳወቁ።

በወቅቱ ከመቶ ሺህ በላይ የሆነ ሠራዊታቸውን ወደ ኤርትራ ለማዝመት ዝግጁ የነበሩት አፄ ምኒልክ 17ሺ ሠራዊት ብቻ ካሰለፈው ባራቴሪ ያገኙት ምላሽ ያልጠበቁት ነበር። ባራቴሪ በመልዕክተኛው ቶማስ ሳልሳ በኩል ለምኒልክ አቋሙን የገለጸው በኹለት ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ተመሥርቶ እንደሚደራደር ነበር። ይኸውም ኢትዮጵያ የውጫሌ ስምምነትን ሙሉ በሙሉ እንድትቀበል እና ጣሊያን ለያዘቻቸው አዳዲስ የኢትዮጵያ ግዛቶች የባለቤትነት ዕውቅና እንድትሰጥ የሚጠይቅ ነበር።

የባራቴሪ ቅድመ ሁኔታ በኢትዮጵያውያኑ ዘንድ ከፍተኛ ቁጣ ቀሰቀሰ። በተሰይ ጣይቱ፣ ወሌ፣ አሉላ እና መንገሻ እጅግ በጣም ነበር የተበሳጩት። ምኒልክ ለባራቴሪ በሰጡት ምላሽም ኹለት ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀመጡ። ይኸውም ጣሊያን የያዘችውን የኢትዮጵያ ግዛት እንድትለቅ እንዲሁም የውጫሌው ስምምነት ሙሉ በሙሉ እንዲስተካከል የሚጠይቅ ነበር።

የአምባላጌ እና የመቀሌውን ኹነት ተከትሎ ኢትዮጵያ ሙሉ የመደራደር ብቃቷን ስታስመሰክር ባራቴሪ በአንፃሩ አጣብቂኝ ውስጥ ነበር የገባው። አገሩ ጣሊያን በመደራደር ከአፄ ምኒልክ ጋር የማትስማማ ከሆነ የሚኖረው አማራጭ ጦርነት በመግጠም ምኒልክን ድል መንሳት ወይም ደግሞ ሽሽቶ በማምለጥ ውርደትን መከናነብ ነበር።





# ምዕራፍ አሥር

## ግራ መጋባት በሳውራ

አፄ ምኒልክ ራሳቸውን ለጦርነት ከማዘጋጀት ጎን ለጎን አልፍሬድ ኤልግ የጂፓሎማሲ ዘመቻውን በአውሮፓ እንዲያፋፍምላቸው ላኩት። ኤልግም ለአውሮፓውያን በራሳቸው ቋንቋ ስለ ኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁኔታ ሲገልፅ ከረመ። የውጫሌ ስምምነት የጣሊያን የማጭበርበሪያ መንገድ መኾኑንም በተለያዩ ጋዜጦች ሲፅፍ *«ለበርካታ ክፍለዘመናት ነጻነቷን ጠብቃ ስኖረች ለገር ላይ እንዴት መሬት ይኖጠቃል?»* በማለት ጠይቋል።

ለጣሊያናውያንም እንዲሁ መንግስታቸው የተዛባ መረጃ እየሰጠ እንዳሳሳተቸው ለመግለፅ ሞክሯል። ወጣት ጣሊያናውያን በማይገባ ጦርነት ላይ ሕይወታቸውን ማጣት እንደሌለባቸውም ኤልግ ቀስቅሷል።

የጣሊያን ጦር በአዲግራት ከፍተኛ ምሽግ ገንብቶ መጠበቁን ምኒልክ እንደማያውቁ እና የተሻለ የውጊያ ዕቅድ እንዳላቸውም ለአውሮፓውያኑ ግልጽ አድርጓል። አፄ ምኒልክ በአዲግራት የመቀሌውን ስሕተት አይደግሙትም። በመኾኑም አዲራግትን በመተው በራሱ ሰዓት የራሱን መፍትሔ እንደሚፈጥር ማቀዳቸውን ነበር ኢልግ የገለጸው።

በኢትዮጵያ ውስጥ መከፋፈል እና የሥልጣን ሽኩቻ መኖሩን ያልደበቀው ኢልግ የጣሊያንን ወረራ ተከትሎ ኹሉም ኃይሎች ልዩነታቸውን በማቻቻል አንድ ላይ መሰለፋቸውን ለአውሮፓውያኑ የገለጸው በምሳሌ አስደግፎ ነበር። *«ኹለት ውሾች በአንድ አጥንት ሊጣሉ ይችላሉ። ነገር ግን አንድ ጅብ ቅርምቱን ሊቀሳቀል ቢምክር ኹለቱ ውሾች ይተባበሩቢታል።»* በማለት ነበር ኢልግ ስለ ኢትዮጵያ ውስጣዊ የፖለቲካ ሽኩቻ ያስረዳው።

አውሮፓውያን የኢትዮጵያን ነጻነት ከራሳቸው አንፃር እንዲመለከቱም ኤልግ ጥሪ አቅርቧል። የአገሪቷን ሉዓላዊ እኩልነትም ሲገልፅ ‹‹ማንም ለአውሮፓዊ ለኢትዮጵያ መገዛር እንደማይፈልግ ሹሉ ሉዐላዊት ኢትዮጵያም ለአውሮፓ ኃያላን የምትገብርበት አግባብ የለም›› ብሏል።

በ19ኛው ክፍለዘመን የነበረው የጦርነት ስሌት በሠራዊት ብዛት እና ወታደራዊ ጥራት ላይ የተመሠረተ ነበር። አፍሪካውያን ከአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች የተሻለ ብዙ ሠራዊት የመመልመል ብልጫ ሲኖራቸው አውሮፓውያኑ ያሰባቸውን የሰው ኃይል አናሳነት ለማካካስ ዘመናዊ ሥልጠና እና የጦር መሣሪያ ብልጫቸውን ይጠብቃሉ። ምኒልክ ለጦርነት የተዘጋጁትም ይህንን ስሌት ቀድመው በመረዳት ነበር። የእርሳቸው አፍሪካዊ ሠራዊት በሥልጠናም ሆነ በትጥቅ የአውሮፓውያንን ያህል የላቀ ባይሆንም ምንም የማያውቅ ግን አይደለም። አብዛኛው የሠራዊት አባል ከምኒልክ ጋር ወደ ወላይታ እና ሌላ ግዛቶች በመዝመት ልምድ ያካበተ ነው። ልምድ የሌለው ወታደርም ቢኖር እንኳን ራሱን ለአውሮፓውያን ጥይት መስዋዕት ለማድረግ የተዘጋጀ ነው። ጦሩ በተለይም ከአምባላጌ እና መቀሌ በኋላ በጠላት ላይ ያለው አቋም ጠንካራ እና ከክብር ጋር የተቆራኘ ሆኗል።

የምኒልክ ጦር ዘመናዊ አደረጃጀት እንዳለው ባራቴሪ ላይቀር መስክሮለታል። ስለ ሠራዊቱ ለጣሊያን መንግሥት በላከው ማብራሪያ ሲጠቅስ ‹‹... የአገሪቷ ጦር በይዘቱም ሆነ በመጠኑ በ1888 ከነበረው ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል።›› በማለት መስክሯል። ከሠራዊቱ ብዛት በተጨማሪ የምኒልክ ወታደሮች ፈረንሳይ ሠራሹን ሆችኪስ መድፍ ጨምሮ በርካታ ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቁ ሲሆን በዚህም ከጣሊያን ትጥቅ የላቁ ነበሩ።

ከወታደራዊ ቁጥር እና ትጥቅ ብልጫው በተጨማሪ የምኒልክ ጦር በቦታ አያያዝ ከባራቴሪ የተሻለ ሆኖ ታይቷል። አዲግራት ላይ ጣሊያንን በመግጠም





ሠራዊታቸውን ማስፈጀት ያልፈለጉት አፄ ምኒልክ የባራቴሪን የአዲግራትን ምሽግ ወደ ጎን በመተው ነበር ያለፉት። ምኒልክ የባራቴሪን የግንኙነት መስመር መቁረጥ ከመቻላቸው በዘዘለ መላው ኤርትራን ለመቆጣጠር የሚያስችላቸውን ቦታ ለመያዝ በመንቀሳቀስ ላይ ነበሩ። የምኒልክን ግስጋሴ ለማስቆም ሲል ነበር ባራቴሪ ከመንገሻ ሽንፈት በኋላ ይዞት የነበረውን ግዛት ለመልቀቅ ያስበው።

ባራቴሪ አዲግራት ላይ አነስተኛ ኃይል በማስቀመጥ ጦሩን ምኒልክ በዜደበት አቅጣጫ ከአዲግራት ወደ አድዋ በመምራት አለቃን ተቆጣጠረ። ምኒልክም ከባራቴሪ እየራቁ ወደ አድዋ ሲቃረቡ ባራቴሪ መከተሉን ቀጠለ። ከዙሰት ቀናት በኋላ የካቲት 3 ቀን ባራቴሪ ከእንጪቾ ከተማ አጠገብ ሳውራ ላይ ጦሩን አሳረፈ። ምኒልክ ደግሞ የካቲት 5 ቀን ጉዳበታ ላይ ጦራቸውን በማደራጀት የሰላም ድርድር ጥሪ በድጋሚ አደረጉ።

በየካቲት ወር 1896 የኢትዮጵያ እና የጣሊያን ጦር በአዲግራት እና አክሱም መሃል ነበር የተፋጠጡት። የምኒልክ ጦር ከነበረበት ጉንዳብታ እስከ ባራቴሪ የጦር ሰፈር ኢንጪቾ ድረስ ያለው ሜዳማ ስፍራ ዙሰት በአምስት ማይል ስፋት ነበረው። ሜዳው ዙሪያውን በተፈጥሮ ሰንሰለታማ ተራሮች የታጠረ ነው። ምኒልክ በምዕራብ አቅጣጫ ያለውን ቦታ ሲይዙ ባራቴሪ ደግሞ ሜዳውን በመሸሽ ምሥራቃዊ ኮረብታውን ይዞ ምሽግ ማስቆፈር ጀመረ።

ዙሰቱ ኃይሎች ሳውራ እና ጉንዳብታ ላይ ቦታ ከያዙ በኋላ ነበር የሰላም ድርድሩን የቀጠሉት። ነገር ግን ከአንድ ሳምንት በኋላ የሰላሙ አማራጭ ተስፋ አስቆራጭ ሆነ። ኢትዮጵያም ለማይቀረው ጦርነት ተዘጋጀች።

**የክፋፍለህ ግዛ መጨረሻ፣ የራስ ስብሃት እና የሓጎስ ተፈሪ መክዳት**

ከአምባላጌ በኋላ በርካታ ጣሊያናውያን ወታደሮችን የጫኑ መርከቦች ወደ ምፅዋ መጓዝ መጀመራቸው ሰባራቴሪ እፎይታን ፈጥሮለታል። በየሳምንቱ በሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮች ምፅዋ እየተራገፉ ነበር። በየካቲት ወር መጨረሻ ላይ ብቻ ሲንጋፖር፣ አንድሪያ፣ ጎታርዶ፣ ዋሽንግተን፣ ሩባቲኖ እና ሚንጌቲ የተባሉ ስድስት መርከቦች ምፅዋ ደርሰዋል።

ጣሊያን ሠራዊት በኩል የተወሰኑ ችግሮች ነበሩ። የመጀመሪያው በጦር ግንባር ያለውንም ሆነ ከምፅዋ ወደ አዲግራት የሚመጣውን ሠራዊት መመገብ ነበር። ከአስመራም ሆነ ከሌሎች አካባቢ በቂ ምግብ ማቅረብ ስላልተቻለ ሥጋ ይመጣ የነበረው ከሀንድ ሲሆን ሌላ አቅርቦት ደግሞ በቀጥታ ከጣሊያን ነበር የሚመጣው። ከምፅዋ ወደ መሃል አገር የሚደረገው የማጓጓዝ ተግባር የራሱ የሆነ ችግር ነበረበት። ከምፅዋ እስከ አስመራ በአነስተኛ ባቡር የተጓጓዙ አቅርቦት እና ወታደሮች ከአስመራ ወደ አዲግራት ደግሞ ይጓዙ የነበረው በጋማ ከብቶች ነበር።

ወደ አዲግራት የሚደረገው ቁሳቁስ ማጓጓዝ ከጋማ ከብት አጥረት በተጨማሪ በሸፍታ ይስተጓጎል ነበር። ከምፅዋ የሚነሱ ተጓዦች አዲግራት ለመድረስ ኢላልያ፣ ማህሎ፣ አዲ ቀይህ፣ ሰንአፈ፣ ባራኺትን እና አዲ ጉደምን ማለፍ የግድ ይላቸዋል።

የባራቴሪ ጦር እንደ ምኒልክ ኹሉ የማፈንገጥ አደጋ አጋጥሞታል። መንገሻ ያስከረፏቸውን ኹለት የአጋሜ አካባቢ አስተዳዳሪዎች (ራስ ስብሃትን እና ሓጎስ ተፈሪን) መመልመል ችሉ ነበር። ኹለቱም የአጋሜን ግዛት በተለያዩ ጊዜያት ካስተዳደሩ ቤተሰቦች የተገኙ ሲሆን በ1895 ባሥነሱት የእርስ በእርስ ግጭት ኹለቱን በማባረር ከግዛት አስተዳዳሪነታቸው ያነሳቸው መንገሻ ነበር።





የሸከረ ግንኙነታቸውን ለማለዘብ መንገሻ ኹለቱንም አኩራፊዎች ወደ አድዋ ጋበዛቸው። ሓጎስ ተፈሪ ተጠራጥሮ ሲቀር ራስ ስብሃት ግን ሄደ። በግብዣው መሃል ግን ራስ ስብሃት በመንገሻ ወታደሮች ታሰረ።

በኋላም ራስ ስብሃት በግዞት ወደ አምባላጌ ተልኮ ታሰረ። ራስ ስብሃት ከአምባላጌ እሥር ቤት በጥቅምት 1895 የተለቀቀው ጦሊያኖች ምህረት ነበር። ከሳምንት በኋላ ከጣሊያን ጎን ሆኖ መንገሻን መውጋት ጀመረ።

በመንገሻ ጭካኔ የተበሳጨው ሓጎስ ተፈሪም ከጣሊያን ጋር በመወገን መንገሻን ሲወጋ ቆይቷል። በ1895 ሰንአፈ ላይ መንገሻ ሲሸነፍ በርካታ የጦር መሣሪያ፣ የቁም ከብት እና የተለያዩ ንብረቶችን ከሸሸው ጦር ላይ በመዝረፉ ሃይሉን አጎልብቷል። በ1895 የመጨረሻ ወራት ላይ ኹለቱ ኢትዮጵያውያን ከጣሊያን ጎን ተሰልፈው ነበር።

ራስ ስብሃትን እና ተፈሪን ከጎኑ ማሰለፍ የቻለው ባራቴሪ የ‹‹ክፋፍለህ ግዛ›› ዕቅዱን ለማሳካት አንድ እርምጃ መራመድ ችሏል። የመንገሻን ኃይል በማሳሳትም የራሱን የሠራዊት ቁጥር ከፍ ከማድረግ አንፃርም የኹለቱ ተከታዮች ከጦሩ ጋር መቀላቀል አስተዋፅኦ አድርጎለታል።

ራስ ስብሃት እና ሓጎስ አጋጣሚውን ለመጠቀም እንጂ ከባራቴሪ ጋር የወገኑት በእርግጥም ከሃዲዎች ሆነው አልነበረም። ከአምባላጌ እና መቀሌ ዘመቻዎች በኋላ በተለይም በየካቲት ወር ላይ የምኒልክን እንቅስቃሴ ከተመለከቱ በኋላ ነበር ባራቴሪን ለመክዳት የወሰኑት። በመኾኑም የካቲት 13 ቀን ኹለቱም ወታደሮቻቸውን ከነ ሙሉ ትጥቃቸው በማስኮብለል የጣሊያንን ካምፕ ሰቀቁ።

የእነ ስብሃት ሠራዊት ምኒልክ ካምፕ ሲደርስ የጀግና አቀባበል ነበር የተደረገለት። ስብሃት እና ተፈሪም ከፍተኛ ውዳሴ ተደረገላቸው። ባራቴሪ የገመተው

ኹለቱ የካዱት መንገሻ ዮሐንስን በመሾኑ በምንም መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ሠራዊት እንደማይቀላቀሉ ነበር። የሠራዊቱ ወደ ምኒልክ መመለስ የኢትዮጵያን ውስጣዊ መረጋጋት ያረጋገጠ ሲሆን የባራቴሪን ከፋፍሎ የመግዛት ዕቅድም ጥያቄ ውስጥ ከተተው።

### የጣሊያን ይዞታ መፍረክረክ

የራስ ስብሃትን እና የተፈሪን መክዳት ተከትሎ የኢጋሜ አካባቢ ነዋሪዎች በጣሊያን ላይ ማመፅ ጀመሩ። በርካቶችም ኹለቱን በመከተል የክዳውን የሠራዊት ቁጥር በሦስት እጥፍ ከፍ አደረጉት። የባራቴሪን ካምፕ ለቀው በወጡ በአምስተኛው ቀን በምኒልክ አበረታችነት የስብሃት እና ተፈሪ ሠራዊት የባራቴሪ የግንኙነት መስመር ላይ የምትገኘውን ባራኪት ከተማ ለመቆጣጠር ተንቀሳቀሱ።

በአዲግራት ዙሪያ የነበረው የሳውራ ጦር ካምፕ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰበት። የካቲት 14 ቀን 110 የጣሊያን ወታደሮች ላይ ጥቃት የተሰነዘረ ሲሆን ድጋፍ ለመስጠት ባራቴሪ የላካቸው 35 ወታደሮች በሙሉ ተገደሉ። የካቲት 16 ቀን የምኒልክ ታማኞች በአዲግራት አቅራቢያ በመመሸግ ከአስመራ ወደ አዲግራት በመንገዝ ላይ የነበረውን የጣሊያን ስንቅ እና ትጥቅ ዘረፉ። በዘረፋ ያገኙትን የጣሊያን ዮኒፎርም በመልበስ ተመሳስለው በመጠበቅም በቀጣዩ ቀን ለቅኝት በወጡ 140 የጣሊያን ወታደሮች ላይ ጥቃት ፈፀሙ።

የዘረፋ ጥቃቱን ተከትሎ ባራቴሪ የግንኙነት መስመሩን በመቀየር የማይመራት እና የደብረዳሞን መንገድ ለመጠቀም ወሰነ። የእነ ስብሃትን መክዳት ቀድሞ የሰማው የደብረዳሞ አካባቢ ነዋሪም ባራቴሪ ላይ በማመፅ ለምኒልክ ታማኝነቱን አረጋገጠ።

የምኒልክ ታማኞች በአዲግራት እና ሳውራ መካከል በመመሸግ የጣሊያንን ወታደራዊ ትጥቅ እና ስንቅ አቅርቦት ማጥቃት ጀመሩ። ጣልያናውያኑ በጭለማ





መንቀሳቀስ ቢጀምሩም የሽምቅ ተዋጊዎች ጥቃታቸውን ቀጠሉ። የስንቅ አቅርቦቱ በመስተጓጎሉም የጣሊያን ወታደሮች በየኹለት ቀናት ብቻ በሚሰጥ የዱቄት፣ ሥጋ እና ቡና ራሽን ለመኖር ተገደዱ። ለባንዳ ሠራዊት ቀድሞ ለጋማ ከብት ይቀርብ የነበረው ንብስ መታደል ጀመረ።

ሠራዊቱ በምግብ እጥረት መቸገር የጀመረው በየካቲት ወር የመጨረሻ ሳምንት ነበር። የተወሰኑ ባንዳ ወታደሮች አጋጣሚውን በመጠቀም ለጣሊያን ወታደሮች ምግብ በመሸጥ ገንዘብ ማግኘት ጀመሩ። ሎጂ ጎጂ እና ካርሎ ዲዮቲ እንደተናገሩት ሠራዊቱ የምግብ መጋዘኖችን መስበር ጀምሯል። ከምግብ አቅርቦት ችግር ጋር በተያያዘ በሠራዊቱ መካከል የዲሲፕሊን ችግር ተፈጠረ።

ባራቴሪ ለጣሊያን የጦር ሚኒስቴር ስታኒስላኦ ሞቼኒ የካቲት 18 ቀን በላከው ቴሌግራፍ ‹‹የስብሃት እና ሓጎስ ሠራዊት በአዲግራት ዙሪያ መሽጓል›› በማለት በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለበት ጠየቀ። ሚኒስትሩ በላኩት ምላሽ ‹‹የተሻለ አማራጭ የምትለውን አሳውቅ። አስፈላጊውን ድጋፍ እናደርግልሃለን›› በማለት የመንግስታቸውን አቋም አሳወቁ።

የጦር ሚኒስትር ሞቼኒ በርካታ ወታደሮች ለባራቴሪ ሲልኩ ቆይተዋል። በዚያው ዓመት የጦርነቱ ወጪ በመብዛቱም ከገንዘብ ሚኒስትሩ ሊድኒ ሶኒኖ ብርቱ ተቃውሞ ሲሰነዘርባቸው ቆይተዋል። የጦርነቱን ወጪ ለመቀነስ የሚቻለው ውጊያው ከአንድ ወር በላይ እንዳይወስድ በማድረግ መሾኑን ሞቼኒ ለሚኒስትሩ ገልፀውላቸው ነበር። ጦርነቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በድል ማጠናቀቅ የጣሊያን ብርቱ ፍላጎት ነበር።

# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## የባራቴሪ አማራጭ

ኦሬስቴ ባራቴሪ በውጣትነት ዘመኑ አገሩ ጣሊያንን ከወራሪው የኦስትሪያ መንግሥት ነፃ ለማውጣት ታግሏል። በነጻነት እንደማያምን የሚነገርለት አርበኛው ባራቴሪ የኢትዮጵያን ነጻነት መጋፋቱን እንዴት እንደተመለከተው ማንም አያውቅም። አገሩ ነጻነት ታግላ ከኦስትሪያ ነፃ ካወጣች በኋላ በቀጥታ የተሳተፈው ሌላ ነፃ አገራትን በመውረር ግዳጅ ላይ ነው።

በወርኃ የካቲት 1896 ትግራይ-ሳውራ ላይ የነበረው ባራቴሪ በሞት ሽረት አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ ነበር። በኢትዮጵያ ላይ የተደረገውን ወረራ መሳው ዓለም ማውገዝ የጀመረበት ወቅትም ነበር። በተመሳሳይ ወቅት አፄ ምኒልክ ግዛታቸውን ከወራሪ ኃይል ለመከላከል ጦራቸውን አዝምተዋል። አልፍሬድ ኢልግ ለአውሮፓውያን ያስተላለፈው መልዕክት ትክክል ነበር። አንድም አውሮፓዊ አገር ለኢትዮጵያ ለመገበር እንደማይሻ ኹሉ ኢትዮጵያ እንድትንበረከለት የሚሻ ኃይል መኖር ነበረበት?

በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘው የጣሊያን ወራሪ ጦር በትግራይ ቆይታው በምኒልክ የጦር አሰላለፍ እየተበለጠ ነበር። የባራቴሪን ዕቅድ ቀድመው የተረዱት አፄ ምኒልክ ባራቴሪን አዲግራት ላይ ለመግጠም አልሞከሩም። ከዚያ ይልቅ ወደ ስሜን ምዕራብ በመንቀሳቀስ ቦታ ይዘው ባራቴሪን ለመጠበቅ ነበር የወሰኑት። ምኒልክ ያሳዩት ብልጫ በባራቴሪ የበታች መኮንኖች ዘንድ ፍራቻን ፈጠረ።

የመኮንኖቹን ተቃውሞ ለማፈን ይረዳው ዘንድ ባራቴሪ ወታደሩን ሳውራ ላይ ምሽግ በመቆፈር ሥራ ጠመደው። ጦሩ ምሽጉን ቢያጠናክርም የግንኙነት መስመሩ





በምኒልክ ስተቋረጠበት ለስንቅ እጥረት ተጋልጧል። የምኒልክ ግዙፍ ሠራዊት በአካባቢው ነዋሪ እየተቀሰበ ስለነበር ከስንቅ ጋር የተያያዘ ችግር አልጋጠመውም።

የምኒልክ ሠራዊት ከመቀሌ ተንቀሳቅሶ ጉንዳብታ ላይ ከመሸገ በኋላ መጠነኛ የስንቅ ችግር ገጥሞት ነበር። ይህንን ለመፍታትም የተወሰኑ ወታደሮች አስክ አድዋ በመግዝ ከገበሬው ላይ ቀሰብ ለመሰብሰብ ችለዋል። የስንቅ አቅርቡቱ አስተማማኝ ባለመኾኑ ምኒልክ ከጊዜ ጋር ግብግብ ገጥመው ነበር።

ባራቴሪን ያስጨነቀው የአቅርቦት ችግር ብቻ አልነበረም። ጠቅላይ ሚኒስቴር ክሪስፒ በተደጋጋሚ የሚልካቸው ቴሌግራሞች ከፍተኛ ጫና ፈጥሮበታል። ለመጨረሻ ጊዜ የላከለት ቴሌግራም በተለይ ማስጠንቀቂያ አዘል ነበር። *«የመደቅኸውን ኹለት ብርጌድ ሠራዊት እና አስፈላጊ ለቅርቦት ልክንልሃል። በአምባላጊ እና መቀሌ የተከለተውን ዓይነት መርደት ጣሊያን እና ንጉሡ መሰማት አይፈልጉም»* በማለት ነበር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያስጠነቀቁት።

ከሮም በተጨማሪ ከባራቴሪ ሥር ከነበሩ አራት ጀነራሎች መካከል ሦስቱ አለቃቸውን መቃወም ጀምረው ነበር። አራቱ ጀነራሎች ማለትም ለቤርቶኒ፣ አሪሞንዲ፣ ዳቦርሚዳ እና ኢሌና ከጣሊያኗ ፕድሞንት ግዛት የተገኙ የመሳፍንት ልጆች ሲኾኑ ከዝቅተኛ ቤተሰብ ለተገኘው አለቃቸው ባራቴሪ ያላቸው ንቀት በግልጽ ይታይ ነበር።

የባራቴሪ እና አሪሞንዲ ግንኙነት በተለይ የከፋ ነበር። ባራቴሪ ወደ ሮም በተንዙበት ወቅት አሪሞንዲ ጦሩን በደርቪሽ ላይ አዝምቶ አቅርሳት ላይ ድል ማድረግ ችሎ ነበር። ድሉን ተከትሎ ከሮም የማዕረግ ዕድገት የተደረገለት ሲሆን እድገቱን ተከትሎ በኹለቱ መኮንኖች መካከል ግልጽ መናናቅ መታየት ጀመሯል።

በአምባላጌ የተሸነፈው ጀነራል ቶሴሊ ለሽንፈቱ እንደዋና ምክንያት ሰሮም ያቀረበው አለቃው ጀነራል አሪሞንዲ ተገቢውን ትዕዛዝ በፍጥነት አለማስተላለፉን ነበር። ይህንን ተከትሎም በሮም የአሪሞንዲ ተቀባይነት ቀነሰ። ባራቴሪም በአሪሞንዲ እዝ ሥር የነበሩትን የባንዳ ሠራዊት አባላት ወደ ጀነራል ማቲአ አልበርቶኒ እዝ አዞረ።



Matteo Albertone. From *L'Illustrazione Italiana*, 19 January 1896.

*ምስል፦ ማቲአ አልበርቶኒ (ከ ሳኢሉስትራዚዮኔ ኢታሊያና ጋዜጣ የተወሰደ) (ጥር 19 ቀን 1896)*





አልበርቶኒ ለመጀመሪያ ጊዜ ኤርትራን ያየው በ1885 ነበር። በወቅቱ የቅኝት ሥራውን ጨርሶ ወደ ጣሊያን የተመለሰ ሲሆን በ1895 ሙሉ በሙሉ በኤርትራ ከመመደቡ በፊት ለሹለተኛ ጊዜ በ1888 ኤርትራ ተመድቦ ነበር።

ጀነራል ቪቶሪዮ አማኑኤል ዳቦርሜዳ በባራቴሪ ሥር ካሉት መከንኖች መካከል የተሻለ የዲፕሎማሲ እና ወታደራዊ ሳይንስ ዕውቀት ነበረው። በተግባር የተፈተነ ወታደራዊ ብቃት ባይኖረውም በሥሩ ለነበሩ መከንኖች የሚያስተላልፋቸው ትዕዛዛት በጥብቅ እንዲከበሩለት ይፈልጋል።

በአፍሪካ የዘመቻ ልምድ ያልነበረው ዳቦርሜዳ በ1896 ጥር ወር ነበር ምፅዋ የደረሰው። ከአድዋ ጦርነት ጥቃት ሳምንታት ቀድሞ የደረሰ ሲሆን በጽሑፍ ከሰፈረ ወታደራዊ ሳይንስ ዕውቀት ውጪ የጦርነት ልምድ አልነበረውም።

ከአራቱ ጀነራሎች ወደ ሳውራ በመምጣት የመጨረሻው ጀነራል ጁሴፔ ኢሴና ነበር። በኢትዮጵያ እና አፍሪካ ምንም ልምድ ባይኖረውም የ56 ዓመቱ ኢሴና ጥልቅ የፖለቲካ ዕውቀት እና የንግግር ችሎታ ነበረው። በጦር ሰፈር ውስጥ በተደረጉ ውይይቶች ሲናገር እንደተደመጠው ከሮም የመጣው የአምባላጌ እና የመቀሌውን ውርደት ለማካካስ ነበር።

አብዛኛው የጣሊያን ወታደር ከመንገሻ ጋር ከተደረገው ውጊያ ጀምሮ ልምድ ያካበተ ሲሆን የመጨረሻውን ውጊያ ለማድረግ ልበ-ሙሉነት ይነበብበታል። ከአምባላጌው ውጊያ በኋላ ከጣሊያን የመጡ አዳዲስ ወታደሮች ውስጣቸው በበቀል እልህ የተሞሉ ናቸው። ከችኩልነታቸው አንፃር ፍፁም የተረጋጋ አመራር በመስጠት ከሚታወቀው ጀነራል ባራቴሪ ጋር መግባባት አስቸግሯቸው ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስቴር ክሪስፒን ጨምሮ የሮም ባለሥልጣናትም ትዕግስት አጥተዋል። ራስ መንገሻን ድል ከነሳ በኋላ ለባራቴረ ልዩ አድናቆት የነበራቸው



Matteo Alaertotte. From *L'Illustrazione Italiana*, 29 January 1899.

ፖለቲከኞች ቀናት በገፉ ቁጥር ባራቴሪ ላይ ያላቸው ዕምነት ቀንሷል። በእገር ውስጥ ያለውን ተቃውሞ ለማርገብ ያግዛቸው ዘንድ ባራቴሪ ተጨባጭ ድል እንዲያስመዘግብ አጣደፉት።

### ሮም ባራቴሪን አባረረች

በባራቴሪ እምነት ያጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ በቦታው ጀነራል አንቶኒዮ ባልዲሴራ እንዲተካ ውሳኔ አስተላለፉ። ባልዴሴራ ሹመቱን በመቃወም ጦርነት በተቃረበበት ሰዓት ባራቴሪን ማንሳት ኪሳራው ከፍተኛ መሸኑን ገለጸ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአቋማቸው በመጽናት ባልዴሴራን አሳመኑት። የካቲት 21 ቀን የሹመት ደብዳቤ የደረሰው ባልዴሴራ ከሹለት ቀናት በኋላ ቢሪንዲሲ በተባለች የእንግሊዝ ደልባ ተሳፍሮ የኤርትራ ጉዞውን ጀመረ።

ከአራት ቀናት በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለባራቴሪ በላኩት ደብዳቤ ቁጣቸውን አበከረው ነበር የገለፁት።

> *ለጠቃሚ ተሰፋህው ወታደራዊ ብዝኃት አንጂ ጦርነት አይመክልም። ጠላቶቻችን ከአኖ በቁጥርም ሆነ በልበ-ሙሉነት እየተሻሉ መቀጠላቸውን አለወደድነውም። በዘታው ተገኝቼ ምክር ልሰጥህ እንደማልችል ታውቃለህ። የአስክ አሁኑ እንቅስቃሴህ በፊትድ ላይ የተመሠረተ አይመክልም። በመሸኑም በጊዜ ዕቅድህን ብታሳክልክ ይሸላል። መንግስታችን የሠራዊታችንን እና የንብረቻችንን ኩባር ለማክበርም አለረባ የሆነውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ አው።*

የባራቴሪ መባረር እየታወቀ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህንን ቴሌግራም ለምን እንደላኩት ለማንም ግልጽ አልነበረም። በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁጣ እና ስድብ





የተደናበረው ባራቴሪ ቀጣይ እርምጃውን በጥልቅ አላለበትም ነበር። በመሪው ቴሌግራም የተነሣ ነበር ወደ አድዋ ለመዝመት የወሰነው።

እስከ መጋቢት 1 ቀን ድረስ የባራቴሪ ዕቅድ ወደ ኤርትራ ማፈግፈግ ነበር። በምኒልክ ሠራዊት የአቅርቦት መስመሩ የተቋረጠበት ሲሆን የኢትዮጵያ ጦር ወደ ኤርትራ መንቀሳቀስ መጀመሩ መላውን የጣሊያን ቅኝ ግዛት አደጋ ላይ ሊጥለው ተቃርቧል። በመሸኑም ባራቴሪ ወደ ኤርትራ አፈግፍጎ በየሳምንቱ የሚመጣውን የጣሊያን አዳዲስ ሠራዊት ለማደራጀት ከበታች መኮንኖች ጋር መክሮ ነበር።

የባራቴሪን ዕቅድ ካስቀየሩት መኮንኖች መካከል ዋነኛው ጀነራል ዳቦር ሜዳ ነበር። ጀነራሉ የምኒልክ ሠራዊትን በተመለከተ ከስለላ ቡድኑ የደረሰውን መረጃ ሳያጠራ ነበር ለውሳኔ የቸኮለው። ‹‹የኢትዮጵያ ሠራዊት በስንቅ እና ትጥቅ እጥረት እየተቸገረ ከመሸኑም በላይ የውጊያ ሞራሉ ወድቋል። ስለዚህ ጣሊያን ጥቃት ብትሰነዝር በቀላሉ ይበተናል።›› በማለት ነበር የባራቴሪን የማፈግፈግ ዕቅድ የተቃወመው።

ምኒልክ ለቀናት በጉንዳብታ መሸጎ ያሳለፈው ጦራቸውን ጥር 22 ቀን እንዲንቀሳቀስ አዘዙ። ጦሩ በቀጥታ የምዕራብ አቅጣጫን በመያዝ ወደ አድዋ አመራ። የምኒልክ እንቅስቃሴ ከፍርሃት የመነጨ የመሰለው ባራቴሪ የንጉሡ ትክክለኛ ዕቅድ የገባው ቆይቶ ነበር። ምኒልክ የአድዋን ሰሜን አቅጣጫ በመከተል በአዲ አቡና በኩል ወደ ኤርትራ ለመግባት ነበር የተንቀሳቀሱት። የምኒልክ መንቀሳቀስ በባራቴሪ ካምፕ ከፍተኛ ውጥረትን ፈጠረ።

### የጀነራሉቹ ስብሰባ

የምኒልክን መንቀሳቀስ ተከትሎ በማስቱ የካቲት 23 ቀን ጦሩ ወደ ደብረጻሞ እንዲያፈገፍግ ባራቴሪ አዘዘ። በደብረጻሞ በኩል ወደ ኤርትራ በማለፍም የጣሊያንን ቅኝ ግዛት እንዲጠብቅ ዕቅዱን ለጀነራሎቹ አስረዳ። የምኒልክን ዕቅድ

ያልተረዱት ጀነራል ዳቦር ሜዳ እና ኮ/ል ሴዛር ፒኒ የምኒልክን መሸሽ ተከትሱ ጦራቸው እንዲያፈገፍግ መወሰኑን እንደ ድክመት በመመልከት ባራቴሪ ላይ አሸፋብት።

ከኹሉም አቅጣጫ የተነሣበትን ተቃውሞ መቋቋም ያልቻለው ባራቴሪ ለከፍተኛ ሕመም ተጋለጠ። ካፒቴን ማርዮ ባሲ ከምሰል ጋር አያይዞ በጻፈው ዘገባ የባራቴሪን ሁኔታ እንዲህ ነበር የገለጸው። ‹‹ባራቴሪ ምግብ መመገብ ያቆመ ሲሆን በከፍተኛ ትኩሳትም መሰቃየት ጀምሯል። ከእካላዊ ሕመሙ በተጨማሪ የአዕምሮ አለመረጋጋት ይታይበታል።›› የባራቴሪ መፍረክረክ እና አለመረጋጋት የጣሊያን ቅኝ ግዛት ዘመቻን ወደ ፍፁማዊ አለመረጋጋት እንዳሸጋገረው ማሪዮ ጨምሮ ጽፏል።

የካቲት 8 ቀን የማፈግፈግ ውሳኔው በመቀልበስ ባራቴሪ አራቱን ጀነራሎች ወደ ድንኳኑ በማስጠራት በቀጣይ እርምጃ ውይይት ማድረግ ጀመሩ። ከጀነራሎቹ በተጨማሪ የባራቴሪ ረዳት አማካሪ የነበረው ኮሎኔል ዲዮቺኖ ቫሌንዛኖ ስብሰባው ላይ ተገኝቶ ነበር።

ባራቴሪ ስብሰባው የጀመረው በተለሳለሰ ንግግር እንዲህ ሲል ነበር፦

> ***አስክ አሁን ድረስ ወታደራዊ ምክራችሁን ያለተቀበልኩት ሰሚፈጠረው አደጋ ተጠያቂው እኔ ብቻ እንደሆንኩ በማሰብ ነበር። በቀናነት ልባችሁን ስፍታችሁ ስለቀጣዩ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ምክር እንድትለግሱን አጠይቃችኋለሁ። በመሸኑም ሠራዊቱ የሚገኝበትን አጠቃላይ ሁኔታ አስረዱኝ።***

ኮ/ል ቫሌንዛኖ የሠራዊቱ ስንቅ ያለበትን ደረጃ በዝርዝር አስረዱ። ሓጎስ ተፈሪ እና ራስ ስብሃት ከከዱ በኋላ በተጀመረው የሽምቅ ውጊያ የስንቅ አቅርቦት አደጋ ላይ ወድቋል። በመጋዘን ያለው ስንቅ በሦስት ቀናት ብቻ የሚቆይ ሲሆን ስንቅ ለመግዛት





የተላኩት የባንዳ ሠራዊት አባላትም ከሳምንት በፊት እይመለሱም። ቫሌንዛኖ በመጨረሻም ሠራዊቱ ከጥቂት ቀናት በኋላ ምግብ ፍለጋ ካምፑን ለቅቆ ሊወጣ እንደሚችል አስጠነቀቀ።

ቀጣይ የወታደራዊ እንቅስቃሴን በተመለከተ ‹‹ማፈግፈግ፣ ማጥቃት እና ወደፊት መቀጠል›› የሚሉ ሦስት አማራጮች ቀርበው ጀነራሎቹ መወያየት ጀመሩ።

የመጀመሪያው ተናጋሪ ጀ/ል ዳቦርሜዳ ሲሆን ማፈግፈግ ፈፅሞ እንደማይታሰብ ተናገረ። ‹‹የሠራዊቱ የውጊያ ሞራል ከፍተኛ በመሸኑ ማፈግፈግ ውድቀትን ያስከትላል። ለሦስት ወራት ከጠላት ጋር ተፋጥጦ የከረመን ሠራዊት እንዲያፈገፍግ መናገር ንቀት ነው። ከመሸሽ ይልቅ ሦስት ሺህ ሠራዊት ማስጨረስ የተሻለ ክብር አለው።›› ማፈግፈግ ለኢትዮጵያውያኑ ድልን ማመቻቸት ሲሆን በቀላሉ ተከትሰው ሠራዊቱን ሲፈጁት እንደሚችሉም ጀነራሉ አስጠነቀቀ።

ቀጣዩ ተናጋሪ አልበርቶኒ ማጥቃት የተሻለ አማራጭ መሸኑን አቀረበ። አሰላዮቹ ባገኘው መረጃ መሠረት የምኒልክ ሠራዊት ለኹለት የተሰነጠቀ ሲሆን ሰውጊያ ዝግጁ የሆነው ሠራዊት ከ15 ሺህ በታች መሸኑን ገለጸ።

ጀ/ል አሪሞንዲ ጦሩ ጥቃት መጀመር ያለበት ሰዓት ላይ መሸኑን በመጥቀስ ቀድሞ ያሳለፋቸውን ወርቃማ እድሎች መጠቀም እንደነበረበት በቁጭት ተናገረ። የጦራቸው መጠን ከጠላት አንፃር አነስተኛ ቢሆንም የተሻለ የቦታ ይዞታ፣ የሥልጠና ብልጫ እና የተሻለ አመራር ስላለው በቀላሉ የምኒልክን ጦር መበታተን እንደሚችል በሰሜት ተሞልቶ ተናገረ። በቀጥታ ወደ አድዋ በመግፋትም ጦርነቱን መጀመር እንደሚያስፈልግ ተናገረ።

ከጦሩ ጋር ኹለት ሳምንታትን ብቻ ያሳለፈው ጀነራል ጁሴፔ ኢሌና የመጨረሻ ተናጋሪ ነበር። የሦስቱን ጀነራሎች የ‹‹ማጥቃት›› አማራጭ በመቃወምም የሃሳብ ልዩነቱን አስመዘገበ።

ተጨማሪ የስለላ መረጃዎችን በመጠበቅ ለቀጣይ እርምጃ እንዲንቀሳቀሱ በማሳወቅ ነበር ባራቴሪ ስብሰባውን የዘጋው። ከስብሰባው የተሻለ ድጋፍ ጠብቆ የነበረ ቢሆንም የጀነራሎቹ መስማማት የእርሱን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አደረገበት። ማፈግፈጉን ሲደግፍለት የነበረው ሪዳቱ ክ/ል ቫሌንዛኖም በመጨረሻ ሃሳቡን በመቀየር ከጀነራሎቹ ጋር አበረበት።

ባራቴሪ የካቲት 29 ቀን አመሻሽ ላይ ውሳኔውን ለጀነራሎቹ ለማሳወቅ ስብሰባ ጠራ። ጦሩ ወደ አድዋ በመንቀሳቀስ ከምኒልክ የጦር ካምፕ አቅራቢያ በመስፈር ኢትዮጵያውያኑ ጥቃት እንዲጀምሩ ለመተንኮስ ወስኗል። ወታደሩ የሚይዘውን ቦታ እና አሰላለፍ በካርታ አስደግፎ ለጀነራሎቹ ካስረዳቸው በኋላ ስለሚጠብቃቸው ፈታኝ ሁኔታ ‹‹ጓዶች፣ የድል ወይም የሞት አማራጭ ብቻ ይጠብቀናል።›› በማለት ገለጸላቸው።






# ምዕራፍ ዐሥራ ኹለት

## የሠራዊቱ ፍልሚያ

አብዛኛው የኢትዮጵያ መሬት ከ6500 ሜማ ከፍታ በላይ ይገኛል። ተፈጥሮአዊ አቀማመጡ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ወራሪ ሃይሎችን በቀላሉ እንዲከላከሉ አስተዋጽኦ አድርጓል። በርካታ ጎብኚዎች ‹‹የአፍሪካ ስዊዘርላንድ›› በማለት ሰንሰለታማ ተራሮቿን ተመልክተው አድንቀዋታል።

የካቲት ወር ዝናብ የሌለበት በመኾኑ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ተራሮች ቡናማ ቀለም በሚሰጣቸው አነስተኛ ቁጥቋጦ እና ደረቅ ሳር ይሸፈናሉ። የጣሊያን ሠራዊት ወደ አድዋ ሲጓዝ ያጋጠሙት ተራሮችም ደረቅ እና ቡናማ ነበሩ። ከሳውራ በመነሳት ወደ ምዕራብ የሚወስዱ ኹለት መንገዶ ሲኖሩ እነርሱን በመያዝ በጉንጭበታ እና አድዋ መካከል የሚገኙት ሦስት ተራሮች (አሻሾ፣ ራዕዮ እና ሰማያታ) የጣሊያን ሠራዊት መመሸጊያ እንደሸኑ ነበር ባራቴሪ ያቀደው።



ምስል፦ የጣራቴሪ የዘመቻ ዕቅድ

የባራቴሪ ዕቅድ ቀላል የሚባል ዓይነት ነበር። ጦሩ በሦስት መስመር በመንቀሳቀስ ወደ ፊት ሲገሰግስ ከጀርባ የጀነራል ኢሌላ ጦር ይከተለዋል። ሦስቱ መስመር በተራሮች መካከል የሚያልፉትን ዥስት መንገዶች ተከትለው የሚሄዱ ሲሆን በጀ/ል ዳቦርሜዳ የሚመራው ጦር የቀኙን አቅጣጫ በመያዝ የእሻሾ እና ራዕዩ ተራሮችን ሰሜናዊ ክፍል ይቆጣጠራል። የጀ/ል አልባርቶኒ ጦር ደግሞ የቀኙን መስመር ተከትሎ በመንቀሳቀስ የራዕዮ እና ሰማያተ ተራራን ምዕራባዊ ጫፍ ይቆጣጠራል። የጀ/ል አሪሞንዲ ጦር ደግሞ መካከለኛውን አካባቢ ይቆጣጠራል። እንቅስቃሴው የሚጀመረው በምሽት እንደሆነም በዕቅዱ ተቀምጧል።

የቦታ አያያዙ ለጣሊያን ዥስት ጠቀሜታ እንደሚኖረው ባራቴሪ ቀድሞ ነበር ያስበው። የመጀመሪያው ጥቅም የኢትዮጵያን ሠራዊት በቅርበት በመከበብ ጥቃቱን እንዲጀምሩ ማድረግ መቻል ነው። ዥስተኛው ደግሞ ከፍታ ቦታ ላይ በመመሸግ የኢትዮጵያን ሠራዊት በጠባብ ቀለበት ውስጥ ማስገባት ነበር።

የባራቴሪ ዕቅድ ዥስት ችግር ነበረበት። የመጀመሪያው የቦታ አያያዙን አስቸጋሪ የሚያደርገው ለሦስት ብርግድ በቂ አለመሸኑ ነበር። ይህም የወታደር መጨናነቅ ስለሚፈጥር የጀነራል አሪሞንዲ ብርግዴ ከአልበርቶኒ ጒላ እንዲንቀሳቀስ ተገድዷል። ዥስተኛው ችግር ደግሞ ሦስቱ ብርጌዶች ከባራቴሪ ጋር ለመገናኘት አለመቻላቸው ነበር።

የባራቴሪ ዕቅድ ወደ ምኒልክ ጦር መጠጋትን እንጂ ማጥቃትን አለማስቀደሙ በጀነራሎቹ ዘንድ ግርታን ፈጥሯል። በተለይ ጀነራል ዳቦርሜዳ የባራቴሪን ዕቅድ ከማፈግፈግ ለይቶ አልተመለከተውም ነበር። በዘመቻው ዋዜማ ዳቦርሜዳ ምክትሉ የነበረውን ጁሴፔ ሜናሪኒ እና ከ/ል ሴዛር አይራጊን ስብሰባ ጠርቶ ‹‹በምንም ዓይነት እናፈገፍግም። ዛሬ ምሽት 3 ሰዓት ላይ እንቅስቃሴ እንጀምራለን።››





በማለት ፊቱን ቅጭም አድርጎ አሳወቃቸው። ለመሸኑ ዳቦርሜዳ የተለየ ሀሳብ ነበረው?

**የጨረቃው ግስጋሴ**

የዘመቻው ትዕዛዝ የተላለፈው በድንገት ነበር። ቀድሞ ለሠራዊቱ ማሳወቅ ለጠላት መረጃ ማስተላለፍ በመሸኑ ነበር በምሽት ወታደሩን ማሥነሳት ያስፈለገው። ትዕዛዙ በተነገረበት ሰዓት በርካታ ወታደሮች የተኙ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ የተለመደ የምሽት ጨዋታ ላይ ነበሩ።

የመድፈኛው ብርጌድ አባል የነበረው ኤርኔስቶ ኮርዴላ ከ12 ቀናት አድካሚ ጉዞ በኋላ ሳውራ የደረሰው የካቲት 27 ቀን ነበር። የአቀባበል እራት ግብዣ የተዘጋጀለት የካቲት 29 ምሽት የነበረ ቢሆንም ትጥቁን እንዲሸከፍ የተነገረው ከግብዣው ደቂቃዎች ቀደም ብሎ ነበር። እንደ ኮርዴላ ዥሉ ፍራንሲስኮ ፍሪሲና ሳውራ የደረሰው ከቀናት በፊት ነበር። ለግዳጅ ዝግጁ እንዲሆን ሲነገረው ይዞት የመጣውን ጓዝ እንኳን ፈትቶ አልጨረሰም ነበር። የዳቦርሚዳ ብርጌድ አባል የነበረው ካርሎ ጺዮቲ ስለ ግዳጁ የተነገረው ከእንቅልፉ ተቀስቅሶ ነበር።

የጣሊያን ካምፕ በጥድፊያ ተሞልቷል። ወታደሮች ጓዛቸውን ሸክፈው እንደጨረሱ በጀነራል ባራቴሪ እና የብርጌድ መሪዎች ፊት በሰልፍ ማሰፍ ጀመሩ። የመጀመሪያዎቹ ሰልፈኞች የነበሩት ባንዳ ወታደሮች በፈገግታ ተሞልተው ነበር ያሰፉት።


የጀነራል አልቤርቶኒ ጦር ዘግየት ብሎ ነበር ካምፑን መልቀቅ የጀመረው። በመጀመሪያ ስድስተኛ ሰባተኛ እና ስምንተኛ የባንዳ ባታሊዮኖች አለፉ። በመቀጠል በኮርዴላ የሚመራው 3 የመድፈኛ ባታልዮኖች ትጥቃቸውን በበቅሎ ጭነው አለፉ። የመድፈኛ ባታሊዮኖች በአጠቃላይ ሰባ ወታደሮችን የያዙ ሲሆን ስምንቱ አስተኳሽ መኮንኖች ነበሩ።

ከምሽቱ 3:45 ላይ ከጥቂት የአገልግሎት ሠራተኞች በቀር መላው የጣሊያን ሠራዊት ጉዞ ጀምሯል። የጠራው ሰማይ ላይ ፍንትው ብላ የወጣችው ጨረቃ ለወታደሮቹ እንደ መንገድ መብራት ነበር ያገለገለቻቸው።

ሜጀር ሉዶቪኾ ዴ ቪቶ የሚመራው የጀ/ል ዳቦርሜዳ ባንዳ ሠራዊት ከፊት ቀድሟል። ከስድስት ሰዓታት ጉዞ በኋላ ከሌሊቱ 9 ሰዓት ላይ ሠራዊቱ እንዲያርፍ ተነገረው። የታሸጉ የሥጋ ቆርቆሮዎቻቸውን በመክፈት ምግባቸውን መብላት ጀመሩ።

### የአልበርቶኒ ጥድፊያ

ጉንዳብታን ከአድዋ የሚለዩት ሰንሰለታማ ተራሮች በየካቲት ወር ደረቅ ናቸው። ከሰሜን እስከ ደቡብ የተዘረጉት እሻሾ፣ ራዕዮ፣ እና ሰማያታ ተራሮች በኹሉቱ መካከል ተፈጥሮአዊ ድንበር መስለዋል። እሻሾ እና ሰማያታ የዘጠኝ ሺ ጫማ ከፍታ ሲኖራቸው ራዕዮ ስምንት ሺህ ጫማ ይረዝማል።



The rendezvous: looking south from Eshasho to Raio and, beyond, Semayata.
From Eduardo Ximenes, *Sul Campo di Adua, marcia giugno 1896*. Milano
Fratelli Treves Editori, 1897.

*ምስል፦ ከደቡብ በኩል የሚታዩት እሻሾ እና ራዕዮ ተራሮች ሲሻሱ በርቀት የሚታየው ደግሞ ሰማያታ ተራራ ነው።*





ባራቴሪ ለጀነራሎቹ የሰጣቸውን የቦታ ካርታ የሳለው ብዙም ልምድ የሌለው ቶማሶ ሳልሳ ነበር። የሦስቱን ተራሮች አቀማመጥ እና በመሃከላቸው የሚገኘውን ሰፊ ሜዳ በትክክል ነበር ያስቀመጠው። ከካርታዎቹ ጋር የባራቴሪ የዘመቻ ዝርዝር ለአራቱም ጀነራሎች ተሰጥቷል።

በዕቅዱ መሠረት ግራ እና ቀኙን የሚይዙት ብርጌዶች ከሦስተኛው የኋለኛ ብርጌድ እኩል መነሳት ነበረባቸው። ሦስቱ ሳይቀዳደሙ በመጠባበቅ እንዲንቀሳቀሱ ነበር ባራቴሪ ያስጠነቀቀው። ምክንያቱም የአንዳቸው መቅደም ለኢትዮጵያ ሠራዊት ጥቆማ ይሰጣል እና ነው።

የግራውን አቅጣጫ ለመያዝ የተመደበው ጀነራል አልበርቶኒ ባልተሰመደ መልኩ ተጣድፏል። በባራቴሪ የተሰላሰለ አድም ሲበሳጭ በመከረሙ አጋጣሚውን ሲጠብቅ የቆየ አስመስሎታል። በፈጣንነቱ የታወቀውን ልዩ ኃይል ከባንዳ ወታደሮች ጋር አጣምሮ የያዘው የአልበርቶኒ ብርጌድ ከኹሉም የተሻለ ነበር። ባራቴሪም የአልበርቶኒን መጣደፍ ቀድሞ በመረዳት በምንም ዓይነት ተነጥሎ ወደፊት እንዳይገሰግስ አስጠንቅቆታል።

በጉዞው ምሽት በሜጀር ዶሚኒኮ ቱሪቶ የሚመራውን ልዩ ኃይል በማዘዝ ነበር አልበርቶኒ ጥድፊያውን የጀመረው። የቱሪቶ ጦርም በሦስት ሰዓታት ውስጥ አስቸጋሪውን የ10 ማይል ርቀት በመሸፈን ጉንዳብታ ደረሰ። የባራቴሪ ዕቅድ የአልበርቶኒ ጦር ጉንዳብታ ላይ እስከ ሌሊቱ 8:30 ጠብቆ እንዲንቀሳቀስ ቢሆንም ትዕግስት አልባው ቱሪቶ ከግማሽ ሰዓት በፊት ነበር የተንቀሳቀሰው።

ከሌሊቱ 9:30 ቱሪቶ በራዕዮ እና ሰማያታ መካከል የነበረውን የአልበርቶኒ መዳረሻ ተቆጣጠረ። ቀሪው የአልበርቶኒ ሠራዊት በቦታው የደረሰው ከግማሽ ሰዓት በኋላ ነበር።

አልበርቶኒ ወደ ቱሪቶ ጆሮ ተጠግቶ ለምን እንደቆመ ጠየቀው። ‹‹ይህ ኪዳነ ምህረት እኮ ነው።›› በማለት የታዘዘው ቦታ መድረሱን ቱሪቶ ለአለቃው መለሰለት። አልቤርቶኒም ቦታውን መሳሳቱን በመንገር ወደ ኪዳነ ምህረት ጉዞውን እንዲቀጥል ለቱሪቶ ትዕዛዝ ሰጠው። የአልቤርቶን የቁጣ ትዕዛዝ የተመለከተው ቱሪቶ ተጨማሪ ክርክር ሳያስማ ነበር ወታደሮቹን ያንቀሳቀሰው።

ለጣሊያን የአድዋ ሽንፈት በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም የአልቤርቶኒ ጥድፊያ ምናልባትን ዋነኛው ሳይሆን አይቀርም። የቦታ ስም ስህተቱ ከጊዜ በኋላ ነበር የታወቀው። ባራቶሪ እንዲመሽጉበት ያዘዛቸውን መተላለፊያ በማለፍ አልበርቶኒ እና ቱሪቶ አራት ሺህ ወታደሮቻቸውን አስከትለው በቀጥታ ወደ አድዋ አመሩ።

የቱሪቶ የ50 ልዩ ወታደሮች ቁልቁለቱን በመያዝ ከሠላሳ ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አድዋ ከተማ መግቢያ ላይ ደረሱ። ከንጋቱ 11፡30 ላይ በአልቤርቶኒ ትዕዛዝ መሠረት የቱሪቶ ወታደሮች ቦታቸውን ያዙ። የሦስቱን ብርጌድ ጦር መጠበቅ ቢኖርባቸውም በመሪያቸው አልቤርቶኒ አጣዳፊነት የቱሪቶ ወታደሮች ወደፊት መጠጋታቸውን ቀጠሉ።

ከቀድሞ ይዞታቸው አራት መቶ ሜማ ያህል በመግፋትም በንጋቱ ብርሐን ታግዘው የአድዋ ከተማ ጎጆ ቤቶችን በግልጽ ማየት ቻሉ። ጥቂት ቢጠጉ ኖሮ ከከተማዋ በስሜን አቅጣጫ የነበሩትን በሺህ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ሠራዊት ድንኳኖች ማየት ይችሉ ነበር።

ሙሉ በሙሉ ብርሐን ሲገለጥ ነበር የቱሪቶ ወታደሮች ራሳቸውን በኢትዮጵያ ሠራዊት ካምፕ ዳርቻ ያገኙት። በጥቢቃ ላይ የነበሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች የቱሪቶን ጦር በመመልከት የማስጠንቀቂያ ተኩስ እከታትለው ተኩሱ። ከንጋቱ 12፡00 ሊሆን ጥቂት ደቂቃዎች ነበሩ የቀሩት። የአድዋ ጦርነትም የጀመረው በዚያ ሰዓት ነበር።





## ምኒልክ እና ጣይቱ መታጠቂያቸውን አጠበቁ

የኢትዮጵያ ጦር የጣሊያንን ሠራዊት እየጠበቀ ስለመሸኑ ምንም ማረጋገጫ አልነበረም። ሪዶልፎ ማዘቾኒ በ1930ዎቹ ባሳተመው ጽሁፍ እንደገለጸው የጣሊያንን ጦር መንቀሳቀስ አፄ ምኒልክ የሰሙት ቅዳሴ ላይ ሳሉ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ላይ ነበር። መልዕክተኖቹ ወደ ጆሮአቸው ተጠግቶ ዜናውን ተናገረ። ንጉሡም ሰምተው እንዳበቁ ፊታቸውን ወደ ቤተ-መቅደሱ በመመለስ የቅዳሴ ሥነ-ሥርዓቱን በአግባቡ ፈፀሙ። ቅዳሴው ሲጠናቀቅ ነበር ሠራዊታቸው ሰውጊያ እንዲዘጋጅ ያዘዙት። ከንጋቱ 11፡30 መላው የኢትዮጵያ ሠራዊት ለውጊያ ዝግጁ ሆነ።

ኢትዮጵያውያኑ ከሰዓታት ቀድሞ መረጃ ባይደርሳቸው ኖሮ ምናልባትም የአድዋ ጦርነት ታሪክ የተሰየ ይሆን ነበር። ለጣሊያንም ሆነ ለምኒልክ የደረሳቸው መረጃ ምንጭ በግልጽ አይታወቅም ነበር። በተሰይ ከጣሊያን ሠራዊት የከዳ ሰላይ ስለመኖሩ ማረጋገጥ አልተቻለም። ዮሴፍ ንኩሴ ለአልፍሬድ ኢልግ በጻፈው ደብዳቤ ስለ ጦርነቱ አጀማመር ሲገልፅ ምኒልክ መረጃው እንዴት ቀድሞ እንደደረሳቸው አልጠቀሰም። ‹‹የቱሪቶ ወታደሮች ተኩስ ሲጀምሩ አንበሳው ምኒልክ የብረት መታጠቂያውን እያጠበቀ ነበር። ከአፍታ በኋላ መላው ሠራዊት ሆ! ብሎ ወጣ።›› በማለት ነበር ዮሴፍ የጦርነቱን አጀማመር የገለጸው።

ኢትዮጵያዊው የታሪክ ፀሐፊ ዮሴፍ የውጊያው ዕለት ማለትም መጋቢት 1 ቀን የአክሱም ቀሳውስት በአድዋ ከምኒልክ እና ጣይቱ ጋር መገናኘታቸውን ጠቅሷል። እንደ ዮሴፍ ገለፃ ካህናቱ የምኒልክ ሠራዊት ለዘመናት ከግብር ነፃ በሆነችው ቅድስቲቷ የአክሱም ከተማ በመግባት ከሕዝቡ ላይ እህል መሰብሰቡን በተመለከተ ወቀሳ ለማቅረብ ነበር አድዋ የመጡት። ውጊያው በተጀመረበት ወቅትም ካህናቱ የማርያምን ታቦት ይዘው የምኒልክን ሠራዊት ሲያበረታቱ ነበር። አፄ ምኒልክ በየትኛውም ዘመቻ ላይ የቅዱስ ጊዮርጊስን ታቦት ይዘው እንደሚሰለፉ ይነገራል። መጋቢት 1 (የካቲት 23) የቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል መሸኑ እንዲሁም የኹለቱ ታቦታት

በጦር ሜዳው መገኘት የፈጣሪን ጣልቃ ገብነት እና ለኢትዮጵያ መወገን ያሳየ ተደርጎ ይታመናል።


ከዋናው የአልበርቶኒ ጦር ኹለት ማይል ያህል ርቆ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር የተፋጠጠው ቱሪቶ በፍርሃት ተዋጠ። የመቀስቀሻ ተኩስ እንደተሰማ የኢትዮጵያ ሠራዊት በእንድ ላይ ተነሳ። የተሪያ ልዩ ኃይል በቀላሉ የመንገሻን ጦር መመከት ቢችልም በባልቻ የሚመራው የንግሥት ጣይቱ 5 ሺህ ጦር እንዲሁም የአፄ ምኒልክ 35 ሺህ ጦር በሰሜን አድዋ ከአባገሪማ እስከ ሸሎዳ ያለውን ቦታ ይሸፍን።

‹‹አይጥ ለመሞቷ የድመት አፍንጫ ታሽታለች›› በማለት ነበር ገብረ ኢየሱስ የቱሪቶ 950 ወታደሮች ያሳዩን ያልተገባ ድፍረት የገለጸው። ቱሪቶ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ነበር ሙሉ በሙሉ የተከበበው። በአልበርቶኒ የተሰጠው ትዕዛዝ ለዋናው ጦር ሽፋን እንዲሰጥ፣ ካልሆነ ግን እንዲያፈገፍግ ነበር። የወትቱ ሁኔታ ቱሪቶን ምንም እንዳያደርግ አደረገው። በተሰይ ወደ ኋላ ማፈግፈግ በጉዞ ላይ የነበረውን የአልበርቶኒ መድፈኛ ሠራዊት ለጥቃት ማጋለጡ አይቀርም። መድፈኛ ሠራዊት ደግሞ መገሪያውን ቦታ ለማስያዝ ብቂ ጊዜ ይፈልጋል። በመሆኑም የቱሪቶ ብቸኛ አማራጭ መጋፈጥ ነበር።

የአልበርቶኒ ሠራዊት አጂ ፍቼ ተራራ ግርጌ ላይ መመሸግ ጀምሮ ነበር። የጥይት ተኩስ የሰማው አልበርቶኒ የፊት ተሰላፊው ቱሪቶ አጣ ፊንታ አሳስቦታል። በመሆኑም በኹለቱ ተራሮች መካከል ያለውን ሰፊ ሜዳ ከሦስት አቅጣጫ በመክበብ የኢትዮጵያን ሠራዊት ለመጠበቅ ወሰነ። ሮዶልፍ ቫሊ የሚመራውን ባለ 900 ወታደር 7ኛ ባታሊዮን የባንዳ ሠራዊት በግራ፣ የሳልቫተሬን ባለ 850 ወታደሮች 6ኛ ባታሊዮን ጦር በቀኝ፣ እንዲሁም የጂዮቫኒ ጋሜራ ስምንተኛ ባታሊዮን ከመሃል አሰለፈ።








Battle of Adwa, phase 1

***ከርታሱ የአድዋ ጦርነት የመጀመሪያ ምዕራፍ***

አፄ ምኒልክ ጦራቸው ከአልበርቶኒ ልዩ ኃይል ይዞታ በተቃራኒ ያሉትን ኹለት ጉብታዎች እንዲይዙ እና እንዲመሸጉ አዘዙ። ሊሊቱ ሙሉ በሙሉ ሲገለጥ አፄ ምኒልክ የጠላትን ጦር በግልጽ መመልከት ቻሉ። ይህንን የፊት ሰፊት ውጊያ ሲጠብቁት ነበር። የጣሊያን ሠራዊት ልዩ ሥልጠናም ሆነ ዘመናዊ ትጥቅ አላሰጋቸውም ነበር።

በወትቱ በውጊያ ወቅደ-ግንባር የነበሩ ባይሬዱትም ጦርነቱ የኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን የመላ አፍሪካን እጣ ፈንታ የሚወስን ነበር። አጠቃላይ ቁጥሩ 4076 ከሆነው የአልበርቶኒ ሠራዊት መካከል ከመቶዎች ያልበለጡ ነጭ አውሮፓውያን ሲኖሩ

የቀሩት ግን ጥቁር የባንዳ ሠራዊት ምልምሎች ነበሩ። በኹለቱ መካከል የነበረው ልዩነት የኢትዮጵያ ጥቁር ሠራዊት ጥቁር መሪ ሲኖረው የጣሊያን ጥቁር ሠራዊት ግን በነጭ መመራቱ ነው። ጦርነቱ በእርግጥም ጥቁር አፍሪካን ከነጭ አመራር ለማላቀቅ ያለመ ነበር።

ከንጋቱ 12:30 የአልበርቶኒ መድፈኛ ሠራዊት ማዕከላዊ ቦታ ያዘ። የኢትዮጵያ ጦር ከአልበርቶኒ ፊት ለፊት ወደነበረው ሽለቆ መንቀሳቀስ ጀምሮ በጣሊያን ሠራዊት ተኩስ ነበር የቆመው። የተከበበው የቱሪቶ ልዩ ኃይል መውጫ ቀዳዳ በመፈለግ ላይ ሳለ በካፒቴን ሄንሪ የሚመራው የተራራው መድፈኛ ኃይል የመጀመሪያውን ጥይት በመተኮስ ከጥዋቱ 1:15 ላይ የጦርነቱን መጀመር አመላከተ።

ኢትዮጵያውያኑ ማጥቃት የጀመሩት ከማዕከላዊው የጠላት ይዞታ ነበር። የምኒልክ ክቡር ዘበኛ ክፊት በመቅደም ነበር ጥቃቱን የመራው። በሰዓቱ የጣሊያን 14 መድፎች ተኩስ ጀምረው ነበር። እቴጌ ጣይቱ ባልተጠበቀ ሁኔታ በእግራቸው ሠራዊቱን እየተከተሉ በፋከራ ሲያበረታቱ ታይተዋል። የወቅቱን ሁኔታ አንድ የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊ ሲገልፅ፦ ‹‹ንግስቲቱ የሴት ተፈጥሮአቸውን ሙሉ በሙሉ ዘንግተውት ነበር የሚፎክሩት። አስፈሪ ገጽታቸው ውጊያ የተጠማ ዘማች አስመስሏቸው ነበር።›› ብሏል። በርካታ ሴቶች ንግስቷን ተከትለው የማበረታቻ ቆከራቸውን ቀጠሉ። ወታደሩም በልበ ሙሉነት መገስገሱን ቀጠለ።

የኢትዮጵያውያኑን መቃረብ ተከትሎ የጣሊያን መድፎች በፍጥነት መተኮስ አልቻሉም። በርካታ ወታደሮች ቢሞቱም ኢትዮጵያውያኑ የበለጠ ተጠጉ። በተመሳሳይ ሰዓት የኢትዮጵያ ሆችኪስ መድፎች የአልበርቶኒን ጠንካራ ይዞታ መደብደብ ጀመሩ። ምኒልክ ለመድፈኞቹ መመሪያ በመስጠት ላይ ሳሉ ጣይቱ በበኩላቸው አምስት መድፎችን ሲያስተኩሱ ነበር። የመድፍ ድብደባውንተከትሎ የራስ ሚካኤል እና የራስ መኮንን 1500 ልዩ ኃይል የአልበርቶኒን ቀኝ ይዞታ መደብደብ ጀመረ።





በአልበርቶኒ የግራ ክንፍ በኩል ደግሞ የንጉሥ ተክለኃይማኖት እና የላስታው ዋግሹም ጓንጉል ሃይሎች ጥቃት ሰንዝረው። የተቀናጀው ጥቃት የኢትዮጵያን ሠራዊት በተለያዩ አቅጣጫዎች በመበታተን ለጣሊያን ዒላማ አስቸጋሪ ሁኔታን ፈጠረ። በዚያ ቅፅበት የኢትዮጵያ ጦር የአልበርቶኒን ማዕከላዊ ይዞታ በቅርበት ማጥቃት ችሎ ነበር።


### ዕቅድ ሲከሽፍ

የዳቦር ሜዳ ብርጌድ በታዘዘው መሠረት በአሻሸ እና ራዕዮ ተራሮች መካከል ያለውን መተላለፊያ ከንጋቱ 11:25 ላይ ተቆጣጠረ። ከአፍታ በኋላ የጥይት ድምፅ የሰሙት የዳርበርሚዳ ወታደሮች በተደበላለቀ ስሜት እርስ በእርስ ተያዩ።

12:30 ላይ የባራቴሪ ጦር ሰሜናዊው መተላለፊያ ላይ ደረሰ። የተኩሱን ድምፅ ባራቴሪም የሰማው በመገረም ነበር። የዕቅዱንባልተጠበቀ መንገድ መከሸፍ አስደንግጦታል። ጀነራል ዳቦርሜዳን አስከትሎ አሻሸ ላይ በመቆም የአልበርቶኒ ጦር የገባበትን አጣብቂኝ በፍርሃት ተመለከተ።

አልበርቶኒ ቀጣይ ትዕዛዝ ያስተላለፈው በፍጥነት ነበር። የዳቦር ሜዳ ጦር በቀኝ መስመር በማለፍ ከአልበርቶኒ ጀርባ እንዲደርስ አዘዘ። የጀነራል አሪሞንዲ ጦር ደግሞ ከጉንዳብታ በመንቀሳቀስ መተላለፊያዎቹን እንዲይዝ ታዘዘ። የዳቦር ሜዳ ጦር ‹‹ማርያም ሽዊት›› ላይ በመድረስ የአልበርቶኒ ጦር እንዲያፈገፍግ ሽፋን እንዲሰጥ አልበርቶኒ አዘዘው።

ቀጥሎ የተከሰተው ነገር ለማንም ምስጢር ነበር የሆነው። ዳቦርሜዳ በቀጥታ ወደ አልበርቶኒ በማምራት ድጋፍ እንዲሰጥ ነበር የታዘዘው። ነገር ግን ጥቂት እንደተጓዘ ወደ አልበርቶኒ ኃይል የሚወስደውን የግራ አቅጣጫ በመተው የቀኙን አቅጣጫ የያዘው። በወቅቱ መንገድ ተሳስቷል ለማለት የማይቻለው የጥይት ድምፅ በቀጥታ ሊመራው በመቻሉ ነው። የዳቦር ሜዳ ወታደሮች የአለቃቸውን ትዕዛዝ በመቀበል ከአልቤርቶኒ ብርጌድ እየራቁ ተጓዙ።




Battle of Adwa, plate 2

*ካርታ፡- የአድዋ ጦርነት ሽለተኛ ምዕራፍ*

‹‹ማርያም ሸዊት›› ጎና ላይ በመቆም ለአርበርቶኒ የጎላ ድጋፍ እንዲያደርግ የታዘዘው የዳቦርሜዳ ጦሩን በቀጥታ ያመራው ማርያም ሸዊትን አልፎ ወደሚገኘው ሸለቆ ነበር። ጀ/ል ዳቦርሜዳ የመረጠው ቦታ አልበርቶኒን ለመደገፍ ምንም ጥቅም አልነበረውም። ምናልባት የምኒልክን ጦር አቅጣጫ ለማስቀየር ካልሆነ በቀር።

የድጋፍ ጥሪ

ሳውራን በለቀቁ በ12 ሰዓታት ውስጥ የባራቴሪ ጀነራሎች የአሲታቸውን ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ መተላለፍ ጀምረዋል። ባራቴሪ የመጀመሪያው መልዕክት የደረሰው ከአልበርቶኒ ነበር። ከንጋቱ 2:15 ላይ የተጻፈው መልዕክት እንዲህ ይላል፡-

*አንደኛ ባታሊዮን የኪዳነ ምህረት መተላለፊያ ላይ በብርቱ ኃይል ታፍኗል። የቀረውን ሠራዊት ከባታሊዮኑ ኋላ ለማለፍ ተገድጃለሁ።*





*የታፈነውን ባታሊዮን ከፈታቸው ካለው ግዙፍ የጠላት ጦር ለማለስለቀቅ አስቸኳይ ድጋፍ ያስፈልጋል።*
*ሚጀ አልበርቶኒ*

ደብዳቤው እስደንጋጭ ነበር። በሰዓቱ መልዕክቱን ያነብ የነበረው ባራቶሪ የታፈነው የቱሪቶ አንደኛ ባታሊዮን ሙሉ በሙሉ መደምሰሱን ሊገምት ይችላል። በመቀጠል ባራቶሪ ዘንድ የደረሰው የአልበርቶኒ ደብዳቤ መጀመሪያ ከደረሰው ቀድሞ ከንጋቱ 1:30 ላይ የተጻፈ ነበር። ደብዳቤው ባፈጠጠ ውሸት ነበር የሚጀምረው።

*የኪዳነ ምህረትን መተላለፊያ የጠላት ጦር ሳይሰማ 12:00 ላይ ተቆጣጥሬያለሁ። ጠላት ከአድዋ ከተማ ዙሪያ እና ከማርያም ሸዊት ጀርባ መሸገል። አንደኛ ባታሊዮንን በማስቀደም ሰድስተኛው ባታሊዮን በቀኝ በኩል ያለውን ገዝ መሬት ተቆጣጥሯል። የቀሩት ሹለት ባታሊዮኖች ደግሞ ከመድፈኛው ጋር ተጣምረዋል። ከፍተኛ ውጊያ እንደሚጠብቀኝ ይታየኛል። የአሪሞንዲ እና ዳቦርሜዳን ቦርጌድ ማንቀሳቀሱ ጠቃሚ ነው። ከተሳካላቸው ከእኔ የተረፈ የጠላት ወታደር ላይ ሊደርሱ ይችላሉ።*

መልዕክቱ የአልበርቶኒን የተሳሳተ ግምት ነበር ያከተመጠው። ከሰሀተቱ በተጨማሪም ለአለቃው ባራቴሪ ወደ ላይ ትዕዛዝ የሚያስተላልፍ ነበር የሚመስለው። እውነታው ግን አስቸጋሪ ነበር። አልባርቶኒ ከተነገረው ቦታ ዐይበልጥ ወደፊት ገብቶ ከምኒልክ ጋር ተፋጧል። በመሸኑም ባራቴሪ የድጋፍ ኃይል ለመላክ ተቸገረ። የአልበርቶኒ ስሕተት የጣሊያን ጦር ቀጣይ እንቅስቃሴን አስቸጋሪ አደረገው።

## ምኒልክ የተጠቀሙበት ክፍተት

አልበርቶኒ ከጀርባው የሚገኙ ብርጌዶች ምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ አያውቅም። ከምኒልክ ጦር የገጠመውን ብርቱ ጥቃት መመከት ሲያቅተው ብቸኛው አማራጭ በሰቅዱ መሠረት ከጀርባ ሆኖ ድጋፍ ወደሚሰጠው የጀ/ል ዳቦርሜዳ ብርጌድ ማፈግፈግ እንደሆነ ገባው።

የስህተቱ ምክንያት ግልጽ ባይሆንም ዳቦርሜዳ ብርጌዱን በሌላ አቅጣጫ ነበር ይዞ የተንቀሳቀሰው። የዳቦር ሜዳ ሠራዊት በዝግታ በመጓዙ ተዳክሟል። ከኹሉም በላይ ደግሞ ወታደሮቹ በውኃ ጥም እየተሰቃዩ ነበር። ከሳውራ በተነሱበት ሰዓት የተወሰኑ የዳቦር ሜዳ ወታደሮች ውኃ ደብቀው የያዙ ቢሆንም ውኃው ግን የተበከለ ነበር።

ዳቦርሜዳ ከታዘዘው አንድ ሰዓት ተኩል ያህል ዘግይቶ ቦታ ያዘ። በመቀጠል ለአለቃው ባራቴሪ የሚከተለውን መልዕክት ከጠዋቱ 3:30 ላይ አስተላለፈ።

> *በሰሜን አድዋ ግዙፍ የጠላት ሠራዊት ካምፕ ይታያል። በርካታ ቁጥር ያለው ሠራዊትም ከዚሁ ካምፕ ተነስቶ ወደ አልበርቶኒ እየገሰገሰ ነው። እኔም ለአልበርቶኒ ለመድረስ እየሞከርኩ ነው። ከዋናው መተላለፊያ ወደ አድዋ የሚገነጠለውን መንገድ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሬያለሁ። በቀኝ በኩል ያለውንም መሬት በቅርበት እየተመለከትኩ ነው።*

አፄ ምኒልክ የጣሊያን ሠራዊትን ስሕተት ለመረዳት ጊዜ አልወሰደባቸውም። ዳቦርሜዳ ከአልበርቶኒ ጋር መገናኘቱን በመተው በማርያም ሽዊት ሸለቆ ጦሩን ሲያሰልፍ የኢትዮጵያ ሠራዊት በአግራሞት ነበር የተመለከተው። አፄ ምኒልክም





በኹሉቱ የጣሊያን ጀነራሎች መካከል የተፈጠረውን ክፍተት በመመልከት 1500 ወታደር በኹሉቱ መካከል አንቀሳቀሱ።

በኹሉቱ ጀነራሎች ይዞታ መካከል የተንቀሳቀሰውን ጦር ራስ መኮንን እና መንገሻ ነበሩ የሚመሩት። ጦሩ ለኹለት ተከፍሎ ግማሹ አልበርቶኒን በቀኝ በኩል ሲወጋ የቀረው ደግሞ ወደፊት ገሰገሰ። አልበርቶኒ በምኒልክ እና ጣይቱ ከሚመራው ጦር ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጠ። ዳቦርሜዳ ደግሞ ማርያም ሽዊት ላይ ተከበበ።

የምኒልክ ሠራዊት እንቅስቃሴ የጣሊያንን ጦር ሦስት ቦታ በመክፋፈል የጥቃት የበላይነትን ተቆጣጠረ። ውጊያው እስከ ምሽት ቢቀጥልም የአድዋ ጦርነት ግን የምኒልክን ልዩ እንቅስቃሴ ተከትሎ ከጠዋቱ 3:30 ላይ ተጠናቋል።

# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

## መሐሉ ሲሰበር

የአፄ ምኒልክ ወታደሮች በአልበርቶኒ እና ዳበርሜዳ ብርጌዶች መካከል በመንቀሳቀስ ያሹለቱን የግንኙነት ሙከራ ሕልም አደረጉት። በዚያ ወቅት ራስ አሉላ በመሸሸ ላይ የነበረውን የጠላት ጦር ተመልክቶ ምኒልክ የአሮሞ ፈረሰኛ ወታደሮችን በመላክ የሚሸሸውን ጦር በምሥራቅ አቅጣጫ እንዲያስቆሙለት ጠየቀ። የአሉላ ጥያቄ የገባቸው ምኒልክ የዶጋሊውን ዘግናኝ ጭፍጨፋ በድጋሚ ላለመመልከት ሲሉ ፈረሰኞቹን ላለመላክ ወሰኑ። የምኒልክ ውሳኔ በሺህ የሚቆጠር የጠላት ሠራዊትን ነፍስ ታደገ።

ግራ የተጋባው ባራቶሪ የዳበርሜዳ ብርጌድ በመሸሽ ላይ ለነበረው አልበርቶኒ ሽፋን እንዲሰጥ አዘዘ። የአሪሞንዲ ብርጌድ ደግሞ ከኤሊነ ተጠባባቂ ኃይል ጋር በመሆን በራዕዮ ተራራ ግርጌ እንዲመሸጉ ታዘዘ። ባራቴሪ ደግሞ ክፍታ ቦታ ሆኖ በመገስገስ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ሠራዊት ሁኔታ መከታተል ጀመረ።

የአሪሞንዲ ብርጌድ በአብዛኛው በቅርቡ ከጣሊያን በመጡ አዳዲስ ምልምሎች የተሞላ ነበር። ምልምሎቹ ምንም ዓይነት የውጊያ ልምድ የሌላቸው ሲሆን ውስጣቸው በበቀል እና ንቀት ብቻ የተሞላ ነበር።

### ፈርጣሎቹ እና አሳዳጆቹ

የአሪሞንዲ ወታደሮች ቦታቸውን በአግባቡ ከመያዛቸው ቀድሞ ነበር ጦርነት የጠበቃቸው። 3:00 ላይ የአልበርቶኒ ባንዳ ሠራዊት በኢትዮጵያውያኑ እየተባረረ ነበር። የባንዳዎቹ ሽሽት የአልበርቶኒን ፍፃሜ አመላክቷል።

የቱሪቶን ልዩ ኃይል በማባረር ላይ የነበሩት የምኒልክ ወታደሮች ከባንዳዎቹ ይልቅ አውሮፓውያን አዛዦቻቸው ላይ ነበር ያነጣጠሩት። በልዩ ዩኒፎርማቸው





በቀላሉ ኢላማ ውስጥ የገቡ ሰባት ነጭ መኮንኖች መጀመሪያ ላይ ተገደሉ። ከሞት የተረፉ ጥቂት የአልበርቶኒ ወታደሮች የአሪሞንዲ ጦር ወደ ነበረበት ራዕዮ ተራራ ግርጌ እና ወደ ሳውራ አቅጣጫ ፈረጠጡ።

ከጠዋቱ 3:30 አካባቢ የአልበርቶኒ ሠራዊት ምንም ዓይነት ድጋፍ እንደማይመጣለት ተስፋ ቆርጠዋል። የዳበርሜዳ ብርጌድ እንደደረሰላቸውም ልላወቁም ነበር። የአልበርቶኒ ወታደሮች የአድዋ ውሎአቸው መደምደም ግልጽ ሆኖላቸው ነበር።

የኢትዮጵያ ጦር በአልበርቶኒ ላይ የበላይነትን መቆናጠጥ የጀመረ የጠላትን የቀኝ መስመር በመምታት ነበር። የጣሊያንን መድፈኞች እስከ 2ሺህ ሜማ በመጠጋት የተቀናጀ ጥቃት ሰነዘረ። በቀኝ መስመር የተደረገው ማጥቃት የጣሊያንን ጦር ማዕከላዊ ይዞታ ለኢትዮጵያ ጦር ክፍት እደረገለት።

ከጠዋቱ 4:00 ላይ የተረፈው የአልበርቶኒ ጦር ሠራዊት ለመሸሽ ሲዘጋጅ የአርኔሉቶ ኮርዶላ መድፈኛ ሠራዊት ደረሰለት። በመልሶ ማጥቃት በርካታ የኢትዮጵያ ወታደሮችን ቢገድሉም የውጊያ የበላይነቱን ግን መጠበቅ አልቻሉም። በተመቱት ወታደሮች ምትክ ሌሎች እየተተኩ አልበርቶኒን ፈተኑት።

የኮርዶላ መድፈኛ ሠራዊት ከመሃመድ አጋ አደም እና ሱልጣን አጋ አሚድ አጠገብ በመሰለፍ ጠንካራ ጥቃት ሲሰነዝር ቆየ። ነገር ግን ለመድፈኛው ብርጌድ ሽፋን ሲሰጥ የነበረው 8ኛ ባታሊዮን 4:10 ላይ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ተከበበ።

ትዕዛዝ መቼ እንደተሰጠ ግልጽ ባልሆነበት ሁኔታ 3:30 ከአልቤርቶ ግራ ጎን ተሰልፎ የነበረው ጌራርዶ ፓንታና ከአሰቃው ካፒቴን ፔኔሊ ትዕዛዝ እንደደረሰው በመናገር አፈገፈገ። የጣሊያን ጦር በመጠኑም ቢሆን የተቀናጀ ጥቃት መሰንዘር የቻሉው 4:00 ላይ ነበር። በግራ እና ቀኝ የተከበበው አልበርቶኒ 3ኛ እና 4ኛ ባታሊዮን

መድፈኞች ጥይታቸው እስኪያልቅ እንዲቷኮሱ አዘዘ። ትዕዛዙ መድፈኞቹ በማፈግፈግ ላይ ለነበሩት ሽፋን እንደሆኑ የታሰመ ነበር። የ8ኛ ባታሊዮን ርዝራዥና ወታደሮች በማፈግፈግ ላይ ሳሉ 5:00 ላይ መድፈኞቹ ጥይት ጨረሱ።

ያለግልጽ ትዕዛዝ ያፈገፈጉት ኮርዴላ፣ ሞሃመድ፣ ሱልጣን እና ኢድሪስ ቁታይ ወደ እሥር ቤት ተወረወሩ። ጀ/ል ባራቶሪ ቆስሎ እጁን ሰጠ። የጀነራሉ መማረክ ለኢትዮጵያ ድልን አጎናጸፈ።

በመሸሽ ላይ የነበሩ የጣሊያን ወታደሮች ለኢትዮጵያ ጥይት ሲላይ ሸኑ። በርካታ መሪዎቻቸው የተገደሉባቸው ወታደሮች በተለያየ አቅጣጫ ፈርጥጠዋል። ከጀርባ ሊደግፋቸው የመጣውን የአሪሞንዲ ሠራዊት በማስፍ ገሚሱ ወደ ኤርትራ ገሚሱ ወደ ሳውራ አቅጣጫ በመሸሽ ሕይወቱን አተረፈ። ካፈገፈጉት መካከል ዴሳ ቶሪ እና ፔፔ አስመራ የደረሱት ከኹለት ሳምንታት በኋላ ነበር።

በአልበርቶኒ ላይ የጀገኑት ኢትዮጵያውያን በድሉ ተበረታትተዋል። በጣሊያን መድፎች በርካታ ወታደሮቻቸውን ቢያጡም በመጨረሻ ያስመዘገቡት የበላይነት የውጊያ ሞራላቸውን ከፍ አድርጎታል። በውጊያ ላይ የሞቱ ኢትዮጵያውያን ቁጥር በትክክል አልታወቀም።

ከጦርነቱ በኋላ ወደ አድዋ የተጓዘው ኤድዋርዶ ሲመንስ የሚች ጣሊያናውያንን ቁጥር ዘግቧል። ከቴሬቶ ልዩ ኃይል 80 ወታደር፣ ከአልበርቶኒ 110፣ በመሸሽ ላይ ከነበሩት 200፣ከ 4000 የጣሊያን ወታደሮች መካከል 400 ያህሉ ሞተዋል።

### በመተላለፊያዎቹ የተደረገ ትንቅንቅ


ከሞት የተረፉ የአልበርቶኒ ወታደሮች በደመ-ነፍስ ነበር የሚሮጡት። ለድጋፍ የተንቀሳቀሰው የዳቦርሚዳ ብርጌድ በአባራራው የኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ተኩስ አልከፈተም። የሽፋን ተኩሱ በመሸሽ ላይ የነበሩትን የጣሊያን ወታደሮች





ሊመታ ይችል ነበር። በዚያ ላይ ግዙፍ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ሠራዊት በመምጣት ላይ ስለነበር ዳቦርሚዳ መጋፈጥ አልፈለገም።

የጠላትን ጦር ከሚያባርረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ቡተጨማሪ በአልበርቶኒ እና ዳቦርሚዳ ብርጌድ መካከል ቆርጦ ገብቶ የነበረው ሠራዊት ራዕዮ ላይ ከመሸገው የጣሊያን ጦር በተቃራኒ የነበረውን ዞባ ዳዕሮ ጉብታ መቆጣጠር ጀመረ። ጉብታውን ለማስለቀቅ ኮ/ል ፍራንሴስኮ ስቴቫኒ ኹለተኛ ባታሊዮንን አዘዘ። የባታሊዮኑን ወታደሮች የተቀበላቸው የኢትዮጵያውያኑ ጥይት ነበር። ጉብታውም በቀላሉ በኢትዮጵያ ቁጥጥር ሥር ዋለ።




Battle of Adwa, phase 3

***ካርታ፦ የአድዋ ጦርነት፣ ሦስተኛ ምዕራፍ***

የአሪሞንዲን የቀኝ መስመር ይከለክል የነበረው የኮ/ል ጋሊያኖ ሦስተኛ ባታሊዮን ከፍተኛ ውጊያ ገጠመው። 4:10 ሲሆን በሐያ ደቂቃ ውስጥ ከግማሽ በላይ ሠራዊቱ

አለቀ። የአልበርቶኒን ሠራዊት በማሳደድ ላይ የነበረው ኃይል በተራራማ ቦታ ላይ የነበረውን 8ኛ ባታሊዮን ሙሉ በሙሉ ሰበረ። በተመሳሳይ ሰዓት የጣሊያን ጦር የቀኝ እና የግዕከላዊ ይዞታ ሳስቶ ስለነበረው ሰሜናዊው ይዞታ ለጥቃት ተጋለጠ።

ዘባ ጻዕሮ ላይ ገዝር መሬት የያዘው የኢትዮጵያ ጦር ከስሩ የነበረውን የጠላት ሠራዊት በቀላሉ መልቀም ጀመረ። በርካታ የጦር አዛዦች በኢትዮጵያውያኑ ጥይት ተረመረሙ። የወቅቱን ሁኔታ ጀኖኒ ቲዶን ሲገልፅ ‹‹ከጥይት የተረፉ አዛዦች በማረኳቸው የኢትዮጵያ ወታደሮች ተገድደው ደፈታቸው ላይ የነበረውን ቀይ እና ሰማያዊ ማዕረግ በጥሰዋል።›› ነበር ያለው። በአድዋ ከተሰለፉት 610 የጦር መሪዎች መካከል የተረፉት 258 ብቻ ነበሩ።



*ምስል፦ ጀ/ል ቪቶሪዮ ዛቦርሚዳ (ከላ ኢሉስትራዚዮኔ ኢታሊያና ጋዜጣ የተወሰደ) መጋቢት 22 ቀን 1896)*





ጀ/ል ዛቦርሚዳ ብርጌዱን ያሰፈረበት ቦታ የተሳሳተ መሆኑን እንዲሁም አልበርቶኒን ለማዳን እንደማያስችለው የበታቹ የነበረውን ኤሚሊዮ ቤላቪታ ነግሮታል። ነገር ግን ጀነራሉ ከእቋሙ ንቅንቅ አላለም ነበር። በእርግጥ ዛቦርሚዳ ተሳስቶ ነበር?

ከጅምሩ በጣሊያን የበላይ መኮንኖች መካከል አለመግባባት ነበር። በተለይ ጀ/ል ባራቴሪን በመቃወም የሚታወቁት ዛቦርሚዳ እና አልበርቶኒ በውጊያ ወቅት የተለየ አጋጣሚን በመፍጠር ባራቴሪን ከቁጥጥር ውጪ ሊያደርጉት ተንቀሳቅሰዋል። በዚህ የተነሣ አልበርቶኒ እና ዛቦርሚዳ ከአለቃቸው ባራቴሪ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ በመተው በራሳቸው ውሳኔ ብርጌዳቸውን መርተዋል።

ጀነራሎች የፈጠሩትን ክፍተት በመጠቀም በርካታ የኦሮሞ ፈረሰኞችን ያሰለፉት ራስ መኮንን እና ራስ መንገሻ አስገራሚ የማጥቃት ዘመቻ ከፈቱ። በጥቃቱም የኹለቱን ጀነራሎች ብርጌድ ተራ በተራ በመደምሰስ ፊታቸውን ወደ ዛቦርሚዳ ብርጌድ አዞሩ።

ዛቦርሚዳ ሠራዊቱን ማርያም ሽዊት ላይ በማስቀመጥ የሚሆነውን ለመከታተል ነበር የወሰነው። ከቀኑ 6፡30 ላይ ሰባራቶሪ በጻፈው መልዕክት ጦሩ ወሳኝ ቦታ በመያዝ በኹለት ግንባር ጥቃት ለመክፈት ዝግጁ መኾኑን አሳውቋ። ዛቦርሚዳ ያላወቀው ነገር ማስታወሻውን በጻፈበት ሰዓት ጀ/ል ባራቴሪ ወደ ኤርትራ መፈርጠጡን ነበር።

ዛቦርሚዳ ብርጌዱ ከመላው ሠራዊት ተገንጥሎ በጠላት እጅ መውደቁን ያወቀው ከቀኑ 7፡00 ላይ ነበር። በዚያ ሰዓት የኢትዮጵያ ጦር ለብቻው የቀረውን የዛቦርሚዳ ብርጌድ ለመምታት ዝግጅቱን ጨርሷል።



ምስል፡- ጀ/ል ቪቶሪዮ ቋቮርሚዳ (ከላ ኢሉስትራዚዮኔ ኢታሊያና ጋዜጣ የተወሰደ መጋቢት 22 ቀን 1896)

ጠይም የቆዳ ቀለማቸው ከቡናማው ተራራው ጋር ያመሳስላቸው የኢትዮጵያ ወታደሮች ከጠላት ዕይታ በቀላሉ ነበር የተሸሸጉት። በመቶ ሜትር ካነሰ ርቀት የተጀመረው ተኩስ የጣሊያን የጦር መሪዎች ላይ ነበር ያነጣጠረው።

የዳቦርሜዳ 6ኛ እና 7ኛ ባታሊዮኖች በቀኝ በኩል ተኩስ ጀመሩ። ለስድስት ሰዓታት ያህል ምን ይደረግ እንደነበር ያላወቁት የዳቦርሚዳ ወታደሮች ውጊያው ያለቀ መስሏቸው ነበር። ለውጊያ ዝግጅት አልነበራቸውም።

ጀ/ል ዳቦርሚዳ በከፍተኛ ድንጋጤ እና ግራ መጋባት ውስጥ ወደቀ። የበታች ተጠሪው ለነበረው ኮ/ል አይራጊ ባስተላለፈው ትዕዛዝ ድጋፍ መምጣቱ አጠራጣሪ መኾኑን ጠቅሶ ሠራዊቱ የቻለውን ያህል ተከላክሎ ከአቅሙ በላይ ሲሆንበት እንዲያፈገፍግ ገለጸለት።

ራስ አሉላ፣ ራስ መንገሻ፣ ራስ ሚካኤል እና በርካታ የኦሮሞ ፈረሰኞች በተሳተፉበት ውጊያ የዳቦርሚዳን ጦር በቀላሉ ነበር የበታተነው። የተኩስ ልውውጡን ተከትሎ የተደረገ የጨበጣ ውጊያ በርካታ የጣሊያን ወታደሮች አለቁ።

ጀ/ል ዳቦርሚዳ በጨበጣ ውጊያው ከባሻ ገብሬ ጋር ተፋጠጠ። በሽጉጡ ሦስት የባሻ ገብሬን ወታደሮች ከገደለ በኋላ ለመሸሸግ አንድ ዛፍ ሥር ገባ። ባሻ ገብሬም ተከትለውት ቀኝ ደረቱ ላይ በጥይት መትተው ገደሉት።

ባሻ ገብሬ ከሚቹ ጀነራል ዳቦርሚዳ ላይ የወሰዱትን ጎራዴ በኋላም ለአፄ ምኒልክ በስጦታ መልክ አበርክተውላቸዋል።





# ክፍል ሦስት

# ድኅረ አድዋ

# ምዕራፍ ዐሥራ ዐራት

## ተስፋ መቁረጥ፣ ድንጋጤ እና ሽሽት

አፄ ምኒልክ ወደ አድዋ ከመዝመታቸው ቀድሞ ሠራዊት ለመመልመል የሚያስችል ህግ በኢትዮጵያ አልነበረም። የንጉሡ ሠራዊት በዐዋጅ የተጠራ ሲሆን በአገልግሎት ምንም ዓይነት ክፍያ አይደረግለትም። በጥንታዊት ፈረንሳይ በነበረው ዓይነት ሥርዓት በጥሪ ለዘመቻ የሚሰበሰብ ሕዝባዊ ጦር ነበር።

ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ክፍያ ባይኖራቸውም በውጊያ ሲሳተፉ ከመሪያቸው ልዩ ክበሬታን ያገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ የዘመቻውን መጠናቀቅ ተከትሎ በምርኮ የሚገኙ ንብረቶችን እና ጠመንጃዎችን ይከፋፈላሉ።

ከአድዋ ድል በኋላ የሆነውም ይህ ነበር። የምኒልክ ወታደሮች ከጠላት የተማረኩትን ንብረቶች በምርኮኞች ፊት ተከፋፈሉ። ከንብረት ክፍፍል እና ሽልማት ጎን ለጎን የተለመደው የድሀራጦርነት ያድል ሰልፍ ተደረገ። ሰልፉን ቁስለኛ እና ምርኮኛ የጣሊያን አስረኞች እንዲመለከቱት መደረጉ ለተሸናፊው ወገን ከፍተኛ ውድቀት ነበር።

### ሽንፈት እና ሽሽት

የአልበርቶኒ ብርጌድ መበታተን የጣሊያንን ሽንፈት በጠዋት ነበር የጠቆመው። በርካታ የጣንዳ ሠራዊቱ በተለያየ አቅጣጫ የፈረጠጠበት ጀ/ል አልበርቶኒ ከአውሮፓውያን የጦር መሪዎቹ ጋር በመሆን እጅ ሰጠ።

የጀ/ል አሪሞንዲ ብርጌድ ራዕዩ ተራራ ግርጌ ደርሶ በአግባቡ ቦታውን ሳይይዝ ነበር በመፈርጠጥ ላይ ከነበሩት የአልበርቶኒ ወታደሮች ጋር የተገናኘው። በወቅቱ ግዙፍ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ሠራዊት የወገናቸውን ጦር ሲያባርር ከመመልከት ውጪ የአርሞንዲ ወታደሮች ምንም ማድረግ አልቻሉም።





ተበታትኖ በመሮጥ ላይ የነበረው ሠራዊት በስልት ወደ ሳውራ እና አዲግራት ምሽግ ለመምራት ባራቴሪ ያደረገው ሙከራ አልተሳካም ወታደሩ ምንም ዓይነት ትዕዛዝ መስማት አይችልም ነበር። የሁኔታውን አስፈሪነት በመመልከት ራሱ ጀነራል ባራቴሪ በቅሎውን ወደ ሰሜን አቅጣጫ ሽምጥ ጋለበ።

የጣሊያን ሠራዊት በመገስገስ ላይ የነበሩትን የኦሮሞ ፈረሰኞች በተመለከተበት ወቅት የሚገባበት ጠፋው። ቀድሞ በሠራዊቱ ውስጥ ስለ ኦሮሞ ፈረሰኞች የተነገራቸው ኋላ ቀር እና ተራ ተዋጊዎች እንደሆኑ ነበር። በጦር ሜዳ ላይ የተመለከቱት ግን ፈረሰኞቹ እጅግ ፈጣን እና የተካኑ መሆናቸውን ነበር።



Oromo cavalry. From *L'Illustration Italienne*, 22 March 1896.

*ምስል፦ የኦሮሞ ፈረሰኛ ወታደሮች (ከላ ኢሉስትራ ዚዮኒ ኢታሊያና ጋዜጣ) መጋቢት 22 1896)*



Oromo cavalry. From *L'Illustrazione italiana*, 22 March 1896.

ምስል፡- የኦሮሞ ፈረሰኛ ወታደሮች (ከላ ኢሉስትራ ዚዮኒ ኢታሊያና ጋዜጣ) ሰ

22 1896)

የጀ/ል አርሞንዲ የበታች ከኾኑት መካከል ጂዮቫኒ ቴዶኔ ለሠራዊታቸው መሸነፍ ቁልፉን ሚና የተጫወቱት የኦሮሞ ፈረሰኞች መሆናቸውን መስክሯል። የወቅቱን አስፈሪ ሁኔታ ሲገልፅም ‹‹ፈረሰኞቹ ወደ ሽሰቀው ሲወርዱ በድንገት የገነፈለ ጥቁር ባሕር ይመስሉ ነበር›› ብሏል። በወቅቱ ሌ/ኮ አጎስቲኖ ቺኒ፣ ሌ/ኮ ሎሬንዞ ከምፐያኖ፣ ሌ/ኮ ጊሊዮ እንዲሁም በመጨረሻ ራሱ ጀነራል አሪሞንዲ አንድ በአንድ መገደላቸውን ጠቅሷል።

በርካታ የጦር መሪዎች ራሳቸውን አጥፍተዋል። ሌ/ኮ ጋሪባልዲ ፔናዞ እና ሌ/ኮ ማዞሌኒ የኦሮሞ ፈረሰኞችን ጦርና ጎራዴ በመፍራት በራሳቸው ሽጉጥ ራሳቸውን አጥፍተዋል። ቴዶኔ ሁኔታውን ሲገልፅ በተለይ ኮ/ል ፔናዚ መጀመሪያ የተኮሰው ጥይት ስላልገደሰው ለኹለተኛ ጊዜ ደረቱን በራሱ ጥይት መምታቱን ገልጿል። ራሱ ታዶኔ ቆስሎ የተማረከ ሲሆን ቦርነቱም በዚያው ተጠናቋል።

### የዳቦርሚዳ ብርጌድ ፍፃሜ

የዳቦርሚዳ ሠራዊት የሌሎቹን ዕጣ መጋራቱ ባይቀርም እስከ ቀኑ 9 ሰዓት ድረስ ግን ሰላም ነበር። አስፈሪው ፍፃሜ ሲቃረብ የካፒቴን ሞቲኖ መድፈኛ ባታሊዮን ሽፋን እንዲሰጥ በማዘዝ ዳቦርሚዳ ጦሩን በሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ ወደ ኤርትራ እንዲያፈገፍግ አዘዘ።

የዳቦርሚዳ ሠራዊት የመረጠው መንገድ ጠባብ ሽሰቆ ነበር። እግረኛ ወታደሩ እና የዕቃ መጫኛ በቅሎዎች እየተጋፉ መራመድ አልቻሉም። ከጠባብነቱ በተጨማሪ እሾሃማ ቁጥቋጦ እና ቁልቋል ሊያስኬዳቸው አልቻለም ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ከኋላ ሲደርስባቸው እርስ በእርስ እየተረጋገጡ በርካቶች አለቁ። ኮ/ል ፓሉምቦ እና ኮ/ል ካምፓራ ራሳቸውን ሲያጠፉ ኮ/ል አይራጊ ቆስሎ ሽሽቱን ቀጠለ።

በመሸሽ ላይ የነበረው የጠላት ጦር ከሽለቆው ጫፍ ሲደርስ አነስተኛ ጅረት አገኘ። የቻሉ ጅረቱን በመዝለል ሽሽታቸውን ቀጠሉ። የተወሰኑ ወታደሮች በውኃ





ጥም ከመሞት በጥይት መሞትን መርጠው ጅረቱ ላይ አጎንብሰው ውኃ ይጠጡ እንደነበር አልቤርቶ ዋኮት የተባለ ወታደር መስክሯል።

ኢትዮጵያውያኑ ማባረራቸውን አቁመው መመለስ ጀመሩ። ወደ 12:00 ገደማ ድንገተኛ ዝናብ ጀመረ። የተበታተኑ የጣሊያን ወታደሮች ጎድጓዳ ድንጋዮችን በማንሳት ከንፈራቸውን በነጠብጣብ የዝናብ ውኃ ሲያረጥቡ ታይተዋል። የተወሰኑት ደግሞ ዝናብ ያራሰው ልብሳቸውን በአፋቸው ላይ ሲጨምቁ ነበር።

### የሳውራ ሹበር

ከአድዋ የተረፉ ወታደሮች በኹለት አቅጣጫ ወደ ኤርትራ እና ሳውራ ካምፕ ነበር የሸሹት። በሳውራ ቀርተው የነበሩ የጣሊያን ካምፕ ሠራተኞች ከሰዓታት ቡኋላ በመነሳት ለሠራዊቱ ስንቅ እና ትጥቅ ለማቀበል መንገድ ጀምረዋል። መንገዳቸውም በጉንጻብታ በኩል በማለፍ ወደ ዛላ የሚያመራው ነበር።

በወቅቱ በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ ይንቀሳቀስ የነበረው ፒዬትሮ ፊልተር ሳውራ አካባቢ ነበር። ከርቀት የኦሮሞ ፈረሰኞችን በመሸሽ ወደ ሳውራ በመሮጥ ላይ የነበረውን የጣሊያን ሠራዊት በመመልከት ሽሽት ላይ የነበሩት ባንዳ እና ነጭ ጣሊያናውያን ‹‹የሰው ወንዝ›› ይመስሉ ነበር ብሏል።

በሽሽት ላይ የነበሩት የጣሊያን ወታደሮች ሳውራ ሲደርሱ ካምፑ ባዶውን ነበር። በቀጣዩ ሽሽታቸው የሚጠቀሙትን የመንገድ አማራጭ በተመለከተ በአርናልዶ ኒኮሌቲ እና አሌሳንድሮ ሳፕሊ መካከል አለመግባባት ተፈጠረ። ኒኮሌቲ በደብረሰላም በኩል ወደ ባራኺት የሚወስደውን መንገድ በመምረጥ በርካቶችን አስከትሎ ወደ ሞት መራቸው። ሳፕሊ በበኩሉ ጥቂቶችን አስከትሎ በሌላ መንገድ ቀጠለ።

ኒኮሌቲ በአጠቃላይ 80 ተከታዮችን በመያዝ ጉዞውን ቢጀምርም መንገድ ላይ በደረሰበት የገበሬዎች ጥቃት ስምንቱ ብቻ በሕይወት ተረፉ።

የኢትዮጵያ ጦር ሳውራ ላይ ከደረሰ በኋላ ማሳደዱን እንዲያቆም አፄ ምኒልክ አዘዙ። ሠራዊቱ ቢመሰስም በመሸሽ ላይ የነበሩ የጣሊያን ሠራዊቶች ከአጋሜ አካባቢ ነዋሪዎች ጥቃት አላመለጡም ነበር። በጦርነቱ ማግስት መጋቢት 2 ቀን በተለያዩ ቦታዎች መጠነ ሰፊ የገበሬ አመፅ ተቀጣጥሎ በመፈርጠጥ ላይ የነበረውን የጣሊያን ሠራዊት ስቀመጠው።

ሳፕሲ ጉዞ በጀመረበት ወቅት የኤርትራ ተወላጅ ከነበረው ባንዳው ደጃዝማች ፈንታ ጋር ተገናኘ። ከረጅም ጉዞ በኋላ የሳፕሲ ቅምጥ የነበረችው አምላኩ መንገድ ላይ አግኝታው በሰላም ከውጊያው ቀጠና ማምለጥ ቻሉ።

አፄ ምኒልክ ጦራቸው ማባረሩን እንዲያቆም ያዘዙ ቢሆንም በተሸናፊ ጣሊያናውያን ዘንድ በርካታ ኃላፊነት ጥያቄዎች መነሳት ጀምረዋል። የዶጋሊ እና የአምባላጌውን ሁኔታ በማስታወስ የምኒልክ ሠራዊት ቀጣይ የቅጣት በትር ምን ይሆን? በማለት ተጨነቁ። ራስ አሉላ በእስመራ የሚገኘው ቤቱን ለማስመለስ ይመጣ ይሆን? የኦሮሞ ፈረሰኞች ወደ ኤርትራ ይዘልቁ ይሆን? ሕዝቡ ጣሊያንናውያን ላይ ይነሳባቸው ይሆን?

ከሰንዓይቲ፣ ኮሉቲት እስከ አስመራ እንዲሁም ከጊንዳ እስከ ምፅዋ ድረስ በምኒልክ ቀጣይ እርምጃ የተጨነቀው የጣሊያን ቅኝ ገዢ በፍርሃት ራደ። በምፅዋ ሐብት ለማከማት ያሰፈሰፉ አውሮፓውያን የአድዋን ዜና እንደሰሙ ነበር በፍርሃት የተዋጡት። የጣሊያን የቅኝ ግዛት ሕልም ከኤርትራ ብቻ ሳይሆን ከመሳው አፍሪካ ተጠራርጎ የሚወጣበት የመጨረሻ ክስተት በምኒልክ ሠራዊት ቀጣይ እንቅስቃሴ ላይ የተመሠረተ መሸኑ ለመላው አውሮፓዊ ግልጽ ሆነ።





# ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

## ያመረቱትን ማንሳት

የውጊያው ውሎ ሲገባደድ የአድዋ ሰማይ ጨላለመ። ምሽቱ ለጣሊያኖች እፎይታ ነበር። ቢያንስ በምሽቱ የምኒልክ ወታደሮች ማሳደዳቸውን እንደሚያቆሙላቸው ተስፋ አድርገው ነበር። ኢትዮጵያውያኑ ውጊያ ሲካሄድበት በዋለው ሜዳ ላይ እዚህም እዚያም እሳት በማንደድ ለምሽቱ ሥራ ተዘጋጁ። በእላቱ ብርሐን በመታገዝ የጠላትን እና የወገንን ሬሳ በማንሳት እንዲሁም ከጠላት ቁስለኛ ወታደሮች እና አስክሬኖች ላይ ንብረት በመልቀም አመሹ። የኢትዮጵያ ወታደሮች ደመወዝተኛ ባለመሆናቸው በዘመቻ ወቅት ከሚያሸንፉት ጠላት ላይ ንብረት የመዝረፍ ልምድ አላቸው።

ቆሰለው ከተማረኩ የጠላት ወታደሮች መካከል የጦር መሪ የነበሩት አልበርት ዋኮት፣ ጀባኒ ቴዶን እና ሉጂ ጎጅ ይገኙበት ነበር። በርካታ ምርኮኞች ከጦርነቱ በፊት ስለ ኦሮሞ ፈረሰኛ ወታደሮች ኢ-ሰብአዊነት ሰምተው ነበር። ከተማረኩ ፈረሰኞቹ ብልታቸውን እንደሚቆርጧቸው በማስፈራራት በጠላት እጅ እንዳይወድቁ የተቻላቸውን ማድረግ እንዳለባቸው ተነግሯቸው ነበር። በዚህ የተነሣም በርካታ ምርኮኞች በፍርሃት ተውጠው ይንቀጠቀጡ ነበር።

### ሰሎሞናዊው ንጉሥ አፄ ምኒልክ

መጋቢት 1 ቀን ምሽት በኢትዮጵያውያን የጦር ካምፕ ታላቅ የደስታ ድግስ ተደረገ። ጠጅ እና ጠላ ለወታደሩ ቀርቦ የነበረ ሲሆን ምግቡም ገደብ አልነበረውም። ወታደሮቹ በቆራ፣ በጦር ሜዳ ጀብዱ ወሬ እንዲሁም በተኩስ ምሽቱን አደመቁት። አስቱ ኢትዮጵያውያን ወራሪውን ኃይል በመመሰስ ተመሳሳይ ሀሳብ ላላቸው ዙሰት ትምህርት የሰጡበት ነበር። የጦር ሜዳ ጀብዱአቸው የኢትዮጵያ ሉዐላዊነት ለዘመናት ተጠብቆ መኖሩን ያረጋገጠ ነበር።

የአድዋ ድል ለኢትዮጵያ በርካታ ጥቅም አስገኝቶላታል። ድሉ በዘመናዊው የአፍሪካ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ሲሆን ኢትዮጵያ ልዕለ-ሐያል አገር መሆኗን አስመስክራለች። ከዚህ በላይ ግን የትኛውንም አውሮፓዊ አገር የቅኝ ግዛት ሕልም ወደ ቅዠት የቀየረ ነው።

ከአድዋ ከተማ በስሜን አቅጣጫ አዲ አሱን መንገድ ላይ የራስ መንገሻ ካምፕ ይገኛል። ምሽቱ ለራስ መንገሻ የተሰየ ነበር። በአለቲት እና ሰንአፈ የደረሰበትን ሽንፈት በአድዋ ለመበቀል ችሏል። በደቡብ እና ምዕራብ የከተማዋ አቅጣጫ በነበረው የምኒልክ ካምፕ የተለየ ሁኔታ ነበር። ድሉ አፄ ምኒልክ ንጉሰ ንግሥናቸው በጸና ዕለት ላይ የገነቡበት በመሸኑ ደስታው የተለየ ነበር።

የድል ፌሽታው ለጣሊያን ምርኮኞች አሳፋሪ ነበር። ሲቆጣጠሩት በዘመቱበት ሕዝብ እጅ መውደቃቸውን ማመን አልቻሉም። የወቅቱን ሁኔታ ጂዮቫኒ ቴዶን እንደሚከተለው ነበር የገለጸው፡-

> *ወደ ኢትዮጵያ የጦር ካምፕ ሰንወሰድ የተመለከትኩት ነገር ለዓመታት የነበረኝን አቋም አስቀይሮኛል። በነጋሪት እና ስበሮ የታጀበው የኢትዮጵያውያኑ የድል ጭፈራ እና ፉከራ አሰፈሪ ነበር። በየቦታው የነደዱት ክምር ችቦ እና ለሰዓታት የዘለቀው የድል ተኩስ የማንንም ባለንጣ ልብ ያርዳል።*

ካርሎ ዲዮቲም በወቅቱ የማረኩትን ኢትዮጵያውያን መመልከት አስፈርቶት ነበር። ከጦር ሜዳው ወደ ካምፑ በተደረገው ጉዞ ኢትዮጵያውያን የቆሰሉ ወታደሮቻቸውን ተሸክመው ሲጓዙ ስሜታቸው ተረብሾ እና በከፍተኛ ቁጭት እና





ጥላቻ ተሞልተው ነበር። ካምፑ መዳረሻ ላይ የተመለከተው የኢትዮጵያውያን ሴቶች አቀባበል የተለየ እንደነበር ዲዮቲ ጠቅሷል።

ካምፑ መግቢያ ላይ አንድ የቆሰለ የኢትዮጵያ ጦር መሪ በቅሎ ላይ ሆኖ መመልከቱን የገለጸው ዲዮቲ መቆም አቅቶት እንደነበር አስታውሷል። ቁስለኛው የጦር መሪ ዲዮቲን ቁልቁል እያየ በሽሙጥ ‹‹ዓሊ›› በማለት ጠርቶት አለፈ። ‹‹አሊ›› ጣሊያናውያን ዙሉንም ኢትዮጵያዊ ለመጥራት ይጠቀሙበት የነበረ የሽሙጥ ስም ነበር። ከድሉ ምሽት ጀምሮ ግን ኢትዮጵያውያን ዙሉንም የጣሊያን ወታደሮች ‹‹አሊ›› በሚለው ቅፅል ስም መጥራት ቀጠሉ።

ነጭ እና ባንዳ ምርኮኞች በተለያየ አጥር ውስጥ ነበር የታሠሩት። ራሱን ለመግደል ሲሞክር ጉንጩ ላይ ቆስሎ የተያዘውን ኮ/ል ግሪቲ ጨምሮ ቴዶኔ፣ ጌራርዶ ፓንታኖ እና ፍራንሴስኮ ፍሪሲ ከእስረኞቹ መካከል ይገኙበታል።

### በንጉሥ ችሎት ፊት መቅረብ

በድሉ ማግስት ከጠዋቱ 4 ሰዓት አካባቢ በመቶዎች የሚቆጠሩ የጦር ምርኮኞች ወደ ምኒልክ ድንኳን ተወሰዱ። በወቅቱ የነበረው ብቸኛ አውሮፓዊ ምስክር ፈረንሳዊው ካፒቴን ክሉቼቲ ጣሊያናውያኑን በሰልፍ ሲጓዙ ተመልክቷቸዋል። ክሉቼቲ የምኒልክን ገጽታ ለአውሮፓውያን ያስተዋወቀው ሞንዶን ቪዳይልሎት ጓደኛ ነበር። የአፄ ምኒልክ የፀሸ ጠመንጃ ግዢ ያስማማው ካፒቴን ክሉቼቲ ምርኮኞቹ ለ3 ሰዓታት ያህል ጠብቀው ምኒልክን ሳያገኙ በሰልፍ ሲመለሱ ተመልክቷቸው ነበር።

እስረኞቹ ምኒልክ ፊት የቀረቡት መጋቢት 3 ቀን ነበር። በበርካታ ሹማምንቶቻቸው ተከብበው የተቀመጡት አፄ ምኒልክ ለፍርድ ተዘጋጅተው ነበር። የ49 ዓመቱ ንጉሠ ነገሥት ከአውሮፓውያን ጋር የሚገዳደር ግዙፍ ጦር የገነቡ የመጀመሪያው አፍሪካዊ መሪ ናቸው። ከጦርነቱ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሕዝባቸው ፊት የቀረቡትም መጋቢት 3 ነበር።



At the court of Menelik. From *L'Illustration*, 1896.

*ምስል፦ አፄ ምኒልክ በቾሎት ተቀምጠው (መጋቢት 3 ቀን 1896)*

ለፍርድ ከመቅረባቸው በፊት ጣልያናውያኑ ለአፄ ምኒልክ የነበራቸው ግምት የተለየ ነበር። ንጉሡ ምሕረት የማያውቁ እና ጨካኝ መስለዋቸው ነበር። ከንጉሡ ጋር በተገናኙበት ወቅት ግን የተመለከቱት የንጉሡን ሰብዓዊ ርህራሄ እና የተረጋጋ ስብዓና ነበር።

የእስረኞቹ ጉዳይ ከጦርነቱ ቀጥሎ ምኒልክን ያፈተነ ነበር። ከአድዋ በፊት በሐረር እና ወላይታ ዘመቻ የተማረኩ በሙሉ በባርነት ነበር የተወሰዱት። በአድዋ እጅግ በርካታ ምርኮኞች የተያዙ ሲሆን በርካታ ነፎች መኖራቸው የተለየ ያደርገዋል።

መጋቢት 2 ቀን በምኒልክ ድንኳን ውስጥ የምርኮኞችን ዕጣ ፈንታ በተመለከተ ከፍተኛ ክርክር ተደርጎ ነበር። በአጠቃላይ 1900 ነፎ ጣሊያናውያን እና 1500 ባንዳ ወታደሮች ተማርከዋል። በክርክሩ ወቅት ንግሥት ጣይቱ እና ራስ





መንገሻ ሁሉም ጣሊያናውያን እንዲገደሉ እንዲሁም ባንዳዎቹ እንዲቀጡ ሃሳብ በማቅረብ ተከራክሩ። በክርክሩ ወቅት የዶጋሊው ባለድል ራስ አሉላ የቅጣት ሃሳቡን መቃወም አስገራሚ ነበር። አሉላ ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲደረግ ተናግሯል።

ራስ መኮንን ለአውሮፓውያኑ ምርኮኞች የተለየ ርኅራኄ እና ለዘብተኝነት በማሳየታቸው በበርካቶች እንደጠላት ነበር የታዩት። በተለይ የሰሜን ኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑት ጣይቱ፣ መንገሻ እና አሉላ የራስ መንገሻን አስተያየት ከአገር ክህደት ጋር በማያያዝ ነበር የተቃወሙት። ከራስ መኮንን በተጨማሪ ራስ ሚካኤል፣ ንጉሥ ተክለኃይማኖት እና ፈረንሳዊው የምኒልክ አማካሪ ካፒቴን ክሎቼቲ ለእስረኞች ምሕረት እንዲደረግ ጠይቀዋል።

አፄ ምኒልክ ነጭ ምርኮኞችን በተለየ መንገድ ሊጠቀሙባቸው አስበው ነበር። በሞት ከመቅጣት ይልቅ በሕይወት ማቆየቱ የተሻለ ጥቅም ነበረው። ወደፊት ጣሊያን በግዙት ያሉ ዜጎቿን ለማስለቀቅ ስትል ከኢትዮጵያ ጋር መደራደሯ አይቀርም። በድርድሩ ወቅት የእስረኞቹ በኢትዮጵያ መያዝ ለምኒልክ ተጨማሪ ጉልበት ይፈጥራል። በመኾኑም እስረኞቹ በመልካም ሁኔታ እንዲያዙ ምኒልክ ወሰኑ።

በቀጣይ የተደረገው ክርክር 1500 ባንዳዎችን የተመለከተ ነበር። በክርክሩ ወቅት ራስ መንገሻ ባንዳዎቹ በክህቲት፣ ሰንአፈ እና አድዋ ከጠላት ጎን በመቆም አገራቸውን ስለወጉ በሞት እንዲቀጡ ጠየቁ። ራስ አሉላ በአምባላጌ የተማረኩ ባንዳዎችን ቀድመው ያስጠነቀቁት እንዲህ ብለው ነበር ፡ - «. . . ንጉሥ እና አገር ያላችሁ ለጠላት ንጉሥ በመወገን አገራችሁ እና ንጉሳችሁን ወግታችኋል። በዚህ ክህደታችሁ ደግሞ እጃችሁን አቆርጣለሁ።»

በመጨረሻም አፄ ምኒልክ ከጣይቱ፣ አሉላ፣ መንገሻ እና አቡነ ማቴዎስ ጋር በመወያየት የቅጣት ውሳኔያቸውን አስተላለፉ። 1200 ባንዳዎች የቀኝ እጃቸው እና የግራ እግራቸው እንዲቆረጥ ፈረዱ። ፍርዱ የተፈፀመባቸው 300 ባንዳዎች ወደ



At the court of Menelik. From *L'Illustrazione Italiana*, 1 March 1896.

ምስል፡- አፄ ምኒልክ በቾሎት ተቀምጠው (መጋቢት 3 ቀን 1896)

ትውልድ መንደሮቻቸው እንዲመለሱ ወደ ኤርትራ ተሸኝተዋል። በፍርዱ አፈፃፀም ወቅት በርካቶች በብዛት ደም ፈሷቸው ሞተዋል።



Askari à exposer. From *L'Illustration* du 4 Mai 1896.

*ምስል፦ ፍርድ የተፈፀመባት ባንዳ ወታደር (መጋቢት 3 ቀን 1896)*

የምኒልክ ፍርድ ከጣሊያውያኑ ይልቅ ባንዳዎችን ጎድቷል። ጣልያውያኑን በመክዳት ወደ ምኒልክ የተመለሱ ባንዳዎች በጣሊያን ተመልሰው ከተማረኩ የሚጠብቃቸው ፍርድ የከፋ ነበር። ከአምባላጌ ቀድሞ ከጣሊያን የከዳ አንድ ባንዳ ለኢትዮጵያ በመዋጋት ላይ ሳለ በጣሊያኖች እጅ ገባ። በአውሮፓውያን ህግ መሠረት ከዳተኛ አገር ክህደት ወንጀል ተከስሶ በሞት ነበር የተቀጣው።

የኤርትራ ተወላጅ ባንዳዎች ላይ የተወሰደው የቅጣት እርምጃ በርካታ የኤርትራ ተወላጆችን አስቀይሟል። ይህ ስሜት እየጎላ በመቀጠሉ ለወደፊቱ የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት ማነቆ ሆኗል። የቅጣት እርምጃው የራስ መንገሻ






ሃሳብ መሸኑን በመጥቀስ ገ/ኢየሱስ አፄ ምኒልክን ለመሸፈን ሞክሯል። ሙከራው ግን ምኒልክን ከተጠያቂነት አላዳናቸውም።

የቅጣት እርምጃውን ኢ-ሰብአዊነት በመግለፅ ለጠየቃቸው አንድ የእንግሊዝ ጋዜጠኛ፣ አፄ ምኒልክ የሰጡት ምላሽ ቁጣ የተቀላቀለበት ነበር። ***«የፈፀሙትን ወንጀል ሰምተሃል? ለብዙ ክርስቲያናትን በመግረፍ እርኩሰትን ፈፅመዋል። መንደሮቻችንን በመዝረፍ ሕዝቤንም ገድለዋል። የፈፀሙት ወንጀል አንድ ሴባ የሚያደርገውን ነው። በእነሱ ላይ የሚሰጠውን ፍርድ ሰጥተናቸዋል። ለእገርህ እንግሊዝ ይህንኑ ንገር።»***

የኢትዮጵያ ጠላቶች እጅና እግራቸው የተቆረጡ ባንዳዎችን ፎቶ በተለያዩ ጋዜጦች ላይ በማውጣት ክፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ ከፈቱባቸው።



Askari imprisoned. From *L'Illustrazione del mondo*, 3 May 1896.

ምስል፡- ፍርድ የተፈፀመበት ባንዳ ወታደር (መጋቢት 3 ቀን 1896)

# ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

## ረጅሙ ጉዞ

በ1830ዎቹ በርካታ የአውሮፓ ጎብኚዎች የትግራዩን ራስ ውቤ ወዳጅ ለማድረግ ይጣጣሩ ነበር። የተለያዩ ስጦታዎችን በማቅረብ ቢደልሏቸውም የራስ ውቤን አመኔታ ማግኘት አልቻሉም። የፈረንሳዩን ንጉሥ ሉዊስ ፍሊፕ ፎቶ ግራፍ ስጦታ ላቀረቡላቸው ፈረንሳውያን የሰጡት ምላሽ ማስጠንቀቂያ ያዘለ ነበር። *«. . . እግራችሁ መሬቱን ሲረግጥ ደምሮ ተጠንቀቁ። እናንተ እና እንግሊዞች ጤናማ ለገራችንን እንደምትመኙ ዐውቃለሁ። ለንጻችሁ አፅዋቶቻችንን ሰተሰቅሙ ሌላችሁ ደግሞ ድንጋይ ታነሰላችሁ። የምትፈልጉት እኔን ከሆነ እንዳትተናኩኝ ተጠንቀቁ።»*

የራስ ውቤ የጥርጣሬ ጥያቄዎች ከ60 ዓመታት በኋላም ነበሩ። አፄ ምኒልክ ጣሊያንን ወደ ቀይ ባሕር በማባረር ለራስ ውቤ ጥርጣሬ ምላሽ ለመስጠት አስበው ይሆን? በጣሊያን የተያዘውን የኤርትራ አገረ-ግዛት ኢትዮጵያ ለዘመናት ስታስተዳድረው ቆይታለች። ነገስታቷ ምፅዋን የንግድ ማዕከል በማድረግ ደጋማውን የኤርትራ ምድር የንግዳቸው መተላለፊያ አድርገው ኖረዋል። አፄ ዮሐንስ እና ራስ አሉላ በ1880ዎቹ የግብፅን እና የጣሊያንን የወረራ ሙከራ በመመከት ኤርትራን በግዛታቸው ሥር አቆይተዋል።

ከአድዋ ድል በኋላ የኤርትራን ቀጣይ ዕድል ለመወሰን እና ጣሊያንን ጠራርጎ የማስወጣት አቋም የተንፀባረቀው በጣይቱ እና ራስ አሉላ ነበር። አፄ ምኒልክ በወቅቱ ዘመቻቸውን ለማስቀጠል ያመነቱት በርካታ ሁኔታዎችን በመገምገም ነበር። ብዙ ቁጥር ያለው ወታደራቸውን መቀለብ የማይቻል ነበር። ከማዕከላቸው በመራቅ የሰሜኑን ዘመቻ መቀጠል ደግሞ የአቅርቦት ችግር ያስከትላል። ክረምት በመቃረቡም ዝናቡ ዘመቻውን አስቸጋሪ ያደርግባቸዋል።





ወደ ኤርትራ ዘመቻውን መቀጠል የባሕል እና ኃይማኖት ግጭት ሊያስከትል እንደሚችል በመገመት ነበር ምኒልክ ጦራቸውን ለማዝመት ያቅማሙት። በምዕራብ ከሱዳን ጀምሮ እስከ ቀይ ባሕር በተዘረጋው ደጋና ቆላ የሚኖሩ የኤርትራ ሕዝቦች የእስልምና ዕምነት ተከታዮች ናቸው። በመኾኑም የሰሜኑ ዘመቻ መቀጠል ለምኒልክ የባህል እና የኃይማኖት ተቃርኖን የመጋፈጥ ያህል ነበር።

በድል በመገፋፋት ዘመቻውን ወደ ሰሜን ማስቀጠል ሠራዊታቸውን ከማዳከሙም በላይ በየሳምንቱ አዳዲስ ወታደሮችን ምፅዋ እያራገፈ ካለው የጣሊያን ጦር ጋር ይጋፈጣል። ይህንን በመመልከት ነበር አፄ ምኒልክ ውጤቱ የማይገመተውን ዘመቻ ያልቀጠሉት። በእጃቸው ያሉ ምርኮኞችን ተፅእኖ ለመጠቀም በመወሰን የሰሜኑን ዘመቻ በመተው በመጨረሻም አፄ ምኒልክ ወደ ማዕከላቸው ሸዋ የመልስ ጉዞ ጀመሩ።

በአድዋ ጦርነት 1000 ጣሊያናውያን መሞታቸውን እና 1900 ደግሞ መመረካቸውን አውሮፓውያን ሲሰሙ የጣሊያንን ወራሪነት ይረዳሉ። ይህንን ለአውሮፓውያን ለመግለፅ አፄ ምኒልክ ምርኮኞችን ለመያዝ ወሰኑ። ወደ ሸዋ ረጅሙን ጉዞ ሲጀምሩ ምርኮኞችን በተለያዩ መኮንኖቻቸው እጅ አከፋፍለዋል። ቁስለኛ ምርኮኞችን ለራስ መንገሻ መተው 800 የሚኾኑትን ወደ ሸዋ ይዘው ለመመለስ ወሰኑ። ከ50 እስከ 100 የሚደርሱ እስረኞችን ለጦር መሪዎቻቸው አከፋፈሉ።

ለከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኞቻቸው ደግሞ የጣሊያንን ምርኮኛ መኮንኖችን አከፋፈሉ። ለንጉሥ ተክለኃይማኖት ጀ/ል ጂዮቫሊ ጋሜራን፣ ለፍትህ ሚ/ር አፈን ንጉሥ ነሲቡ ደግሞ ሌ/ኮ ጌራርዶ ፓንታኖን በእደራ መልክ ሰጡ። የተሰጧቸውን እስረኞች በመልካም ሁኔታ እንዲይዙም መኮንኖቻቸውን አስጠንቅቀው ነበር።

ከአድዋ ወደ አዲስ አበባ የተደረገው የመልስ ጉዞ በሹሰት አቅጣጫ ነበር የተደረገው። የተወሰኑ ተመላሾች የምዕራቡን አቅጣጫ በመያዝ በተምቤን እና ላስታ በኩል ወደ ሰቆጣ ወረዱ። የምኒልክ የጉዞ መስመር ደግሞ በምሥራቅ በኩል በእዲግራት እና መቀሌን በማለፍ አሸንጌ ሐይቅ በኩል ወደ አዲስ አበባ የሚያመራው ነበር።

የመልስ ጉዞው በአጠቃላይ ዠሰት ወር ከግማሽ የፈጀ ነበር። አፄ ምኒልክ አዲስ አበባ የገቡት ግንቦት 22 ቀን ነበር። ወደ ሐረር እና ሌሎች ግዛቶች የሚደረገው የመልስ ጉዞ እስከ ሐምሌ መጨረሻ ድረስ ቀጥሏል።

የመልስ ጉዞው በዠሰቱ ሕዝቦች መካከል መላመድን እና የበለጠ መተዋወቅን ፈጥሯል። በጉዞው ላይ ጣሊያናውያን የአማርኛ ቋንቋ፣ ባሕልና ምግቦችን ተለማመዱ። በኢትዮጵያውያን ባህል መሠረት ከብት እና ዶሮ የሚታረደው ሥርዓቱን የጠበቀ ጸሎት ተደርጎ ነው። ካርቴን ማኒ የተባለ ጣሊያናዊ በአውሮፓ እንደተለመደው የዶሮ አንገት በመጠምዘዝ እርድ ሲፈጽም በመታየቱ ውግዘትን አስከትሏል።





# ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት

## የመንፈስ ልጆች እና የፍቅር እስረኞች

የአፄ ምኒልክ ሠራዊት አዲስ አበባ የደረሰው ግንቦት 22 ቀን 1896 ዓ.ም ነበር። ከተማዋ ከባሕር ጠለል በላይ 7000 ሜትር ላይ ትገኛለች። የመጀመሪያው የአፄ ምኒልክ መቀመጫ የነበረው እንጦጦ ደግሞ በ9000 ሜትር ከርታ ላይ ይገኛል። ሠራዊቱ እንጦጦ እንደደረሰ ነበር የአቀባበል ሥርዓቱ የጀመረው።

ሠራዊቱ በስልፍ ነበር ወደ ከተማ የገባው። ጣይቱ ባማረ ሁኔታ ታጅበው ካሰፉ በኋላ ራሶች እና ደጅአዝማቾች ተከተሉ። ዝቅተኛ ማዕረግ ያላቸው መከንኖች የነበር እና የለቦ ሸማኔ ቆዳ ለብሰው አለፉ።

አፄ ምኒልክ ታጅበው ቤተ-መንግስታቸው ሲደርሱ ሰበርካታ ግዚያት መድፍ ተተኮሰ። ከመድፍ እና ጠመንጃዎች አፈ-ሙዝ የወጣው ጭስ ለሰዓታት እንደ ደመና ፀሐይዋን ጋርዷት ቆይቷል። ንጉሡ ቤተ-መንግስታቸው ከመድረሳቸው ቀድሞ ከአድዋ የማረኳቸው የተለያዩ የጦር መሣሪያዎች ተደርድረው ነበር። ንጉሡ ወደ አልፈኖቸው ያለፉት የተደረደሩትን የጦር መሳሪያዎች በኩራት ገርመም አድርገው ነበር።

በ1897 አዲስ አበባ ከከተማነት ይልቅ የአንስተኛ መንደር ገጽታ ነበራት። ከተሰመረተች ገና ዐሥር ዓመት ያልሞላት ስትሆን ከ10 ሺህ ያልበለጡ ነዋሪዎች ብቻ ነበሯት። ከፍ ባለ ቦታ የተገነባውን የአፄ ምኒልክ ቤተ-መንግሥት በመከበብ የተሰሩ ጥቂት መኖሪያ ቤቶች የነበሩ ሲሆን ልዩ የሆነ የገበያ ሥፍራ እንዲሁም መጠሪያ ስም የነበረው ጎዳና አልነበረም።

ከቤተ-መንግስቱ ሰሜን አቅጣጫ የራስ ሚካኤል፣ በደቡብ ምሥራቅ በኩል ደግሞ የራስ ደርጌ መኖሪያ ቤቶች ነበሩ። ጉበታ ላይ የተገነቡ ቤቶችን ያቀፈው የምኒልክ ግቢ ከየትኛውም አቅጣጫ ይታያል። የንጉሡ መኖሪያ አልፍኝ ባለ 8 ጎን እና አንድ ፎቅ ሲሆን በቀይ ቆርቆሮ ጣሪያው የተከደነ ነበር። ከአልፍኙ አጠገብ 600 ሰዎች የሚያስቀምጥ አዳራሽ ነበር። የንጉሡ ግምጃ ቤት፣ ፖስታ ቤት፣ እና የቴሌግራፍ ቢሮ በኹለተኛው ዙር ይገኛሉ። የቤተ-መንግስቱ ማዕድ ቤት፣ የእቃ ግምጃ ቤት፣ የንጉሡ በቅሎ ቤት፣ የኮርቻ ቤት፣ የክቡር ዘበኞች መኖሪያ፣ የጥገና ቤት እና የሰዓት ማማ በሦስተኛው ዙር የነበሩ ቤቶች ናቸው።

የቤተ-መንግስቱ ጊቢ በበርካታ የባሕር ዛፍ ችግኞች የተሞላ ነበር። ለኢትዮጵያ እንግዳ የሆነው ባሕር ዛፍ በቶሎ በመድረስ የአካባቢውን የማገዶ ችግር ለመቅረፍ አግዟል። ሐረር በ1887 በምኒልክ ቁጥጥር ሥር ከዋለች በኋላ ከሐረር አዲስ አበባ የተዘረጋው የንግድ መስመር በርካቶችን ወደ ከተማዋ ስቧቸዋል።

በ1889-1892 ከነበረው ረኃብ የተነሣ በርካታ ሕዝብ ከተለያየ አቅጣጫ ወደ አዲስ አበባ መጉረፍ ጀመሩ። የንጉሡን የምግብ እርዳታ ፈልገው የመጡ ሕዝቦች በመጨረሻም ከተማዋን ሙኖሪያቸው አደረጓት። በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት ወታደራዊ መንደር ትመስል የነበረችው አዲስ አበባ በ1890ዎቹ በፍጥነት በማደግ የኢትዮጵያ የፖለቲካ እና የንግድ ማዕከል ለመሆን የሚያስችሳትን ቅርፅ ያዘች።

በርካታ የፈረንሳይ፣ አርሜኒያ፣ ህንድ፣ ግሪክ እና አይሁድ ነጋዴዎች በከተማዋ መንቀሳቀስ የጀመሩት በ1890ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ነበር። ነጋዴዎቹ ከሶማሊ ጠረፍ ከሚገኙት የአቦክ፣ ታጁራ፣ እና ጅቡቲ ወደቦች ዕቃ በማምጣት በአዲስ አበባ ይሸጡ ነበር። በምዕተ ዓመቱ መገባደጃ የአዲስ አበባ ነዋሪ ቁጥር ከ50ሺ በላይ ደርሶ ነበር።





## የእስረኞች መኖሪያ

አዲስ አበባ ለእሥረኞች የተለየ ቦታ አልነበራትም። ከወላይታ ተይዘው የመጡ ምርኮኞች በባርነት ለምኒልክ ቤማምንቶች የተከፋፈሉ ሲሆን እንደ እስረኛ የተቀመጡ አልነበሩም። ከአድዋ በኋላ ወደ አዲስ አበባ የመጡትን ወደ 2 ሺህ የሚጠጉ የጣሊያን ምርኮኞች ለማስቀመጥ የሚሆን ወህኒ ቤት አልነበረም። አፄ ምኒልክ እስረኞችን ለድርድር ለማዋል በማሰባቸው እንዲያዙ አዘዋል። እሥረኞችን በአንድ ቦታ ማሳር ሰፕበቃ ሥራ ቀላል ቢሆንም ለእስረኞች ጤንነት ግን መልካም አልነበረም።

አፄ ምኒልክ እሥረኛ ጣሊያናውያን ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅለው እንዲኖሩ ወሰኑ። በውሳኔያቸውም ኹሰት ሦስተኛ የሚኾኑት እስረኞች በአዲስ አበባ ከጠባቂዎች ጋር እንዲኖሩ ሲደረግ የቀሩት ደግሞ ከላስታ እስከ ሐረር ባሉ ከተሞች ተበተኑ። የተወሰኑ እስረኞች ለማምለጥ ሙከራ ቢያደርጉም ነጭ አውሮፓውያን በቀላሉ ስለሚለዩ ወዲያውኑ ይያዙ ነበር። አብዛኛው እስረኛ ወደ አገራቸው ለመመለስ የሚያስችላቸውን ድርድር በጉጉት መጠበቅ ጀመሩ።

በርካታ እስረኞች ከጠባቂዎቻቸው እና የተቀረው ነዋሪ ጋር ተላምደው ኑሮ ጀመሩ። በዘመናዊ የቅኝ ግዛት ታሪክ ብዙ ቁጥር ያላቸው አውሮፓውያን ከጥቁር አፍሪካውያን ጋር ተቀላቅለው የኖሩበት አጋጣሚ በአዲስ አበባ ታይቷል። ጥቂት እስረኞች ከኢትዮጵያውን ሴቶች ጋር ፍቅር እስከመጀመር ደርሰው ነበር። የተለያዩ ገጠመኞቻቸውን በግል ማስታወሻቸው እና ጋዜጦች ላይ ያሰፈሩ እስረኞችም ይህንኑ መስክረዋል።

በኹለቱ ሕዝቦች መካከል የተፈጠረው መቀራረብ ቀድሞ እርስ በእርሳቸው እንደ ልዩ ፍጡር ይተያዩ የነበሩ ሕዝቦች ተመሳሳይ ሰብዓዊ ፍጡራን መሆናቸውን

እንዲያውቁ አግዟል። የተወሰኑ ጣሊያናውያን ቤት በመገንባት እና በንግድ እንቅስቃሴ በመሳተፍ የከተማዋ ነዋሪ ኾኑ።

ጣሊያናውያኑ ካደረጉት እንቅስቃሴ መካከል የመጀመሪያው መገለጫ የገነቡት ቲያትር ቤት ነበር። በጣሊያኗ የወደብ ከተማ ኔፕልስ ታዋቂ የነበረውን ቲያትር ቤት ለማስብም ‹‹የአዲስ አበባው ሳን ካርሊኖ›› በማለት ሰየሙት። ከቲያትር ቤቱ ቀጥሎ ደግሞ ‹‹የምኒልክ ሳሎን›› የተባለ መጠጥ ቤት ተከፈተ።

የጣሊያናውያኑን ‹‹የምኒልክ ሳሎን›› የተመለከቱት አፄ ምኒልክ በባለቤትነት የሚያስተዳድሩት ሆቴል ከፈቱ። ሆቴሉ በተመጣጣኝ ዋጋ የተለያዩ ምግቦችን እና ጠጅ በማቅረብ በርካታ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን ያስተናግድ ነበር። የምኒልክ ሆቴል የበርካታ ጣሊያናውያን መሰባሰቢያም ነበር። በአንድ ወቅት ጣሊያኖችን በማጣጣል በፈረንሳይ ጋዜጣ ላይ የጻፈው የምኒልክ ወዳጅ ሞንዶን ቪላልሄይት በሆቴሉ መመሳለስ ሲያዘወትር ጣሊያናውያን ደንበኞች ወደ ሆቴሉ መምጣት አቆሙ። ይህንን የተመለከቱት አፄ ምኒልክ ሞንዶንን ከሆቴላቸው በማስቀረት የጠፉ ደንበኞቻቸውን መመለስ ቻሉ።

እስረኛ ጣሊያናውያን አዲስ አበባ እንደደረሱ ከአፄ ምኒልክ የፋናስ እና እስከ ሰባት አሞሌ የሚደርስ የገንዘብ ስጦታ ተደረገላቸው። ራስ ሚካኤልም እንዲሁ ለእስረኞች የልብስ መግዣ የሚሆን ገንዘብ አድለዋቸው ነበር። እስረኞች ወደ ገበያ ሥፍራ በማምራት የፈለጉትን ይገዙ ነበር።

በወቅቱ እንደተቋቋመ የሚነገርለት መርካቶ በሳምንት ለስድስት ቀናት የሚያገለግል የገበያ ሥፍራ ነው። በመርካቶ የማይሸጥ ዕቃ አልነበረም። የምግብ ቁሳቁስ፣ አልባሳት፣ እንስሳት፣ የጠፍር አልጋ፣ ጌጣጌጥ፣ መስታወት፣ ሳምባ፣ የሸክላ ምርቶች እና የቆዳ ውጤቶች ይገኙ ነበር። ጣሊያናውያንን የበለጠ የሳባቸው በአድዋ ከሞቱ የጣሊያን ወታደሮች ላይ የተሰቀሙ ኒሻኖች፣ አልባሳት፣ የግል ማስታወሻዎች





እና የተለያዩ ፎቶዎች ነበሩ። በአዲስ አበባ የነበሩ ምርኮኞች የጓደኞቻቸውን ማስታወሻ ለመግዛት ጥረት ሲያደርጉ ይታዩ ነበር። ከአዕምሯቸ ብዛት እና የዋጋ ውድነት አንፃር ኹሉንም ለመግዛት አልቻሉም። ከእስረኞቹ መሃል ኒኮላ ዲ አማቶ የአንድ ጓደኛውን የግል ማስታወሻ ለመግዛት ጠይቆ ዋጋው ተወደደበት። ጠባቂው የነበሩት አቶ ገብርኤል በመጨረሻም ማስታወሻውን እንዲገዙለት ጠይቋል።

እስረኞች በተለያዩ ሥራዎች መሰማራት ጀመሩ። በአነስተኛ ክፍያ ተቀጥረው በአናጢነት፣ በግንበኝነት እና ሕክምና ሥራ የተሰማሩም ነበሩ። በአዲስ አበባ የመንገድ ግንባታ ከተሰማሩት በተጨማሪ 24 እስረኞች የምኒልክን ቤተ-መንግሥት ለመገንባት እና የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለመሥራት በንጉሡ ተቀጥረው ነበር። የሕክምና ባለሙያ እስረኞች የተለየ እንክብካቤ ይደረግላቸው ነበር። በቤተ-መንግስቱ ግቢ የመኖሪያ ቤት ተሰጥቷቸው የሚኖሩ ታማኝ እስረኞችም ነበሩ።

## የፍቅር እስረኞች

በርካታ እስረኛ ጣሊያናውያን ባለሙያ እንደኾኑ በማስመሰል በአዲስ አበባ ለመቆየት ተጣጣሩ። የእጅ ሙያ ያልነበራቸው ጣሊያናውያን እስረኞች ወደተለያዩ ግዛቶች ይላኩ ነበር። ካርሎ ዲዮቲ የአናጢነት ሙያ እንደሚችል በመግለፅ ከጂዮቫኒ ሮሲ ጋር በመሆን አርማንዶ ሳቮሬ በተባለ ፈረንሳዊ ነጋዴ ተቀጠሩ።

ሮሲ ለሥራ ከከተማ በወጣበት አጋጣሚ ተዋበች ከተባለች ሴት ጋር ለመቀራረብ የቻለው ዲዮቲ መልካም የሥርቆሽ ፍቅር ማሳለፉን ጽፏል። የተዋበች ባል ነጋዴ በመኾኑ ብዙ ጊዜ ከአዲስ አበባ ውጪ ስለሚቆይ ዲዮቲ እና ተዋበች ሰፊ ጊዜ ማሳለፍ ችለው ነበር። ስሰ ቤተሰቦቹ እና በጦር ሜዳ ስለሞቱ ጓደኞቹ በሚያወራላት ወቅት ታለቅስ እንደነበር ጠቅሷል።

እስረኞች ከኢትዮጵያውያን ጋር ተቀላቅለው በመኖራቸው የተነሣ ኹሉቱ ሕዝቦች በባህል ልውውጥ ለማድረግ ችለዋል። ቤተሰባዊ ቅርርብ በፈጠረው ጥልቅ

መግባት፣ አንዳንድ ጣሊያናውያን ከኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ጋር ጥልቅ መተሳሰር ፈጥረው ነበር።

በሳስታ እሥር ሳይ የነበረው ፍራንሲስኮ ፍሪሲና በግዞት ከተቀመጠበት ቤተሰብ ጋር ጥሩ ቁርኝት ፈጥሮ ነበር። ቆይታውን ጨርሶ ሊመለስ ሲል ከጣሊያን ቀይ መስቀል የተላከለትን ሳሙና፣ የታሸጉ ፍራፍሬዎችን፣ የጽሁፍ መሣሪያዎችን፣ አልባሳትን፣ ሲጋራ፣ መጠጦችን እና አልባሳትን ላስተናገዱት ቤተሰቦች ሰጥቷቸዋል። ከዓመታት በኋላ እንኳን ሊረሳቸው የማይችሉ ቤተሰቦቹ መሆናቸውን ተናግሯል።

ሌላው አስረኛ ጂዮቫኒ ቴዶን ሀረር አካባቢ በሚገኝ አንስተኛ መንደር ብሩ የተባሉ ባላባት ቤት በግዞት ተቀምጦ ነበር። ባላባቱ ስድስት ሚስቶች ነበሯቸው። የንጉሡ ሚስቶች ከቴዶን ጋር በቀላሉ መላመዳቸው ባለቤታቸውን አስቀንቷቸው ነበር። ሁኔታው ያላማራቸው ብሩ ቴዶን እንዲያንባ ሀሳብ አቀረቡለት። ሀሳባቸውን አለመቀበሉ ያበሳጫቸው ብሩ ቴዶንን ለሌላ ባላባት ሰጡት።

በሹለተኛ ማረፊያው ቤት ትንሽ እንደቆየ ዘውዲቱ ከተባለች ሴት ጋር ተቀራረበ። በወቅቱ የ24 ዓመት ወጣት የነበረው ቴዶን በጣም መልከመልካም በመሆኑ ጓደኞቹ ከጀርመኑ ንጉሥ ዊልሄልም ኹለተኛ ጋር ያመሳስሉት ነበር። ዘውዲቱ በፍቅሩ በመውደቅ አብራው ወደ ጣሊያን ለመሄድ ወሰነ እንደነበር በማስታወሻው ፅፎታል። ቴዶን በማስታወሻው ራሱን ‹‹የፍቅር አስረኛ›› በማለት ነበር የገለጸው።

### አፈ-ንጉሥ

ጌራርዶ ፓታኖ ለአፈ-ንጉሥ ነሲቡ በአደራ የተሰጠ አስረኛ ነበር። አፈ ንጉሡ ለፓታኖ ቤተሰቦች ደህንነቱን ለማሳወቅ ብርቱ ጥርት እንደሚያደርጉ ቃል ገቡለት። በጊታቸውም እንደ ልጃቸው እንደሚያኖሩት ቃል ገቡለት። ከአንድ ወር በኋላ ፓታኖ እና አፈንጉሡ ነሲቡ በደንብ ተግባቡ። በአፈ-ንጉሡ ቤትም ‹‹የመንፈስ ልጅ›› ሆኖ መኖር ጀመረ።







Le Negus Ne'ilik. From Gabriel Sellassié, *Chronique du règne de Ménélik II, roi des rois d'Ethiopie*. Paris, Missionnaires Frères, 1930.

***ምስል፦ አፈ-ንጉሥ ነሲቡ***

አፈ-ንጉሥ ነሲቡ ከልጅነታቸው ጀምሮ የኢትዮጵያ መሠረታዊ የሕግ ዕውቀት እና ፍትሐ ነገስት ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። በ18 ዓመት ዕድሜያቸው በፍርድ ቤቶች ጥብቅና መቆም ቻሉ። ይህንን የተመለከቱት አፄ ምኒልክ ወጣቱ ነሲቡን አፈ-ንጉሥ ልዩ ዐቃቢ ሕግ፣ በኋላም የፍርድ ሚኒስትር አድርገው ሾሟቸው።

አፈ-ንጉሥ ነሲቡ የምኒልክ ቀኝ እጅ ለመሆን የበቁት በአጭር ጊዜ ውስጥ ነበር። ንጉሡ የሕግ ተርጓሚ እና ይግባኝ ሰሚ የነበሩበትን ሥርዓት ለማሻሻል አፈ-ንጉሥ ነሲቡ በዳኝነት ማገልገል ጀመሩ። በዚያ የተነሣም ከፈቱ መኮንን፣ ራስ መንገሻ እና ራስ ወሌ አኩል ተፅእኖ ፈጣሪ መሆን ቻሉ።

ፓታኖ ጥልቅ የመፅሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ነበረው። ከአፈ-ንጉሥ ነሲቡ ጋር ይበልጥ ያቀራረበውም የመፅሐፍ ቅዱስ እውቀቱ ነበር። አፈ-ንጉሥ ፍርድ የሚሰጡበት አዳራሽ ፓታኖን ከጎናቸው በማስቀመጥ ምክር እና እገዛ ያገኙ ነበር። በፓታኖ እገዛም በኢትዮጵያ እና ጣሊያናውያን አስረኞች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን እና ክሶችን በቀላሉ መጻኘት ቻሉ።



Ras Negous Neriha. From Gabbre Sellassé. *Chronique du règne de Menelik II, roi des rois d'Ethiopie*. Paris: Maisonneuve Frères, 1930.

# ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት

## ምኒልክ ከአድማስ ባሻገር

‹‹አትላንታ ኮንስቲቲውሽን›› ጋዜጣ መጋቢት 1 1896 እትሙ ወደ አፍሪካ የመመለስ ዓላማ ለነበራቸው ጥቁር አሜሪካውያን የሚሆን መልዕክት ይዞ ነበር የወጣው። በዕትሙ የተጻፈው መጣጥፍ ከጃርጂያ ወደ አፍሪካ የመመለስ ፍላጎት የነበራቸው ጥቁር አሜሪካውያንን አስጠንቅቋል። የአፍሪካ ሙሉ በሙሉ በነጭ አውሮፓውያን ቁጥጥር ሥር በመዋሏ የጥቁር አሜሪካውያን የመልስ ጉዞ ውጤት አልባ መሽኑን መጣጥፉ ጠቅሷል።

የአድዋ ድል ዜና ለዓለም በተለማ ማግስት የአትላንታው ጋዜጣ ሚዛናዊ ዜና አወጣ። በመጋቢት 4 እትሙ ‹‹የጣሊያን ከፉ ዕጣ›› በሚል ርዕስ ያወጣው ጽሁፍ 3000 የጣሊያን ወታደሮች በአቢሲኒያ ሕዝቦች መገደላቸውን ገለጸ። ጽሑፉ ጀ/ል አሬስቴ ባራቴሪ በከፍተኛ ውርደት ራሱን ማጥፋቱን የገለጸ ሲሆን ኢትዮጵያ በደቡብ አፍሪካ የምትገኝ መሆኗን አሳስቶ ጠቅሷል።

በተከታታይ የወጡ የአትላንታ ኮንስቲቲውሽን ጽሑፎች የኢትዮጵያውያን የቆዳ ቀለም ላይ ያተኮሩ ነበሩ። ‹‹የአቢሲኒያ ጥያቄ›› በሚል ርዕስ የወጣ ጽሁፍ ‹‹. . ***ኢትዮጵያውያን እንደተቀሩት ጥቁር አፍሪካውያን እና የሆቴንቶ ሕዝቦች ሰፊ አንር እና ድፍጥጥ አፍንጫ የላቸውም። እንደ ኮንጎ ሕዝቦችም ለጭር እና ለስቀያሚ አይደሉም። ጥቁር አይደሉም***›› በማለት አትቷል። የኢትዮጵያ ንጉሥ ከኒኮላስ ዝለተኛ ተመሳሳይ መልክ እንዳለውም በጽሁፍ ተገልጿል።

ኒውዮርክ ወርልድ እና ቺካጎ ትሪቢውን ጋዜጠኞችም ተመሳሳይ ጽሑፎችን ነበር ያወጡት። አፄ ምኒልክ ነጭ ቀለም እንዳላቸው የሚያሳዩ ፎቶዎችን በማስደገፍ የካውካሰያን ዝርያ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ጣሊያንን የማሸነፋቸውን ዜና አራገቡት። ‹‹የአቢሲኒያ ሕዝቦ በአብዛኛው ካውካሰያን ሲሆን የተስተካከለ የፊት ቅርፅ ያላቸው ቆንጆ ሕዝቦች ናቸው።››







THE ATLANTA

VOL. XXVIII ATLANTA, GA., WE

ITALIANS FELL.

MENELIK VICTORIOUS

ITALIAN FAILURE

A LAW AGAINST GOLD COINTI

Menelik in America. From the *Atlanta Constitution*. 4 March 1896.

***ምስል፦ አፄ ምኒልክ በአሜሪካ (ከአትላንታ ኮንስቲቲውሽን ጋዜጣ፣ መጋቢት 4 ቀን 1896)***

## «ምኒልክ» - የንግድ ምልክት

እንደ ዛሬው «ታይም» መፅሔት ሹሱ በ19ኛው ክፍለዘመን «ቫኒቲ ፌይር» ታዋቂ ነበር። በ1897 ቫኒቲ ፌይር የፊት ገፁ ላይ የአፄ ምኒልክን ምስል ይዞ በመውጣት ንጉሡን ለመላው ዓለም አስተዋወቃቸው። ከቻርልስ ዳርዊን፣ የሩሲያው አሌክሳንደር፣ ናፖሊዮን ላልሳዊ እኩል የአፄ ምኒልክ ፎቶ ግራፍ ተከትሎ አፄ ምኒልክ እና እቴጌ ጣይቱ ከዓለም ታዋቂ ግለሰቦች ተርታ ተሰለፉ።

የምኒልክ እና ጣይቱ ዝና በሰፊው መናኘቱን ተከትሎ የተለያዩ አዳዲስ ክስተቶች ታይተዋል። በርካታ አውሮፓውያንም አዳዲስ ለተወለዱ ሕፃናት ልጆቻቸው «ምኒልክ» የሚል ስም ሰጡዋቸው። ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአድናቆት ደብዳቤዎች የምኒልክን ቤተ-መንግሥት አጣበውት ነበር። አንዳንድ ደብዳቤዎች ንጉሡን የገንዘብ ውለታ የሚጠይቁም ነበሩ። አንዲት አድናቂያቸው በጻፈችላቸው ደብዳቤ አፄ ምኒልክ ለጅምር መኖሪያ ቤታ ማስጨረሻ የሚሆን 200 ፍራንክ እንዲልኩላት ጠይቃቸው ነበር።



*ምስል፦ አፄ ምኒልክ በአውሮፓ (ቫኒቲ ፌይር ጋዜጣ፣ ሐምሌ 29 ቀን 1897)*





የምኒልክ እና የጣይቱ የዓለም አቀፍ ዝና በጨመረ መጠን በርካታ ጥያቄዎች ከየአቅጣጫው መነሳት ጀምረው ነበር። ኢትዮጵያ የመጀመሪያ የአፍሪካ ልዕለ-ሐያል እየሆነች ነው? ፖለቲካዊ ድሉ የኢትዮጵያ የንግድ ትንሳኤ መነሻ ይሆን? የይሁዳ አንበሳ ነገድ የሹኑት አፄ ምኒልክ የመላው ጥቁር ሕዝብ መሪ መሆን ይችላሉ?

ከአድዋ ድል በኋላ መላው ዓለም የኢትዮጵያን የንግድ እና ዲፕሎማሲያዊ ወዳጅነት ለማግኘት መንቀሳቀስ ጀምረዋል።




Tayitu trading card. Private collection.

*ምስል፦ የጣይቱ የመገበያያ ካርድ (ከግል ስብስብ)*

ክበቶቶች ታይተዋል። በርካታ አውሮፓውያንም አዳዲስ ለተወለዱ ሕፃናት ልዩቻቸው ‹‹ምኒልክ›› የሚል ስም ሰጡዋቸው። ክፍተኛ ቁጥር ያለው የአድናቆት ደብዳቤዎች የምኒልክን ቤተ-መንግሥት አጣበውት ነበር። አንዳንድ ደብዳቤዎች ንጉሡን የገንዘብ ውለታ የሚጠይቁም ነበሩ። አንዲት አድናቂያቸው በጻፈችላቸው ደብዳቤ አፄ ምኒልክ ለጅምር መኖሪያ ቤቷ ማስጨረሻ የሚሆን 200 ፍራንክ እንዲልኩላት ጠይቃቸው ነበር።



*ምስል፦ አፄ ምኒልክ በአውሮፓ (ቫኒቲ ፌይር ጋዜጣ፣ ሐምሌ 29 ቀን 1897)*






Tsaru trading card. Private collection.

*ምስል፦ የጣይቱ የመገበያያ ካርድ (ከግል ስብስብ)*



Ethiopia, Africa's Switzerland. Private collection.

*ምስል፦ ኢትዮጵያ - የአፍሪካ ሰዊዘርላንድ (ከግል ስብስብ)*

በርካታ ሐያላን አገራት የኢትዮጵያን ወዳጅነት ለማግኘት መንቀሳቀስ የጀመሩት ከአድዋ ድል በኋላ የምኒልክ እና ጣይቱን ዝነኝነት ተከትሎ ነበር። «. . . ምኒልክ በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በመላው አውሮፓ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ስብዕና ነው። የንጉሡ ወዳጅነት ለአውሮፓውያኑ ልዩ ጥቅም ይኖረዋል።»

የሩስያ ልዑካን ወደ አዲስ አበባ የመጡት ምኒልክ እና ጣይቱ ከአድዋ ከተመለሱ ከጥቂት ወራት በኋላ በ1896 ነበር። ልዑካኑ በሩስያ እና ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን መካከል ግንኙነት ለማጠናከር ያለመ ነበር። ከልዑካኑ ጋር የሕክምና ቡድን አብሮ የመጣ ሲሆን በአድዋ ጦርነት ለቆሰሉ ወታደሮች የሕክምና እርዳታ አድርጓል። የሩሲያ ቀይ መስቀል ማህበርም በርካታ የሕክምና ቁሳቁስ እና መድኃኒት አቅርቦ ነበር።






የፈረንሳይ መንግሥት የጅቡቲ አስተዳዳሪ የነበረውን ሊዮንስ ላጋርዴ በጥር 1897 ወደ አዲስ አበባ ላከ። የፈረንሳይ ጋዜጦች ከአድዋ በኋላ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ልዕለ-ኃያል እየሆነች መምጣቷን ገልፀዋል።

የስፔን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ደግሞ የንግድ እና የኃይማኖት ግንኙነት ለመፍጠር ነበር ከምኒልክ ጋር የተቀራረቡት። የስፔን አቀራረብ በተወሰነ መልኩ ከቫቲካን ጋር ይመሳሰል ነበር።

እንግሊዝ በ1897 ፀደይ ወቅት ሰር ሬኔል ሮድን ወደ ኢትዮጵያ ላከች። የልዑካን ቡድኑ በኢትዮጵያ ከፍተኛ አቀባበል ተደርጎላቸዋል። ሰር ሮድ ለምኒልክ የነበረው አመለካከት የተቀየረው የተደረገለትን አቀባበል ከተመለከተ በኋላ ነበር።

አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነቷን የጀመረችው በንግድ ነበር። ግቡ 600 ሺህ ዶላር የሚደርስ የጥጥ ምርት ኢትዮጵያ ከአሜሪካ ገዝታለች። ማርሴ የነበረው መልዕክተኛዋ ሮበርት ፒት ስኪነርስ ወደ ኢትዮጵያ በመላክ ነበር አሜሪካ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቷን የጀመረችው። በአጠቃላይ 90 አባላት የነበሩት የአሜሪካ የልዑካን ቡድን ኢትዮጵያ ሲደርሱ ከፍተኛ አቀባበል ተደርጎላቸዋል።

በስኪነር የተመራው የልዑካን ቡድን አዲስ አበባ ሲደርስ በሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮች አቀባበል ተደረገለት። ልዑካኑ ወታደሮቹን አልፈው የተገኙት ከምኒልክ ከፍተኛ ሹማምንት ጋር ነበር። ሹማምንቱ የቆዳ ኮፍያ እና የአንበሳ ቆዳ የለበሱ ሲሆን ጋሻ እና ጦርን ጨምሮ በወቅቱ ዘመናዊ የነበሩ ጠመንጃዎችንም ታጥቀው ነበር። በወቅቱ አፄ ምኒልክ የአልማዝ ፊርጥ የነበረው ትልቅ ሱቲ ጀርአቸው ላይ አጥልቀው ነበር። ሙሉ ነጭ ልብስ የለበሱ ሲሆን ራሳቸው ላይ የጠቀለሉት ነጭ ሻሽ ከጀርባ ትከሻቸው ላይ የወረደ ሲሆን ጥቁር ኮፍያም ከላይ ደርበው ነበር።



Ethiopia, Africa's Switzerland. Private collection

**ምስል፡- ኢትዮጵያ - የአፍሪካ ሰዊዘርላንድ (ከግል ስብስብ)**

በውይይቱ ወቅት አፄ ምኒልክ አሜሪካ አፍሪካን ከአውሮፓውያኑ ጋር ለመቀራመት አለመሞከሯን አድንቀዋል። አብርሃም ሊንከን ባርነትን ለማጥፋት ያደረገውን አስተዋጽኦ በማድነቅ እሳቸውም የባሪያ ሥርዓትን ለማስቆም ቃል ገቡ። ‹‹በቅርቡ ባወጅኩት መሠረት ባሮች በባለቤቶቻቸው ይዞታ የሚቆዩ ቢሆንም ልጆቻቸው ግን ነጻ ይሆናሉ። ከዚያ በመጀመር ባርነትን ሙሉ በሙሉ እናስቆማለን›› በማለት ነበር አፄ ምኒልክ ለስኪነር የገለፁት።

ሩዝቬልት በጠየቁት መሠረት ኹለት የአፍሪካ የሜዳ አህያ እና ኹለት አናብስትን አፄ ምኒልክ በስጦታ መልክ ለአሜሪካ እቻቸው ላኩ። ሩዝቬልት ያለ ውሃ ረጅም ርቀት መጓዝ የሚችሉ የሜዳ አህዮችን ከበቅሎ ጋር ለማዳቀል በማሰብ ነበር ጥያቄውን ያቀረቡት። ከኹለቱ አናብስት አንዱ ብቻ ዋሽንግተን የሚገኘው ናሽናል የእንስሳት ማቆያ በሕይወት መድረስ ቢችልም የሜዳ አህዮቹ ግን መንገድ ላይ ሞቱ።

ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ ለጋዜጦች በሰጠው ቃለ ምልልስ ስኪነር ‹‹አቢሲኒያ የአፍሪካዋ ጃፓን ናት›› በማለት ነበር የገለጸው። ኢትዮጵያ የአሜሪካ ጠንካራ የንግድ አጋር እንደሆነ መግለፁን ተከትሎ የቆዳ እና ሴጣ ነጋዴ የነበረው ኤሚል ግሪበስቶክ በኒውዮርክ 529 ጎዳና ላይ ‹‹የአሜሪካ-ኢትዮጵያ ንግድ ኩባንያ›› ን በይፋ ከፈተ። ከቀናት በኋላም ከስኪነር ላይ ደብዳቤ ተቀብሎ ወደ ኢትዮጵያ ተጓዘ።

ግሪበስቹክ ሐረር ሲደርስ ራስ መኮንን አቀባበል አደረጉለት። የሐረርን ውበት እና የንግድ እንቅስቃሴ እንዲሁም የራስ መኮንን መልካም አቀባበል በከፍተኛ አድናቆት ነበር የገለጸው። አዲስ አበባ ሲደርስ አፄ ምኒልክ አቀባበል ያደረጉለት ሲሆን፣ ዘመናዊ ዊንቸስተር ጠመንጃ በስጦታ አቅርቦላቸዋል።

ወደ ኒውዮርክ ከተመለሰ በኋላ በጉዞው ያገኘውን ልምድ በመጠቀም የመንግሥት ኃላፊነትን አገኘ። በኢትዮጵያ የአሜሪካ መልዕክተኛ ለመሆን ጥያቄ ቢያቀርብም የአገሩ መንግሥት ጥያቄውን አልተቀበለውም።





ከመንግስታዊ ልውጣኑ ባልተናነሰ በርካታ ግለሰቦች ወደ አዲስ አበባ መምጣት ጀምረው ነበር። አንድ ግሪካዊ ወጣት ገጣሚ በአዲስ አበባ ዝነኛ የመሆን ሕልም ይዞ ቢመጣም ከሥነ-ጽሑፍ ይልቅ የተሻለ ወታደራዊ ብቃቱ በምኒልክ ተቀባይነት አስገኝቶለታል።

ሐብተ ጊዮርጊስ በማለት ስሙን ቀይሮ ከሠራዊቱ ጋር ተቀላቀለ። ለኢትዮጵያውያን ብቻ የሚሰጠውን የፊትአውራሪ ማዕረግ በማግኘት የመጀመሪያው የውጪ ዜጋ መኮንን ለመሆን ቻለ።

ቲግራኔ የሚባል አርመናዊ ወጣትም በምኒልክ ቤተ-መንግሥት በአብሳይነት እና በአትክልተኝነት ያገለግል ነበር። ከቆይታ በኋላ የንጉሡ ብር እና ወርቅ ሰሪ በመሆን ዳጎስ ያለ ክፍያ ማግኘት ቻለ። የግሉን የወርቅ ቤት በመክፈትም ጌጣጌጥ ከመሸጥ ጎን ለጎን የአራጣ ብድር አገልግሎትም ይሰጥ ነበር።

አፄ ምኒልክ ነጋዴዎችን በመደገፍ ይታወቁ ነበር። የውጪ አገር ነጋዴዎች የሐብት ምንጭ ከመሆናቸውም በላይ ለሕዝባቸው ንግድ እንደሚያስተምሩላቸው ተስፋ በማድረግ ነበር ንጉሡ ድጋፍ የሚያደርጉት። የድጋፍ ተጠቃሚ የነበረው ፈረንሳዊው አርማንድ ሳቮሪ በአዲስ አበባ የጥይት ፋብሪካ በመክፈት ሙያውን ለኢትዮጵያውያን ማስተላለፍ ችሏል። የጥይት ምርቱን በዝሆን ጥርስ እና ወርቅ በመለውጥም በአጭር ጊዜ ሃብታም መሆን ችሎ ነበር።

የሳቮሪን ስኬት የሰሙ በርካታ አውሮፓውያን ወደ አዲስ አበባ በብዛት መምጣት ጀመሩ። የአውሮፓውያኑ የንግድ እንቅስቃሴ ፍትሐዊ አለመኾኑን በመመልከት አፄ ምኒልክ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ጀመሩ። ዋና የንግድ እንቅስቃሴዎች በአውሮፓውያኑ እጅ መግባት የአገሪቱን የንግድ ሥርዓት በውጪ ዜጎች ቁጥጥር ሥር አደረገው። በአድዋ ጦርነት መነሻ የነበረው የኢትዮጵያውያን በውጪ ሃይሎች ቁጥጥር ሥር ያለመዋል እምቢተኝነት ለነጋዴ አውሮፓውያን

አስፈሪ ሁኔታ መፍጠር ጀመረ። ሕዝቡም ሆነ ንጉሡ ነጋዴዎቹን በመልካም ዐይን መመልከት አቆሙ።

## ኢትዮጵያ በአፍሪካ ዲያስፖራዎች

ከሰሃራ በታች ያሉ አፍሪካውያን ስለ አድዋ ድል ወቅታዊ እና ሚዛናዊ መረጃ አልነበራቸውም። የናይጀሪያው ሌጎስ ስታንዳርድ፣ የጋናው ጎልድ ኮስት ክሮኒክል፣ እና የሴራሊዮን ታይምስ ጋዜጦች በአውሮፓውያን እጅ የሚታተሙ በመሆናቸው የአድዋን ድል ማብሰር አልፈለጉም። በመሸኑም የኢትዮጵያ የድል ዜና ጥቁር አፍሪካውያን ጆሮ ለመድረስ በርካታ መሰናክሎችን ማለፍ ነበረበት።

ከአፍሪካ ውጪ የነበሩ ጥቁር የዲያስፖራ ማህበረሰብ አባላት ኢትዮጵያን ከአድዋ በፊት ጀምሮ ያውቋታል። ከጥንታዊ ሥልጣኔዋ በተጨማሪ የክርስቲያን አገር መሆኗ በክርስቲያን ስደተኞች ዘንድ የበለጠ ታዋቂ አድርጓት ነበር።

የአፍሪካ አሜሪካውያን አብያተ ክርስቲያናት ከስማቸው በፊት ‹‹ኢትዮጵያ›› እና ‹‹የአቢሲኒያ›› የሚሉ ቅፅሎችን ይጠቀሙ ነበር። በ1808 የተቋቋመው የሃርለሙ ‹‹የአቢሲኒያ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን እና በ1892 የተቋቋመው የደ/አፍሪካው ‹‹የኢትዮጵያ ፕሪቶሪያ ቤተክርስቲያን›› ከአድዋ ድል ቀድሞ የነበረውን የኢትዮጵያ ዕውቅና ያሳያሉ። የድል ዜናው ለኢትዮጵያ ተጨማሪ ዝና አስገኝላት እንጂ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዲያስፖራው ጋር አላስተዋወቃትም።

## ሃይቲ እና ኢትዮጵያ

ከአድዋ ድል ማግስት ኢትዮጵያ እና ሃይቲን በማገናኘት ሰፊ የማስተዋወቅ ሥራ የሠራው የካሪቢያን ተወላጅ የሆነው ቤኒቶ ሲልቬይን ነበር። ስለ ጥቁሮች መብት በፈረንሳዩ ላ ፍራተርኒቲ ጋዜጣ ላይ በመፃፍ የሚታወቀው ሲልቬይን በጥር 1897 ነበር ወደ ኢትዮጵያ የመጣው።





ሰልቬይን የኢትዮጵያ እና ሃይቲን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በመፍጠር ቅኝ ግዛትን እና የባሪያ ሥርዓትን በመታገል አስቦ ነበር ወደ ኢትዮጵያ የመጣው። ለአራት ጊዜያት በመመላለስም አፄ ምኒልክን ለማላመን ጥሯል። የንጉሡን ይሁንታ ማግኘት ባይችልም ዓላማውን በማንገብ በ1900 ዓ.ም በመጀመሪያው የፓን አፍሪካ ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያን እና ሃይቲን ወክሎ ተሳትፏል።

የሃይቲን 100ኛ ዓመት የነጻነት በዓል በአዲስ አበባ ለማክበር በ1904 ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ከአሜሪካው ልዑክ ሮበርት ስኪነር ጋር በአጋማሚ አዲስ አበባ ተገናኝተው ነበር። በወቅቱ አፄ ምኒልክ የባሪያ ሕዝቦችን ኑሮ በመላው ዓለም ለማሻሻል እንዲያግዙት ሲጠይቃቸው የሰጡት ምላሽ ያልጠበቀው ነበር።

> *ሃሳብህ በጣም ጥሩ ነው። ባሮች ከሰው አኩል መታየት አለባቸው። ሀሳብህን በመደገፍ መልካም ፍቃዴን ለመግለፃለሁ። ነገር ግን እንደምታውቀው ለኔ ባሪያ አይደለሁም። ካውካሲያን ነኝ።*

የቆዳ ቀለም እና ዝርያ ክካሪቢያን የባሪያ ቤተሰብ ለተወለደው ሲልቬይን እና ለዘመናት ነፃ የነበረች አገርን በመምራት ላይ ለነበሩት አፄ ምኒልክ የተለያየ ትርጉም ነበራቸው። የምኒልክን ምላሽ በርካቶች በተለያዩ መንገድ በመመንዘር ኢትዮጵያን ከጥቁር አፍሪካውያን የተሰዩ ዘሮች መሆናቸውን ፅፈዋል። አንዳንዶች የፎኔሽያ ሕዝቦችን ባህል ከኢትዮጵያ ጋር በመቀያየር ሲናገሩ ተደምጠዋል።

ሲልቬን የሃይቲን መቶኛ ዓመት የነጻነት በዓል በክቡር ዘበኛ ሰልፍ ታጅቦ በአዲስ አበባ አከበረ። በዕለቱ በርካታ ጥይት በመተኮስ ‹‹ረጅም እድሜ ለሃይቲ እና ለኢትዮጵያ›› የሚል መፈክር በወታደሩ ሲነገር ዋለ። ምሽት ላይ ሲልቬይን ምኒልክን

ለማግኘት ቢሞክርም ንጉሡ አዲስ ዓለም ወደሚገኘው ቤተ-መንግሥት መሄዳቸው ተነገረው። ሁኔታውም በወቅቱ ሲልቪን አስከፍቶት ነበር።

በዚያው ዓመት ወደ አገሩ ሃይቲ የተመለሰው ሲልቬይን ለሃይቲ ፕሬዚዳንት ናርድ አሌክሲስ የአፄ ምኒልክን ሰላምታ አቅርቧል። ከምኒልክ የተላከላቸውን ሜዳሊያ እና የማዕረግ ስም ለፕሬዚዳንቱ አቅርቧል።

ሌላው የካሪቢያን ተወላጅ ጆሴፍ ቪታሊዮን በ1903 ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ነበር። የሕክምና ባለሙያው ቪታሊዮን የአፄ ምኒልክ የግል ዶክተር በመሆን አብሯቸው እንዲኖር ራስ መኮንን ቢጠይቁትም ፅድሱን ሳይቀበል ቀርቷል። ዘኹለተኛው የፓን አፍሪካ ኮንግረስ ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያን በመወከል ሲሳተፍ በወቅቱ የኮንግረሱ መሪ ከነበረው ደብሲው ኢ.ቢ.ዱ ቦይስ ጋር ተገናኝቶ ስለ ኢትዮጵያ ተነጋግረው ነበር።

ሲልቪይንን እና ቪታሊዮን ተከትለው በርካታ የራስ ተፈሪያን ተከታዮች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት መኖር ጀመሩ። እንደ ቦብ ማርሊ ኹሉ ለበርካታ የዕምነቱ ተከታዮች ኢትዮጵያ አዲሲቷ የተስፋ ምድር ‹‹ጽዮን›› ነች። አፄ ምኒልክም የዓለም በመላው ዓለም ላሉ ጥቁሮች ሕዝቦች ተስፋ እንደሸኑ ይታመን ነበር።





# ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ

## ተገኳር እና መታሰቢያ

ሰኔ 5 ቀን 1896 ጀ/ል አሬስቲ ባራቴሪ ከጠዋቱ 1 ሰዓት ላይ አስመራ በሚገኘው የጦር ፍርድ ቤት በር ላይ ደረሰ። በወቅቱ በቦታው የነበረ ፎቶ እንሺ የጀነራሉን ምስል አስቀርቶታል። 1፡15 ሲሆን አምስት የጣሊያን ዳሞች ቦታውን በመያዝ የፍርድ ሥነ-ሥርዓቱን መጀመሩን አሳወቁ።

ከአስመራ በብዙ ኪሎ ሜትሮች ርቀው ደግሞ 250 ጣሊያናውያን የሚኙ ወገኖቻቸውን አስክሬን በአድዋ በመለየት ላይ ነበሩ። ከጣርነቱ ቡኋላ 14 መኮንኖች እና 240 አባላት ያሉት የጣሊያን ልዑካን ቡድን የአድዋን የጦር ሜዳ እንዲመለከት እና የቀብር ሥነ-ሥርዓት እንዲፈፅም በትግራዩ ገዢ ራስ መንገሻ ተፈቅዶለት ሥራውን ጀምሯል።

በጀ/ል አሪሞንዲ ታናሽ ወንድም ኮ/ል ፍራንሲስኮ አሪሞንዲ የተመራው ቡድን ግንቦት 1896 ምፅዋ ደረሰ። ዠስት የካቶሊክ መነኮሳትን እና ገብረ እግዚአብሔር የተባለ የባንዳ ወታደር በመያዝ ነበር ቡድኑ ወደ አድዋ ያቀናው።

የኮ/ል አሪሞንዲ ተልዕኮ ለበርካታ ጣሊያናውያን ወላጆች የልጆቻቸውን ዕጌታ የማሳወቅ ዓለማ ነበረው። ሽንፈቱን ተከትሎ በጣሊያን የተነሣውን ተቃውሞ ለማርገብም መረጃ ማሟላት አስፈልጎ ነበር። በርካቶች ጀ/ል ባራቴሪን ለሽንፈቱ ተጠያቂ ቢያደርጉትም እውነታው ግን የተለየ ነበር።

ጀ/ል ባራቴሪ ለጣሊያኑ የጦር ሚኒስትር ስታኒስላኦ ምሴኒ መጋቢት 3 ቀን በጻፈው ደብዳቤ የወታደሮች ትዕዛዝ አለመቀበል እና ያጀ/ሎች የአመራር ጉድለት

የአድዋን ሽንፈት እንዳስከተለ በመዮቀስ ሰማስተባበል ሞክሮ ነበር። የባራቴሪ ደብዳቤ ባልታወቀ መንገድ ጋዜጦች እጅ በመግባቱ ዜናው ለሕዝብ ደረሰ። በመጨረሻም የጣሊያን ሕዝብ መቃወም ጀመረ።

የከ/ል አሪሞንዲ ቡድን ወደ አድዋ በመጓዝ ላይ ሳለ ከጦር ሚዳው ተርፈው በአዲግራት የተሸሸጉ 55 ወታደሮችን አግኝቷል። 27ቱ ወታደሮች በጽኑእ የቆሰሉ ነበሩ። ቀስለኞች ከምኒልክ ጋር ወደ ሸዋ መጓዝ ባለመቻላቸው በራስ መንገሻ ሥር እንዲቆዩ የተደረጉ ነበሩ።

ከ/ል አሪሞንዲ አንጢኞ ሲደርስ የአካባቢው አስተዳዳሪ የነበረው የ20 ዓመት ወጣት ልጅ አብርሃ አቀባበል አደረገለት። ልጅ አብርሃ የፒየድሞንት አካባቢ ታና ባለው የጠራ ጣሊያንኛ ሰላምታ ሲያቀርብለት ከ/ል አሪሞንዲ እጅግ ተንርሞ ነበር።



Lagg Abrahatin Teeny. From Edoardo Ximenes. *Sul Campo di Adua: memorie-ricordi 1896*. Milan: Fratelli Treves Editori, 1897.

***ምስል፡- ልጅ አብርሃ (ቴሬን፣ ጣሊያን) በትምህርት ዘመናቸው***





ከአፍታ ቆይታ በኋላ ልጅ አብርሃ በ13 ዓመት እድሜው ወደ ጣሊያን በማምራት ቱሪን በሚገኝ ትምህርት የተማሪ መሸኑን ለከ/ሉ ገለጸለት። በልጅ አብርሃ እገዛም ቀሪውን ተልዕኮ በተቀላጠፈ መልክ ለማከናወን ቻለ።

ጦርነቱ እንደተጠናቀቀ ኢትዮጵያውያን የሞቱ ወታደሮቻቸውን በአግባቡ ቀብረዋል። በርካታ የጣሊያን እና የባንዳ ሬሳዎች ግን ለአሞራ እና ለጅብ ተጥለው ነበር።

ቡድኑ ፀውደ ግንባሩ ላይ የወደቁ ከ1ሺህ በላይ አውሮፓዊ እና 39 ባንዳ አስከሬኖችን በመጀመሪያው ዕለት ቀበረ። በርካታ አስከሬኖች በአሞራና ጅብ በመበላታቸው ማንነታቸውን መለየት አስቸጋሪ ነበር። ሰኔ 3 ቀን ቡድኑ የ900 ጣሊያናውያን እና 144 ባንዳዎችን አስከሬን ቀበረ። ሰኔ 4 ቀን የጀ/ል ዳቦር ሚዳ አስከሬን ማርያም ሸዊት አቅራቢያ ተገኘ። ሰኔ 5 ቀን የጀ/ል አሪሞንዲ ብርጌድ የተዋጋበትን የራዕዮ ተራራ ግርጌ በማሰስ የበርካቶችን አስከሬን ቢያገኙም ከ/ል አሪሞንዲ የወንድሙን አስከሬን ሳያገኝ ቀረ። በቦታው የመታሰቢያ ሃውልት በማቆም የሐሊና ጸሎት አደረጉላቸው።



Memorial service on Raio. From Eduardo Ximenes. *Sul Campo di Adua: memorie-ricordi 1896*. Milan: Fratelli Treves Editori, 1897.

***ምስል፡- በራዕዮ ተራራ ለአባቢ የመታሰቢያ ሃውልት በማቆም የጸሎት ሥነሥርዓ ሲያደርግ***




Ugog Abraham Ilirta. From Eduardo Ximenes. *Sul Cuanfo di Adua. marzo-giugno 1896*. Milan: Fratelli Treves Editori, 1897.

**ምስል፦ ልጅ አብርሃ (ቱሪን፣ ጣሊያን) ዘትምህርት በነበረበት ወቅት**



**የሕሊና ጸሎት አደረጉላቸው።**



Memorial service on Raio. From Eduardo Ximenes. *Sul Cuanfo di Adua. marzo-giugno 1896*. Milan: Fratelli Treves Editori, 1897.

**ምስል፦ በራዕዮ ተራራ አካባቢ የመታሰቢያ ሃውልት በማቆም የጸሎት ሥነ-ሥርዓት ሲያደርግ**

የአሪሞንጻ ቡድን ተልዕኮውን ጨርሶ ወደ ጣሊያን በመሞሰስ ሪፖርት አቀረበ። በአጠቃላይ 3643 አስከሬኖችን ማስቀበሩን ገለጸ። 3246 አስከሬን የተገኘው በጦር ሜዳ ሲሆን 397 ደግሞ የጣሊያን ሠራዊት ሲሸሽ ከነበረበት መንገድ መኾኑን በመግለፅ አብዛኛው ሠራዊት በጀግንነት ጦር ሜዳ ላይ እንደተሰዋ ለጣሊያን ሕዝብ ገለጸ።

የቡድኑ ሪፖርት በመሸሽ ላይ ሳሉ የሞቱትን 166 የዳቦርሚዳ ወታደሮች እና ወደ የሃ በመሸሽ ላይ ሳሉ የተገደሉትን 1267 ወታደሮች በውጊያ ላይ እንደሞቱ አድርጎ ማቅረቡ ስሕተት ነበር። የሪፖርቱን ጉድለት በመመልከት የባራቴሪ የመከላከያ ሃሳብ ትክክል እንደነበር መገንዘብ ይቻላል። ባራቴሪ ለሸንፈቱ የወታደሩን መሸሽ አስተዋፅኦ ማድረጉን ገልፆ ነበር።

የአሪሞንጻን ሪፖርት የበለጠ አጠራጣሪ ያደረገው አጉስተስ ዋይልድ የጦር ሜዳውን በመጎብኘት ማንቺስተር ጋርዲያን ጋዜጣ ላይ እውነታውን ይፋ ማድረጉ ነበር። ዋይልድ ከጦርነቱ በፊት በ1884 አድዋን የጎበኘ ሲሆን ከጦርነቱ አራት ወራት በኋላ በቦታው በመገኘት የጦርነቱን ሁኔታ ተመልክቷል። በጽሑፉ «አድዋን ለሹለተኛ ጊዜ ስጎበኝ የተመለከትኩት ብዙ መካነ መቃብሮችን ነው።» በማለት ገልጿል።

በጉብኝቱ ወቅት በርካታ የጣሊያን አስከሬኖች በየቦታው ወዳድቀው መመልከቱን ገልጿል። በተለያዩ ቦታዎች የጅምላ መቃብር ቢመለከትም በየጥጋጥጉ ቆስለው የተሸሸጉ ወታደሮች በዚያው መሞታቸውን እና አስከሬኖቻውም ለወራት ሳይቀበር መቅረቱን ጠቅሷል። በየቦታው የወዳደቁ የሰው፣ የፈረስ እና የሚመል አስከሬኖች የአካባቢውን ውሃ በመበከላቸው ከጦርነቱ በኋላ የአካባው ሕዝብ እንደ ታይፎይድ እና ቲስቦ ባሉ ውኃ ወለድ በሽታዎች መጠቃቱን ገልጿል።





የዋይልድ ጽሁፍ በርካታ አስከሬኖች በጦር ሜዳው ዙሪያ እስከ አርባ ማይል ርቀት መመልከቱን ገልጿል። ብዙ የጣሊያን ወታደሮች እስከ አክሱም ድረስ ሲሸሹ በመንገድ ላይ መሞታቸውን አስታውሶ በአብቃላይ የሞቱት ወታደሮች ከአንድ ትንሽ አገር ጦር ሠራዊት እንደሚበልጥ መስክሯል።

የኢትዮጵያ ወታደሮች ከአድዋ ቅድስት ሥላሴ ቤተ-ክርስቲያን መቀበራቸውን የጠቀሰው የዋይልድ ሪፖርት በርካታ ኢትዮጵያውያን ጅምላ መቃብር በጦር ሜዳው አካባቢ መኖሩንም ጠቅሷል። ዋይልድ በጽሑፉ መጨረሻ የሚከተሰውን የመቃብር ጽሁፍ አስፍሯል።

> *«ፈፅሞ የማይረሱ ጥቂት ነገሮች አሉ። በሺህ የሚቆጠሩ የነጭ፣ የጥቁር እና የጠይም ወታደሮች አስከሬን በዚህች ውድ አገር ገጽ ላይ ነጠብጣብ በመሆን እንጸዘመራት ሳስብ ውስጤ ይላወሳል።»*

### የባራቴሪ ክሱ ቀን

የህል አሪሞንጻ ሪፖርት የባራቴሪን ክስ በተወሰነ መልኩ አጠናክሮታል። ከአሰመራው ጊዜያዊ የጦር ፍርድ ቤት ይልቅ የባራቴሪ ክስ በሮም ነበር መታየት ያለበት። በሮም ባሉ ከፍተኛ መኮንኖች መዳኘት የተሻለ ፍትሕ ሊያስገኝለት ይችል ነበር። የተሻለ የፕሬስ ሽፋን መኖሩ የፍርዱን ፍትሃዊነት ሊያስጠብቅ ቢችልም የክርስፒን መንግሥት ግን ለክፍተኛ ተቃውሞ ያጋልጠዋል። በመኾኑም የባራቴሪ ክስ በአስመራ በነበሩ የበታች መኮንኖች ዳኝነት እንዲታይ ተወሰነ።

ሰኔ 2 ቀን ከጠዋቱ 1:30 ሲሆን የ50 ዓመቱ ጎልማሳ ጀ/ል ዴል ማይኖ የፍርድ ቤቱን መክፈት ገለጸ። ጥቂት ታዳሚ በተገኘበት የጀ/ል ባራቴሪ ክስ መሰማት ጀመረ። ከጥቂት የጣሊያን ጋዜጦች ሌላ የአውሮፓ ታላላቅ ጋዜጦች የፍርድ ሥርዓቱን እንዳይከታተሉ ታግዶ ነበር።

ጀ/ል ኤሚሊዮ ባቺ በባራቴሪ ላይ የተመሠረቱትን ኹለት ክሶች በንባብ አሰሙ። የመጀመሪያው ክስ ባራቴሪ ጦሩን ወደ አድዋ በማንቀሳቀስ በግሉ ስሜት ተገፋፍቶ ምኒልክ ላይ ጦርነት አውጇል የሚል ነበር። ኹለተኛው ክስ ደግሞ ጦሩ እንዲያፈገፍግ በቂ አመራር ባለመስጠቱ በርካታ ወታደሮችን ማስገደሉን የሚመለከት ነበር።

የባራቴሪ ጠበቃ የነበሩት ካፒቴን ኤርኔስቶ ካንቶኒ ባራቴሪ የጣሊያን ሕግ አውፊኒ ም/ቤት አባል በመኾኑ ያለመከሰስ መብት እንዳለው በማስታወስ ክሱ እንዲቋረጥ ጠየቁ። ባራቴሪ ግን ክሱ እንዲቀጥል በመስማማቱ የጠበቃው ጥያቄ ውድቅ ሆኖ ክሱ ቀጠለ።

በመጀመሪያው ፍርድ ቤት ውሎ ጀ/ል ማርዮ ላምቤኒ ስለ አድዋ ዘመቻ ውሎ እና የባራቴሪ አመራር በዝርዝር ለፍርድ ቤቱ አቀረቡ። የጀነራሉ ምስክርነት ከሰዓት በኋላም ቀጥሎ ዕለቱ ተጠናቀቀ።

በቀጣይ ቀናት የባራቶሪ ምስክሮች ስለ ዘመቻው አመራር፣ እንቅስቃሴ፣ ጥቃት እና ማፈግፈግ ሲያስረዱ ከረሙ። የራስ ስብሃት እና ሓጎስ ቁፈሪን መከዳት ተከትሎ የተፈጠረውን የሽምቅ ውጊያ በማንሳት ባራቴሪ ተከራከረ። በሰሩ የነበሩትን ጀነራሎች ትዕዛዝ አለመቀበልንም ጠቀሰ። ይሁን እንጂ በውጊያ ላይ የሞተውን ጀ/ል አሪሞንዲ እና ጀ/ል አልበርቶኒን በግልጽ አልወቀሰም ነበር።

የባራቶሪ የመጀመሪያ ምስክር የነበሩት ኮ/ል ኮርቲሴሲ የባራቶሪ አመራር ትክክል እንደነበር እና ኖችግሩ መንስኤ ለነበረው የጀ/ል አልበርቶኒ በተመደበበት ቦታ አለመገኘት መኾኑን መሰከሩ። አልበርቶኒ ትዕዛዝ ቢያከብር ኖሮ የአድዋው ውርደት እንደማይከሰትም ጠቁመው ተናገሩ።





ኹለተኛው እና ሦስተኛው ምስክር የነበሩት ጂዮሽኒ ፒታሉጋ እና ጊያቺኖ ቫሌንዛኖ በዘኩላቸው የባራቴሪ የበታች ጀነራሎች የማፈግፈግ ውሳኔውን እንዳላከበሩ መሰከሩ። በተጨማሪም የምኒልክን ሠራዊት ከንምት በታች በመመልከታቸው ጀ/ሎቹ የባራቴሪን ትዕዛዝ አለመቀበላቸውን አስታውሱ።

የጀ/ል ዳቦርሚዳ እና አልበርቶኒን ችኩልነትን በተመለከተ የመከላከያ ምስክሮች ሰፍርድ ቤቱ አስረድተዋል። ኤሚሊዮ ቤላቪታ በስጠው ምስክርነት አለቃው የነበረው ዳቦርሚዳ ከጀ/ል ባራቴሪ የተሰጠውን ትዕዛዝ ለማንም የበታች መኮንን አለመናገሩን መሰከረ።

የመከላከያ አስተያየት እና ቅጣት ማቅለያ እንዲያቀርብ ለባራቴሪ በመግለፅ ፍርድ ቤቱ ለሰኔ 12 ቀጠሮ ያዘ።

የባራቴሪ ጠበቃ የነበሩት ካንቶኒ የነኛውን ክስ መከላከያ በዝርዝር ለፍርድ ቤቱ አቀረቡ። የባራቴሪን ወታደራዊ ሥነ-ሥርዓት እና ልምድ በመዘርዘር በምኒልክ ላይ ጦርነት አለማወጁን ከዚያ ይልቅ የተሻለ ቦታ ለመያዝ መንቀሳቀሱን ገለጸ።

ባራቴሪን ለመቀንቀሳቀስ ካጣደፉት ምክንያቶች መካከልም ከጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ የተላከው ቴሌግራም አንዱ እንደነበር ጠበቃው አስረዱ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባራቴሪ እንዲንቀሳቀስ ማጣደፋቸውንም በማስረጃ አቀረቡ። የመጀመሪያውን የክስ መከላከያ ሲያጠቃልሉ ‹‹ባራቴሪ በግል ስሜቱ ተገፋፍቶ ሳይሆን ክሱሩ የነበሩት ጀነራሎች የፈፀሙት ስሕተት ነበር ሰሽንፈት የጻረገው። ብለዋል።

ኹለተኛውን ክስ በተመለከተ ጠበቃው ያቀረቡት መከራከሪያ የጥፋቱ ተጋሪ የነበሩት ጀ/ል ዳቦርሚዳ በውጊያው ላይ በመሞታቸው እንዲሁም አልበርቶኒ በመግረኩ ሙሉ ጥፋቱን ባራቴሪ ላይ ማሳረፍ ተገቢ አለመኾኑን ገለፁ። የማፈግፈግ ውሳኔውን ተከትሎ ባራቴሪ ተገቢውን አመራር አለመስጠቱን በማመን በወቅት

ከተበተነው ጦር ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ያልተቻለው ከኢትዮጵያ ሠራዊት በተሰነዘረባቸው መጠነ-ሰፊ ጥቃት የተነሣ እንደነበር ጠበቃው አስረዱ። በመጨረሻም ጀ/ል ባራቴሪ ምሕረት እንዲያደርግለት አስተያየት ሰጡ።

እሁድ ሰኔ 12 ቀን በማለዳ ነበር የፍርድ ውሳኔው የተሰማው። ፍርድ ቤቱ በሰጠው ረጅም ገለፃ ባራቴሪ ለአድዋው ሽንፈት ተጠያቂ አለመሆኑን በመግለፅ በነፃ አሰናበተው። ለሽንፈቱ ተጠያቂ የሻኑትን የባራቴሪ የበታች ጀነራሎች ባላጋለጠ መልኩ ነበር የባራቴሪ ነፃ መሆን የተገለጸው። የፍርድ ውሳኔውን በተመለከተ መንግሥት ላይ ተቃውሞ አስከትሎ ነበር። በርካታ ጣሊያናውያን መንግስታቸው ጀ/ል ባራቶሪን ለመታደግ የተለየ የፍርድ ሥርዓት ማድረጉን እንዲሁም ፍርዱ ከሮም ውጪ መታየቱን ጠቁመዋል።





# ምዕራፍ ሐያ

## የመታደግ ዘመቻ

የአድዋ ሽርንፍ ዜና በችጋገ ለነበሩ ጣሊያናውያን አስቸጋሪ ሁኔታን ፈጥሯል። ‹‹ቺካጎ ትሪቢውን›› ጋዜጣ የጣሊያንን በአፍሪካ መሸነፍ በሰፊው የዘገበ ሲሆን ጣሊያን ለፀቀል እየተዘጋጀች እንደነበርም ጠቅሷል።

የጣሊያን ጋዜጦች የሕዝብ አስተያየት በመሰብሰብ ባወጡት ዘገባ ሽንፈቱ ለአገራቸው ውርደት እንደሆነ ገልፀዋል። ላ ኢታሊያ ጋዜጣ ‹‹ድርብ ድል›› በሚል ርዕስ ባሥነበበው ጽሑፉ ኢትዮጵያ የጣሊያንን ሠራዊት በአምባላጌ፣ መቀሌ እና አድዋ ደጋግማ ማሸነፏን ገልጿል። የመጋቢት 7 1896 ዕትም የፊት ገጽ ‹‹እጅግ አስፈሪው የአፍሪካ ጦር የጣሊያንን ሠራዊት በላው›› የሚል ትልቅ ርዕስ ይዞ ወጥቷል።

በቺካጎ የሚኖሩ የጣሊያን ተወላጆች መጋቢት 8 ቀን ባደረጉት ስብሰባ ለሚችው ቤተሰቦች እርዳታ የሚውል ገንዘብ አሰባስበው ለጣሊያን ቀይ መስቀል ልከዋል። ተሰብሳቢዎቹ አገራቸው ለበቀል መዝመት እንዳለባት ጥሪ ያቀረቡ ሲሆን 40 ጣሊያናውያንም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ቃል ገቡ። ድርጊታቸው በአሜሪካ የተዋረደ ስማቸውን ለማደስ ያለመ ነበር።

በጣሊያን ቀድሞ ይደገፍ የነበረው የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ ከአድዋ በኋላ ብርቱ ተቃውሞ ገጥሞታል። በሚላን የሚታተመው ኮሪየሬ ዲላ ሴራ ጋዜጣ የተቃውሞው ዋና አቀጣጣይ ነበር።

የጣሊያን ሕዝብ ለድጋፍ እና ለተቃውሞ እጅግ ፈጣን ነው። ጦራቸው በ1895 ራስ መንገሻን ሲያሸንፍ ከፍተኛ የድጋፍ ሰልፍ አድርገው ነበር። በአምባላጌ፣ መቀሌ እና አድዋ አውደ-ግምባሮች ሽንፈት ያጋጠመው ጦራቸውን ለማውገዝም ጊዜ አልፈጁም። የሮም ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የተቃውሞው ዋና መሪ የነበሩ ሲሆን ‹‹ሺሻ ምኒልክ›› የሚል መፈክር ይዘው ነበር ለሰልፍ የወጡት።

ተቃዋሚዎቹ በኮሎና አደባባይ ዙሪያ በመሰብሰብ የጀመሩት ሰልፍ ኮፐቋት ደቂቃዎች በኋላ አቅጣጫውን ቀየረ። በሽንፈቱ የተበሳጨ ወጣት ጣሊያናውያን የጠ/ሚኒስቴር ክሪስፒ መኖሪያ ቤትን ጨምሮ የአገሪቱን ፓርላማ እና የመንግሥት ደጋፊ እንደሆነ የሚታወቀውን የላ ኢታሊያ ጋዜጣ ሕንፃ በድንጋይ ደበደቡ።

ተቃውሞው በሺኒስም ተቀጣጥሎ ነበር። በኢንቶኒ ሺጎ ቀስቃሽነት በተደረገው ሰልፍ የጣሊያን መንግሥት ኤርትራን ለቅቆ እንዲወጣ ጠይቋል። በሰልፉ ላይ ሺጎ ከተናገራቸው ንግግሮች መካከል ‹‹አፍሪካን ለአፍሪካውያን እንተውላቸው። እኛም በውስጥ ችግራችን ላይ እናተኩር›› የሚለው አንዱ ነበር።

## የጣሊያን ምርኮኞች

በመላው ዓለም የሚኖሩ ትውልደ ጣሊያናውያን ልጆቻቸውን በአድዋ ዘመቻ በሞት ለተነጠቁ ቤተሰቦች እርዳታ የሚውል ገንዘብ አሰባስበዋል። ከብራዚል 1104 ሊሬ፣ ኡሯጋይ 50000 ሊሬ፣ ፔሩ 43000 ሊሬ፣ ኒውዮርክ 55000 ሊሬ እንዲሁም በኒውጀርሲ ከነበሩ ዜጎቹ የ2405 ሊሬ የገንዘብ መዋጮ ተደርጓል።

ወደ ኢትዮጵያ የዘመቱ ወታደሮች መጨረሻ አለመታወቁ በጣሊያን የነበሩ ወላጆቻቸውን አስጨንቆ ከርሟል። የሞቱ እና የተማረኩ ወታደሮች ብዛት እና ማንነት ባለመታወቁ የወላጆች ተቃውሞ እያደር ጨመረ። ምርኮኞች ከአድዋ በመነሳት አዲስ አበባ ነበሩ የአውሮፓ ዜጎችን እንደ ዜና መንም በመጠቀምም የጣሊያን ጋዜጦች የምርኮኞችን ሁኔታ መዘገብ የጀመሩት ከ3 ወራት በኋላ ነበር።





ልጆቻቸው በጦርነቱ የተገደሉባቸው ቤተሰቦች በጎዘን ሲቀመጡ የተማረኩባቸው ደግሞ ሰል ልጆቻቸው ቀጣይ ዕጣ ፈንታ ተጨነቁ። በተመሳሳይ ወቅት የምኒልክ ቴምብር የተለጠፈባቸው ደብዳቤዎች ጣሊያን መድረስ ጀምረው ነበር።

ከጦርነቶቹ በኋላ የሚደረጉ የካሳ ክፍያ እና የምርኮኛ ልውውጥ ተግባራት በኢትዮጵያ አይታወቁም ነበር። በአውሮፓ ተሸናፊ አገራት ለባለድል አገራት ካሳ እንዲከፍሉ ይጠይቃሉ። ከአድዋ በፊት በ1870 በተደረገው የኦስትሪያ እናነ ፕሪሲያ (ጀርመን) ጦርነት ባለድል የነበረችው ጀርመን የ5 ሚሊዮን ፍራንክ ካሳ እንዲከፈላት ጠይቃ ተሳክቶላታል። አፄ ምኒልክም የካሳ ገዳይን በተመለከተ ከአማካሪያቸው አልፍሬድ ኢልግ ምክር እንደደረሳቸው ይገመታል።

አፄ ምኒልክ እና ንግሥት ጣይቱ ከጣሊያን ጋር የሚደረገው የምርኮኛ ድርድር ጠቀም ያለ ጉርሻ እንደሚያስገኝላቸው ተረድተውታል። በመሆኑም ጣሊያንን የጦር ካሳ ክፍያ ለመጠየቅ ተዘጋጁ። ከካሳው በተጨማሪም ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ዕውቅና እንድትሰጥ የሚያስገድድ ቅድመ ሁኔታም አቀረመጡ።

## የቫቲካን ሽምግልና

ጣሊያን እንደ አዲስ በተዋሃደችባቸው የ1850ዎቹ እና 60ዎቹ ዓመታት ቀድሞ በቫቲካን የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሥር የነበሩ በርካታ ግዛቶች ወደ ጣሊያን ተጠቃለለዋል። በ1870 ጀምሮም የጳጳሱ መቀመጫ የነበረችው ሮም በወታደሮች ቁጥጥር ሥር ውላ ጳጳሱም በቫቲካን ለመቀመጥ ተገደዋል። ሁኔታው በጣሊያን እና ቫቲካን መካከል መቃቃር የተፈጠረው ከዚያ ጀምሮ ነበር።

የአድዋውን ሽንፈት ተከትሎ በኢትዮጵያ የተማረኩ ጣሊያናውያንን ዕድል በተመለከተ ቫቲካን በድርድሩ እጇን እንድታስገባ በጣሊያን መንግሥት ተጠየቀች። በመሆኑም ከኢትዮጵያ ኮፕቲክ እርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጋር ያላቸውን ወዳጅነት በመጠቀም እስረኞችን ለማስለቀቅ ተንቀሳቀሱ።

በውጤቱ ሞንሊኞች ማካሪዮስ የተመራው የሽማግሌ ቫቲካውያንን ቡድን ነሐሴ 14 ቀን 1896 አዲስ አበባ ሲገባ አፄ ምኒልክ በክብር ተቀበሉት። ለቡድኑ ጣሊያናውያን የምግብ አብሳዮችን በመመደብ አፄ ምኒልክ ለእንግዳ ያላቸውን ክብር አሳይተዋል።


LA TRIBUNA SUPPLEMENTO
illustrato della Domenica

MONSIGNOR MACARIO PRESENTA AL PAPA LA DELEGAZIONE DI ABISSINIA

*ምስል፦ ሞንሊኞር ማካሪዮስ ከኢትዮጵያ ተመልሶ ከጳጳሱ ጋር ሲገናኝ (ሐምሌ 22 ቀን 1896)*





## ራሱን የሸመው ጂፕሎማት ኒኮላይ ሊዮንቲየቭ

ኒኮላይ ስቴፋኖቪች ሊዮንቲየቭ በዮክሬን የተወለደ ሩሲያዊ ነው። በወታደርነት ተቀጥሮ ሳለ የመጓዝ ልምድ ያካበተ ሲሆን በከፍተኛ ብድር ውስጥ በመዘፈቁ ከሩሲያ በመውጣት ወደ ሌላ አገር ተጉዞ ሥራ ለመሥራት ይወስናል። በመሸኙም ዕዳውን ለመሸሽ ከአገሩ በመውጣት በ1895 ወርኃ ጥር ላይ ወደ አዲስ አበባ ተጓዘ።

በአዲስ አበባ ቆይታው ከአፄ ምኒልክ ጋር በመገናኘት የሩሲያ ንጉሥ መልዕክተኛ በመሾኑን ገለጸላቸው። በቆይታውም ከጥር 1895 ጀምሮ የሩሲያ አምባሳደር በመሆን ራሱን ሾመ። በመቀጠል አፄ ምኒልክን አግባብቶ የኢትዮጵያ ጂፕሎማቶችን በመያዝ ወደ ሞስኮ ተጓዘ።

ሀዳር 1894 ላረፉት ንጉሥ አሌክሳንደር ሦስተኛ የመታሰቢያ ስጦታ እንዲሰጥ አፄ ምኒልክ የተለያዩ የኢትዮጵያ ውድ ጌጣጌጦችን ሞስኮ ንጉሥ ልከዋል። ሐምሌ 17 ቀን 1895 ልዑካኑን በፒየትሮቭ ቤተ-መንግሥት አቀባበል ያደረጉላቸው ንጉሥ ኒኮላስ ነበሩ።


The Leontiev mission to Russia. From *L'Illustrazione italiana*, 28 July 1895.

*ምስል፦ በሊዮንቲቭ የተመራው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን በሩሲያ (ሐምሌ 22 ቀን 1895)*




MONSIGNORE MACARIO PRESENTA AL PAPA LA LETTERA DI MENELIK

*ምስል፡- ሞንሲኞር ማካሪዮስ ከኢትዮጵያ ተመልሶ ከጳጳሱ ጋር ሲገናኝ (ህዳር 22 ቀን 1896)*



መልዕክተኛ በመሾኑን ገለጸላቸው። በቀይታውም ከጥር 1895 ጀምሮ የሩሲያ አምባሳደር በመሆን ራሱን ሾመ። በመቀጠል አፄ ምኒልክን አግባብቶ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶችን በመያዝ ወደ ሞስኮ ተጓዘ።

ህዳር 1894 ላረፉት ንጉሥ አሌክሳንደር ሦስተኛ የመታሰቢያ ስጦታ እንዲሆን አፄ ምኒልክ የተለያዩ የኢትዮጵያ ውድ ጌጣጌጦችን ሞስኮ ንጉሥ ልከዋል። ሐምሌ 17 ቀን 1895 ልዑካኑን በፒየትሮቭ ቤተ-መንግሥት አቀባበል ያደረጉላቸው ንጉሥ ኒኮላስ ነበሩ።



The Leontiev mission to Russia. From *L'Illustrazione italiana*, 22 July 1895

*ምስል፡- በሊዮንቴቭ የተመራው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን በሩሲያ (ሐምሌ 22 ቀን 1895)*

ልዑካኑ ፒተርስበርግ ሲደርሱ ከፍተኛ አቀባበል ተደርጎላቸው በንጉሡ ትዕዛዝ መሠረት በአገሪቱ ታላቅ በሆነው ሆቴል ዮሮፕ እንዲያርፉ ተደርገዋል። በአጋጣሚ መጠቀም የቻለው ሊዮንቲቭ በንጉሡ ዘንድ ተመራጭ ሆነ። በመሸኑም ንጉሡ በኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ አድርገው ሾሙት። ልዑካኑ ነሐሴ 9 ቀን 1895 የመልስ ጉዞአቸውን ሲጀምሩ 135 የቤርዳን ጠመንጃዎች በስጦታ ተበርክቶላቸዋል።

ራሱን ለሾመው ሊዮንቲቭ ምስጋና ይግባው እና በአዲስ አበባ ከነበሩ በርካታ አውሮፓውያን መካከል የሩሲያ ተወካይም ዕድል አገኘ።

አፄ ምኒልክ ወደ አድዋ ለመዝመት በሚዘጋጁበት ወቅት ሊዮንቲቭ ወደ አውሮፓ አቀና። በአውሮፓ ቆይታውም ኢትዮጵያን እና ጣሊያንን ለመሸምገል ሞክሯል። ኮሚሊያን የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አልቤርቶ ዲ ብላንክ ጋር ያደረገው ውይይት ውጤት ስላላስገኘለት ድርድሩ ሳይሳካ ቀረ።

ሊዮንቲቭ ወደ አዲስ አበባ የመለሰው ኮሮኒቱ በጊላ ነበር። በወቅቱ አፄ ምኒልክ ለጣሊያኗ ንግሥት ማርጋሪታ የልደት ስጦታ እንደሸኙ 50 ምርኮኞችን በነፃ ለቀቁ በመቀጠልም በሊዮንቲቭ አማላጅነት ለሩሲያው ንጉሥ በአስ ሹመት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በወርኃ ሐምሌ ሌላ 50 ምርኮኞችን ለቀቁ።





## የኔራዚኒ ጥያቄ እና የምኒልክ ርኅራኄ

አፄ ምኒልክ በርካታ እሥረኞችን በመልቀቅ ርኅራኄአቸውን አሳይተዋል። ያም ሆኖ ግን የድርድር ጉልበት የሚሆኗቸውን በመቶዎች የሚቆጠሩ እሥረኞች ለማቆየት ወሥነዋል። ኮቪቲካን የተሳከው ማካሪዮስ ጥቅምት 1 ቀን 1888 ወደ አገሩ ሲመለስ ኹሰት የታመሙ እሥረኞችን ብቻ እንዲወሰድ ነበር አፄ ምኒልክ የፈቀዱለት።

አፄ ምኒልክ ለቮቲካኑ ጳጳስ ሊዮ ፲፫ኛ በጻፉት ደብዳቤ እሥረኞችን ያልለቀቁበትን ምክንያት በትሕትና አስረድተዋል።

> "ከአንድ ክርስቲያን ንጉሥ የሚጠበቀውን ምሕረት ባለማሳየቴ እጅግ አዝኛለሁ። የሕዝቤ አባት እንደመሆኔ መጠን የልጆቼን ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ አለብኝ። እሥረኞችን በመመለስ የሰላም ዋስትናቸውን መስዋዕት እንዳላደርግ ሕሊናዬ ይወቅሰኛል።"

አፄ ምኒልክ የጳጳሱን ምልጃ ባይቀበሉም ለእናቶች ጥያቄ ግን ርኅራኄ አሳይተው ነበር። ከበርካታ ደብዳቤዎች መካከል እጓቴት እናት "በአዲሲኒያ ለታሠርከው ልጄ አንቶኒዮ" የሚል ጽሑፍ ያለው ፖስታ ወደ ኢትዮጵያ ልከው ነበር። ፖስታውን የተመለከቱ ጣልያናውያን በአልፍሬድ ኢልግ አማካኝነት ደብዳቤውን ለምኒልክ አደረሱ።

ደብዳቤው ሲነበብ "ውድ ልጄ - ዘወትር ወደ ፖምፔይ በመሔድ በቅድስት ፖምፔይ ሐውልት ሥር ተምበርከክ በመጸለይ ሽማ አበራለሁ። ወደ አገርህ በሰላም እንድትመለስ እየጸለይኩልህ ነው" የሚለው መልዕክት የምኒልክን ልብ ነካው። ንጉሡም እንቶኒዮን ወደ ቤተ መንግሥታቸው አስጠርተው የሚከተለውን በመናገር ወደ አገሩ ሸኝተውታል።

> "በእናትህ ዕምነት እና ፀሎት ልቤ ተነክቷል። እናትህ ንጹህ ሴት እንደሆነች ይሰማኛል። ጸሎቷ ምላሽ እንዲያገኝም አፈልጋለሁ። ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ነፃ ነህ። ለጉዞ የሚበቃ ገንዘብ እና በቅሎ ይዘጋጅልሃል። ከመጀመሪያው መንገደኞች ጋር ትሔዳለህ።"

ከሻቲካን መልዕክተኞች ቀጥሎ በፖላንዳዊው እንደራሴ ዊርሶዊትዝ የተመራ የሸማግሌዎች ቡድን የአዲስ አበባ ጉብኝቱን ግንቦት 20 ቀን 1896 ከኔፕልስ በመነሣት ጀመረ። ቡድኑ ከኹሰት የሕክምና ባለሙያዎች በተጨማሪ ራይናልድ ዴ ቾይሴል፣ ካዚሚሮ ሻኮውስኪ እና ሉጂ ፋንዋሊ የተባሉ ግለሰቦን የያዘ ነበር።

ቡድኑ ጅቡቲ የደረሰው ሐምሌ ወር ላይ ነበር። የቡድኑ መሪ የነበረው ዊርሶትዊዝ ባጋጠመው የጎዳድ ሕመም ጅቡቲ ላለ ሀይውቱ አለፈ። የቀሩት አባላት ከጣሊያን ጭነው የመጡትን መድኃኒት፣ መጠጥ፣ ሲጋራ፣ ሳሙና እንዲሁም 2,626 ደብዳቤዎችን በመያዝ ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል።

ሴዛር ኔራዚኒ አሥረኞችን ለማስለቀቅ ከአፄ ምኒልክ ጋር ለመደራደር አዲስ አበባ የገባው ጥቅምት 6 ቀን 1896 ነበር። ድርድሩ ጥቅምት 26 ቀን ሲጠናቀቅ ጣሊያን ለአሥረኞች ቆይታ የአገልግሎት ክፍያ ይሆን ዘንድ ለኢትዮጵያ 10 ሚሊዮን ሊሬ ለመክፈል ተስማማች። ክፍያው በሦስት ዙር የሚፈጸም ሲሆን ለእያንዳንዱ አሥረኛ ግልጋሎት በነፍስ ወከፍ 6,301 ሊሬ የሚከፈል ሲሆን ይኸውም በቀን በእንድ እሥረኛ 27 ሊሬ ለኢትዮጵያ የሚከፈል ይሆናል። በወቅቱ የኢትዮጵያ ገቢያ ኹለት ሊሬ አንድ ሙሉ ዶሮ እና አንድ ሊትር ጠጅ ይገዛ ነበር።

ክፍያው ከተፈጸመ በኋላ የአሥረኞችን ጉዞ በተመለከተ ልዩ ዕቅድ ተዘጋጀ። እሥረኞችን አዲስ አበባ እና ሐረር ላይ በመሰባሰብ በእንድ ጊዜ ከ100 እስከ 150 የሚደርሱትን ለማጓጓዝ ተወሰነ። ከአዲስ አበባ በመነሣት ኔፕልስ ለመድረስ የ8 ሳምንታት ጊዜ ያስፈልግ ስለነበር ለአሥረኞች በቂ ስንቅ ለመቋጠር ሲባል በቡድን ተከፋፍለው በተለያየ ጊዜ እንዲጓዙ ተደረገ።

ጎዳር 24 ቀን 1896 የመጀመሪያዎቹ ተጓዦች ከአዲስ አበባ በመነሣት ወደ አገራቸው ተጓዙ። የመጨረሻው ቡድን በጀ/ል አልበርቶኒ የተመራ ሲሆን በግንቦት ወር 1897 ኔፕልስ ደርሷል።

በርካታ አሥረኞች ከኢትዮጵያውያን ወዳጆቻቸው ጋር መለያየት ከብዷቸው ነበር። ስሜቱ ከጣሊያናውያን ጋር ለተወዳጁ አንዳንድ አበሾችም ተመሳሳይ ነበር። ሐረር አቅራቢያ የነበረው እሥረኛ ጂዮቫኒ ቴዶን ወደ አገሩ ለመመለስ ሲሰናበታቸው በግዞት የቆዩት ኢትዮጵያን መርቀውታል። ለፍቅረኛው ዘውዲቱ እና በቆይታው





ላወቃቸው የመንደሪቱ ሴቶች ጣሊያን ከደረሰ በኋላ የበርካታ አልባሳት፣ ሽቶ እና ጌጣጌጥ ስጦታ ልኮላቸዋል። ለወንዶቹ ደግሞ ከትንሽ ሽጉጥ ጀምሮ የተለያዩ የጠመንጃ ስጦታዎችን ልኮላቸዋል።

በቆይታቸው የተደሰቱ በርካታ እሥረኞች ወደ አገራቸው ለመመለስ ጥድፊያ አላሳዩም ነበር። የተወሰኑ እሥረኞች ከኢትዮጵያውያን ጋር በመላመዳቸው፣ አንዳንዶች ደግሞ ተመልሰው የሚቀላቀሉት ቤተሰብ ስላልነበራቸው በኢትዮጵያ ለመቆየት ወሥነዋል። የጣሊያን ቀይ መስቀል ማኅበር እንደገለጸው በ1897 መባደጃ ከዘጠኝ እሥረኞች በስተቀር ኹሉም ምርኮኞች ወደ አገራቸው ተመልሰዋል። ዘጠኙ በኢትዮጵያ ለመቅረት የወሰኑ ሲሆን ከእሥር ነፃ ተደርገዋል።

በርካታ እሥረኞች አዲስ አበባን የተሰናበቱት ፀድፀታ እና ጎዘን ነበር። የካቲት 13 ቀን ፍራንሲስኮ ፍሪሊና ከተማዋን ለመጨረሻ ጊዜ ዞሮ ሲመለከታት ዐይናቹ በእንባ ተሸፍነው ነበር። በርካቶች ደግሞ መንገድ ከጀመሩ በኋላ ውሳኔአቸውን በመቀየር ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል።

ሰርጀንት ሱዳቪኮ ባርቤሪ አዲስ አበባን ለቅቆ የወጣው በምሽት ነበር። የወቅቱ ስሜቱን የገለጸው የከተማዋን የአመሻሽ ገጽታ ከከፍታ ስፍራ ላይ ሆኖ ለመጨረሻ ጊዜ የተመለከተውን በዐይነ ሕሊናው ቀርፆ ነበር።

> ". . . ፀሐይዋ በመጥለቅ ላይ ነበረች። የፀሃይዋ የምሽት ወርቃማ ብርሐን ከተማዋን እንደቀለበት ከከበቧት ተራሮች ጀርባ ይታያል። የምሹቱ ጸሐይ የመጨረሻ ብርሐን ያረፈበት የንጉሡ ቤተ-መንግሥት ጣሪያ ክርቱት ስሚመስከተው ባወርቅ የተከደነ ይመስል ነበር። ከአንዳንድ ቤቶች ክዳን ላይ የሚወጣው ጭስ ፈዘዝ ብሎ ይታያል። ከየጎጆው የሚወጣው ሰማያዊ ጭስ በከተማዋ ሰማይ ላይ ተዝርግቶ ከሥሩ ያለውን ዓለም ሽፍኖታል። . . ."

ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦችም ከእሥረኞች ጋር ሲለያዩ የጎዘን ስሜት ደብቷቸው ነበር። አንዳንድ ሰዎች ለወራት አብረዋቸው የከረሙትን እሥረኞች ከከተማዋ ውጪ አርቀው ሸኝተዋቸው ነበር የተመለሱት። አንዳንዶች ደግሞ ሰቀናት ያህል አብረው በመጓዝ እሥረኞችን የሸኙ ሲሆን ወደ ቤታቸው ሲመለሱ የባዶነት ስሜት ይታይባቸው ነበር።[13]

# ምዕራፍ ሐያ አንድ

## መጨረሻው

በ1896 ዓ.ም. ማክሀደጃ በአፄ ምኒልክ ቤተ-መንግስት በመገኘት አስገራሚ የጎዘን ትዕይንት ከተመለከቱት እሥረኞች መካከል ኒኖ ዲአማቶ አንዱ ነበር። በወቅቱ የተመለከተውን የገለጸው በከፍተኛ ጎዘን ውስጥ ሆኖ ነበር። በጦርነቱ ልጆቻቸውን፣ ወላጆቻቸውን እና ዘመዶቻቸውን ያጡ ጎዘንተኞች በከፍታ ስፍራ ላይ በመሰመር ቆመዋል። አፄ ምኒልክ በጎዘንተኞቹ መካከል ተቀምጠዋል።

ንጉሡ ፊታቸው በጎዘን ስሜት የተሞላ ሲሆን በዝምታ ነበር የተቀመጡት። በርካታ ለቀስተኞች ጥቁር ኮፍያ እና ነጭ ጋቢ ለብሰው በዝግታ በንጉሡ ፊት ያልፉ ነበር። ንጉሡ ወንበር ፊት ሲደርሱ በማጎንበስ ለንጉሡ ሃዘናቸውን በመግለፅ የቤተ-መንግስቱን ግቢ ለቀው ይወጡ ነበር። የለቅሶው ሥነ-ሥርዓት ለአምስት ተከታታይ ቀናት ቀጥሎ ነበር። በሥነ-ሥርዓቱ አፄ ምኒልክ ለቅሶ ደራሾችን በክብር ሲያሰናብቱ ከርመዋል።

የአድዋን ድል ተከትሎ አፄ ምኒልክ የአፍሪካ የምንጊዜም ታላቅ መሪነታቸው በደማቅ ቀለም አስፅፈዋል። ድሉ የኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካን መዓኪ እድል የወሰነ ነበር። በዚህም የአድዋ ጦርነት የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካም ጭምር ነው። ምክንያቱም በቀጣይ መቶ ዓመታት የአውሮፓ የበላይነት እና አገዛዝ በአፍሪካ አክትሟል። የዘመናዊት አፍሪካ የሉዓላዊነት መሠረት ድንጋይ የጣለው አድዋ ላይ ነበር።

ድሉ የኢትዮጵያን ነፃነት ለዘንዶ እና ለመጪረሻ ጊዜ ያረጋገጠ ነበር። አድዋ ታላቅ ድል ብቻ አይደለም። አገሪቷን በመታደግ ንጉሢ አዲስ የተማከለ ስልጣናቸውን ለመሳው ዓለም የገለጸበትም ጭምር እንጂ። ከ1895-1898 የተደረጉ ጦርነቶች አድዋ ላይ ፍጻሜ ሲያገኙ የኢትዮጵያ አንድነት በወታደራዊ ድል የተረጋገጠበትን ዅነት አመላክቷል። ይህ ታሪክ ኢትዮጵያን እና ደርመንን ያመሳስላቸዋል። ዅሉቱም አገራት





ነገሥታቶቻቸው ባስመዘገቧቸው ወታደራዊ ድሎች አማካኝነት አንድነታቸውን አረጋግጠዋል።

የአድዋ ድል የምኒልክ እና ጣይቱን ዕጣ ፈንታም ወስኗል። በጦርነቱ ቢሸነፉ ኖሮ የጥንዶቹ ቀጣይ እጣ ፈንታ ግልፅ ነበር። የጣሊያን ሠራዊት አሊያም የራሳቸው ሕዝብ ክስልጣን ያስወግዳቸው ነበር።

በጦርነቱ በርካታ ሕዝብ ቢያልቅም የተመዘገበው ድል እና የአገሪቱ አንድነት መረጋገጥ ጎዘኑን ቀላል አድርጎታል። በአድዋ ህይወታቸውን የሰጡ አርበኞች ለዘመናዊት ኢትዮጵያን ቅርጽ እና ውስጣዊ አንድነትን ሰጥተው ነው ያለፉት። የፈጸሙትን አኩሪ ታሪክ ሕዝብ ሲዘክረው ይኖራል።

የአድዋ ድል በበርካታ ሥዕሎች መገለፅ የጀመረው ከጦርነቱ ማግስት ነበር። ኢትዮጵያን በኦርቶዶክስ ዬክርስቲያን ተፅዕኖ ሥር የቆየ የሥነ-ሥዕል ባህል አላቸው። የአድዋን ወታደራዊ ድል በሥነ-ሥዕላቸው ለመግለፅ የተጠቀሙት በዘመቻው ወቅት ታቦት የተሸከሙ መነኮሳትን እና የጦር መሣሪያ ያነገቱ አርበኞችን ጎን ለጎን በመሣል ነበር። የዅሉቱ የተቀናጀ መንፈሳዊ ጥምረት የተቀደሰ ድልን በመራራ ትግል ማስገኘት እንደቻለ በሥዕሎቻቸው ለመግለፅ ችለዋል።

አብዛኞቹ ሥዕሎች ተመሳሳይ አቀባብ ነበራቸው። በሥዕሎቹ ላይ የኢትዮጵያ ወታደሮች በግራ መስመር ክስተር ብለው የሚታዩ ሲሆን የጣሊያን ወታደሮች ደግሞ በቀኝ መስመር ተሸብረው ይታያሉ። በዅሉቱ መካከል በጀግንነት ከጠላት ጋር የሚዋደቁ ወታደሮችን ሥዕሎቹ የሚያሳዩ ሲሆን ከዅሉም በላይ ግን ቅዱስ ጊዮርጊስ ፈረስ ላይ ሆኖ ጦሩን ወደ ጣሊያን ወታደሮች እየወረወረ ይታያል።

የአድዋ ጦርነት በዕለተ-ጊዮርጊስ መካሔዱ ለድሉ የመንፈሳዊ እርዳታ አስተዋፅኦ ያደረገው ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንደሆነ በርካታ ኢትዮጵያውያን ያምናሉ። ከጦርነቱ ማግስት አፄ ምኒልክ በአዲስ አበባ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤክርስቲያን እንዲገነባ አዘዙ። ቤተ-ክርስቲያኑ በአንድ ዓመት ውስጥ ተገንብቶ ተጠናቀቀ።

በቤተ-ክርስቲያኑ ጣሪያ ላይ የክርስቶስ እና ደቀ-መዛሙርቱን የመጨረሻ ዕራት እንዲሁም ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ሲያጥብ የሚያሳዩ ሥዕሎች

አሉ። ከኹለቱ ሥዕሎች በታች የአድዋን መለከታዊ ድል የሚያሳይ ምሥል ተስሏል። ሥዕሉ ኢትዮጵያ ጠላቶቿን በፈጣሪ እርዳታ ድል መንሣቷን የሚመለክር ነው።

እስከ 1920ዎቹ የሥኑ-ሥዕል ገለጻው የቀጠለ ሲሆን የእቴጌ ጣይቱን የጦር ሜዳ ውሉ የሚዘክሩ በርካታ ሥዕሎች ሥለዋል። ንግስቲቱ እጃቸውን ዘርግተው ጦር ሲያዘምቱ እንዲሁም ጠመንጃ ይዘው የሚያሳዩ ሥዕሎች በብዛት የተሳሉት በ1920ዎቹ ነበር። የራስ መኮንን ምስሎችም በብዛት የታዩት በተመሳሳይ ዓመታት ነበር። ምስሎቹ በቀጣይነት የልጃቸው ኃይለ ሥላሴን የስልጣን ጉዞ ያመላክቱ ነበሩ።

## ተፋላሚው

የሃይቲው ተወላጅ ቤኒቶ ሲልቬይን የአድዋን ድል ለማክበር ወደ አዲስ አበባ በመጣበት ወቅት የጦርነቱ ዋና ተፋላሚ የነበረውን ጀ/ል ማቲኦ አልበርቶኒ አግኝቶታል። ሲልቬይን በወቅቱ የተመለከተውን ጀ/ል "መላው ሽንፈት ፊቱ ላይ ይዞ የሚዞር ይመስላል" በማለት ነበር የገለጸው።

በርግጥም የአልበርቶኒ ጥፋት ጣሊያንን ለሽንፈት ዳርጓል። የባራቴሪን ትዕዛዝ በመተላለፍ አነስተኛ ግምት ወደ ሰጠው የምኒልክ ሠራዊት ጦሩን በማዝመት የጣሊያንን ሠራዊት ለከፍተኛ ሽንፈት የዳረገው አልበርቶኒ ነበር። በእሥር ላይ ሳለ ለወጣቱ ጌራርዶ ፓንታኖ ለሽንፈቱ የነበረውን ተጠያቂነት እንዲህ ሲል ነበር የተናዘዙለት።[6]

> ". . . አንተ ወጣት ነህ። ከእኔ የተሻለ ወደ አገርህ የመመለስ ዕድል አለህ። አሁን የምነግርህን ፈጽሞ እንዳትረሳ። ለሕዝባችን ጀ/ል ባራቴሪ በጀነራሎቹ መከዳቱን ንገርልኝ።"

ከተናት በኋላ ወደ አገሩ የመመለስ እድል እንዳለው የተገነዘበው ጀ/ል አልበርቶኒ በጦር ሜዳ ስለፈጸመው ክህደት ሊያወራ አልተደመጠም ነበር። በተሰያዩ አጋጣሚዎች ስሕተቱን የፈጸመው እርሱ ሳይሆን ጀ/ል አሪሞንዲ እንደነበር ሲናገር ተደምጧል። አሪሞንዲ ወደፊት ተንቀሳቅሶ በዳቦርሚዳ እና በአልበርቶኒ ብርጌዶች መካከል የነበረውን ክፍተት አለመሙላቱ ለሽንፈቱ ምክንያት እንደሆነ ሲናገር ነበር።





በጦር ሜዳ ልምድ መሠረት ኃይልን አሰመከፋፈል ማንኛውም እግረኛ ወታደር የሚረዳው የመጀመሪያ ሕግ ነው። እንደ አልበርቶኒ እና ዳቦርሚዳ ያሉ ከፍተኛ ጀኔራሎች ይህንን ህግ አይረዱትም ለማለት ያስቸግራል። ስለዚህ ኹለቱ ጀነራሎች በብርጌዳቸው መካከል የፈጠሩት ክፍተት ከምን የመነጨ እንደሆነ ለማንም ግልጽ አይደለም።

አልቤርቶኒ ራሱን መውቀስ ቢያቆምም በውጊያው ላይ የሞቱትን ጀ/ል ዳቦርሚዳ እና ጀ/ል አሪሞንዲን ተጠያቂ አላደረገም። ወደ ጣሊያን ከተመለሰ በኋላ በወታደራዊ ሥራው የቀጠለ ሲሆን ጋዜጦች የተወሰነ ተቃውሞ አሰምተውበታል። ሆኖም ግን ጥፋተኛ መኾኑን ሊያረጋግጡ አልቻሉም።

የአልበርቶኒን ጥፋተኝነት ያስተባበለው ሲዛር ፔኒ ሲሆን በግል ማስታወሻው ያሰፈረው ምስክርነት በርግጥም የአልበርቶኒን ትዕዛዝ አለማክበር የሚያረጋግጥ ነበር። "የአልበርቶኒ ስሕተት ለማሸነፍ ካለው ጉጉት የመጣ ነበር። ለድል በመቻኮሉ የተነሣ ጦሩን አንቀሳቅሷል" በማለት ነበር ፔኒ ምስክርነቱን የጻፈው።

አልበርቶኒን ለሽንፈቱ ተጠያቂ ያደረገው ከአድዋ ጦርነት የተረፈው ጀ/ል ኢሌና ነበር። ወደ ጣሊያን በሰላም ከተመለሰ በኋላ ስለ ጦር ሜዳው ውሉ ሲፅፍ ጀ/ል አልበርቶኒ፣ ዳቦርሚዳ እና አሪሞንዲ የአለቃቸውን ትዕዛዝ መጣሳቸውን ገልጿል።

## የባራቴሪ የመጨረሻ ቀናት

በ1896ቱ የፍርድ ሂደት በነፃ ከተለቀቀ በኋላ ባራቴሪ ከዕይታ ተሰውሮ መኖርን ነበር የመረጠው። ከትውልድ መንደሩ ትሬንቲኖ አቅራቢያ በምትገኘው አርኮ በመሸሸግ ከሕዝብ ወቀሳ በመራቅ መኖር ጀመረ። የብሬሽያ ግዛትን በመወከል ለሐያ ዓመታት በጣሊያን ሕግ አውጪ ም/ቤት አባልነት የቆየ ቢሆንም ከአድዋ ሽንፈት በኋላ ከም/ቤቱ ራሱን አግልሏል። ሰም/ቤቱ ባስገባው የመልቀቂያ ደብዳቤ መጨረሻ ላይ "ሰዎች ያልፋሉ፣ አገር ግን ትኖራለች" በማለት ጽፏል።

ባራቴሪ በእርኮ ተሸሽጎ የብቸኝነት ሕይወትን መምራት ጀመረ። በኢትዮጵያ ቆይታው የዘውትር ጠያቂው የነበረችው እጉቱ ሱይላ እና ሴት ልጁ ማሪያ ኮንዛቲ ቤተሰባዊ እንክብካቤ አድርገውለታል። ከትንሽ አረፍት በኋላ ባራቴሪ የትግል

ቆይታውን የሚዘክር መጽሐፍ መፃፍ ጀመረ። ከወራት በኋላ በ1898 ባለ 500 ገፅ ግሑሀይወቱን እና የአድዋ ስሕተቱን የሚከላከል መጽሐፍ "የአፍሪካ ትውስታዎች" በሚል ርዕስ አሳተመ።

ባራቴሪ በእንቅልፍ እጦት እና አለመረጋጋት መሰቃየት የጀመረው መጽሐፉን ካሳተመ በኋላ ነበር። ቀሪ ዓመታትን ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የኖረ ሲሆን ማንነቱ በማይታወቅባቸው ማድሪድ፣ ባደን ባደን፣ ኒቼ፣ ካርልስባድ፣ ትሬስቴ፣ ቄስዲን፣ ቬኒስ፣ ሞንቴ ካቲኒ እና ፓሪስ ከተሞች በመዘዋወር ኖሯል።

የግል ማሕደሩ በ1867 ትዳር መመሰረቱን ቢጠቅስም የሚስቱ ማንነትም ሆነ ከባራቴሪ ጋር የኖረችባቸው ዓመታት አይታወቁም። ከጋብቻው በኋላ ከባራቴሪ ሕይወት ውስጥ የጠፋች ሴት ናት። ቁስ ጌሬሚያ ቦኖሜሊ የባራቴሪ አብሮ አደግ እና የልብ ወዳጅ ናቸው። ኤርትራ በነበረበት ወቅት ከቁስ ወዳጁ ጋር በርካታ ደብዳቤዎችን ተላልኳል። ከአድዋ በኋላ ከፃፈው ደብዳቤ ላይ የወሰዱትን ንግግር ባራቴሪ ከሞተ በኋላ የመቃብር ድንጋዩ ላይ አስቀርጸውለታል። ጽሑፉ "በጦር ፍርድ ቤቱ ችሎት ፊት ሰቆም ጥቂት ንግግር ብቻ እንዳደርግ ተገድጃለሁ። የሌሎች መኮንኖችን ጥፋት የሚሸፍኑ ንግግሮቼ ብቻ ተሰሚ ነበሩ።"

በ1901 ዓ.ም. ባራቴሪ በብርቱ ሕመም ተዳከመ። በአልፓይን አቅራቢያ ስቴርዚግ በተባለች አነስተኛ መንደር በመኖር ላይ ሳለ በርካታ ደብዳቤዎች ይደርሱት ነበር። በጽኑአ የመታመሙን ዜና ጋዜጦች ለሕዝብ ከገለፁ በኋላ አንድ የላኪው አድራሻ ያልተጠቀሰ ደብዳቤ ለባራቴሪ ደርሶታል። "በጽኑአ መታመምህን ከጋዜጦች አውቄአለሁ። ደስም ብሎኛል። ያም ሆኖ ግን ሞትን አልመኘልህም። ምክንያቱም ሞት ላንተ ቀላል ቅጣት ነው። ለሺህ ዓመታት ኖልህ ብትሰቃይ ደስ ይለኛል።"

ባራቴሪ ደብዳቤውን ካነበበ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ሞቷል። ፀትጎሿ የስቴርዚግ መንደር ያለ ምንም አስታማሚ ሞቶ ቢገኝም ከህልፈቱ በኋላ ስሙ ተደጋግሞ በ1920ዎቹ ተነስቷል። ፋሽስታዊው የጣሊያን መንግስት በኢትዮጵያ ላይ የበቀል ጦርነት ለማወጅ ቡተዘጋጀባቸው የ1920ዎቹ ዓመታት በአድዋ የወደቁ የጦር ጀነራሎችን እና የመሪያቸው ጀ/ል ባራቴሪን ስም በተደጋጋሚ ያነሣ ነበር።





## የጀግኖቹ የመጨረሻ ዓመታት

በኢትዮጵያ ጠላቶች እንደ ጦር የሚፈሩት ራስ አሉላ ከአድዋ ጀግኖች መካከል የመጀመሪያው ሟች ነበሩ። የአሉላ አሟሟት በግልፅ ባይታወቅም በመሬት ይጣሻል ግጭት በጥይት ተመትተው እንደቆሰሉ እና ከጥቂት ቀናት በኋላ እንደሞቱ ይነገራል። ከአድዋ የመጀመሪያ ዓመት የድል በዓል ጥቂት ሳምንታት ቀድመው ያረፉት ራስ አሉላ በበርካታ አውሮፓውያን ከበሬታ እና አድናቆትን ያገኙ ጀግና ናቸው።

ጌራርድ ፓታኖ በአሥር ላይ ሳለ ከበርካታ የኢትዮጵያ ከፍተኛ መሳፍንት እና መኳንንት ጋር ተገናኝቶ መነጋገር ችሏል። ራስ አሉላን የገለፃቸው በአድናቆት ነበር። ". . . ከኹሉም መሳፍንት የተለየ፣ አስተዋይ እና ንቁ ሰው ነው።" የእንግሊዙ ጋዜጠኛ እና ዲፕሎማት አንስተስ ዋይልድ በበኩሉ "ራስ አሉላ ከፍተኛ ወታደራዊ ጥበብ የታደለ፣ አስፈሪ የጦር መሪ ነው። ከአገሬቱ ፖለቲካ ጀርባ የሚቆም ግዙፍ ደጀን ቢሆንም እንደ ሌሎቹ መሳፍንት ራሱን ለታይታ አያቀርብም" በማለት ገልጿቸዋል።

ራስ መኮንን ከአድዋው ጦርነት በፊት በነበረው የመቀሌ ምሽግ ሰበራ ሙከራ በርካታ ወታደሮቻቸውን በማስገደላቸው በመሳፍንቱ እና ንበዛዝቱ ዘንድ ሲወቀሱ ነበር። በአድዋ ውጊያ ላይ ታፋቸውን በጥይት ተመትተው የነበረ ሲሆን ለማገገም በርካታ ሳምንታት አስፈልጓቸው ነበር። በውጊያ ላይ መቁሰላቸው ለመቀሌው ስሕተት ይቅርታ ሊሆናቸው ችሏል።

ራስ መኮንን የአፄ ምኒልክ ተመራጭ እና ታማኝ በመሆን ከአድዋ ጦርነት በኋላም በርካታ ሥራዎችን ሰርተዋል። በ1898 ዓ.ም. ወደ ፓሪስ በመጓዝ በኤሊሲ ቤተ-መንግሥት ከፍተኛ አቀባበል ተደርጎላቸዋል። የዲፕሎማሲ ሥራቸውን በመቀጠልም ከኹለት ዓመታት በኋላ ተመልሰው ወደ ፓሪስ ያመሩ ሲሆን በዚያውም ኢየሩሳሌምን ጎብኝተዋል። በ1901 የኢትዮጵያ ልኡካንን በመምራት በለንደን የንጉሥ ኤድዋርድ ዐሥራ ኹለተኛ በዓለ ሲመት ላይ ተገኝተዋል።



Makonnen at the coronation of King Edward VII. From Richard Pankhurst and Denis Gérard, *Ethiopia Photographed: Historic Photographs of the Country and Its People Taken between 1867 and 1935*. London: Kegan Paul International, 2006.

***ምስል- በራስ መኮንን ለንጉሥ ኤድዋርድ በለሰ ሲመት ለንደን በተገኙበት ወቅት***

ራስ መኮንን የአፄ ምኒልክ ዘውድ ወራሽ እንደሚኾኑ በበርካቶች ቢገመትም ከአድዋ በኋላ ካረፉ ጀግኖች ኹለተኛው በመሆን በ1906 በሕመም አርፈዋል።[11] በተመሳሳይ ዓመት የአፄ ምኒልክ ጤና መዳከም ጀምሮ ነበር። የንጉሡን የጤና መቃወስ ተከትሎ የአማካሪያቸው አልፍሬድ ኢልግ ተሰሚነት እና ተፅዕኖ በዘውዱ አካባቢ ቀንሷል።

አልፍሬድ ኢልግ ለንጉሡ የነበረውን ፍቅር በተለያዩ ጊዜያት ያሳየ ሲሆን ወንድ ልጁን ምኒልክ ሲል ስም ሰጥቶታል። የንጉሡን ሕመም ተከትሎ ባለቤቱን እና ልጁን በመያዝ በ1906 ወደ ስዊዘርላንድ ተመለሰ። ከ10 ዓመታት በኋላም ህይወቱ አለፈች።[12]

ከአድዋ ጀግኖች ትውልድ መካከል ረጅም ዓመታት መቆየት የቻሉት እቴጌ ጣይቱ ናቸው። አፄ ምኒልክ በጠና በታመሙበት ወቅት ከፍተኛ ፖለቲካዊ ሥልጣኑን በእጃቸው ለማስገባት ይሯሯጡ በነበሩ የሸዋ ጎበዛዝት እና መሳፍንት የተገፉት ንግስቲቷ በ1910 ሥልጣናቸውን ቀስ በቀስ ተቀሙ። ፖለቲካውን በመተውም





ህመምተኛ ባለቤታቸውን ማስታመም ላይ አተኮሩ። አፄ ምኒልክ በ1913 ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ እቴጌ ጣይቱ ወደ እንጦጦ ቤተ-መንግሥት በመሔድ ህይወታቸው እስካለፈበት 1918 ድረስ በዚያው ኖረዋል።



The Lion of Judah in winter. From Lincoln de Castro, *Nella terra dei negus: pagine raccolte in Abissinia*. Milan: Fratelli Treves, 1915.

***ምስል- የይሁዳ አንበሳ አፄ ምኒልክ በክረምት ወራት (ከሊንከን ዲ' ካስትሮ የተወሰደ 1915)***



Makonnen at the coronation of King Edward VII. From Richard Pankhurst and Denis Gérard, *Ethiopia Photographed: Historic Photographs of the Country and Its People Taken between 1867*



The Lion of Judah in winter. From Lincoln de Castro, *Nella terra dei negus: pagine raccolte in Abissinia*. Milan: Fratelli Treves, 1915.

**ምስል፡- የይሁዳ አንበሳ አፄ ምኒልክ በክረምት ወራት (ከሊንከን ዴ' ካስትሮ የተወሰደ 1915)**

አፄ ምኒልክ እና ጣይቱ ክሞት በኋላ ስማቸው በሰፊው መነሣት ቢችልም የራስ መኮንን ስም መደጋገሙ በቀላሉ ሽፍኗቸው ነበር። በ1960ዎቹ የልጃቸው አፄ ኃይለ ሥላሴን ንግስና ተከትሎ ራስ መኮንን የአድዋ ታላቅ ጀግንነት እና የዘመናዊት ኢትዮጵያ መሥራች መሆን በስፋት መነጋገር ጀምሮ ነበር። የራስ ተፈሪያን ዕምነት መሠረት ተደርገውም የተጠቀሰብት ወቅት ነበር።

የራስ መኮንን ምስል በኢትዮጵያ ሰፊ ስፍራን መያዝ ቢችልም የልጃቸውን ዓለም አቀፍ ዕውቅና መጣደር ግን አልቻለም ነበር። በ1930 ሃይለ-ስላሴ በሚሰው የንግስና ስማቸው ዘውድ የጫኑት ራስ ተፈሪ መነሻውን ጃማይካ ያደረገው የራስታ ዕምነት መሲህ መሆናቸው ይታመናል።

አፄ ኃይለሥላሴ የአባታቸው ራስ መኮንን ምስል እና የራሳቸው ዝና ለመገንባት ባደረጉት ብርቱ ጥረት በ1960ዎቹ የምኒልክ እና ጣይቱ ምስል በሕዝቡ እና የቀረው ዓለም ዘንድ ደብዛዛ ሆነ። በአድዋ ሰመላው ጥቁር ምሳሌ የሚሆን ድል ያስመዘገቡት አፄ ምኒልክ በራስ ተፈሪ (ኃይለ ሥላሴ) ምስል የተዋጡበት አካሔድ ራሱን የቻለ ታሪክ ነው። በ1950ዎቹ እና 60ዎቹ አፄ ኃይለስላሴ የአፍሪካ የነፃነት አባት ተደርገው ሲነሱ የምኒልክ ድል የሆነው አድዋ ግን ታሪካዊ ድምቀቱን አጥቶ ታይቷል። ታሪካዊ መዋዋጡንም ሆነ የአድዋን ድል መደብዘዝ ቀጣይ የኢትዮጵያ ትውልድ እንደሚረዳው ይታመናል።

የአድዋ መልዕክት ግን ግልፅ ነው። አድዋ ብሔራዊ ኩራት ብቻ ሳይሆን ለዘመናዊት ኢትዮጵያ መመሥረት የመሠረት ድንጋይ የተጣለበት ሁነትም ጭምር ነው። ምኒልክ እና ጣይቱ ወደ ሰሜን የዘመቱት ስልጣናቸውን በፅኑ መሰረት ላይ ለመገንባት ብቻ አልነበረም። በዘመቻቸው የትግራይ፣ የሸዋ፣ የኦሮሞ፣ የወላይታ የሌሎች ሕዝቦችን ውስጣዊ አንድነት በደም አስተሳስረው በጋራ ጠላት ላይ በማሥነሣት የጋራ አገር መገንባት ችለዋል።

የሕዝቦች ጥብቅ መተሳሰር የሚፈጠረው በእያንዳንዳቸው የጎይማኖት፣ የብሔር እንዲሁም የቀለም መለያ ላይ ተመሥርቶ አይደለም። ዙሉን በአንድነት የሚያስተሳስረው የጋራ ነፃነትን ለማግኘት የሚከፈል መስዋዕትነት ነው። ይህ ዓይነቱ





መተሳሰር ብቻ ነው የኢትዮጵያ የነፃነት ከፍታ መገለጫ። የአድዋም ትምህርት ይኸው ነው።

ልንታደሰው የሚገባን ነፃነት ልንከላከለው የሚገባ ዓይነት መሆን እንዳለበት አድዋ ያስታውሰናል። የአድዋ ድል ያስገኘውን ነፃነት ብቻ በመመልከት ሳይሆን የተገኘበትን መንገድ ብናጤነው በእውነት የዘመናችንም ታላቅ ወታደራዊ ድል እንደሆን እንረዳለን። ኢትዮጵያ በጠመንጃ በመታገዝ ብቻ ያገኘችው ድል አይደለም አድዋ። የበርካቶችን ልብ በማሸነፍ መጠነ-ሰፊ ድጋፍ እና ዲፕሎማሲያዊ ብልጫ ያሳየችበትም ጭምር እንጂ።

አድዋ የ19ኛው ክ/ዘመን ታላቅ ወታደራዊ ዘመቻ ለመሸኑ በርካታ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል። በርካቶች የአንድን ዘመቻ ታላቅነት የሚለኩት ዘመቻው በሚያካልለው የቦታ ስፋት እና በሚወስደው የጊዜ እርዝማኔ ነው። በዙሰቱ መስኪያዎች፣ የ19ኛው ክ/ዘመን ታላቅ ዘመቻ የናፖሊዮን ሠራዊት በ3 ወራት ውስጥ ከቪልንየስ እስከ ሞስኮ ያለውን 490 ማይል መራት የሸፈነበት እንደሆነ በርካታ ፀሃፍት ገልፀዋል። የአፄ ምኒልክ የአድዋ ዘመቻ በአጠቃላይ ወራትን የፈጀ እና 580 ማይል ርቀትን የሸፈነ በመሸኑ ብቻ ከናፖሊዮን ዘመቻ የላቀ ያደርገዋል። ከዙሉም በላይ ደግሞ የአድዋ ዘመቻ በድል የተጠናቀቀ ሲሆን የናፖሊዮን ዘመቻ በሽንፈት ነበር የተፈጸመው። የክ/ዘመኑ ታላቅ ወታደራዊ ዘመቻ የናፖሊዮን ሳይሆን የአፄ ምኒልክ ነው።

የምኒልክ ታላቅ ወታደራዊ ድል የተመዘገበው በአድዋው ዐውደ-ግምባር አለመሸኑ አንዱ የዘመቻው ታላቅነት ማሳያ ነበር። ከዋናው ጦርነት ጥቂት ሳምንታት ቀድሞ አፄ ምኒልክ አዲግራት ላይ መሸን የነበረውን የባራቴሪ ጦር አልፈው ወደ ኤርትራ በመንቀሳቀስ ነበር የዘመቻውን የበላይነት የተቆጣጠሩት። በወቅቱ ባራቴሪን ከመግጠም ይልቅ ኤርትራን መያዝ ላይ ማተኮራቸው የጣሊያን ሠራዊት ምሽጉን እንዲለቅ አስገድዶታል። የምኒልክን አካሔድ የተረዳው ባራቴሪም ወደ ኤርትራ ለማፈግፈግ ቢወስንም በጀነራሎቹ ችኩልነት እና ትዕዛዝ አለመቀበል የተነሣ አድዋ ላይ ከግዙፉ የአፄ ምኒልክ ጦር ጋር እንዲጋፈጥ አስገድዶታል።

የአድዋ ድል ለኢትዮጵያ እና ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለአውሮፓውያን እና ለአሜሪካ ልዩ መልዕክት አስተላልፏል። የአውሮፓ ተስፋፊዎች በአድዋ ዋዜማ መላው አፍሪካ በቁጥጥራቸው ሥር አለመሸኑን በአድዋ የንቃት ደወል ተገልጦላቸዋል።

የአድዋ ድል የተመዘገበው በአሜሪካ ወሳኝ የታሪክ ምዕራፍ ወቅት ነበር። የጥቁር እና ነጭ ሕዝቦችን አብሮ መኖር፣ መሥራት እና መጋባት የሚያግደው የጂም ክሮው ሕግ በወቅቱ በአሜሪካ ውስጣዊ ውጥረትን ፈጥሮ ነበር። ከሕጉ በተጨማሪ የManifest Destiny ፖሊሲ የምዕራብ መስፋፋት ቀጥሎ በ1898ቱ የስፔን እና አሜሪካ ጦርነት የተገታበት ነበር። የጦርነቱ ውጤት አሜሪካ የመጀመሪያዋ የድኅረ-ቅኝ ግዛት ልዕለ-ኃያል መሆኗን መስክሯል።

የ1896ቱ የአድዋ ድል ዜና ከሹሰት ዓመታት በኋላ ለመደረግ በመጋጋል ላይ ከነበረው የኩባ እና ስፔን የጦርነት ዋዜማ ዜና እኩል ሽፋን አልተሰጠውም ነበር። በጋዜጦች ኢ-ሚዛናዊ ሽፋን የተነሣ በወቅቱ ለተስፋፊነት ታላቅ ትምህርት ሊያስተላልፍ የሚችለው የምኒልክ ዜና በአግባቡ ሳይገለጥ ቀረ። አድዋ ለአብሪተኝነት፣ ጠባቂነት፣ ወራሪነት እንዲሁም የቀለም ልዩነትን በማጉላት ለሚደረግ ተስፋፊነት ያስማው ታላቅ የማስጠንቀቂያ ደወል ድምፅ በጦረኞች ጩኸት ተዋጠ።

የታሪክ ምሁራን 20ኛው ክፍለዘመን የአሜሪካ ጊዜ እንደሆነ ሲገልፁ ይደመጣል። ለገለፃቸው ድጋፍ ሲያቀርቡም የአውሮፓ መጻክምን ተከትሎ አሜሪካን በዓለም ብቸኛ ልዕለ ኃያል መሆኗን ይጠቅሳሉ። በ1898 ዓ.ም. አሜሪካን በፊሊፒንስ የስፔንን አገዛዝ ለፍጻሜ ያበቃ ድል አገኘች።[14] የስፔን ሽንፈት በአውሮፓ የበላይነት ዘመናት የተከሰተ የመጀመሪያው የታሪክ ጠባሳ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ እንዲት አውሮፓዊ አገር አውሮፓዊ ባልሆነ ኃይል የተሸነፈችበት የመጀመሪያ ክስተት መሸኑ ነው።

ከስፔን ቀጥሎ ሩሲያ ሽንፈት ያስተናገደች አውሮፓዊ ኃይል ሆና በታሪክ ተመዘግባለች። ከ1905ቱ የጃፓን እና ሩሲያ ጦርነት በኋላ የአውሮፓ የበላይነት ማክተሙ ተመለከተ። የዓለም ፖለቲካ የኃይል ሥርዓት እንዲሁም የሕዝቦች እና የቀለም ልዩነቶች የደረጃ አቀማመጥ በተለየ መስፈሪያ መለካት ጀመረ።





በመጨረሻም መላው ዓለም ታሪክን በተሻለ መንገድ መረዳት ችሏል። የአዲሱ ክ/ዘመን ጅማሬ አመላካች እና የታሪካዊ ለውጥ ምስክር የሆነውን ሂደትም መረዳት ችሰናል። ለዘመናት የነበረውን የታላቅነት እና የልዕለ-ኃያልነት መረዳት ያስቀየረ ማረጋገጫ የተገኘው በ1905 ወይም በ1898 አይደለም። በ1896 አድዋ በተባለ ቦታ እንጂ።

# የተመረጡ ዋቢ መጻሕፍት


**ምዕራፍ አንድ**

1. Augustus Blandy Wylde, Modern Abyssinia (London: 1901) ገፅ 249
2. Elizabeth Biasio, Minilik and Alfread IL9 (Zurich, 2004) ገፅ 13
3. ጣይቱ ብጡል ለአልፍሬድ ኢልግ የጻፋቸውን ደብዳቤዎች hEthiopian Records ገፅ 401-405 ይመልከቱ
4. Assefa Yilma; Haile Silassie: Emperor of Ethiopia (London 1936) ከገፅ 89-90 ይመልከቱ
5. Luigi Sambon (Rome 1896) እና Bairu Tafla, "Two of the Last Provincial Kings" Journal of Ethiopian Studies (1973) ገፅ 35
6. Haggai Erlich, "Egyptian Reaction" (March 1996) ገፅ 26
7. Rechard Seetzer, Ethiopia Through Russian Eyes (Red Sea Press, 2000) ገፅ 118
8. Marcus, A History of Ethiopia, ገፅ 80-81

**ምዕራፍ ኹለት**

1. Gherardo Pantano (Florence 1932) ገፅ 5 (የግል ማህደር)
2. Cesare Pini (Rome 1912) ገፅ 63-64 (የጉዞ ማስታወሻ)

**ምዕራፍ ሰባት**

1. Richard Pankhurst, "Ras Alula, Dogali and the Beginning of Italian Colonialism in East Africa" (AAU Press, 1987) ገፅ 123-124
2. የስምምነቱ ዝርዝር h Wylde, "Modern Abyssinia" ከገፅ 472-473 ይመልከቱ







3. የጣሊያን የውጪ ጉዳይ መ/ቤት መግለጫ (Rome, January 1885) ገፅ 157
4. የንግስት ቪክቶሪያ ደብዳቤዎች ለኢትዮጵያ (August 11, 1887) ከእንግሊዝ ፓርላማ ማህደር የተወሰደ
5. Cesar Pini - ገፅ 217 ይመልከቱ
6. ---------- - ገፅ 53
7. ---------- - ከገፅ 143-145
8. Jean – Marie Carre (Paris, 1931) ገፅ 213
9. Bairu Tafla "The Political Crisis in Tigray, 1889-1899) ገፅ 110

**ምዕራፍ አራት**

1. Harold Marcus, The Life and Times of Minilik II (Oxford, 1975) ገፅ 156
2. ተስፋ ስላሴ (ፓሪስ 1930) ገፅ 362
3. Vanderheym, The Expedilion (ገፅ 181-182)
4. "Letters of Ethiopia" Le' Temples, 27 April 1895

**ምዕራፍ አምስት**

1. Edward Alpers, "Flight to Freedom, 1750-1962" ገፅ 51
2. Francesco Frisina; Italy in Abyssinia and Assab, 1869-1897 (Alexandria, 1919) ገፅ 282
3. Augustus Wylde, Modern Abyssinia (London, 1901) ገፅ 350

**ምዕራፍ ስድስት**

1. Vanderheym, (ገፅ 41-42)
2. Vigo Montegaza, La' Guerra in Africa (Florence, 1896) ገፅ 448
3. Swayne, Seventeen Trips, ገፅ 272
4. Zaghi, Rimband in Africa, ገፅ 76-77

5. Pankhurst, Economic History of Ethiopia ገፅ 103፤ 107
6. Mondon – Vidailhet
7. "Occupation of Asmera", Observatore Romano 30 August, 1889
8. "Rome's Mission", Corriere Della Sera, 27 August, 1889
9. Zaghi, "Prottetoreto Italiano" ገፅ 159
10. Zaghi, La Missione Mekonen Italia, ገፅ 373-374

**ምዕራፍ ሰባት**

1. Carlo Rosetti, History of Ethiopian Diplomacy During Minilik II (Turin, 1910) ገፅ 78
2. "Italy Protectorate of Ethiopia", Osservatore Romane, 30 August 1889
3. Pianavia Vivaldi, Tre Ani ገፅ 166
4. Zaghi, "Dispach of Luigi Capucci" ገፅ 520

**ምዕራፍ ስምንት**

1. Luigi Cappucci, Summary Account, 15 April 1897 in Carlo Zaghi ገፅ 553
2. Sellassie, Chronicle, ገፅ 391
3. George F.H. Berkeley, The Campaign of Adwa and the Rise of Minilik (New York, 1969) ገፅ 14

**ምዕራፍ ዘጠኝ**

1. Oreste Baratieri, Memories of Africa, 1892 – 1896 (Torino, 1898) ገፅ 235
2. Guido Moltedo, "Hold Ambalage" ገፅ 560





3. Alfonso Riguzi, "Mekelle – Personal Diary" (Palermo 1901) ገፅ 74
4. Mekonnen's Letter to Barateri at Adigrat" (Moltedo, Assadio) ገፅ 122
5. Riguzi, ገፅ 31
6. Riguzi, ገፅ 128
7. Felter, Vicenda Affricana, ገፅ 37-38
8. Felter, ገፅ 49
9. Felter, ገፅ 51

**ምዕራፍ አሥር**

1. Corriere Della Sera, 27- 28 January 1896
2. Corriere Della Sera, 15-16 February 1896

**ምዕራፍ አሥራ አንድ**

1. Telegram on 25 January 1896
2. Bellavita, Adwa ገፅ 322
3. Bellavita, Adwa ገፅ 310-312
4. Barateri, ገፅ 363
5. Lembo, IL Processo Barateri, ገፅ 73

**ምዕራፍ አሥራ ሁለት**

1. Guiseppe Menarini, Dabormida at the Battle of Adwa (Naples 1897) ገፅ 44
2. Yoseph Nigusse, Report to Alfred ILg (31, March, 1896) ገፅ 460
3. Ximens, Sul Campo di Adua, ገፅ 287
4. Mezzuconni, ገፅ 248

5. Barateri, ገፅ 419
6. Barateri, ገፅ 420-426
7. Barateri, ገፅ 409

**ምዕራፍ አሥራ ሶስት**

1. Fransesco Frisina, ገፅ 149
2. Ernesto Cordella, General Albertoni in Adwa (Rome 1930) ገፅ 11-15
3. Cordella, ገፅ 14
4. Ximens, ገፅ 289
5. Tendone, The Battle of Aba Gerima (1897) ገፅ 168
6. Ximens, ገፅ 265 እና ገፅ 289
7. General Albertone's Letter to Dabormid, from Collected Letters, ገፅ 86

**ምዕራፍ አሥራ አራት**

1. Eugenio Dolcioti, Adwa and the Campaign in Africa (Tivoli, 1913) ገፅ 66
2. Pietro Felter, La Vicenda Africana 1895-1896 (Brecia 1935) ገፅ 81
3. Augustus B. Wylde, "An Unofficial Mission to Abyssinia" Manchester Guardian, 20 May 1897

**ምዕራፍ አሥራ አምስት**

1. Tedone, "Empress Zewditu and Minilik II" ገፅ 158
2. Edward Gleichen, "Mission to Minilik II, 1897" (London 1898) ገፅ 216-217
3. Wylde, Manchester Guardian, ገፅ 10





**ምዕራፍ አሥራ ስድስት**

1. Stuart Munro-Hay, Ethiopia; the Unknown Land (London 2002) ገፅ 110
2. Tedone, ገፅ 30

**ምዕራፍ አሥራ ሰባት**

1. Biasio, ገፅ 721 Frisina (May, 1897) ገፅ 28
2. Harold G. Marcus, ገፅ 93
3. Frisina, ገፅ 328

**ምዕራፍ አሥራ ስምንት**

1. "Italians feu" Atlanta Constitution, 4 March 1896
2. "Notes on Abyssinia" Chicago Tribune, 9 March 1896
3. "Our Own Correspondant, Berlin" Time, 4 March 1896
4. Private Collection
5. Heneri Philip Marry Orleans, Emperor Minilik (Paris, 1898), 166
6. "II Nigus Minilik" Ossevatore Romano, 12 January 1897
7. Boston Transcript, 17 December 1903
8. "Back from Abyssinia" New Jersey Record, 1 February 1904
9. Joseph Coan, The Expansion of Missions of the African Methodist Episcopal Church in South Africa 1880-1920 (West Port 1931) ገፅ 192-193
10. Skinner, "Abyssinia of Today" 130-131

**ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ**

1. Francesco Frisina, ገፅ 183
2. Manchester Guardian, 17 May, 1897

3. Wylde (1901) ገፅ 147-148

**ምዕራፍ ሃያ**

1. "Vittorie Sopra Vittorie" La' Italia 18-19 January 1896
2. "Demonstrations in Rome" IL Mattino 8 March 1896
3. IL Senza Preterse, 13 May 1896
4. Osservatore Romano, 23 September 1896
5. Zaghi, ገፅ 159
6. ASMA I, Eritrea, Empress Taitu, ገፅ 184
7. Giusepe Canuti, Massawa and Adwa (Florence 1911) ገፅ 244-245
8. Pantano ገፅ 134 እና Frisina ገፅ 325
9. Pantano ገፅ 135
10. La' Tribuna, 5 January 1897
11. Tedone, ገፅ 187
12. Frisina, ገፅ 337
13. Frisina, ገፅ 322

**ምዕራፍ ሃያ አንድ**

1. Nicola D' Amato, From Adwa to Addis Ababa (Salermo, 1898) ገፅ 64
2. Girma Fisseha "Ethiopian Paintings on Adwa" (AAU Press, 1998) ገፅ 691
3. Edward Gleichen (London 1898) ገፅ 131
4. Richard Pankhurst, "The Battle of Adwa 1896" (London 1889) ገፅ 86
5. Antoine Bervin, Benito Sylvain (Port an Prince 1969) ገፅ 43
6. Gherardo Pantano, ገፅ 97





7. Cesare Pini, Records of Africa (Rome 1919) ገፅ 198
8. Letters from Ellena to Barater, 9 October 1896
9. Barateri 42
10. Bici Rizzi, Quadrin Della Trentino (1934)
11. Coloreed American Magazine, September 1909 ገፅ 167-168; Wylde, ገፅ 148-149
12. Biasio, Prunk and Pracht, ገፅ 14-15
13. Warren Zimmerman, First Great Truimph: How Five Americans Made Their Country a World Power (New York, 2002)
14. Claude Fohlen, Les Etats-unis (Paris, 1988)

# የ2012 የቶይን ፋሎላ አፍሪካ ሽልማት አሸናፊ መጽሐፍ

## ስለ ደራሲው

ሬይሞንድ ጆናስ ሲያትል ውስጥ በሚገኘው የዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የታሪክ አስተማሪ ሲሆን በአፍሪካና አውሮፓ ጉዳዮች ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት ይታወቃል::
ይህ መጽሐፉ የ2012 የቶይን ፋሎላ አፍሪካ ሽልማትን በማሸነፍ ልዩ አድናቆትን አስቸንቶታል::

***

የአድዋ ድል አውሮፓን የዓለም ፖለቲካ እና ዘር ልዕለ ኃያል ከመሆን ያስቆመ ብቸኛው አጋጣሚ ነበር:: ከአድዋ በፊት ባሉ ዓመታት በርካታ የአውሮፓ እና የአሜሪካ ጋዜጦች መላው ጥቁር አፍሪካ በአውሮፓ ሙሉ ቁጥጥር ሥር የሚሆንበት ቀን መቃረቡን በአርግጠኝነት ይጽፉ ነበር:: የአሜሪካኑ አትላንታ ኮንስቲቲውሽን ጋዜጣም የሚከተለውን ጽፎ ነበር::

«መላዋ አፍሪካ በአውሮፓ መንግሥታት ቅርምት የምትጠናቀቅበት ቀን ዝርቧል» አውሮፓውያኑ በአሜሪካ ያሳኩትን የዘር የበላይነት በአፍሪካ ለመድገም ተዘጋጅተዋል:: በአሜሪካ ቀይ ሕንዶችን በማስወገድ ለራሳቸው ዝርያ መኖሪያ መፍጠር የቻሉበትን ብቃት በአፍሪካ ለመድገም የጥቁር አፍሪካ ዝርያዎችን በቅርቡ ማጥፋት ይጀምራሉ::» ይሄንን የመሳሰሉ የአውሮፓ የዘር እና የፖለቲካ የበላይነት ስብከቶች በዝተው ነበር::



ይህንን የመሰለ የዘረኝነት እና የተሰፋፋ የበላይ[illegible]ው አንግዲህ አድዋ ላይ ያከተመው:: በደቡብ አፍሪካ ኢፓርታይድ አከትሞ የጥቁር ዘር [illegible] ከመሪገጡ ሥር ዓመታት በፊት አድዋ ላይ ኢትዮጵያውያን የነጭ አውሮፓውያንን የበላ[illegible]ት በመስበር የጥቁር ሕዝብን አረጋግጠዋል::

ታሪክ በተለየ መልኩ ልዩ ክስተቶችን ይወሳል:: ይህ መጽሐፍ የአድዋን ታሪካዊ ልዩ ክስተትነት ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን ለድሉ አመክንዮአዊ ማረጋገጫ ለመለጠፍም የተጻፈ ነው:: እንደ አድዋ ዓይነት ልዩ ክስተቶች የታሪክን ተለምዷዊ ጉዞ በማስቀየስ ሰዎች ለዘመናት ዕምነው ከተቀበሉት ንግርት የተለየ እውነታ እንዳለ ያመላክታሉ:: አድዋም ለሰው ልጆች መረዳት የሰጠው ይሄንን ማረጋገጫ ነው::

አድዋ አንዲት አፍሪካዊት አገር ከወራሪ ጋር በመታገል ነፃነቷን ያወጀችበት ታሪካዊ ምስክር ነው:: አድዋ ለበርካታ ቅኝ ግዛቶች በራስ የመተማመን ጉልበትን በመስጠት የዘመናት ጥርጣሬያቸውን የገለጠ ድል ነው:: ከምንም በላይ ግን አድዋ የታሪክ ዑደት በተለየ አቅጣጫ የሚቀጥልበትን የጨዋታ ሕግ ያስተዋወቀ እውነታ ነው::

***

እንደ ዛሬው «ታይም» መፅሔት ዅሉ በ19ኛው ክፍለዘመን «ቫኒቲ ፌይር» ታዋቂ ነበር:: በ1897 ቫኒቲ ፌይር የፊት ገፁ ላይ የአፄ ምኒልክን ምስል ይዞ በመውጣት ንጉሠን ለመላው ዓለም አስተዋወቃቸው:: ከቻርልስ ዳርዊን፣ የሩሲያው አሌክሳንደር፣ ናፖሊዮን ሳልሳዊ አኩል የአፄ ምኒልክ ፎቶ ግራፍ ተከትሎ አፄ ምኒልክ እና አቴጌ ጣይቱ ከዓለም ታዋቂ ግለሰቦች ተርታ ተሰለፉ::
የምኒልክ እና ጣይቱ ዝና በሰፈው መናኘቱን ተከትሎ የተለያዩ አዳዲስ ክስተቶች ታይተዋል:: በርካታ አውሮፓውያንም አዳዲስ ለተወለዱ ሕፃናት ልጆቻቸው «ምኒልክ» የሚል ስም ሰጡዋቸው:: ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአድናቆት ደብዳቤዎች የምኒልክን ቤተ-መንግሥት አጣበውት ነበር::

ዋጋ $ 26.99 ር

HY International printing Enterprise PLC